
አለቃ አያሌው ታምሩ
(ካህን፤ሐዋርያ፣ ደራሲና ተርጓሚ)
በተለያዩ ጋዜጦችና፣ መጽሔቶች
ያስተላለፏቸው ማሳሰቢያዎችና
ትምህርቶች።
ኢትዮጵያ የዓለም ብርሃን
ኢትዮጵያ የዓለሙ ገዢ

# ክቡር አለቃ አያሌው ታምሩ

## (ካህን፣ሐዋርያ፣ ደራሲና ተርጓሚ)

## በተለያዩ ጋዜጦችና፣ መጽሔቶች ያስተላለፏቸው ማሳሰቢያዎችና ትምህርቶች።

# ያለፈውን ማስታወስ በሚመጣው ለመጠንቀቅ ይረዳል።

## (አለቃ አያሌው ታምሩ)

(ማዕበል ጋዜጣ፤ ኅዳር ፯ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ. ም. )

**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።**

**«ቀላይ ለቀላይ ትጼውዖ በቃለ አስራቢከ።»** «በፏፏቴ ድምፅ ቀላይ ቀላይን ትጠራለች።» (መዝ፤ ፵፩ ፥ ፯።)

ታሪካዊ ንጽጽር ያላቸውን ጊዜዎች፥ ቦታዎች፥ ምክንያቶች በሚመለከት የተነገረ ቃል ነው። በተለይ መተርጕማን አበው፤ በሙሴና በኢያሱ ዘመን በኤርትራ፥ በዮርዳኖስ የተደረገውን ተአምር፥ ከዚያም ዐልፎ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት ጊዜ የሆነውን ለመግለጽ ሰፊና ጥልቅ ትምህርት ሰጥተውበታል። የእኔ አስተሳሰብ ይህን አይመለከትም። እንደምታውቁት ዛሬ ኅዳር ፯ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስንና የእመቤታችንን የቅድስት ድንግል ማርያምን ወደ ግብጽ መሰደድና በጊዜው ፍጻሜም ወደ ምድረ እስራኤል መመለሳቸውን መታሰቢያ በዓል የምታደርግበት ዕለት ነው። ይህ በዓል በቤተ ክርስቲያናችን ስያሜ ቍስቋም እየተባለ ይጠራል። ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ በዚህ ዓለም በተገለጠበት ወቅት ከፈጸማቸው ሥራዎች የአንዳንዶቹ መታሰቢያ በቤተ ክርስቲያናችን የሚታወቀው ሥራው በተፈጸመበት ቦታ ስም ነው። ለምሳሌም ቃና ዘገሊላ፥ ደብረ ዘይት፥ ደብረ ታቦር፥ እንዲሁም ቍስቋም የመሳሰሉት ሁሉ ናቸው።

ቍስቋም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ልጇን ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አዝላ የሦስት ዓመት ከመንፈቅ የስደት ጉዞ ከፈጸመች በኋላ ወደ ምድረ እስራኤል ስትመለስ ለመጨረሻ ጊዜ በአፍሪካ ምድር በአንድ የፈረሰ ግንብ ውሥጥ ያደረችበት፤ «ወፍም ለራሷ ቤት አገኘች፤ ዋኖስም

ግልገሏን የምታሳርፍበት አገኘት፤» ሲል ነቢዩ የተናገረው ትንቢት የተፈጸመበት ስፍራ ሲሆን፤ ከሦስት መቶ ዓመት በኋላ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ቅዱስ ቴዎፍሎስ በእመቤታችን ስም ቤተ ክርስቲያን ሠርቶበታል። አገልግሎት ሲጀምርም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እናቱንና ሐዋርያቱን ይዞ በመገለጥ ቅዳሴ ቤቱን አክብሮለታል። ኢትዮጵያውያን ነገሥታትም ለዚህ በረከት ብዙ ተሳትፎ ያደርጉ እንደ ነበረ ታሪክ ይናገራል። ይልቁንም የዐፄ ኢያሱ እናት እቴጌ ምንትዋብ በሊቃውንቱ አስመክረው ከመስከረም ፳፮ እስከ ኅዳር ፰ ለሦስት ዓመት ከመንፈቅ የስደት ዘመን የዐርባ ቀን የጾም፥ የምስጋና፥ የበዓል መታሰቢያ ከማቆማቸውም በላይ በታላቁ የጥበብ መዲና የጎንደር ከተማ በእመቤታችን ስም ቤተ ክርስቲያን አሠርተው፥ ቦታውን ደብረ ቍስቋም አሰኝተው በየዓመቱ ኅዳር ፮ ቀን የአምላካችንና የእናቱ የእመቤታችን የስደት መታሰቢያ እንዲከበር አድርገዋል። ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክም የቀደሚቸውን አርኣያ በመከተል መንበረ መንግሥት ቍስቋም ቤተ ክርስቲያንን አሠርተው አነሆ ምእመናን በዓሉን በየዓመቱ ያከብሩታል።

ይህ በዓል በዚህ ብቻ የተሰወነ አይደለም። በዓለ እግዚአብሔር እንደ መሆኑ መጠን ጾሙ ጾመ ጽጌ ወይም የጽጌ ጾም፥ ምስጋናው ማኅሌተ ጽጌ፥ ግብዣው ጽጌ እየተባለ በመላ ኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያን የሚታሰብ ሲሆን፤ በልዩ ልዩ ስፍራ ደግሞ በቍስቋም ስም ብዙ አብያተ ክርስቲያን ተሠርተው በዓሉ ሲከበር ኖሯል። በዓሉ ስሙን ያነሣው ወይም ያገኘው ከቦታው ቢሆንም ከጊዜ ወደ ጊዜ ግን የእመቤታችን መታወቂያ ሆኗል። ሌሎችም ይህን የመሰሉ አሉ። ለምሳሌ ፅንሰታ፥ ልደታ፥ በዐታ፥ ሕንጸታ፥ ኪዳነ ምሕረት እነዚህን የመሳሰሉ ሁሉ እየተለመዱ ሲሄዱ የመጠሪያ ስሟ ያህል የእመቤታችን መታወቂያ ሆነዋል። ፅንሰታ ማለት መፀነሷን፥ ልደታ ማለት መወለዷን፥ በዐታ ማለት ወደ ቤተ መቅደስ መግባቷን፥ ሕንጸታ ማለት በስሟ ቤተ ክርስቲያን መሠራቱን፥ ኪዳነ ምሕረት ማለት የዕርቅ ምልክት መሆኗል፥ አስታራቂ መሆኗን፥ ስለዚህም ከልጇ የተቀበለችውን ቃል ኪዳን የሚያመለክቱ ሲሆን፤ ቍስቋም ለስደት ከአገር መውጣቷን፥ ኋላም ወደ አገር መመለሷን፥ ስትመለስም ለመጨረሻ ጊዜ በአፍሪካ ምድር በዚህ ስፍራ ማደሯን የሚያመለክት ቃል ነው። አሁን የምንነጋገረው በታሪኩ ጫፍ ላይ ነው።

በዝርዝር ሳይሆን በማሳጠር፥ በመጠቅለልም ቢሆን ወደ ታሪክ እንመለስ። በሥጋዊም ሆነ በመንፈሳዊ የታሪክ መሥመር የኢትዮጵያ ዕድል ከዓለም አህጉር ልዩ፥ እጅግ በጣም ልዩ መሆኑን የማያውቅ ካለ እኛ ራሳችን ኢትዮጵያውያን ብቻ ነን፤ ከዚያም የዘመኑ ኢትዮጵያውያን ነን። እግዚአብሔር እንደ ልቤ የታመነ ሰው ሲል የጠራው ነቢዩ ዳዊት በመንፈስ ቅዱስ እየተቃኘ ከተናገራቸው ቃላት አንዱ በመዝሙር ፷፯ ቊ፤ ፴፩ ላይ የሚገኘው፤ **«ይምጽኡ ተናብልት እምግብጽ፤ ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር፤»** የሚለው ነው። ትርጕሙም፤ «ገባሮች ወይም አስታራቂዎች ከግብጽ ይምጡ፤ ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች፤

» ማለት ነው፡፡ ነቢዩ ይህንን የሚናገረው በኢትዮጵያ እንዳለ ሆነ ነው ማለት ነው፡፡ **ተናብልት** የሚለው የግእዝ ቃል ሁለት ትርጉም ያሳያል፡፡ በአንድ በኩል የዓመት ግብር ወይም ገጸ በረከት ይዘው ከመንግሥታት ወደ መንግሥታት የሚላኩትን መልእክተኞች የሚያመለክት ሲሆን፤ በዚህ ጊዜ ኢትዮጵያውያን ነገሥታት ለረጅም ጊዜ ግብጽን የገዙበት ዘመን እንደ ነበረ የሚያስታውሰን ከመሆኑም በላይ በዐባይ ውሃ ምክንያት ግብጾች ለኢትዮጵያ ግብር ሲከፍሉ እንደ ነበረ ያመለክታል፡፡ በሁለተኛው ትርጕሙ ደግሞ አስታራቂዎች፥ አማላጆች ማለትን የሚያመለክት ሲሆን፤ በመጀመሪያ ክፍል እግዚአብሔር ዓለምን የታረቀበት ልጁ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስና፤ «አገሪቱን ርስት፥ ሕዝቧን ዐሥራት አድርጌ ሰጥቼሻለሁ፤» ብሎ ልጇ ጌታችን ቃል ኪዳን የገባላት እናቱ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በስደታቸው ጊዜ ከግብጽ ወደ ኢትዮጵያ መግባታቸውን፥ ኢትዮጵያም በጌታችን ልደት ከተደረገላት ትንቢታዊ ጥሪና ካገኘችው የእጅ መንሻ ማቅረብ ተሳትፎ ሌላ ሰው የሆነውን አምላክ አማኑኤልንና ወላዲተ አምላክን ንጽሕት ድንግል እናቱን በሃይማኖት፥ በክብር፥ በፍቅር እጇን ዘርግታ ለመቀበልና ለማስተናገድ መታደሏን ያሳያል፡፡

በሁለተኛውም መተንብላን ሊቃነ ጳጳሳት እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ማለት እስከ ፲፱፻፵ ዓመተ ምሕረት ድረስ ወደ ኢትዮጵያ መምጣታቸውን፥ ኢትዮጵያም እነሱን እየተቀበለች ስታስተናግድ መኖሯን ያመለክታል፡፡ በዚህ ታሪክ መሠረት ጻድቁ ዮሴፍ ሕፃኑን አማኑኤልንና እናቱን ይዞ ከሄሮድስ ሸሽቶ ወደ ግብጽ በመጣ ጊዜ ዕድሉ የግብጽ ብቻ አልነበረም፤ የኢትዮጵያም ጭምር ነበር፡፡ ነቢዩ ኢሳይያስ፤ «ጌታ በፈጣን ደመና ሆኖ ወደ ግብጽ ይወርዳል፤ የግብጽ የእጃቸው ሥራ ይነዋወጣል፤» ብሎ ሲናገር፤ (ኢሳ፤ ፲፱ ፥ ፩፡፡) ነቢዩ ዕንባቆም ደግሞ፤ **«ወፍኖቶሂ ዘእምዓለም ርኢኩ፤ አዕፃዳተ ኢትዮጵያ ይደነግፃ፡፡»** «ከጥንት የታሰበ መንገዱን አየሁ፤ የኢትዮጵያ አውራጃዎች ይደነግጣሉ፤» አለ፡፡

ጌታ ወደ ግብጽ ሲገባ አምልኮተ ጣዖትን ከግብጽ ለማፍረስ፥ ምድረ ግብጽን በኪደተ እግሩ ለመቀደስ ሲሆን፤ ወደ ኢትዮጵያ መግባቱ ደግሞ በኢየሩሳሌም በሄሮድስ ዘመን የነበረው መቅደስ ከጽላት፥ ከሕግ ባዶ ስለ ነበር፤ **«መሥዋዕተ ወቍርባነ ኢፈቀድኩ መሥዋዕተ ዘበእንተ ኃጢአት ኢሠመርኩ ውእተ ጊዜ እቤ ነየ መጻእኩ ውስተ ርእሰ መጽሐፍ ተጽሕፈ በእንቲአየ፡፡»** **«መሥዋዕትን ቍርባንን አልወደድኩም፤ ስለ ኃጢአት የሚቀርበውን መሥዋዕት አልወደድኩም፤ ብለሃልና በመጽሐፍ አርእስት ስለ እኔ እንደ ተጻፈ ያን ጊዜ እሺ በጄ ብየ መጣሁ፤»** ሲል የተናገረውን ትንቢት ለመፈጸም ጽላትና ሕግ ወዳሉበት ወደ ኢትዮጵያ ወደ አኵስም ቤተ መቅደስ ለመግባት ፈቃዱ ስለ ሆነ ነው፡፡ ስለዚህ ሁለቱም አገሮች ማለት ግብጽና ኢትዮጵያ በረከተ ስደቱን ለመሳተፍ ታድለዋልና ጌታና እናቱ ከኢየሩሳሌም ወደ ግብጽ፥ ከግብጽም ወደ ኢትዮጵያ መጡ፡፡ ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡም ዛሬ ደብረ

ዳሞ ቀድሞ ደብረ ሃሌ ሉያ ተብሎ በሚጠራው በአቡነ አረጋዊ ገዳም ሲቃነ መላእክት፥ ሠራዊተ መላእክት ሃሌ ሉያ እያሉ በዳዊት የምስጋና መዝሙር ተቀበሏቸው። ከዚያም ወደ አኵስም ቤተ መቅደስ ሲገቡ ሁሉን ቻይ አምላካችን የሚሳነው ነገር የለምና በዚያ ትንቢተ ነቢያትን ፈጸመ። ምሳሌም የውጣ አማናዊው አካላዊ ቃል ሲመጣ በኢየሱስ ተፈጸመ። ምሳሌዩቱ ጽዮንም በአማናዊት ጽዮን ድንግል ማርያም ታድሳ ወደ ሐዲስ ኪዳን ተላለፈች።

**ኢትዮጵያውያን ሁሉ ሃይማኖትን የተቀበሉ እንደ አባቶቻቸው በምሳሌ ሳይሆን በወልደ እግዚአብሔር ደም ታድሰውና ተቀድሰው ደቂቀ ጽዮን ተባሉ፤ አዋልደ ጽዮን ተባሉ። እምነ ጽዮን (እናታችን ጽዮን) ብለው ለማመን፥ ለማመስገን ታደሉ። ይህም በረከተ ስደት በምድረ ትግሬ ብቻ ሳይወሰን በመላው ምድረ ኢትዮጵያ ተዳርሶ ከዕንቢተኞች በቀር ዕድሉ ለአመኑ ሁሉ ተፈቅዷል። በዚህ ምክንያት ነው ከመስከረም ፳፮ እስከ ኅዳር ፮ የጾም፥** የምስጋና፥ የበዓል መታሰቢያ የታወጀው፤ ጸንቶ የኖረው። ዛሬ የቊስቋምን በዓል የምናከብረው በዚህ ምክንያት ነው። ቀደም ሲል፤ «በፏፏቴ ድምፅ ቀላይ ቀላይን ትጠራለች፤» ያልኩትም ግብጻዊት ገዳመ ቊስቋም፥ ደብረ ሃሌ ሉያ ደብረ ዳሞ፥ ደብረ ጽዮን አኵስም፥ ገዳመ ዋሊ ዋልድባ፥ ደሴተ ጣናና ገዳማቶቿ፥ መንዝና ምድረ ጉራጌ፥ ሌሎችም የኢትዮጵያ ቅዱሳት መካናት ታሪክ ያስተሳሰራቸው፥ የታሪክ ተዘምዶ ያላቸው መሆናቸውንና ዛሬ በቊስቋም ስም በዚህ ስፍራና በሌላ ቦታም የምናከብረው በዓል በታሪክ የፏፏቴ ምድፅ የሚገናኙ መሆናቸውን ለማመልከት ነው።

ያለፈን ማስታወስ በሚመጣው ለመጠንቀቅ ይጠቅማል እንዳልኩት አሁንም የማስታውሳችሁ ነገር አለ። በ፲፱፻፹፰ ዓመተ ምሕረት በዛሬው ቀን በመንበረ መንግሥት ቊስቋም ቤተ ክርስቲያን ተገኝቼ ይህንኑ ታሪክ የሚመለከት ሰፊ ትምህርት መስጠቴንና ታላቁ የትግሬ ክርስቲያን ሕዝብ የኢትዮጵያ አምላክ የሰጠውን ጣምራ ዕድል ከታሪክ ጋር አገናዝቦ መጠበቅ እንደሚኖርበት ያቀረብኩት ጥያቄ ያዘለ ማስታወሻ ትዝ ይለኛል። ምድረ ትግሬ ከታቦተ ጽዮንና ከጽላተ ኪዳን፥ ከሕገ ኦሪት ጀምሮ ለምድረ ኢትዮጵያ የልዩ ልዩ ሥጋዊና መንፈሳዊ በረከት ምንጭ፥ ቦይ ሆና መኖሯ የታወቀ ነው።

ከለውጥ ወዲህ ደግሞ ኢትዮጵያ ሰይጣንና ሠራዊቱ እየነቀነቁ ባመጡት የመከራ ማዕበል ተውጣ በምትገኝበት ጊዜ ልዑል እግዚአብሔር ሥጋዊና መንፈሳዊ ሥልጣን ለትግሬ ሕዝብ በመስጠቱ ቸርነቱ የዚህን ታላቅ ሕዝብ እምነት የሚያመለክት ስለሆነ፤ እምነቱ ጸንቶ ከትዝብት እንዲድን፥ አገሩንና ቤተ ክርስቲያኑንም ከውድቀት እንዲያድን ቀንም ሌትም ተግቶ መሥራት ያለበት መሆኑን ማስታወሴ ትዝ ይለኛል። በልዩ ልዩ ጊዜ ልዩ ልዩ ዐሳቦችን በመቈርቈር በቅንነት አቅርቤአለሁ። ተንኮለኞች ግን ቀናውን እያጣመሙ ብዙ አሉባልታ መንዛታቸውንንም ዐውቃለሁ።

እኔ ግን ከእውነት በስተቀር በዚህ ታላቅ ሕዝብ ላይ መጥፎ አስተሳሰብ እንደሌለኝ አምላኬ ያውቃል።

ለፍርሃቴ ምክንያት ከሆኑ ነገሮች ግን ብዙዎቹ ተፈጽመዋል። የሥጋዊውን መሥመር ብንተወው እንኳ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ አቡነ ጳውሎስ ከነ አክሊላቸው፥ ከነ ልብሰ ተክህኗቸው ለሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መግባት (የጌታ ዐዳር) መግባታቸው፥ በተራ ምእመን ደረጃም ከፓፓው ቡራኬ መቀበላቸው፥ የክሕደትና የኑፋቄ መጽሐፍ ማሳተማቸውና መበተናቸው፥ ኦርቶዶክሳዊውን የሊቃውንት ጉባኤ ማፍረሳቸው፥ ተጠሪ የሆኑለትን ሲኖዶስ መሻራቸው፥ በኢየሱስ ክርስቶስና በመንፈስ ቅዱስ ፈንታ ርእሰ ቤተ ክርስቲያን፥ ለሲኖዶስ አመራር ሰጪ አድርገው ራሳቸውን መሰየማቸው፥ ሲኖዶሱን የግል ተጠሪአቸው ማድረጋቸው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ልዕልና፥ የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖትን እውነትነት፥ የአኵስምንና የታላቁን የትግሬን ክርስቲያን ሕዝብ ታላቅነት የሚፈታተንና በትዝብት ላይ የሚጥል ነው።

ሌላው በደብረ ዳሞ አደገኛ ሁኔታ ላይ አባ ጳውሎስ ያሳዩት ፌዝ ወይም ቸልታ ነው። በነጻው ፕሬስ እንደ ተገለጠው በደብረ ዳሞ ቤተ ክርስቲያን ታሪካዊ ግምጃ ቤት ላይ የደረሰው አደጋ ነሐሴ ፲፫ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓመተ ምሕረት ሲሆን ዜናው የተሰማው ግን ከስድሳ ቀን በኋላ ወይም ከሁለት ወር በኋላ ነው። አባ ጳውሎስም ቦታውን የጎበኙት ጥቅምት ፲፫ እና ፲፬ እንደ ሆነ ተነግሯል። እስከዚህ ለምን ተደበቀ? ለምን ተሸፈነ? የቦታው ርቀት ከልክሎ፥ መገናኛ ጠፍቶ አይመስልም። እንግዲያስ የተሰዓቱ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ መሰደድና የሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሥራ፤ «በፏፏቴ ድምፅ ቀላይ ቀላይን ትጠራለች፤» እንደ ተባለው ዐይነት ስለ ሆነ አባ ጳውሎስ በደብረ ዳሞ በደረሰው አደጋ ላይ ያሳዩት ቸልታ፥ የፈጸሙት ፌዝ ከዚያ ተለይቶ አይታይም።

ሌላው የማስታውሳችሁ ባለፈው ዓመት በአኵስም ቤተ መቅደስ የጽዮን ማርያም በዓል በሚከበርበት ጊዜ ጳጳሳት ትምህርት በመስጠት ላይ ሳሉ አንድ ተአምራት ተደርጓል። ለረጅም ጊዜ በቤተ ክርስቲያኑ ውሥጥ የኖረ የወይራ ዛፍ ያለ አንድ ግፊት ድምፅ አሰምቶ ተሰንጥቆ በመውደቁ አደጋ ማድረሱ ይታወሳል። ይህ ምልክት ሃይማኖት አልባ ጳጳሳትና ፓትርያርካቸው በአኵስም ቤተ መቅደስ የሚፈጽሙትን ደባ፥ በደል፥ ተጋፊነት ሰዎች እያወቁ ዝም ቢሉም ሥነ ፍጥረት መስክሯል ማለት ነው። አሁን በቅርቡ ደግሞ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ በመቀሌ አስተናግደዋል። መቼም ለጽድቅ አለመሆኑ የታወቀ ነው። ጠላቶቻችንም በዚህ ዐይነቱ ሁኔታ ወዳጅ መስለው እየቀረቡ ነው ንዋያተ ቅድሳቶቻችንን የሚዘርፉት። በቅርቡ ቀን በነጻው ፕሬስ እንደ ተገለጠው የዓለም ልዩ ልዩ ክፍሎች አባል መሆናቸው በፎቶግራፍ ጭምር ተደግፎ ወጥቷል። ስለዚህም በደብረ ዳሞ የታየው

ተንኮል የተሞላበት ሥራ በአኵስም እንዳይደገም ትልቅ ጥንቃቄ ያሻል። ነቢዩ፤ **«ዕግትዋ ለጽዮን ወሕቀፍዋ ወተናገሩ ውስተ ማሕፈዲሃ ደዩ ልበክሙ ውስተ ኃይላ ወትትካፈልዎ ለክበዲሃ።» «ጽዮንን ክበቧት፤ ዕቀፏት፤ በቤተ መቅደሷ ስለ እሷ ተነጋገሩ፤ ታድነናለች፥ ትጠብቀናለች፥ ትረዳናለች ብላችሁ አምናችሁ ልባችሁን በልጇ በኃይሏ ላይ አሳርፉ፤ በረከቷን ትታደላላችሁ፤» ብሏል።**

ስለዚህ የጸጋ ብኵርና የታደላችሁ እናንተ አኵስማውያን! ጳጳሳቶቻችንና ፓትርያርካቸውም እምነት የምንጥልባቸው ሆነው ስላልተገኙ ጽዮንን ከነክብሯ መጠበቅ የመላው ኢትዮጵያውያን ድርሻ መሆኑ ቢታወቅም በቅድሚያ የእናንተ ጥንቃቄ ያሻል።

አሁንም ታላቁ የክርስቲያን ሕዝብ ዳኝነት እንዲያይልኝ እጠይቃለሁ። አባ ጳውሎስና አባ ገሪማ ከነ ግብር አበሮቻቸው የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ልዕልና አዋርደዋል። መጻሕፍቶቿን በመለወጥ ላይ ናቸው። አቤቱታ ማቅረብ ከጀመርኩ ሁለት ዓመት ዐለፈ። ሌሎች ክርስቲያኖችና የምእመናን ኮሚቴ አባሎችም ከእኔ ጋር አቤቱታ ማቅረብ ከጀመሩ ሰባት ወር ዐልፏል። ጌታ፤ **«እኔ በአባቴ ስም መጣሁ አልተቀበላችሁኝም፤ ሌላው በራሱ ስም ቢመጣ እሱን ትቀበላላችሁ፤» እንዳለው፤ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና ለአምላኳ ክብር፥ ለሃይማኖቷ፥ ለሥርዐቷ ይቆማሉ፥ ይከላከላሉ ተብለው የተሾሙ ጳጳሳት፥ መነኮሳት፥ የአድባራትና የገዳማት አስተዳዳሪዎች፥ ቀሳውስትና ዲያቆናት፥ የሰበካ ጉባኤ አባላት እግዚአብሔርን ንቀው ጥፋቱን እያወቁ ከአባ ጳውሎስ ጋር ወግነው እንኳን ዳኝነት ሊያዩ አቤቱታችንን መስማት አልፈለጉም።** በመልእክተኛና በመንግሥት ፖስተኛ የላክነውን አቤቱታ ሳይቀር አንቀበልም ብለው የመለሱ አሉ። መንግሥትም በሃይማኖት ጉዳይ አያገባኝም ብሎ ዝም ብሏል። ሌላው ሕዝብ እንዳይናገር የመንግሥትን አባባል ለአባ ጳውሎስ ድጋፍ እንደ መስጠት የቆጠረው ይመስላል። ማለት ብንናገር መንግሥት ይጠላናል የሚል ዐሳብ ያለው ይመስላል። ስለዚህ ታላቁና ክርስቲያኑ የትግሬ ሕዝብ ትናንትም የታሪክ ባለቤት የነበርክ፥ ዛሬም የታሪክ ትዝብት የሚጠብቅህ፥ ከኢትዮጵያ አምላክ ታላቅ ዐደራ የተሰጠህ ስለ ሆንክ አባ ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚፈጽሙትን ዐመፅ እየተመለከትክ በቸልታ እንዳታልፈው፥ እውነቱን እንድትናገር፥ እውነቱን እንድትፈርድ በታቦተ እግዚአብሔት ጽዮንና በአምላኳ ስም ተማጽኜ አቤቱታየን አቀርባለሁ። ክብር ምስጋና ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ይሁን። የእግዚአብሔር በረከት ለቤተ ክርስቲያናችንና ለልጆቿ ይሁን።

አለቃ አያሌው ታምሩ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ጉባኤ ዋና ሰብሳቢ።

(ማዕበል ጋዜጣ፤ ኅዳር ፯ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ. ም. )

# እግዚአብሔር ያጥናችሁ።

«እግዚአብሐር ያጥናችሁ የሚባል ሰው የለኝ፤ ኀዘንተኛዪቱም ሟቺቱም እኔው ነኝ።» (ቤተ ክርስቲያን።)

**(አለቃ ፡ አያሌው ፡ ታምሩ)**

**(ማዕበል ጋዜጣ፥ የካቲት ፲ ቀን ፲፱፻፺ ዓ. ም.)**

## በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤ አሜን።

**«ንዑ ትልዉኒ።» «ኑ ተከተሉኝ።» (ማቴ፤ ፬፥ ፲፱።)**

**«ይበጽሕ መዋዕል አመ ይነሥእዎ ለመርዓዊ እምኔሆሙ ይእተ አሚረ ይጾውሙ።»** «ሙሽራውን ከእነሱ የሚወስዱበት ቀን አለ፤ ያን ጊዜ ይጾማሉ።» (ማቴ፤ ፱፥ ፲፬ - ፲፯። ሉቃ፤ ፭፥ ፴፫ - ፴፭።)

የተወደዳችሁ ምእመናን ሕዝበ ክርስቲያን! በታላቂቱ፥ በነባሪቱ ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያናችን ሥርዐት ይህ ሳምንት የቅበላ ሳምንት ሲባል ከሚቀጥለው ሳምንት ጀምሮ ለ፶፭ ቀናት ከእግዚአብሔር ጋር የምንቆይበት ወርኀ ጾም፥ የጾም ወራት ነው። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዐት ዓመት ክፍላተ ዘመን አሉት። ክፍላተ ዘመን መደባቸው ፫ ቀን ሆኖ በ፫ ቀን ውስጥ ደግሞ የተከፋፈሉ ወቅቶች አሉ። ይህ ያለንበት ክፍለ ዘመን በግእዙ ቋንቋ ሐጋይ (በጋ) ይባላል። የዋእይ ምግብና አለው። የሙቀት ዘመን ነው። ነገር ሁሉ ያልበሰለው ይበስላል፤ ያልደረቀው ይደርቃል፤ ይታጨዳል፤ ይወቃል፤ በሪቅ፥ በጎታ በጎተራ ይከተታል። «በየካቲት ነገር ክተት፤» ይባላል።

በሌላ በኩልም በቤተ ክርስቲያን የውሥጥ ሥርዐት ዘመነ ልደት፥ ዘመነ አስተርእዮ፥ ዘመነ መርዓዊ ወይም ቅበላ ተብሎ ይከፈላል። ዘመነ መርዓዊ፥ ቅበላ የሚባለው ከጾመ ነነዌ ፋሲካ እስከ ዐቢይ ጾም መግቢያ ዋዜማ ዘወረደ እሑድ ያለው ቀን ነው። ሙሽራ ያለው ቤተሰብ በማንኛውም ሰዓት ሙሽራውን መጠበቅ እንዳለበት ክርስቲያኖችም ሙሽራውን ኢየሱስ ክርስቶስን ለመቀበል የሚዘጋጁበት ሳምንት ነው። ጌታችንን ሙሽራ ስንል በእኛ ዐሳብ፥ ግምገማ የሰጠነው ስም አይደለም። መጥምቁ ዮሐንስ፥ የሙሽራው ሚዜ፤ **«ሙሽራ ያለችው እሱ ሙሽራ ነው፤» ሲል መስክሮለታል። በኋላ እሱ ራሱ፤ «ሙሽራው ከሚዜዎቹ መሐከል የሚወሰድበት ቀን ይመጣል፤» ሲል አጽድቆታል።**

ቅዱስ ጳውሎስም፤ «የእግዚአብሔርን ቅናት እቀናላችኋለሁ፤ ለአንዱ ንጹሕ ድንግል ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ እሱ ላቀርባችሁ አጭቼአችኋለሁና፤» ይላል። ይህም በመሆኑ ሐዋርያት ጌታ በሰጣቸው ትእዛዝ መነሻነት በዲድስቅልያ መጽሐፋቸው በአንቀጽ ፳፱ ምእመናን የጌታን ጾም፥ የሕማሙንና የሞቱን መታሰቢያ በዓመት በዓመት እንዲያደርጉ፤ በጾማቸው ፍጻሜም በዓለ ትንሣኤውን እንዲያከብሩ አዝዘዋል። በዚህ መሠረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በትምህተ ሃይማኖቷ በተሠራው ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን ለ፶፭ ቀናት የጌታን ጾም ትጾማለች። በዚህም፤ «ኑ ተከተሉኝ፤ መታሰቢያዬን አድርጉ፤» ያለውን ተቀብላ የእሱን ጾም ትጾማለች። የሕማሙን፥ የሞቱን መታሰቢያ ታደርጋለች።

ጾመ ኢየሱስ ይባላል። እሱ የጾመው፥ ከእሱ የተቀበልነው ነውና። ዐቢይ ጾም ይባላል። እስከ ፶፭ በሚደርሱት የቀኖች ቊጥር ምሳሌነት የሰው ዘር በመንጸፈ ደይን ወድቆ በእግረ አጋንንት ሲጠቀጠቅ፥ በሥቃየ ገሃነም በፍዳ ቊራኘነት ሲጨነቅ የኖረበት የ፭ሺ፭፻ ዘመን ዓመተ ፍዳ፥ ዓመተ ኲነኔ ተፈጽሞ በክርስቶስ ጾም፥ በክርስቶስ ሕማም በሰማይ በምድር ነጻነትን፥ በጠላቱ በሰይጣን ላይ ድል አድራጊነትን ያገኘበት ነውና። ስለዚህ ዐቢይ ይባላል። ለዚህ ጾም ተመሳሳይ፥ እኩያ፥ ጓደኛ የለውም። ፈሪሳውያን የጌታ ደቀ መዛሙርት የእሱን ዐይነት ጾም እንዲጾሙ ጠይቀውት ነበር። እሱ ግን፤ የአዲስ ልብስ እራፊ በአሮጌ ልብስ ላይ አይጣፍም፤ ብሎ አምላክ ራሱ ጾሞ ለምእመናኑ የሰጠው የክርስቲያን ጾም ከሰው ሠራሽ ሊነጻጸር፥ ሊመሳሰል፥ ሊደባለቅና ሊቀላቀል እንደማይችል አስረድቷል። በኋላ ዘመን የተነሡት ተፈታታኞች ደግሞ፤ ጾም የለም፥ እሱ ጾሞልናል፤ የሚሉ ሆነው ተገኝተዋል። ክርስቶስ ግን፤ **«የሙሽራ ሚዜዎች ሙሽራው ከእነሱ ጋር ሳለ ሊጾሙ አይችሉም፤ ግን ሙሽራው ከእነሱ የሚወሰድበት ቀን ይመጣል፤ ያን ጊዜ ይጾማሉ፤» በማለት በጊዜው የሥርዐት መሥራች ጓደኛ እንደ ሌለው፤ በኋላ ግን ምእመናን ሁሉ በጾም ሊመስሉትና ሊከተሉት እንደሚቻላቸው፥ እንደሚገባቸውም አስረድቷል።**

በዚህ መሠረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለተከታዮቿ የአምላካቸውን ጾም ታውጃለች። በዚህ ጊዜ ያለው የቤተ ክርስቲያን ሥርዐት እጅግ ልዩ ነው። ፍጹማኑ የዕረፍት ጊዜ የላቸውም። ወጣንያኑና ማእከላውያኑም ቤተ ክርስቲያን የሰጠቻቸውን መመሪያ ተከትለው በሥርዐት ይጾማሉ። ካህናት ሌሊቱን በሰዓታት ያድራሉ። ቀንም እግዚአብሔር ለቅዱስ ያሬድ በገለጸው መመሪያ መሠረት ከመዝሙረ ዳዊት፥ ከልዩ ልዩ ቅዱሳት መጻሕፍት በዜማ በተቀናበረው ጾመ ድጓ፥ ምዕራፍ፥ ዝማሬ በተባለው ክፍለ መዝሙራት በጸሎት፥ በምስጋና እግዚአብሔርንና ቤተ ክርስቲያኑን ሲያገለግሉ ይውላሉ። የመዓልት ሰዓታትና ምህላም አለ። ከዚህም ጋር፤ **«ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ስብሐተ ሐዲሰ።» «እግዚአብሔርን አዲስ ምስጋና አመስግኑት፤» ተብሎ በቅዱሳት መጻሕፍት በመታዘዙ (መዝ፤ ፺፭፥ ፩፤ ፺፯፥ ፩። ) እንደየአግባቡ አዲስ የቅኔ ድርሰት ይታከልበታል።**

በዚህ የጾም ወራት አበው የጌታን ነገረ ስቅለቱን በሚያስታውስ ሥርዐት ከ፲፰ እስከ ፳ ሰዓታት የሚውሉት በጾምና በአገልግሎት ነው። ይህም ኢትዮጵያን ከማንኛውም አሳዛኝ ፈተና ለረጅም ጊዜ ጠብቆ የኖረ ነው። የዚህ መጓደልም ነው በ፳ኛው ክፍለ ዘመን ይልቁንም በእነዚህ ፳፭ ዓመታት ኢትዮጵያን ከነሕዝቧ በመከራና በውርደት አዘቅት ውስጥ የጣለ። ይህም በግዳጅ

አልመጣም። ኢትዮጵያውያን ራሳቸው በፖለቲካ ውዥምብር ስለ ተጠመዱ፥ ሃይማኖታቸውን ስለ ካዱ፥ ዓላማቸውን ስለ ሳቱ፥ የባዕድ ወራዳ ጠባይ ስለ ጎተቱ እንጂ አሁንም እንመለስ። ልዑል እግዚአብሔር አሁንም በጾም በጸሎት ወደ እኔ ተመለሱ፤ እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ፤ ልብሳችሁን ሳይሆን ልባችሁን ቅደዱ፤ መለከት ንፉ ማለት ምከሩ፥ አስተምሩ፥ ቀስቅሱ፥ ጹሙ ማለት በመብል አትጠመዱ፥ ማኅበራችሁን ቀድሱ፥ ከርኩሳን ተለዩ፤ ወንድ ሙሽራ ከጫጉላው፥ ሴት ሙሽራ ከመጋረጃዋ ይውጡ፤ ሰዎችን ሰብስቡ ጡት የሚጠቡ ሕፃናት ሳይቀሩ ፤ ለጌታቸው መሥዋዕት የሚያቀርቡ ካህናት ያልቅሱ ብሎአል። በዚህ መሠረት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ሰዓት ወስነው፥ ምግብ ለይተው፥ ዕረፍትና ምቾት ትተው ለረጅም ጊዜ ሲጾሙት ኖረዋል። ልዩ ምልክታቸው ነው።

እንደ ዛሬው፤ እግዚአብሔር ምን ሠራችሁ እንጂ ምን በላችሁ አይልም፥ የተፈቀደለትን ምግብ ከልክሎ በጾም ሥጋን መበደል በእግዚአብሔር ፊት ያስጠይቃል፤ የሚሉ ፊዘኞች ከመነሣታቸው አስቀድሞ ኢትዮጵያውያን ራሳቸውን፥ ቤተሰባቸውን፥ አገራቸውን፥ ሃይማኖታቸውን፥ ክብራቸውን ከማንኛውም ጥፋት፥ ከማንኛውም ውርደት ጠብቀው የኖሩት በዚህ ማንም በማይቋቋመው በእግዚአብሔር ኃይል ነው።

በአሁኑ ጊዜስ የኢትዮጵያ የሕዝቧ፥ የቤተ ክርስቲያንስ ሕይወት እንዴት ነው? ብዙ መናገር ይቻላል። ግን ተከድኖ ይብሰል ካላልን በስተቀር ምን እንዳለ እናውቃለን። ይልቁንም በቤተ ክርስቲያን አንጻር ትምህርተ ሃይማኖቷ ፈልሷል፤ ሥርዐቷ ፈርሷል፤ ሕጓ ተጥሷል፤ ክብሯ ተገሏል። የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች ዓለም እንኳ በማያደርገው ሥጋዊ ኀይል ታጥቀው ግድያን፥ ድብደባን፥ ምዝበራን፥ ልዩ ልዩ ቅሌትን ከማካሄዳቸውም በላይ ሲኖዶሷን በማፍረስ ስለ ተፈታተኗት ሕልውናዋ በሞትና በሕይወት መካከል ይገኛል። አቤቱታ የሚሰማ ዳኛ የለም። አቤት የሚሉ ይታፈናሉ። በጠላትነት የተሰለፉባት ልዩ ልዩ ተቃዋሚ የእምነት ድርጅቶች የራቁትን በገመድ፥ የቀረበውን በጫማ ስፍር በመከፋፈልና በሀገረ ስብከቷ ላይ አዲስ ዓለም ለመመሥረት በመዘጋጀት ላይ ሲሆኑ፤ የውስጥ መሪዎቿና ቤተሰቦቿ ደግሞ ከውስጥ ግድግዳዋን፥ ከውጪ አጥሯን እያፈረሱ ለጠላት በማስረከብ መቃብር እንኳ እንዲተርፉት አላደረጉም።

የሚገርመው በውስጥም ሆነ በውጭ ቆመው ክንድ ለክንድ ተደጋግፈው ቤተ ክርስቲያኒቱን ለማፍረስ የሚጣደፉ ሁሉ የራሷ የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆችና የልጅ ልጆች መሆናቸው ነው። የዘመኑ ትውልድ የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከነ ሃይማኖቷ፥ ከነ ሥርዐቷ፥ ከነ ምልክቷ፥ ከነ ታሪኳ የራሱንና የአባቶቹን ታሪክ ከርሷ ጋር ዐብሮ ገድሎ፥ ቀብሮ የዕዝን ለመብላትና እግዚአብሔር ያጥናችሁ ለመባል የተዘጋጀ መስሎ ነው **የሚታየው። ግን የቤተ ክርስቲያን ህልውና ከሌለ ገዳዩም፥ ማቹም ራሱ ዘመናዊው ትውልድ ነው። እግዚአብሔር ያጥናችሁ የሚናልም የለም። «እግዚአብሔር ያጥናችሁ የሚባል ሰው የለኝ፤ ኀዘንተኛዪቱም ሟቺቱም እኔው ነኝ፤» ትላለች ቤተ ክርስቲያን።**

ምእመናን! ስለ ክብራችሁ፥ ስለ ቤተ ክርስቲያናችሁ፥ ስለ አምላካችሁ ክብር በእነ አባ ጳውሎስ፥ በጳጳሳቶቻቸው፥ በአለቆቻቸው፥ በካህናቶቻቸው፥ በግብር አበሮቻቸው ጉልበት የተፈጸመውን

በደል በመዘርዘር፥ ልታደርጉት የሚገባችሁን በመዘከር አቤቱታ ማቅረብ ከጀመርኩ ድፍን ሁለት ዓመት ሆነኝ። አባ ጳውሎስና ግብር አበሮቻቸው ዓለም ሊያደርገው የሚጸየፈውንና የሚነቅፈውን፥ ሌላውን የሚነቅፍበትንና የሚከስበትን በደል ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ላይ ያለማቋረጥ እየፈጸሙ መንግሥትም ሕዝብን እነሱን ዐቅፎ፥ አዝሎ ከመንከባከብና እሹሩሩ ከማለት በስተቀር ለራሱም ሆነ ለአገሪቱ የሚበጅ ሥራ መሥራት አልቻለም።

እንግዲህ በእኔ በኩል አቤቱታዬን ሁሉን ማድረግ ለሚቻለው ለኢትዮጵያ አምላክ ማቅረብ ብቻ ነው። እናንተም ምእመናን ፈቃዳችሁ ከሆነ በፖለቲካ ስብከት የሚደረደርላችሁን ሁሉ ወደ ጎን ትታችሁ በዚህ የዐቢይ ጾም ወራት በየቀኑ ጧትና ማታ ለተወሰኑ ደቂቃዎች በኃያሉ አምላክ ፊት ስለ ቤተ ክርስቲያናችሁ፥ ስለ ሃይማኖታችሁ፥ በዚህ ምክንያትም ከሚመጣው ፍርድ ለመዳን በእግዚአብሔር ፊት በመቆምና አቤቱታ በማቅረብ እንድትተባበሩኝ በኢትዮጵያ አምላክ ስም እጠይቃችኋለሁ። ግን በአሁኑ ጊዜ ሁሉን ነገር እንደ ፌዝ በመቊጠር የዓለማዊ ቋንቋ ትርጒም በመስጠት በየስብሰባው የአንድ ደቂቃ የሕሊና ጸሎት እንደሚባለው ዐይነት አድርጋችሁ እንዳትወስዱትና እንዳይፈረድባችሁ ዐደራ እላለሁ።

ኀሙስ ማታ በስቅለቱ ዋዜማ ሌሊት በጌቴሴማኒ የአትክልት ቦታ ጌታ የተናገረውን ላስታውሳችሁ። *«ወደ ፈተና ወይም ወደ ጥፋት እንዳትገቡ ትጉ፤ ጸልዩ። መንፈስ ብርቱ ነው፤ ሥጋ ደካማ ነውና።»* ***«ትግሁ ወጸልዩ ከመ ኢትባዑ ውስተ መንሱት፤ እስመ መንፈስ ይፈቅድ ወሥጋ ይደክም።»*** (ማቴ፤ ፳፮፥ ፵፩።) ስለዚህ ዐሳቤን እንደ ፌዝ ሳትቈጥሩ በየቤታችሁም ሆነ በቤተ ክርስቲያን፥ በሆነው ስፍራ ሁሉ ቢቻል፤ «**ወአንበርኩ አንብዕየ፤**» ብሎ ነቢዩ እንደ ተናገረ ከዕንባ ጋር በየቀኑ ጧትና ማታ ዐምስት ዐምስት ደቂቃ በኢትዮጵያ አምላክ ፊት በጸሎት ቁሙ። ስለ ሀገራችን ጸልዩ። አትጠራጠሩ። የኢትዮጵያ አምላክ ለጸሎታችሁ መልስ ይሰጣል። ጥሪዬ ለኢትዮጵያውያን ሁሉ ነው።

«ንዑ ስምዑን እንግርክሙ ኵልክሙ እለ ትፈርህዎ ለእግዚአብሔር።» «እግዚአብሔርን የምትፈሩ፥ የምታመልኩ ሁሉ ልንገራችሁ፤ ኑ ስሙኝ።»

አለቃ አያሌው ታምሩ።
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ጉባኤ ዋና ሰብሳቢ።

(ማዕበል ጋዜጣ፥ የካቲት ፲፬ ቀን ፲፱፻፺ ዓ. ም.)

# ታሪክ ይናገራል፤ መልስም ይጠብቃል።

## (አለቃ አያሌው ታምሩ)

### (ማዕበል ጋዜጣ፤ መስከረም ፲፭ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ. ም. )

«ኢትዮጵያ እርስዎ ለሚመልኩት አምላክ ጸሎት ልታሳርግ አትችልም። ሌላው ዓለም እንደዚሁ ወደ እርስዎ አምላክ ሊጸልይ አይችልም። እርስዎ ከእግዚአብሔር ይልቅ ለሰውየው ለሙሶሊኒ የሚገዙ ሆነዋልና።»

**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤ አሜን።**

ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ ምእመናንና አባሎች እንደገና፥ ደግሞ እንደገና፥ አሁንም እንደገና አቤት እላለሁ። ጩኸቴ በውሃ ውስጥ እንደሚናገር ሰው ሰሚ ማጣቱ፥ ሁሉም ዝም ማለቱ አቤቱታዬን አይገታውም። ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውድቀት፥ ክብሯ ስለ መገሠሡ፥ ትምህርተ ሃይማኖቷ ስለ መፋለሱ፥ ነባር ሕንጻ ታሪኳ ስለ መፍረሱ፥ ሕጓ፥ ሥርዓቷ ስለ መጣሱ፥ ሰማንያ አሐዱ መጻሕፍቶቿ ስለ መደምሰሳቸው፥ ፓትርያርኳና ጳጳሳቶቿ፥ የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎችና ካህናት ተባብረው በላይዋ ስለ ማመፃቸው፥ ምእመናንና ሊቃውንት መናገር የሚገባቸው ሁሉም እየሰሙ እንዳልሰሙ፥ እያዩ እንዳላዩ ዝም በማለታቸው አሁንም እንደገና አቤቱታዬን አሰማሁ።

**«አፉሁ ለጻድቅ ይትሜሃር ጥበበ ወልሳኑ ይነብብ ጽድቀ።» «የጻድቅ ሰው አንደበቱ ጥበብን ይማራል፤ መላሱም እውነትን ይናገራል።»** ስለ እግዚአብሔር ክብር እውነቱን፥ እውነተኛውን መናገር በሚያስፈልግበት ጊዜ ዝም ማለት እግዚአብሔርን ያሳዝናል። ጌታችን አምላካችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዕለተ ሆሣዕና ወደ ቤተ መቅደስ በገባ ጊዜ ሕፃናት ሲያመሰግኑት የካህናት አለቆች ተቆጡ። ጌታም፤ «እነዚህ ዝም ቢሉ ድንጋዮች ይጮሃሉ፤» የሚል መልስ ሰጥቷቸዋል። (ሉቃ. ፲፱፥ ፵።) አዎ። ስለ እግዚአብሔር ክብር ሊናገሩ፥ ሊመሰክሩ የሚገባቸው በጊዜው እምቢ ካሉ ድንጋዮች ወይም ሌሎች ፍጥረታት ይናገራሉ። የሞዐብን ሰው በለአምን የተቀመጠባት አህያ ገሥፃዋለች። ስለ እግዚአብሔር ክብር መናገር፥ መመስከር የማይገባው፥ ከዚህ ጸጋ የሚከለከል በአንደበቱ እውነት የማይገኝበት የሐሰት አባት ሰይጣን ብቻ ነው። ጌታችን ወንጌልን ሲያስተምር በነበረበት ወቅት በሰንበት ቀን ወደ ምኩራብ ገብቶ ሳለ በስፍራው ጋኔን የያዘው ሰው ስለ ነበር በሰውየው ላይ ያደረው ጋኔን ስለ ጌታ ሊመሰክር ሊጀምር ጌታ፤ «ዝም በልና ውጣ፤» ብሎ እንደ ገሠፀው በወንጌል ተጽፏል። እንግዲህ ሊናገሩ

የሚገባቸው ዝም ቢሉ ወይም ሊናገሩ የሚገባቸውን የሚከለክሉ ቢኖሩ ሁለቱም የሚገባቸውን አላደረጉም ማለት ነው። ግን የእግዚአብሔርን ክብር እንዳይናገሩ የሚከለከሉ ሰይጣናት መሆናቸውን ልናውቅ ይገባል። (ማር. ፩፥ ፳፫ - ፳፯። ያለውን መመልከት ይጠቅማል።) ሰው ግን የእግዚአብሔርን ክብሩን ሊወርስ፥ ስሙን ሊቀድስ የተፈጠረ ስለ ሆነ በእግዚአብሔር ላይ ራሱን ሊወዘውዝ፥ ምላሱን ሊያስረዝም፥ ትከሻውን ሊያሳይ፥ ስለ እግዚአብሔር ስም ሊናገር፥ ሊመሰክር ሲገባው፥ ሲቻለውም ሊያፍርበትና ዝም ሊል አይገባም።

የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ለመግዛት የሚመኙ ቢኖሩም ዕድሉ የገጠማት ግብጽና ዕድሉ እየራቃት በትግል ላይ የምትኖረው የሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ተፈትነዋል ማለት ይቻላል። ሆኖም ከቀንበር ወደ ቀንበር እየተዛወረች የምትኖረው የግብጽ ቤተ ክርስቲያንም ብትሆን በኢትዮጵያ ላይ ለረጅም ጊዜ ሥልጣን ይዛ የመኖሯን ያህል ለኢትዮጵያ ምእመናን ያሳየችውና የምታሳየው ፍቅር እጅግ በጣም አነስተኛ ነው። እንዲያውም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በኢየሩሳሌም ባላት ይዞታ ላይ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን በባለ አደራነት ገብታ ራሷ ቀማኛ ሆና ከመገኘቷም በላይ ለሌሎች ከመስጠት ዐልፋ በቀሪው አነስተኛ ይዞታ ላይ የፈጠረችው ተንኮል እስከ አሁንም መዘዙ ያላለቀ በመሆኑ የሁለቱ እኅትማማች አብያተ ክርስቲያናት ግንኙነት ባሳዛኝ ሁኔታ ላይ ይገኛል።

ነገሩ ከውሥጥም ከውጭም ብዙ ግፊት ያለው ቢሆንም በ፲፱፻፴፯ ዓ.ም. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተሰይሞ የነበረው መንፈሳዊ ጉባኤም ከግብጽ ጋር የነበረው ግንኙነት ፍጻሜ አግኝቶ፤ «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በራሷ ልጆች እንድትመራ ያስፈልጋል፤» ወደሚለው ፍጻሜ ለመድረስ ያስገደደው ይህ ከዚህ በላይ የጠቀስነው ሁኔታ ነበር አንጂ በግብጽ ላይ በሌሎች ምክንያት ያጣችውን የገዢነት ሥልጣን በኢትዮጵያ ላይ እንድታስፋፋ በሰባኪዎቿ፥ በመልእክተኞቿ፥ ከዚያም ዐልፎ በጦረኞቿ ስትታገል ለኖረችው ለሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አመቻችቶ ለመስጠት አልነበረም። የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ኢትዮጵያን እጅ ለማድረግ ባደረገችው የረጅም ጊዜ ትግል ይልቁንም ከ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. - ፲፱፻፴፫ ዓ. ም. ከሙሶሊኒ ጋር ተባብራ በጥቁር ሸሚዝ ለባሽ ፋሺስት ጦረኛዋ የፈጸመችው ግፍ፥ በተከለከለ የመርዝ ጋዝና የአውሮፕላን ድብደባ የኢትዮጵያን ሕዝብ በመጨረስ ያሳየችው ጎምዛዛና መራር አድራጎት እንኳን ለኢትዮጵያውያን ለባዕዳን ሕሊና የሚሰቀጥጥ እንደ ነበር ታሪክ መዝግቦታል።

በጊዜው ያልነበረ ሊያውቀው ሊረዳው አይችል ይሆናል። እኔ ግን በጊዜው በልጅነት ዕድሜዬ የነበርኩባት አገሬ ዲማ ጊዮርጊስ በአውሮፕላን ከዐርባ ቀን በላይ ስትደበደብ ከላይ የአውሮፕላን ከታች የመድፍ፥ የመትረየስ ድምፅ ምድሪቱን ሲያንቀጠቅጣት በነበረ ጊዜ ከዚያው ስለ ነበርኩ አሁንም ትዝታው ያስጨንቀኛል። ይልቁንም በ፲፱፻፴፩ ዓ. ም. ነሐሴ ፲፪ ቀን እኔና የልጅነት ዕድሜ ጓደኞቼ ከቤተ ክርስቲያን ውሥጥ በቅሎ ባደገው ሣር እየተሳሰርን ስንጫወት አቶ አየለ ኀይሉ የተባሉ ምእመን ቤተ ክርስቲያን ለመሳለም መጥተው እኛ ከምንጫወትበት ዘንድ ሰፊ ድንጋይ ስለ ነበር የሣሩን ጤዛና የመሬቱን ጭቃ ሸሽተው ዘንጋቸውን ተመርኩዘው ከድንጋዩ ላይ ቆመው ዳዊት ይደግሙ ነበር። እኛ በጨዋታችን ላይ በጤዛው እየተነከርን፥ በጭቃው እየተለወስን ስንጫወትና ስናስቸግራቸው አንዳንድ ጊዜ ጸሎታቸውን እያቋረጡ ይገሥፁን

ነበር። እኛ ግን ጨዋታችንን ስለ ቀጠልን ሁለቱ ጓደኞቼ ሰውየው ከቆሙበት ድንጋይ ሥር ጥለው እንደ ብራና ወጥረው ከግራና ከቀኝ ሣሩን እያስተላለፉ አሰሩኝ። እጆቼን ግራና ቀኝ ዘርግተው በጀርባዬ አንጋለው እግሮቼን ገጥመው በቁመት አምስት ላይ ሁለቱን እጆቼን ጨምሮ በጠቅላላው ከሰባት ላይ አስረው ጥለውኝ ሄዱ። እኔም ያንን ሁሉ ለመፍታትም ሆነ ለመቁረጥ ዐቅም አልነበረኝም። ሰውየው ወደ ጸሎታቸው እንጂ ወደ እኔ አልተመለሱም። ጊዜው ከቀኑ ፫ ሰዓት ይሆናል። የክረምት ፀሐይ ብልጭ ብላለች። እኔንም ለጨዋታና ለድንጋጤ የጋበዘችኝ እሷው ነበረች። የፍልሰታ ቤተ ክርስቲያን ሳሚ ሕዝብ እንዲሁም በዕለቱ አንድ ሰው ሞቶ ነበርና ከሩቅም ከቅርብም የመጣው ሕዝብ በቤተ ክርስቲያኑ ግቢ ሙሉ ነበር። አቶ አየለ ኀይሉም ነጭ ልብሳቸውን ለብሰው ዘንጋቸውን ተመርኩዘው ከድንጋያቸው ላይ ቆመው ዳዊታቸውን ይደግሙ ነበር። ከአፍ የወደቀች ጥሬ የምታህለው ሕፃን አያሌው ታምሩም በበቀለው እንግጫ፥ ሙርጅና አክርማ ከመሬት ጋር ተጣብቃ ታስራ እንደ ቅሪላ ትለፋ ነበር። በድንገት የሚያስገመግም ድምፅ ተሰማ። የጣሊያን ቦምብ ጣይ አውሮፕላን ነበር። ሕዝቡም አልጠረጠረውም ነበር። እንደ ደረሰም ነጭ ልብስ ለብሰው በቆሙት ዳዊት ደጋሚ ላይና ከእግራቸው ሥር በበቀለው ሣር ታስራና ተጠፍራ፥ እንደ ብራና ተወጥራ ከመሬት ላይ ተለጥፋና ተዘርግታ በነበረችው ሕፃን አያሌው ታምሩ ላይ ቦምቡን አዘነበው። ኀይሉም አየለ ኀይሉን ከቆሙበት አንሥቶ ከቤተ ክርስቲያኑ ዕቃ ቤት ግቢ ውሥጥ ሲጥላቸው ድንጋዩም ተፈንቅሎ ተከተሏቸው ሄዶ ከዕቃ ቤቱ ግቢ በር ላይ ወደቀ። የአካባቢውም መሬት ተገለባበጠ። ተስፋ የለሽ አያሌውም በሊቀ መላእክት በቅዱስ ሚካኤል በሰማዕቱ በቅዱስ ጊዮርጊስ ይልቁንም አምላክን በወለደች በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት ቸር እግዚአብሔር ባደረገላት ተአምራት ከሞት ተርፋ በመሬቱ መገለባበጥ ከእስራቷ ተፈታ በቀኝ እጇ የታሰረችበትን ሣር ግን ከነጉሊቱ ተሸክማ ከወደቀችበት ተነሥታ ወደ ቤተ ክርስቲያን ገብታ ተጠለለች። አየለ ኀይሉ ሞቱ። አያሌው በአስደናቂ ተአምራት ከሞት ዳነች።

ያቺ ሕፃን ናት ከታሪክ ጋር ቆማ ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፥ ስለ ምእመናኖቿ የሮማን ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የምትሟገት፤ አባ ጳውሎስንም ከሮም ጋር በመተባበር በፈጸሙት ደባ የምትከስ፥ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳት፥ ሊቃውንት ለቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎችና ካህናት፥ ለሰበካ ጉባኤ አባላትና ለምእመናን በጠቅላላውም ለኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎችና ካህናት፥ ለሰበካ ጉባኤ አባላትና ለምእመናን፥ በጠቅላላውም ለኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባሎች ልጆችና አባቶች አቤቱታዋን ባለ ማቋረጥ የምታቀርበው ያን ጊዜ በተአምራት ከሞት የተረፈችው ሕፃን ናት። ዛሬም የእግዚአብሔር የተአምራት ምርኮኛው አለቃ አያሌው ታምሩ ነኝ። የእኔን ከነገርኳችሁ በሌላ በኩል የተመዘገበውን ታሪክ ደግሞ ላሳያችሁ በሚከተለው ተመልከቱ።

«ከዚህ ላይ ለቤተ ክርስቲያን ታሪክ አስከፊና አሳፋሪ ሁኖ የሚታየው የኢትዮጵያን ሕዝብ ለመደምሰስ ቫቲካን ከሙሶሊኒ ጋር መተባበሩ ነው። እንዲያውም ከሙሶሊኒ ጎን ተሰልፈው ምክር ይሰጡ የነበሩና ብዙ ካህናትንም ያስፈጁ የወታደር ልብስ ለብሰው የመጡ የሮማ ካቶሊክ ቄሶች ናቸው ይባላል። ፓፓውም የተቀደሰ ዘመቻ ነው ብለው መድፉንና ታንኩን ባርከዋል። በዚህ ሁሉ ድርጊታቸውም በዓለም ክርስቲያኖች ዘንድ ተነቅፈውበታል።

ከብዙዎቹም መካከል ኤሊክ ሲንድሩም የሚባሉት የስዊድን ጋዜጠኛ ፓፓውን እንዴት እንደ ወቀሷቸው (ሲሞን ረስቲን የተረጎመውን) ከዚህ ቀጥለን እናቀርባለን። «ቅዱስ ሆይ፤ እኔ በሰሜን አገር የተወለድሁ አንድ ፕሮቴስታንት ነኝ። ባገራችንም በስዊድን በግንባራችን የምንደፋው በእልፍኛችን ሁነን ከእግዚአብሔር ከአምላካችን ጋር ስንናገር ነው እንጂ ከሰው ጋር ብንናገር ቁመን እንነጋገራለንና በእግርዎ ላይ ወድቄ ጫማዎን ስለማልስምዎ አይቆጡብኝ። ቅዱስ ሆይ፤ እኔ አንድ ምስኪን ኃጢአተኛ፤ እርስዎ ግን የመድኀኒታችን ምትክ የማይሳሳቱም ኖት፤ ይሁን እንጂ እኔ እነቅፍዎታለሁ። እርስዎ የካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ዋና ነዎት፤ ካቶሊካዊት ማለትም የሁሉም ማለት ነው። ዛሬ እንግዲህ የርስዎ ቤተ ክርስቲያን በእውነት የሁሉ ቤተ ክርስቲያን ናት? እርስዎ ከሙሶሊኒ ጋር ሆነው ከሌላው ዓለም ጋር በጠብ አሉ። እርስዎና ከርስዎ በታች ያሉት ሌሎችም ጳጳሳት ኢትዮጵያ ለኢጣሊያ ቅኝ አገር እንድትሆን የሚገባ ነው ብለው ተናገሩ። እርስዎ መቼም የሐዋርያው የጴጥሮስ ተከታይ ነዎትና አይሳሳቱም። እንግዲህ ሌላው ዓለም ሁሉ ቃልዎን ሳይሰማ በኢጣልያ ላይ «ሳንክሲዮ» ቢያደርግ መሳሳቱ ነው? ቅዱስ ሆይ፤ ኢጣሊያ የፍርድ ሥራ ትሠራለች ብለው ሰብከዋል።

የመሲና የቢረንዲቤም ጳጳሳት ወርቃቸውን ሁሉ ለጦርነቱ ኪሳራ እንደ ሰጡ ሰማን። እናንተ ጳጳሳት ይህንን ስታደርጉ እግዚአብሔር ከኢጣሊያ ጋር ነው የማለት ያህል ይመስለኛል። እንግዲህ ሌላው ዓለም ሁሉ የኢጣሊያን ሥራ ቢቃወም የእግዚአብሔርን ፍርድ ይቃወም ይሆን? ኢትዮጵያስ አገራቸውን ሲጠብቁ በእግዚአብሔር ላይ ተነሥተው ይህንን እርስዎ እንዳሉ ኢጣሊያ የጽድቅ ውጊያ የምትዋጋ ከሆነ ሌላውም ዓለም ይህንን የጽድቅ ጦርነት ቢቃወም መቼም ከእናንተ በቀር ሌላው ዓለም ሁሉ እግዚአብሔርን የካደ ይመስላል። እንግዲህ እርስዎ እንደሚሉት እግዚአብሔር አምላካችን የኢጣሊያ መንግሥት ቃሉን ሊያፈርስ፥ መሐላውንም ሊሰብር ፈቅዷል። እርስዎ እንደሚሉት የኢትዮጵያ ሰዎች አገራቸውን ለመጠበቅ ቢሰበሰቡ የኢጣሊያ አውሮፕላን ጥርግ አድርጎ ቢያጠፋቸው እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሥራ ነው። ሴቶችንና ሕፃናትን በቦምብ ሲያጠፉ እግዚአብሔርን ያገለግላሉ። ይህንን ሁሉ ካሁን በፊት በመጽሐፍ ቅዱስ አላገኘንም ነበርና እርስዎ አሁን ስላስተማሩን ትልቅ ነገር ነው።

ይህንን ሁሉ የምታስተምረን ቅድስቲቱ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ናት። በዱሮ ዘመን ግን ቤተ ክርስቲያን ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር መታዘዝ ይገባል ብላ ታስተምር ነበር። ቅዱስ ሆይ፤ የእርስዎ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት አይደለችም፤ የሁሉም አይደለችም። እግዚአብሔር መሐላን ማፍረስ ይወዳል ብለው ቢያስተምሩን ውሸትዎን ነው ብለን እንመልስልዎታለን። እርስዎም የዓለም ሁሉ አባት ነኝ ሲሉ የሙሶሊኒ ባርያ ሁነዋል። በኢጣሊያ ላይ ሥጋዊ «ሳንክሲዮ» ማድረግ የግድ ነው። እርስዎ የሚያመልኩት አምላክ ጣዖት ነው እንጂ አምላክ አይደለም። ኢትዮጵያ እርስዎ ለሚያመልኩት አምላክ ጸሎት ልታሳርግ አትችልም። ሌላው ዓለም እንደዚሁ ወደ እርስዎ አምላክ ሊጸልይ አይችልም። እርስዎ ከእግዚአብሔር ይልቅ ለሰውየው ለሙሶሊኒ የሚታዘዙ ሆነዋልና። እርስዎ መናገር በተገባዎ ጊዜ ዝም አሉ፤ ዝም ማለት በተገባዎ ጊዜ ተናገሩ። አሁንም ከሌሎች ጳጳሳት ጋር የሙሶሊኒን ጫማ ስመዋል።

የዓለምን ሰላም የሚያውከውን ወንበዴውን ቢያወግዙት ኖሮ ለቤተ ክርስቲያንዎ እንዴት ያለ ጥቅም በሆነ ነበር። ምናልባት እርስዎም በታሰሩ ነበር። ምናልባትም እንደ ድሮ ዘመን

ክርስቲያኖች ወደ ሰማዕትነት ሞት በደረሱ ነበር። ዓለም ሁሉ ከርስዎ ጋር በሆነ ነበር። ክርስቲያን ቢሆን አረመኔም ቢሆን ሰው ሁሉ እርስዎ የእግዚአብሔር አገልጋ እንደ ሆኑ በተረዳ ነበር። አሁንም በቅርብ የገና በዓል ነው። ለግፍ ጦርነት ወርቃቸውን የሰጡ ጳጳሳትም እንግዲህ ለእግዚአብሔር ክብር ይሁን በምድር ላይ ሰላም ይሁን ለሰውም በጎ ፈቃድ ይሁን ብለው ሊዘምሩ ናቸው። ይህንንም ሲዘምሩ በደረታቸው የወርቅ መስቀል ሳያደርጉ አይቀርም። ነገር ግን በጀርባቸው ላይ የእንጨት መስቀል ቢሸከሙ ይሻል ነበር። ቅዱስ ሆይ፤ በዓሉን ያሳምርልዎ ብዬ ምኞቴን እገልጻለሁ።» ይህ የጭካኔ ድርጊት በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል እንደ ትልቅ ገደል ሆኖ ይኖራል።»

ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት፥ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት፥ ክቡራን ሊቃውንት፥ የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎችና የሰበካ ጉባኤ አባላት፥ ቀሳውስት፥ ዲያቆናት መምህራንና ደቀ መዛሙርት፥ የተወደዳችሁ ምእመናን! መላው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባሎች አባቶችና ልጆች! ከዚህ በላይ የተጻፈውን ታሪክ ተመልከታችሁ ታሪክ እየተናገረ ስለ ሆነ ሁላችሁም በየራሳችሁ መልስ እንድትሰጡት ትጠየቃላችሁ። ፋሺስቶች በኢትየጵያ ላይ ምን ምን እንደ ፈጸሙ በኢትዮጵያ ያለ ሰው ብቻ ሳይሆን እንስሳው፥ አውሬው፥ ወፉ፥ አሞራው፥ እንጨቱ፥ ድንጋዩ፥ ሣሩ፥ ቅጠሉ፥ ቆላ፥ ደጋው፥ ተራራው፥ ኮረብታው፥ ሜዳው ጎድጓዳው የሚመሰክረው ነው። የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አፍአውያንና ውሣጣውያን ጦረኞቿን አስታጥቃና አሰልፋ በኢትዮጵያ ላይ ሥውርና ግልጥ ጦርነት ማድረግ ከጀመረችበት ጊዜ ጀምሮ የፈጸመችውንና ታሪክ የመዘገበውን ሁሉ በዚህ ጠባብ ዐምድና ጊዜ መግለጥ ባይቻልም በፋሺስቶች ጊዜ የተፈጸመውን ስዊድናዊው ጸሐፊ ከተመለከቱት፥ ከገመገሙት፥ ከመዘኑት ሁኔታ የተነሣ፤ «እርስዎ ለሚያመልኩት አምላክ ኢትዮጵያ ጸሎት አታሳርግም፤ መላው ዓለምም ጸሎት አያሳርግም።

እርስዎ የሚያመልኩት አምላክ ጣዖት ነው፤» ከማለታቸውም በላይ፤ «ይህ የጭካኔ ድርጊት በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል እንደ ትልቅ ገደል ሁኖ ይኖራል፤» ብለዋል። አስደናቂ ነው። ቁንጥጫው ያልደረሰባቸው፥ በኢትዮጵያ ላይ የተፈጸመው ግፍ እጅግ ያስጨነቃቸው ሰዎች ይህን ያህል የሚናገሩ ከሆነ ኢትዮጵያውያን ለሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ቤተሰብ መሆናቸው፥ ቤተሰብ ለመሆን መጣራቸው፥ ለስሟ ለክብሯ ሽንጣቸውን ገትረው መቆማቸው፥ መሚገታቸው፥ እናታቸውን ኢትዮጵያንም በሷ ፍቅር መለወጣቸው፥ በኢትዮጵያና በሷ መሐከል የኖረውን ታላቅ ገደል ማን በምን ቆፍሮና ደልድሎ አስተካክሎት ነው? ያንንስ በመካከላቸው በኢትዮጵያውያን ዐጽምና ደም የታነጸውን ሰማይ ጠቀስ ግንብ ማን ንዶ ከመንገድ አስለቅቆት ነው? ያ ግንብ እኮ የባቢሎን ግንብ አይደለም። ዛሬም ነገም የሚኖር፥ ምን ጊዜም የማይናድ ግንብ ነው። ተሰዓቱ ቅዱሳን አበው የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን ጥርስ ሸሽተው በእግዚአብሔር ስምና ሥልጣን በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ወደምትታደጋቸውና ወደምትጠብቃቸው ወደ ኢትዮጵያ ገቡ። ሁሉም ገድላቸውን ጨርሰው በሰላም ወደሚፈልጉት አዲስ ሕይወት ገቡ። በሥዋሬ ያሉም አሉ፤ ወደ ሌላ ዓለም ያለፉም አሉ።

**ዛሬ ፓትርያርክ አቡነ ጳውሎስ አክሊለ ክብራቸውን ተሸክመው ለሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ያለ ጦርነት ተማርከው እጃቸውን ሲሰጡ፥ በተራ ምእመን ደረጃ ከካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን**

**እግረ መንበር ሥር ተቀምጠው የልዮንን ተወካይ ቡራኬ ሲቀበሉ እነ አቡነ ገሪማ፥ እነ አቡነ አረጋዊ ተሰዓቱ ቅዱሳን አበው በጠቅላላው፥ የገዳማተ ትግሬ ቅዱሳን፥ የመላዋም ኢትዮጵያ አበው አይታዘቧቸው ይሆን?** መቼም በምድር ላይ የክርስቶስ እንደራሴ ለተባለው የሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ፓፓ ራሳቸውን አሳፈው ሰጥተዋልና፥ በእምነቱም መሠረት ግዴታ መወጣት የተለመደ ነውና ምናልባት ቫቲካን አቡነ ጳውሎስን በመንግሥቴ ላይ ዐምፀው ወደ ኢትዮጵያ የገቡትን ያሉትን በሕይወታቸው፥ የሞቱትንም ከመቃብራቸው ማምጣት አለብዎ ብላ ብትጠይቃቸው መልሳቸው ምን ይሆን? የዕውቀት ፍጻሜ ነው ብለው የያዙት ፈሊጥ ነውና ምናልባትም ለእኔ ጥያቄ ዝም እንዳሉ ያንንም በዝምታ ያልፉት ይሆን? አይመስለኝም። ይህማ እንዳይሆን ከዚያ ወዲህ የክሕደት፥ የኑፋቄ መጽሐፍ በመሳተምና በመበተን፥ ኦርቶዶክሳዊውን የሊቃውንት ጉባኤ በማፍረስ፥ በቤተ ክርስቲያን ሕግ የቆመውን፥ በቃል ኪዳን በወልደ እግዚአብሔር ደም ምለው ተጠሪ የሆኑለትን ኦርቶዶክሳዊውን የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ በማፍረስ በሮም ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት አመራር ሰጪ የሆኑለትን፥ ለራሳቸው ተጠሪ ያደረጉትን ሚያዝያ ፴ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ. ም. በተፈረመ ሕገ ጣዖት ሰው ሠራሽ ሲኖዶስ በማቋቋም ታላቅ ማረጋገጫ የሰጡ ስለ ሆነ የቫቲካንን ጥያቄ በቸልታ የሚያልፉት አይመስልም። በሕይወት ያሉት የነ አቡነ ገሪማ፥ የነ አቡነ አረጋዊ፥ የነ አቡነ ዮሐኒ ሕይወት የማያሰጋ ቢሆንም በልዩ ልዩ ገዳማተ ትግሬ ያረፈው የልዩ ልዩ ቅዱሳን አበው ዐጽም እየተቆፈረ ለሮማ ቤተ ክርስቲያን ገጸ በረከት እንዳይሰጥ ታላቁና ሃይማኖታዊው የትግሬ ክርስቲያን ሕዝብ ማስተዋል የተሞላበት ጥንቃቄ እንዲደርግ ያሻል። በኢያሱ ዘመን እርም የሆነውን ደብቆ የተገኘ አካን ወልደ ከርሚ በሕዝቡ ላይ ብርቱ ጥፋት አስከትሎ እንደ ነበር መጽሐፍ ይናገራል። አቡነ ጳውሎም እርም የሆነውን፥ ከሮማ ጋር የተከለከለውን ግኙነት ከተሾሙባቸው ክርስቲያኖች ደብቀው በፈጸሙት ሥራ ሁሉ ሕዝባቸውን ለጥፋት እያጋለጡ ነው።

አበው ጳጳሳት! ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ አራት ታላላቅ ሌላም ጥቃቅን ሃይማኖቶች አርግዛ እያማጠችና እየተጨነቀች ነው። እንኳን ይህን ያህል ሽል ሁለት መፅነስ ክብደቱ ምን ያህል እንደ ሆነ በርብቃና በትዕማር ታሪክ የታወቀ ነው። ይህ ብዙ ሃይማኖትን በአንድ ጊዜ ማርገዝ በኢትዮጵያ ብቻ ለሙከራ የቀረበ ሲሆን ሽሎቹ በመታገል ላይ መሆናቸውና ይልቁንም አንዱ እንደ ፋሬስ ጥሶ ለመውጣትና ብኵርናውን ለመውሰድ እየታገለና ወላዲቱንም እያስጨነቃት መሆኑ እየታየ ነው።

አበው ጳጳሳት፥ መነኮሳት፥ ሊቃውንት፥ ቀሳውስት፥ እናቶች፥ አባቶች! ሌላው ቢቀር ተሰብስባችሁ ማርያም ማርያም ብትሉ አይሻልምን? ኧረ ዝምታው አያዋጣም። አሁን እኔ አይደለሁም የምናገር። ታሪክ ነው የሚናገር። ስዊድናዊው ታላቅ ጸሐፊ የመዘገቡላችሁን ካነበባችሁ በኋላ፤ **«እርስዎ ለሚያመልኩት አምላክ ኢትዮጵያ ጸሎት ልታሳርግ አትችልም፤»** ያሉትን አስታውሳችሁ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ለሰበከችው፥ አቡነ ጳውሎስ ለተቀበሉት፥ ሰው ሠራሽ ሲኖዶስ ላቆሙለት ሰው ሠራሽ ሃይማኖት እንዳትንበረከኩ መላው የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ጎሣ ቋንቋ ሳይለያችሁ ለሃይማኖታችሁ አንድ ሆናችሁ እንድትቆሙ፤ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃማኖታችሁን ያፋለሱትን፥ የቤተ ክርስቲያናችሁን ክብር የገሠሡትን

አቡነ ጳውሎስን በአንድ ቃል እንድትቃወሙ ወርቀ ደሙን ዋጋ፥ መስቀሉን የድል ገበያ አድርጎ በደሙ በዋጃችሁ በኢትዮጵያ አምላክ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እጠይቃችኋለሁ።

እንዲሁም የመስቀሉ ጠላቶች ሲሆኑ በአንገታቸው መስቀል አድርገው፥ በእጃቸው መስቀል ጨብጠው ከሚታዩት ከአቡነ ጳውሎስና ከአቡነ ገሪማ፥ ከደጋፊዎቻቸውም ጋር የመስቀልን የደመራ በዓል እንዳታከብሩ ለአባቶች ለሐዋርያት ለእኔም በተሰጠው በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ሥልጣን ገዝቼአለሁ። በዚህ ፈንታ በየደጃችሁ ቤተሰብ ከቤተሰብ፥ ጎረቤት ከጎረቤት ተባብራችሁ በዓላችሁ በጸጥታ አክብሩ። በበዓሉ ላይም ፲፪ ጊዜ እግዚኦታ፥ ፲፪ ጊዜ በእንተ ማርያም፥ ፲፪ ኪራላይሶን አድርሱ። በዓላችሁ በጸሎት፥ በኀዘን የተጠበቀ ይሁን።

ያለነው እጅግ በሚያዝን ሁኔታ ውሥጥ ነው። ሃይማኖት በሌለበት ዓለምም ሰላምም አሉ ማለት አይቻልም። ሰላም ደግሞ ከዓለም የሚገኝ ስጦታ አይደለም። ሰላም ከእግዚአብሔር የሚገኝ ስጦታ ነው። እግዚአብሔር የሌለው ሰላም የለውም። ይህ ደግሞ የሚያከራክር አይደለም። ኢትዮጵያ ከእግዚአብሔር ጋር በሃይማኖት ጸንታ የኖረችበትን ረጅም ዘመንና ከሱ ተለይታ ወደ ፖለቲካ ገበያ ገብታ የሃይማኖት ሽቀጥ እያማረጠች ያለችበትን ከለውጥ ወዲህ ያለውን ዘመን በሚዛን ላይ አድርጎ መመልከት ይቻላል። ስለዚህ ሰው ምንም ሊያደርግ የማይችልበት የመከራ ሌሊት ነግቶ የሃይማኖት ብርሃን ወደሚታይበት ጊዜ ለመድረስ እጅግ በጣም አጥብቆ መጸለይ ያስፈልጋል። ትጉ ጸልዩ። ሃይማኖታችሁን ጠብቁ።

የእግዚአብሔር አብ ጸጋ፥ የእግዚአብሔር ወልድ ቸርነት፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ፍቅር ከእናንተ ጋር ይሁን።

**አለቃ አያሌው ታምሩ ዘዲማ ጊዮርጊስ፤ የኦርቶዶክሳዊው የሊቃውንት ጉባኤ ሰብሳቢ።**

**(ማዕበል ጋዜጣ፤ መስከረም ፲፩ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ. ም. )**

# በዓለ ጥምቀት።

## (አለቃ አያሌው ታምሩ)

### (ኢትኦጵ ጋዜጣ ጥር ፲፪ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ. ም.)

(ኢትኦጵ ጋዜጣ ጥር ፲፪ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ. ም.)

ሊቀ ሊቃውንት አያሌው ታምሩ ትናንት የተከበረውን የጥምቀት በዓል ምክንያት በማድረግ ለምእመናን መልእክት አስተላልፈዋል። አቡነ ጳውሎስ የካቶሊኩ ካርዲናል ከዚህ ዓለም በሞት በተለዩበት ወቅት በቀብር ሥነ ሥርዐቱ ላይ በመገኘት የሰጡት ቡራኬ ሃይማኖቱን የጣሰ ነው ሲሉም በዝርዝር ተችተዋል። የአለቃ አያሌው ሙሉ መልእክት ቀጥሎ ቀርቧል።

## በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ።

ልዩ ሦስት አንድ አምላክ በሚሆን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እንባርካለን፤ መልእክታችንንም እንጀምራለን። «**ይቤ እግዚአብሔር ወፂእየ እገብእ ወእትመየጥ እንተ ቀላየ ባሕር።**»

የጥምቀት በዓል ከአባቶቻችን ዘመን ጀምሮ በኢትዮጵያ በታላቅ ሥነ ሥርዐት ከሚከበሩት በዓላት አንዱ ነው። ስለዚህ የኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን በየትኛውም ሥፍራ ብትሆኑ እንኳን ለዚህ በዓል አደረሳችሁ እላለሁ። በነቢያትም በልዩ ልዩ ሥፍራ በትንቢት እንደ ተጠቀሰው ነቢዩ ዳዊት፤ «**ይቤ እግዚአብሔር ወፂእየ እገብእ ወእትመየጥ እንተ ቀላየ ባሕር።**» «እስራኤልን ይዤ ከወንዝ ከወጣሁ በኋላ እንደገና ወደ ጥልቁ ባሕር እመለሳለሁ ብሏል እግዚአብሔር፤» ይላል። ጌታ እስራኤልን በሙሴ መሪነት ቀይ ባሕርን ከፍሎ ካስገባቸው በኋላ በኢያሱ መሪነት ደግሞ ዮርዳኖስን ከፍሎ አሻግሯቸዋል። ቀደም ሲል ከሦስት ቀን በፊት ኢያሱን ቀስቅሶ ሕዝቡ ከሦስት ቀን በኋላ ዮርዳኖስን ስለሚሻገር ተዘጋጅ የሚል ትእዛዝ ሰጠው። በሦስተኛው ቀን ታቦተ ጽዮንን የተሸከሙ ካህናት ቀድመው ሕዝቡ ተከትሎ ሺ ሜትር ያህል ርቆ እያጀበ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ገቡ። የካህናት እግር ውሃውን ሲረግጥ ውሃው ከመውረድ ተገታ። ጊዜው በሀገሩ ሥነ ሥርዐት ክረምት ስለ ነበረ ውሃው ተርፎ ይፈሳል ነገር ግን የካህናት እግር ሲረግጠው ውሃው ተቋረጠ። ወደ ታች ያለው ጨው ባሕር ገብቶ አለቀ። ወደ ላይ ያለው ግን ተቆልሎ ይታይ ነበር ይባላል። ይህን በመሰለ ኀይል ነው ዮርዳኖስን ያሻገራቸው።

ይህ ተአምራት ከሆነ ከሺ ፭፻ ዓመት በኋላ ጌታ ሰው ሆኖ ሥጋ ለብሶ ወደ ዓለም መጣ። በ፴ ዘመኑ በእደ ዮርዳኖስ በዮርዳኖስ ወንዝ በዚሁ እስራኤል በተሻገሩበት ወንዝ ላይ ተጠምቆ ከአባቱ ፥ ከመንፈስ ቅዱስ የባሕርይ ልጅነቱን፥ አምላክነቱን አስመስክሮ ይህን በዓል መሥርቶታል። በወንጌል እንደ ተጻፈው፤ ተጠምቆ ከውሃው ወጥቶ ሲጸልይ ሰማይ ተከፈተ። የሚያስደንቅ ቃል ነው። እስከዚህ ዘመን ድረስ ወይም ከዚያ ዘመን በኋላ ሰማይ ተከፈተ የሚል ቃል ተጽፎ አናገኝም። ሰማይ ተከፈተ፤ መንፈስ ቅዱስም በርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ ዐረፈ። «የምወደው ልጄ ይህ ነው፤» የሚል የእግዚአብሔር አብ የምስክርነት ቃልና ዐዋጅ፤ «እሱን ስሙት፤» ከሚል መልእክት ጋር ተላለፈ። ከዚያ ጊዜ ከምሮ ሰውና እግዚአብሔር ፊት ለፊት የተያዩበት ነው።

ስለዚህም ይህን በዓል የምናከብረው። የበዓሉ አከባበርም ከሌሎች በዓላት ሥርዐት ለየት ያለ መልክ አለው። ይህ በዓል ኢትዮጵያ ሁለት ጊዜ ያከበረችው ነው። አንደኛ በብሉይ ኪዳን በበዓለ መፀለት ሥርዐት ከቤት ወጥቶ፥ ወንዝ ወርዶ፥ ወይንም ድንኳን ተክሎ በማኅበር የመከሩን መጨረሻ ዘመን ማክበር የተለመደ ሥርዐት ነበር። አሁን ግን ያ በጥምቀት በዓል ተለወጠ። ጌታ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ወረደና ዮሐንስ ወዳለበት ሄደ። ከዚያም በዮሐንስ ተጠመቀ። በዮሐንስ እጅ ይጠመቁ የነበሩ ሰዎችም እዚያው ስለ ነበሩ ይህ በዓል በየዓመቱ መታሰቢያቸውን በነበረበት መልኩ ለማቆየት ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ ቤተ ክርስቲያን ከወንዝ ወርዳ፥ ድንኳን ጥላ ታከብረዋለች። በዚህም ትንቢት ሁሉ መፈጸሙን ታረጋግጣለች። ቀደም ብዬ እንደ ተናገርኩት የትንቢቱ መሠረት እስራኤል ወንዝ ከፍለው መሻገራቸው ሲሆን ፍጻሜውም የጌታ ጥምቀት መሆኑ ነው። እስራኤል ዮርዳኖስ ተከፍሎላቸው ወደ ምድረ ርስት እንደ ገቡ ጌታም ጥምቀትን ባርኮ ወደ መንግሥተ ሰማያት ለሚሸጋገሩ ምእመናን ሁሉ በር መክፈቱ ነው።

እርግጥ ሠሪና ተቀባይ ሥርዐታቸው እኩል አይደለም። ጌታ ሠሪ ስለ ሆነ ሁሉን ነገር ከ፴ ዘመን በኋላ ነው ያከናወነው። ከግዝረትና ወደ ቤተ እግዚአብሔር ከመግባት በስተቀር የቀረው ሁሉ ከ፴ ዘመን በኋላ በሥነ ሥርዐት የተፈጸመ ነው። የተጠመቀውም በ፴ ዘመኑ ነው። ለእኛ ግን በ፵ ቀን፥ በ፹ ቀን ነው ጥምቀት የተሰጠን። ይህም በኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ ፲፪ ስለ ወላዲቱ በተጻፈው ተደንግጓል። እግዚአብሔር የሰጠው ትእዛዝ ነው። መጀመሪያ ለሙሴ የሰጠውን ትእዛዝ ሰው ሆኖ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ በሥጋ በተገለጠ ጊዜ በ፵ ቀኑ ወደ ቤተ እግዚአብሔር በመግባት አጽንቶታል። በ፵ ቀን፥ በ፹ ቀን ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ፥ ከማሕፀነ ዮርዳኖስ ወይንም ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ለሚወለዱ ሁሉ መሠረት አድርጎታል። ይህንንም በ፴ ዘመኑ አጽንቶታል። ምክንያቱም እሱ የሚጠመቅ ለአባትነት ነው፤ ወላጅ ነው። እኛ ግን የምንጠመቀው ለልጅነት ነው። ስለዚህም እኛ በ፵ ቀን፥ በ፹ ቀን እንጠመቃለን። ከዚህ ያለፈ ቢመጣም አልተከለከለም። የጥምቀት ሥርዐት በወንጌል የተቀመጠው በሁለት መልኩ ነው። አንዱ፤ «ሂዱና እስከ ምድር ዳርቻ አስተምሩ፤ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው፤ ያዘዝኳችሁንም ሁሉ አስተምሯቸው፤» የሚል ነው። ይህ በልጅነታቸው ለሚጠመቁ የተሰጠ ነው። ሌላው፤ «ሂዱ፤ ለፍጥረት ሁሉ ወንጌልን ስበኩ፤ ያመነ የተጠመቀ ይድናል፤ ያላመነ ያልተጠመቀ ይፈረድበታል፤» የሚለው ነው። ይህ ደግሞ ፵ ቀን፥ ፹ ቀን ካለፈ በኋላ ቢመጣም ጥምቀት የማይከለከል መሆኑን ነው የሚያሳየን። ሥርዐቱ በሁለት መልክ የሚከናወነው ለዚህ ነው። ለሁሉም ግን መሠረቱ ጌታ ዮርዳኖስ ወርዶ በመጠመቅ ከአብ፥ ከመንፈስ ቅዱስ የባሕርይ ልጅነቱን አስመስክሮ፤ «እሱን ስሙት፤» የሚለውን ዐዋጅ አሳውጆ ስለ መሠረተው ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ጥር ፲፩ ቀን የዚህ በዓል መታሰቢያ ሆኖ እስከ ዛሬ ደርሰንበታል። ለዚህ ነው በተለይም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የምታከብረው ይህን መንፈሳዊ ሕግ መሠረት በማድረግ ነው።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከመሠረቱ ጀምሮ የሃይማኖትን ትምህርት እድገት እየተከታተለች የኖረችና መጀመሪያ በሕገ ልቡና የኖኅ ልጆች ምድርን ዕጣ በዕጣ ብለው ተከፋፍለው በየአገራቱ ሲሰማሩ የእኛም አባት ካም ልጆቹን ኩሽን፥ ሚዝራይምን፥ ኦፌርንና አጋድን ይዞ ወደ ኢትዮጵያ በመጣ ጊዜ ለኖኅ እግዚአብሔር የሰጠውን የዕርቅ ምልክት ቀስተ ደመናውን ምልክት አድርጎ ነው የገቡት። የሰንደቅ ዓላማችን ቀለም ያን ጊዜ የተገለጠና የዕርቅ ምልክት የሆነ ነው።በዚህ ጊዜ ከሳምንት በዓላት ሰንበትን፥ ቀዳምን፥ ከዓመት በዓላት የዘመን መለወጫን ይዘው ነው የገቡት። ኋላ በብሉይ ኪዳን ደግሞ የቅዳሜ ሰንበትነት

ሳይለወጥ በዚያ ላይ በዓለ መፀለትን፥ በዓለ ፋሲካን ጨምረው ተቀብለዋል። ይሁን እንጂ በዓለ ጥምቀትን ኢትዮጵያውያን በነበረው ሥርዐት ከማክበር በስተቀር አልለወጡትም። የዘመን መለወጫም መስከረም ነው፤ አልተለወጠም። ለምሳሌ የእስራኤል የዘመን መለወጫ ሚያዝያ ነው። እኛ ግን ከአበው ከሔኖክና ከኒኅ በተቀበልነው መሠረት እያከበርን ነው፤ አልለወጥንም። ዓመተ ምሕረትንም እንዲሁ ኢትዮጵያውያን የተቀበሉት ከፅንሱ ጀምሮ ነው። ጌታ በመጋቢት ተፀንሶ በታኅሣሥ ተወለደ። በመሓል መስከረም ነበር፤ የዘመን መለወጫ። ከዓመተ ብሊት ወደ ዓመተ ምሕረት የተሸጋገርነው በፅንስ ነው። የሰው ልጆችም ተስፋ በዚህ መሠረት ነው የሚሄደው። ቅዱስ ገብርኤል፤ «ወንድ ልጅ ትወልጃለሽ፤ ስሙን ኢየሱስ ትዪዋለሽ፤ እግዚአብሔር አምላክ የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፤ በያዕቆብ ወገንም ለዘለዓለም ነግሦ ይኖራል ፤ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም፤» ካለበት ጊዜ ጀምሮ ሥጋ የባሕርይ አምላክ ሆኖአል፤ አምላክም ሰው ሆኖአል። እሷ፤ «እኔ የእግዚአብሔር ባርያው ገረዱ ነኝ፤ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ፤» ብላ ስለ ተቀበለችው ዋሕድ ቃለ እግዚአብሔር በማሕፀንዋ በመጠነ ሕፃናት ተቀረጸ። ዓመተ ምሕረትም ተጀመረ። ይህ ነው መሠረቱ። አውሮፓውያን እኛ ከሰማን በኋላ ፯ ዓመት ቆይተው ነው የሰሙት እያሉ ዛሬም ይቀልዳሉ። ነገር ግን የሚቀልዱት በራሳቸው ነው። የነሱን ዓመተ ምሕረትም የወሰኑት ዓመተ ምሕረት ካለፈ ከሺ ዓመት በኋላ በአንድ ጳጳስ አማካይነት ነው። ከዚህ ውጪ ከመጀመሪያ የቈጠሩት ቍጥር የላቸውም፤ ሲያዘባርቁት ነው የኖሩት። ይልቁን ሊጠይቁን ከፈለጉ ኢትዮጵያውያንን መጠየቅ ነበረባቸው። ምክንያቱም ለራሳቸው ለአይሁድ እንኳ፤ «ኮከብን በምሥራቅ አይተን ልንሰግድለት መጥተናልና የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ የት ነው?» ብለው በመጠየቅ የአይሁድ ንጉሥ መወለዱን ለእስራኤላውያን ያበሰሯቸው ኢትዮጵያውያን ናቸው። ወርቅ፥ ዕጣን፥ ከርቤ ያቀረቡ፥ በትንቢትም የተጠሩ ኢትዮጵያውያን ናቸው። ኋላም ሥርዐቱ የተፈጸመላቸው በኢትዮጵያውያን ስለ ሆነ ሳያፍሩ እኛን ሊጠይቁ ይገባ ነበር። መማር አያሳፍርም። መቼም ከማቃለል መጠየቅ የሚያሳፍር አይመስለኝም። ስለዚህ በዓለ ልደቱም ሆነ የዓመተ ምሕረት አቆጣጠሩ፥ የበዓል አከባበሩም ጭምር የኢትዮጵያን ሕይወት መሠረቱን ጠብቆ የመጣ እንጂ አንድም የተዛነፈና የተሳሳተ የለበትም።

የተሳሳተ ነገር አለ ከተባለ በዚህ ፵ ዓመት ውስጥ የሆነው ብቻ ነው። አዎን፤ ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት ተለያይተዋል የሚል ሕገ መንግሥት ከተረቀቀበት ጊዜ አንሥቶ እስከ ዛሬ ድረስ የተለወጠው ሥጋዊ አስተዳደር ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊያኑ ሥርዐታቸውን መጠበቅ አልቻሉም። ደርግ፤ **«እግዚአብሔር የለም፤» ብሎ ሲነሣ ቤተ ክርስቲያንም፤ «ወንጌልና ሶሻሊዝም አንድ ነው፤» ብላ ዐብራ መጮህና መደናቆር ጀመረች። «ሃይማኖት አይለያየንም፤»** ብላ ሁሉንም ያቀላቀለ ማኅበር መመሥረት ጀመረች። የእናት አገር ጥሪ ብላ በዐቢይ ጦም እያሳረደች አበላች። ይህን ያደረገችው ቤተ ክርስቲያን በጥፋተኛ መሪዎቿ ግዴለሽነት ነው። ይባስ ተብሎ ጨርሶ ስሟም ጠፍቶ፥ ክብሯም ተራቁቶ የካቶሊክ ጥገኛ ከመሆን ደርሳለች። በዚህ ምክንያት፤ «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት፥ ሥርዐተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት፤» በሚባለው መጽሐፋቸው ተምህርተ ሃይማኖቱን ከመለወጣቸውም በላይ፤ **«ከእሑድ በቀር ኤጲስ ቆጶስ ሊሾም አይገባውም፤» የሚለውን ሕገ ቤተ ክርስቲያን ሻሩ። ይህ ጌታ ራሱ በትንሣኤው ቀን የመሠረተውን ንደው በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሥርዐት ሰኞ ቀን ፲፪ ኤጲስ ቆጶሳትን ሾመዋል። ይህ ራሱ ለዘመናት ያልተደፈረችውን ቤተ ክርስቲያን፥ ለዘመናት በጕልበት ያልተደፈረውን ነጻነታችንን አሳልፈው የሰጡ የዛሬዎቹ የቤተ ክርስቲያን ጳጳሳት ናቸው። ይህም ሳይሰማቸው ቀርቶ ጳጳሳትና ካህናት ዐምፀው እስከ ዛሬ ድረስ ሕዝቡን አፍነው እንደ ያዙት ናቸው።**

በአሁኑ ጊዜ የምንመለከተው ሁሉ እንደ ፖለቲካው ባሕሪ ሃይማኖቱም በዚያው መልኩ እየተመራ መሆኑን ያስረዳናል። ከዚያም ብሶ የቴአትር መልክ ይዞ ይታያል። የሩቁን ንቀን እንተወው ብንል እንኳ ባለፈው ስለ ዘመን መለወጫና ስለ ልደት በዓል የሆነውን ብንመለከት የሦስት ሃይማኖት ባለቤቶች ቀርበው የኢትዮጵያን ሕዝብ እንኳን አደረሰህ ይሉ ነበር። ይህን የሚሉት የማን ነው ብለው ነው? መቼም የኢትዮጵያ አይደሉም፤ ይህ የታወቀ ነው። ካቶሊክ የሮም፥ ፕሮቴስታንት የአውሮፓ ነው ወይም የጀርመን፥ የእንግሊዝና የስዊድን። የዛሬዎቹ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችም የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እንደራሴዎች ናቸው። ታዲያ

የማን ነን ብለው ነው የኢትዮጵያን ሕዝብ እንኳን አደረሰህ የሚሉት? በየትኛውስ ሥርዐት? እነሱ የዘመን መለወጫ ያደረጉት በታኅሣሥ ነው። የእኛ የዘመን መለወጫ ደግሞ መስከረም ነው። እነሱ የልደትን በዓል ያከበሩት ታኅሣሥ ፲፭ ቀን ነው። እኛ በዓሉን ያከበርነው ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ነው። በምን ተገናኝተን እንኳን አደረሳችሁ ይሉናል? ጉዳዩ እንዲህ ሆኖ ሳለ በመድረክ ላይ ወጥተው የሚቀልዱት በእግዚአብሔር ወይንስ በሰው ነው? እውነት ሃይማኖት አለን ካሉ፥ እንበልጣለን እናስረዳለን ካሉ መድረክ ይከፈትና እንነጋገርበት። ቅር የሚያሰኝ ነገር የለም።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እኮ ይህን መንፈሳዊ ትምህርት የተማረችው ከሰው አይደለም፤ ከመንፈስ ቅዱስ ነው። ሐዋርያው ፊሊጶስ ሲያስተምር ከነበረበት ቦታ፤ «ሂድ ይህን ሠረገላ ተከተለው፤» ሲል ያዘዘው መንፈስ ቅዱስ ነው። ወንጌላዊ ሉቃስ በግብረ ሐዋርያት ላይ ጽፎታል። በምዕራፍ ፰ ከቍጥር ፳፮ እስከ ፴፱ ያለውን መመልከት ይቻላል። የኢትዮጵያ ንግሥት ጃንደረባ የነቢዩን የኢሳይያስን ትንቢት ያነብ ነበር፤ «እንደ በግ ሊታረድ መጣ፤» የሚለውን። ሐዋርያው ሲሰማው ተደነቀ። ሐዋርያው ይህን ትምህርት ያገኘው ከተቀበለው ከጳራቅሊጦስ መንፈስ ቅዱስ ነው እንጂ ቀድሞ አያውቀውም፤ አልተማረውም። ጃንደረባው ግን ከመሠረቱ ጀምሮ የኢሳይያስን ትንቢት በትምህርት ያውቀው ነበረ፤ በተስፋም ይጠብቀው ነበረ። ኢየሩሳሌም በዓለ ፋሲካን አክብሮና ተሳልሞ ሲመለስ መንፈስ ቅዱስ ፊልጶስን፤ «ይህን ሠረገላ ተከተለው፤» አለው። ጃንደረባው ወደ ጋዛ የሚያወርደውን መንገድ ይዞ ይወርድ ነበር። ተከተለው። ትንቢቱን ሲያነብ ሰማው። «የምታነበውን ታውቀዋለህ ወይ?» አለው ሐዋርያው። ጃንደረባው፤ «ያስተማረኝ የለም፤ በምን ዐውቀዋለሁ፤ ካወቅህ ሠረገላው ላይ ውጣና አስረዳኝ፤» አለው። ከሠረገላው ወጣ። ሐዋርያው የመንፈስ ቅዱስ ምሩቅ ነበረ። የባለ ፸፪ ቋንቋ ባለቤትም ነበረ። እሱም ግእዝ አልተማረም። ነገር ግን በግእዝ ቋንቋ ሲያነብ ለነበረው ሰው ያስተማረው በግእዝ ቋንቋ ነው። በዚያው መጽሐፍ ስለ ጌታ ጠቅላላ ትምህርት ሰጠው። አምላክ ሰው ስለ መሆኑና ስለ ልደቱ፥ ስለ ጥምቀቱ፥ ስለ ስቅለቱና ከዚያም ለቤተ ክርስቲያን ስለ ሰጠው ትምህርት ሁሉ አጠቃሎ እያስተማረው ሳለ ውሃ ካለበት ደረሱ። አስቀድሞ ስለ ጥምቀት ተነጋግረው ነበረና፤ «ታዲያ ውሃ ይኸውና፤ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ማነው?» አለ ጃንደረባው። ሐዋርያውም እዚህ ላይ ተጠነቀቀ። «ግዴለም ትችላለህ፤» አይደለም ያለው። **«በፍጹም ልብህ ልታምን ይገባሃል፤» ነው ያለው።** ልብ እንበል። «ልታምን ይገባሃል፤» ብቻ አይደለም ያለው። «በፍጹም ልብህ ልታምን ይገባሃል፤» ሲል ነው የገለጠለት። የመንፈስ ቅዱስ ተጠሪ የሆነው ጃንደረባው፤ **«እኔ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ አምናለሁ፤»** አለ። ይህን ከተናገረ በኋላ አጥማቂውና ተጠማቂው ወደ ወንዝ ወረዱ፤ አጠመቀው። ተጠማቂው ጥምቀቱን ተቀብሎ፥ መልእክቱን ይዞ ወደ ኢትዮጵያ ገባ። አጥማቂውም በመንፈስ ቅዱስ ትእዛዝ ወደ ሌላ ቦታ ሄደ። በዚህ መሠረት ነው ኢትዮጵያም ሃይማኖትን የተቀበለችው። ያ ሰው ሲናገር፤ «የእግዚአብሔር ልጅና ሰው የሆነው፤» አላለም። «ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ አምናለሁ፤» ነው ያለው እንጂ። «ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እና ሰው እንደ ሆነ ዐውቃለሁ፤» የሚል ሁለት ባሕርይ አድርጎ አልገለጠም። አንድ አካል አንድ ባሕርይ መሆኑን አረጋግጦ፤ **«እኔ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ አምናለሁ፤» ነው ያለ። ይህ ሰውና ጴጥሮስ ጋር በእምነት እኩል ናቸው። ይህም ስለ ሆነ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከሮም ቤተ ክርስቲያን ጋር የሚቀላቅላት ምንም ነገር የለም።** ዛሬ የሮም ቤተ ክርስቲያን የኢትዮጵያን ክርስቲያኖች እንኳን አደረሳችሁ ልትም መብቱም የላትም። ሁለተኛ፤ **«እኔ ኢየሱስ አማላጅ መሆኑን አምናለሁ፤» አይደለም ያለው። «ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አምናለሁ፤» ነው ያለ። «ኢየሱስ አማላጅ ነው፤» የምትል መካነ ኢየሱስ የኢትዮጵያን ሕዝበ ክርስቲያን፤ «እንኳን ለልደቱ አደረሳችሁ፤» ማለት መብቷም አይደለም።** የዛሬዎቹም የካቶሊክ ጥገኞች እዚያው በበሉት ፍርፋሪ ሄደው መጮህ አለባቸው እንጂ እዚህ መጮህ የለባቸውም።

የኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን! ጳጳሳትና ካህናት ዐምፀው ኢትዮጵያን ከሃይማኖቷና ከሃይማኖት ጸጋ አራቁተዋታል። እያየን ነው። በዚህ ፳፩ ዘመን የሚነደው እሳት፥ የሚወርደው መቅሠፍት ከሰው አእምሮ በላይ መሆኑን እያየን ነው። ረኃቡ፥ ቸነፈሩ፥ ልዩ ልዩ መቅሠፍት፥ በሽታዎች፥ አረሙ ሳይቀር ጥንዚዛ እየበቀለበት ነው። ጥንዚዛ ደረቅ ዕንጨት የሚበላ እንጂ ከመሬት ፈልቆ አዝመራ የሚያጠፋ ሆኖ እንኳን እኛ፥ አባቶቻችን

አላዩም። ዛሬ ግን የሚሆነው ሁሉ እየሆነ ነው። ታዲያ አንድም የተገሠፀና የተመለሰ የለም። እንደ ትናንትናው ሁሉ ዛሬም ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት ተለያይተው ነው ያሉት። መንግሥት በሃይማኖት ጣልቃ አልገባም ብሏል። የሚሆነውን ሁሉ በዝምታ እየተመለከተ ነው። ነገር ግን ከእግዚአብሔር በትር አላመለጠም። ራሱም መንግሥት እየተገረፈ ነው። ሕዝቡም ከቅጣት አላመለጠም፤ እየተገረፈ ይገኛል።

አሁንም ይህን በዓል በማክበር ላይ ያለ ምእመን ሁሉ ስለ ሃይማኖቱ በጥሞና ሊያስብበት ይገባል። የሩቁን ይተወው። ብዙ በደል በሃይማኖት መሪዎች ተፈጽሟል። ምናልባት ስለ እኔ ሲነገር፤ «ይህን የሚለው ጥቅሙ ስለ ተነካ ነው፤» እያሉ ሕዝቡን የሚያደናግሩ ብዙዎች አሉ። እኔ ምንም የተነካብኝ ጥቅም የለም። ደግሞስ ጥቅም ብፈልግ ኖሮ አሁን እንዳሉት ሰዎች ምላሴም አሳርፌ መብላት ያቅተኝ ነበርን? ያቅተኝም ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር የሰጠኝን ዐደራ አልለውጥም ብዬ ነው የማስተምረው።

እንደ ተናገርኩት የሩቁን ብንተወው፤ **ታኅሣሥ ፲፪ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓመተ ምሕረት ካርዲናል ጳውሎስ በሞቱ ጊዜ የእኛ ጳውሎስ መቃብሩ ላይ ባራኪ ነበሩ። ይህ ልክ ነው ወይ? በእኛ ሥርዐት አለ ወይ? ይህንን ዐይናችሁ አላየም ወይ? ማን ነው በማን ቤት ገብቶ ባራኪ የሚሆን?** እነሱም አይቀበሉት እኛም አናደርገውም ነበር። ከእኛ የተሻለ ባለ ቡራኬ አለ ብለው በእነሱ ቤተ መቅደስ ላይ ቡራኬ የሚፈቅዱበት አንድም የእኛ ሰው የለም። አባ ጳውሎስ ግን አባላቸው ስለ ሆኑ ነው የፈቀዱላቸው። ታዲያ ይህን እያያችሁ ምእመናን ዝምታን መምረጣችሁ በጣም አስደንጋጭ ነው። አሳዛኝም ነው። አሳፋሪም ነው። እንዴ! እናንተ ሞኞች መስላችሁኝ በቃ። እስከ አሁን ጌታ የቀጣው ቅጣት አልሰማችሁ ብሎ ከሆነ እንጃ። እኔ ከዚህ በፊትም ሰማይም ምድርን ምስክር አድርጌ ያስተላለፍኩትን ቃል አስታውሳለሁ። አሁንም ደግሞ እንቢ ካላችሁ እግዚአብሔር ለዚህም ደግሞ ሀብታም ነው። የሚያመጣው አያጣም። **ኋላ እንዳይቆጫችሁ አሁኑኑ ንስሐ ብትገቡ ይሻላል።** በዓል እናከብራለን ካላችሁ ቶሎ ንስሐ ግቡ። ያለዚያ መለየት ነው ያለባችሁ። ዝም ብላችሁ በእግዚአብሔር ማሾፍ የሚያዋጣ አይመስለኝም። በዚህ ዐሥር ዓመት ጥምቀቱ በሥነ ሥርዐቱ አልተከበረም፤ ታውቃላችሁ። በየዓመቱ የውጭ ዕንግዳ እየመጣ እየተደባለቀ የበዓሉ መልክ እየተቀየጠ ከሚታይ በስተቀር በሥነ ሥርዐቱ፥ በነበረ ጠባዩና ባሕሪው አልተከበረም። ካለፉት ፲፪ ዓመታት ወዲህ ይህ በዓል አልተከበረም ማለት ይቻላል። በነዚህ ዓመታት ውስጥ በዓለ ጥምቀቱ አለመከበሩን እያወቃችሁ እስካሁንም ለመመለስ አልቻላችሁም። ተዉ የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ ተመለሱ። ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ።

**እግዚአብሔር በረከተ ጥምቀቱን ለአገራችን ለሕዝባችንም ይፍቀድልን። አሜን።**

## አለቃ አያሌው ታምሩ ዘዲማ ጊዮርጊስ፤ የኦርቶዶክሳዊው የሊቃውንት ጉባኤ ሰብሳቢ።

**(ኢትኦጵ ጋዜጣ ጥር ፲፪ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ. ም.)**

# እኛ የእግዚአብሔር እንጂ የዓለም አይደለንም።

**(ጦማር ጋዜጣ፤ ጥር ፲፩ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ. ም. )**

## (አለቃ አያሌው ታምሩ)

«እኔ ከዓለም እንዳይደለሁ እነሱም ከዓለም አይደሉም።» (ዮሐ፤ ፲፯፥ ፲፮።)

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤ አሜን።

**«ንዑ ትልዉኒ።»** «ኑ ተከተሉኝ።» (ማቴ፤ ፬፥ ፲፱።)

**«ወንትልዎ ለፍጹም መልአክነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘተዐገሠ ኀፍረተ መስቀል አናኅስዮ በእንተ ፍሥሓሁ ዘጽኑሕ ሎቱ ወመነና ለኀፍረት፤ ወነበረ በየማነ መንበረ እግዚአብሔር።»** «ፍጹም አለቃችንን ኢየሱስ ክርስቶስን እንከተለው፤ ኀፍረተ መስቀልን የታገሠውን፤ አቃሎ፤ ለእሱ ስለ ተጠበቀው ደስታው ኀፍረትን የናቃትን፤ በእግዚአብሔር የጌትነት ክብርም ተቀመጠውን።» (ዕብ፤ ፲፪፥ ፲፪።)

ምእመናን! አባቶቻችን ሲናገሩ፤ **«ክፉ ባላጋራ ይተክላል፤ መልካም ባላጋራ ይነቅላል፤» ይሉ ነበር።** በድሮ ጊዜ ኢትዮጵያውያን የርስት ባለቤት በነበሩበት ጊዜ የሚነሣ የርስት ክርክር ነበር። አንዳንዱ ባላጋራ አነሳሡ በሐሰት መሆኑን ሲያውቅ ድነበሩን ለይቶ የሚያውቅ ሽማግሌ እስኪታጣ፥ ምስክር እስኪጠፋ አንገቱን ቀብሮ፤ ወዳጄ፥ ወንድሜ ሲል ቆይቶ ጊዜ ጠብቆ ነው የሚነሣ። አንዳንድ ችኩል ደግሞ በአንድ ጊዜ ሁሉን ያገኘ እየመሰለው በተለይም ሀብት፥ ሹመት፥ ወይም ወገን ያገኘ ሲመስለው ያንንም ያንንም እንቅ እንቅ ያደርጋል። ሁሉን ልያዘው፥ ልጨብጠው ይላል። ያን ጊዜ ሰዎችን ያነቃቸዋል። ሰዎችም ወሰኑን፥ ድንበሩን፥ ሕጉን፥ ወጉን፥ ሐረገ ትውልዱን፥ ታሪኩን በሚያውቁ ምስክሮችና ሽማግሌዎች አስመስክረው፥ በብሔራዊ ዳኛ፥ በሕዝባዊ ሸንጎ ተከራክረው ርስታቸውን ከመነጠቅ፥ መብታቸውንም ከመገፈፍ ያድናሉ።

በአሁኑ ጊዜ እንደሚታየው ጠላት የዘራቸው የእንክርዳድ ዘሮች፥ የጠላት ልጆች ትምህርተ ሃይማኖታችንን ሊያፈልሱ፥ ቤተ ክርስቲያናችንን ሊያፈርሱ እየታገሉን

ነው። በሀብታቸው በሹመታቸው የሚያደርሱት ዐመፅ፥ ግፍ፥ ረገጣ ሳያንስ ጥቅማቸውን ለማስከበር ብቻ የመንግሥት መስለው ከመንግሥት ሊያጋጩን ይሞክራሉ። አባ ገሪማና አባ ጳውሎስ፥ ተባባሪዎቻቸውም የራሳቸው ናቸው እንጂ እግዚአብሔርም የመንግሥትም አይደሉም። እኛ የእግዚአብሔር እንጂ የዓለም አይደለንም። እነ አባ ገሪማ ባልዋልንበት ሊያውሉን፥ ባልተሰለፍንበት ሊያሰልፉን፥ ባልተመደብንበት ሊመድቡን ይፈልጋሉ። እነሱ በልብስ ቤተ ክርስቲያንን፥ በጠባይ ሰይጣንን፥ በሽር ፖለቲካን ተጠግተው መሥራቱን ለምደውታል። በስንዴ መሐከል ጠላት የዘራው እንክርዳድ ቡቃያው ስንዴ ቢመስልም በአደገ ጊዜ ይለያል። እነ አባ ገሪማም ክርስቲያን ያውም መነኮሳት ከዚያም አልፎ ጳጳሳት ቢመስሉም ሲገቡ መሰሉ እንጂ አሁን ግን እያደጉ ሲመጡ ማንን እንደሚመስሉ ለግብር አባታቸውም ዳግማውያን እየሆኑ መምጣታቸው በሥራ እየተገለጠ ነው።

እኛ ጥሪኃችን የእግዚአብሔር ነው። «ኑ ተከተሉኝ፤» ብሎ የጠራን መሪያችን፥ ፊታውራሪያችን እኛን ለማዳን ሲል በቀራንዮ ዐደባባይ ግንድ ተሸክሞ፥ ጨርቅ አጠርቅሞ የዋለው ሰማይን፥ ምድርን፥ ባሕርን በውስጣቸው ያለውንም ሁሉ ፈጥሮ የሚገዛ ሁሉን ቻይ፥ ኃያል፥ ምንም የማይጎድለው ባለ ጠጋ ሲሆን በአይሁድና በሮማውያን ፊት ራቁቱን ሲቆም፥ ሲገፈፍ፥ ሲገረፍ፥ ሲቸነከር፥ ሲሰቀል ቅር ያላለው፥ ኀፍረተ መስቀልን የታገሠው ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። አዝማቻችንም፤ «ፍጹም አለቃችንን ኢየሱስ ክርስቶስን እንከተለው፤» እያለ ወደፊት የሚገሠግሠው ቅዱስ ሐዋርያ ነው። እኛ ከዓለም አይደለንም። የማንኛውም ፖለቲካ ቡድን አዳባሪዎች፥ አጫፋሪዎች፥ አጀርጃሪዎችም አይደለንም። ይህ ጠባይ ያላቸው ሌሎች ናቸው።

ጥያቄዎቻችን፤ **«የተቀበሉትን ዐደራ ያልጠበቁት ፓትርያርክና ሊቃነ ጳጳሳት በቤተ ክርስቲያንና በምእመናኖቿ ላይ ከሚፈጽሙት ዐመፅና በደል ይመለሱ፤ ይታገሡ። ክብረ ቤተ ክርስቲያንን አይርገጡ፤ አያስረግጡ። ሃይማኖቷን፥ ትምህርቷን አያፋልሱ፤ ሥርዓቷን አይጣሱ፤ ሕጓን አያፍርሱ። በመምህራኖቿ ወንበር ከተቀመጡ በሚቀርብላቸው ሃይማታዊ ጥያቄ ሃይማኖታዊ መልስ ይመልሱ። ከዚያ አልፎ የምእመናኖቿን ደም ዐውደ ምሕረት ላይ አያፍስሱ። ይህን ካደረጉ ደግሞ፤ «ነፍስ አትግደል፤ ወንድምህን በከንቱ አታሳዝን፤» ያለውን አምላካዊ ሕግና ብሔራዊ መንግሥታዊ ሕግ የጣሱ ያፈረሱ እነሱ ናቸውና በሕግ ለፍርድ ይቅረቡ እንጂ ሌላውን በሐሰት አይክሰሱ፤» የሚሉ ናቸው።** ከእነዚህ ከተዘረዘሩት ጥቄዎች የትኛው ነው ሃይማኖትን ከለላ አድርጎ መንግሥትን ለመቃወም የተነሣ ነው፥ ወይም በቤተ ክርስቲያን ዐውደ ምሕረት ላይ ለመሪዎቿ መቅረብ የማይገባው ነው የሚባለው የትኛው ነው; ጥቄዎቻችን በሙሉ መንፈሳውያን፥ ሕጋውያን፥ ኢትዮጵያውያን፥ ኦርቶዶክሳውያን ናቸው። በቤተ ክርስቲያን ዐውደ ምሕረት ላይ ለመሪዎች፥ ለአስተማሪዎች መቅረብ የሚገባቸው ትምህርታውያን ናቸው። እርግጥ

ዓለማውያንና ፖለቲካውያን አይደሉም፡፡ አዎ፡፡ ለነ አባ ገሪማና ለደጋፊዎቻቸው ሊጠቅሟቸው አይችሉም፡፡ ስለዚህም በሆነላቸው ጊዜ በጉልበታቸው በሥልጣናቸው ሊያጠቁን፥ ሳይሆንላቸው ደግሞ ከመንግሥት ሊያጋጩን ይፈልጋሉ፡፡ አዲስ አይደለም፡፡ ያረጀ ያፈጀ የካህናትና የሮማውያን ፖለቲካ ነው፡፡

በቀራንዮ ዐደባባይ የተፈጸመው ያስረዳል፡፡ የአይሁድ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ሕዝብ ለመንግሥት (ለቄሣር) ግብር እንዳይከፍሉ ቅስቀሳ ደርጋል እያሉ በሮማውን ዳኝነት ሲከሱ፥ ኦሪትን ነቢያትን ሊሽርባችሁ ነው እያሉ ሕዝቡን ሲያነሳሡ፥ ሲቀሰቅሱ መዋላቸው፤ ሮማውን ጭፍሮችም ከካህናት ጉቦ፥ መቅቡጥ፥ ገንዘብ ተቀብለው እኛ እንደ ተኛን ደቀ መዛሙርቱ ሰርቀው ወሰዱት እያሉ ትንሣኤውን ማስተባበላቸውን ቅዱስ ወንጌል ገልጾታል፡፡ ከዚያ ቀን እስከ ዛሬ በዓለም እየተነገረ ነው፡፡ የሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ገዢዎና ግብረ በላዎች ከጌቶቻቸው በተማሩት ፈሊጥ እውነቱን በሐሰት እየለወጡ ቢከሱን አንደነቅም፡፡

**አንደኛ፡- ለጥቅማቸው የቆሙ፤**

**ሁለተኛ፡- እውነቱ ቢጋለጥ በሰውም በእግዚአብሔርም ፊት ራቁታቸውን እንደሚቀሩ ስላወቁ ነው፡፡** መንግሥት የራሱ የሆነ የአመራር ሥርዓት አለው፡፡ ማንም ሊያጭበረብረው አይችልም፤ አይገባምም፡፡ ጥያቄያችን ይኸው ነው፡፡ ከስንዴ ጋር በቤተ ክርስቲያን የተዘሩት እንክርዳዶች ይነቀሉ፡፡ ከበጎች ጋር በበጎች ስፍራ የተቀላቀሉት ተኵላዎች ይለዩ፡፡ በክርስቶስ ስም በሐዋርያዊት መንበር ላይ ሠርጎ ገብቶ የተቀመጠውና የሚያጭበረብረው፥ መንግሥትን ከቤተ ክርስቲያን፥ ቤተ ክርስቲያንን ከመንግሥት ለማጋጨት የሚሞክረው ሰይጣን ከመንበሩ ይውረድ፤ ከቤተ ክርስቲያን ይሰደድ፡፡ **«ተፈጸም ወፃእ መንፈስ ርኩስ፤» «አንተ ርኩስ መንፈስ አንዱን ከአንዱ ማጋጨትህን፥ የሆነ ያልሆነ መቀባጠርህን ትተህ ውጣ፤»** የሚል ነው የምእመናንና የቤተ ክርስቲያን ጥያቄ፡፡ ይህ መሆኑ እየታወቀ እነ አባ ገሪማ የሚያግተለትሉት ዘባተሎ ቋንቋ ትርጉም የለሽ ነው፡፡

በነገራችን ላይ ለመሆኑ ጥር ፳ የወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ በርእሰ አንቀጹ የጻፈው አስተያየት ምን ለማለት፥ ምን ለማሳየት ፈልጎ ነው፡፡

**አንደኛ፡-** ኢትዮጵያ ከእነዚህ ስድስት ዓመታት በፊት ሃይማኖት አልባ እንደ ነበረችና በአሁኑ ጊዜ ሃይማኖትን እንዳገኘች፤

**ሁለተኛ፡-** ቀደም ሲል ኢትዮጵያ የአንድ ሃይማኖት ደሴት ተብላ ሌሎች ሲቸገሩ እንደ ነበሩ፤

**ሦስተኛ፡-** የእምነት ነጻነት የተገኘው በታጋዮች ደም እንደ ሆነ፤

**አራተኛ፡-** ጥር ፩ ቀን በቅዱስ እስጠፋኖስ ቤተ ክርስቲያን የቀረበውን ጥያቄ ያለ ቦታው የቀረበ ካስመሰለ በኋላ በዘመናዊ መሣርያ ታጥቀው ለጸሎት ለምስጋና በተሰበሰቡት ምእመናን ላይ ባሩድ እንደ ክረምት ዝናም ያርከፈከፉትን ወንጀለኞች የተገፉ፥ የተበደሉ ጻድቃን አስመስሎ ሲያቀርብ፤ የተገደሉትን፥ የተደበደቡትን፥ ሃይማኖታዊ ጥያቄያቸውን በቦታው በሚገባው ያቀረቡትን ኮንኖአል፡፡ እሱ ማነው; ብዕሩስ የማነው; ከዚያም አልፎ በኅብረት ልንታገላቸው ይገባል ሲል ጥሪ አቅቦአል፡ ፡ እሱ ማነው; አስቀድመን ወደ ታሪክ እንመለስ፡፡

**አንደኛ፡-** ኢትዮጵያ ከዓለም አህጉር በፊት ሃይማኖት ያላት፥ ያለ ሃይማኖት የኖረችበት ጊዜ የሌለ ሲሆን በዚህም ብሉይ፥ ሐዲስ ስለሚመሰክሩላት ማንም ጣቱን ሊቀስርባት፥ አንደበቱን ሊሰነዝርባት አይችልም፡፡

**ሁለተኛ፡-** የአንድ ሃይማኖት ደሴት ትባል ነበር ለማለት ሞክረዋል፡፡ መባል ብቻ አይደለም ናት፡፡ ማንም ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት በፊት የተሰበከ የለም፡፡ «ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ አምናለሁ፤» ብሎ በልቡ አምኖ፥ በአፉ ታምኖ ከተጠመቀው ኢትዮጵያዊ በቀርም ሌላ ተወዳዳሪ ባለ ታሪክ የለም፡፡ ዛሬ በኢትዮጵያ አለን አለን፥ ፈጀን ፈጀን የሚሉት ልዩ ልዩ የሃይማኖት ድርጅቶች ሁሉ ከ፩፻ ዓመት በኋላ የተነሡ፥ ግማሹ በስደት ሌሎችም በፖለቲካ ወታደርነት የመጡ እንጂ መሠረታውያን ባለቤቶች አይደሉም፡፡ ይህን ራሳቸውም ያውቁታል፡፡ ያም ሆኖ በየጊዜው ራሳቸው በሚያደርጉት ስርሰራ፥ ቡርቦራ እንጂ በሃይማኖታቸው ምክንያት የፈለጉትን ሃይማኖት ስለያዙ የደረሰባቸው ከሰሳ፥ ወቀሳ የለም፡፡

እነሱ የፈጸሙትን ሥራ በጉዲት፥ በግራኝ፥ በሱስንዮን ዘመን፥ በአድዋ፥ በማይጨው፥ በአምባላጌ፥ በሰለክለካ፥ በኦጋዴን ጦርነት የተደረገባቸው ሜዳዎች፥ አደባባዮች በልዩ ልዩ ጸሐፊዎች የተዘገቡ ታሪኮች ይመሰክሩታል፡፡ ክርስቲያኑም እስላሙም ይህን ያውቃል፡፡ **«ሃይማኖት የግል ነው፤ አገር የጋራ ነው፤» የሚለው አዋጅም በአጤ ኃይለ ሥላሴ መነገሩንና መታወጁን፤ ከዚያ ጊዜ ጀምሮም ክርስቲንንም እስላምም በእኩልነት መተዳደራቸውን፤ የካቶሊክ መንበር፥ የመካነ ኢየሱስ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን፥ የአንዋር መስጊድ በይፋ መክፈታቸውን፤ ካቶሊክ፥ ፕሮቴስታንት፥ እስላም የሆኑ ሚኒስትሮች፥ አገረ ገዢዎች፥ በጦር በሲቪል ይሠሩ የነበሩ ሹማምንትና ባለ ሥልጣኖች እንደ ነበሩ ታሪክ ከሚያውቀው በላይ ያን ጊዜ የነበሩ ዛሬ ያሉ ዕድሜአቸው የ፵ የ፶ ዘመን የሆኑ ሰዎች የሚያውቁት፥ የሚመሰክሩት ነው፡፡** የዛሬው የአዲስ ዘመን ርእሰ አንቀጽ ጸሐፊ ይህን ሁሉ የሚተቸው፥ ያውም ደግሞ በግል ጉዳያችን ገብቶ የሚፈተፍተው፥ ከዚያም አልፎ መንግሥትንና ክርስቲያኑን ሕዝብ ለማጣቆስ የሚሞክረው ከየት መጥቶ፥ የት ኑሮ፥ መቼ ተወልዶ ነው; አዎ አዲስ ዘመን፡፡ ለመሆኑ ጋዜጣው (አዲስ ዘመን) ይህን ስም ያገኘው መቼ ነው; ርእሰ አንቀጽ ጸሐፊው ያውቀዋል; ጋዜጣው ስሙን ያገኘው፥ አዲስ ዘመን

በመባል የተሰየመው ከአጤ ኃይለ ሥላሴ፥ በአጤ ኃይለ ሥላሴ ዘመንና ታሪክ ነው፡ ፡ እስከ ደርግ ዘመን ድረስም በዚሁ ስሙ የዘውድን መንግሥት ይልቁንም የአጤ ኃይለ ሥላሴን ታላቅ ሰውነትና ከፍተኛ መሪነት፥ ጥልቅ አስተዋይነት፥ ሰፊ ችሎታና ቸርነት፥ ፖለቲካና ጀግንነት ሲመሰክር ኖሮአል። በደርግ ዘመንም በሶሺያሊስት ኢትዮጵያ ይህንኑ ስሙን እንደ ያዘ በአዲስ ዘመን ኮሚኒስታዊ ቋንቋ ደርግን ሲያሞካሽ፥ በፈጸመው ሥራ ሁሉ ደርግን ሲያሞግስ ኖሮአል። አሁን ደግሞ በዘመነ ኢሕአዴግ ለሦስተኛ ጊዜ በዚያው ስሙ ማለት በአዲስ ዘመን ዘውድንና የቀደመውን አስተዳደር እያማ ኢሕአዴግን ሲያመሰግን፥ የዕለት ተለት ሥራውንም እኃነነ ሲያወራ እያየን እየሰማን ነው። አይ አዲስ ዘመን! እውነትም በየቀኑ አዲስ ዘመን፡ ፡ **«ያለ ዛሬ ጥሩ ወጥ በልቼ አላውቅም የሚል መራቂ ወዳጁን ሳያውቀው ያረጃል፤ » ይባላል።** አጤ ኃይለ ሥላሴንም፥ ደርግንም፥ ኢሕአዴግንም በአንድ ቋንቋ ሲያመሰግን ፶ ዘመን አለፈው። ወዳጁን ሳያውቀው ማርጀቱ ነው። ለዚህም የሚያበቁት ከእውነት ውጪ የራሳቸውን አስተሳሰብ በሌላው አእምሮ ለማሳደር የሚጣጣሩ ጸሐፍት ናቸው። ነገሩ ስላነሳሣኝ እንጂ እኔ በጋዜጣው የሥራ ጉዳይ የፈለገውን ቢያማ፥ የፈለገውን ቢያመሰግን ግድ የለኝም። ግን ቤተ ክርስቲያናችንን ለመጻረር፥ ክብረ ሃይማኖታችንን ዝቅ ለማድረግ፥ በእኛ ላይ ጉዳት ለማድረስ፥ ሞራላችንንም ህልውናችንንም ለመጉዳት የመንግሥትን ሥራ ሽፋን አድርገው የሚዋጉን ሁሉ እንዳወቅንባቸው ሊያውቁን እንደሚገባ ማሳወቅ እወዳለሁ።

የእስልምና እምነት የተለየ መሥመር ያለው ነው፤ አያከራክርም። ያም ቢሆን የድሮዎቹ ሳይሆኑ የዛሬ የዛሬ ጸሐፊዎች ከወሰን እያለፉ እንደ ጻፉ በቅርብ ጊዜ ተመልክቼአለሁ። እንደ እውነቱ ከሆነ በገዛ መጽሐፋችን ሃይማኖታችንን ሊያስተምሩን እንደ ሞከሩ ተመልክቼአለሁ። ከፈለጉ መድረኩ ይከፈትና፥ ፈቃደኝነታቸውን ይግለጡና፥ መንግሥትም ይወቀውና በመጽሐፍ ቅዱስ ሳይሆን በቁርዓን እውነቱን መነጋገር እንችላለን። በክርስትና ስም ከልዩ ልዩ አገር የዘመቱብን፥ ልዩ ልዩ ወሬ የሚያወሩብን ክፍሎችም የእኛይቱ እናታችን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከሰበከችው ሌላ ከአውሮፓ፥ ከአሜሪካ ያመጡት ሌላ ኢየሱስ ካለ፥ ወይም ቤተ ክርስቲያናችን የማታውቀው ሌላ መንፈስ ካለ፥ ወይም ቤተ ክርስቲያናችን ያልሰበከችው ሌላ ወንጌል ካለ መድረኩ ይከፈትና ያቅርቡት፤ እንይላቸው፤ እንስማላቸው፤ ያስረዱን፤ እናስረዳቸው። ያለበለዚያ የእምነት ነጻነት በሚል ሽፋን በቤተ ክርስቲያናችን ላይ የሚደርጉትን ወረራ ያቁሙ። እግዚአብሔር አንድ ነው፤ ሃይማኖት አንድ ነው፤ ጥምቀትም አንዲት ናት። የታወቀ ሃይማኖታዊ መሥመር ከሌለው ሀገር በቀር በማንኛውም ዓለም አህጉር ለአንድ መንግሥት አንድ ሃይማኖት ነው። ይህን የሚያስተባብል የለም። በኢትዮጵያ ብቻ እንደ ክረምት አግባ ምድር ያፈራችው ሃይማኖት ሁሉ ብሔራዊ መሆን አለበት የሚባለው አስተሳሰብ ትክክል አይደለም። ማንም ሰው የወደደውን ሃይማኖት ሊይዝ፥ በዚያው ሊኖር ይችላል። ሁሉ ብሔራዊ ሃይማኖት መሆን አለበት የሚለው አስተሳሰደብ

ግን እውነት አይደለም። ሃይማኖት ከመባል ጥያቄ ውጪ ነውና። ተከራክሮ አሸንፎ መንበሩን መያዝ ይቻላል። ያለዚያ በወሬ እያታለሉ፥ በገንዘብ እየደለሉ የሕዝብን መንፈስ መበረዝ፥ ያለዚያም መንግሥትንና ሕዝብን በማጋጨት ያውም በማያገባ እየገቡ ደም ለማፋሰስ መሞከር ለአንድ አገር ጉዳትን እንጂ ጥቅምን አያመጣም። ለእኔ እንደሚሰማኝ ከሆነ ለመንግሥትም ቢሆን ዓለም የወለደውን ሃይማኖት ሁሉ ተሸክሞ እንኳን ሥራ ሊሠራ ለእነሱ ቦታ መድቦ ማኖሩ እንኳ የሚያስቸግረው ይመስለኛል። ስለዚህ ሊያስብበትና በኢትዮጵያዊ አስተሳሰብ ለአንድ ሀገር፥ ለአንድ መንግሥት አንድ ሃይማኖት ያውም ኀረቤት፥ ውሽማ የሌላትን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖን ቢመርጥ፥ እሷንም ቢጠብቅ የሚሻለው ይመስለኛል። በኢሕአዴግ ዘመነ መንግሥት በሥራው ተገምግሞ ለአንድ ሥራ ይበጃል፥ ይበቃል ተብሎ መመረጥ የተለመደ እንደ ሆነ ሁሉ፥ ተገምግሞ ቀሎ፥ ጎድሎ፥ እምነቱን አጉድሎ ሲገኝም ከነበረበት መሻር፥ መውረድ በሕግ መጠየቅም የተለመደ ሆኖአል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ተባባሪዎቻቸውም ይሆናሉ ተብለው ወደ ቤተ ክርስቲያን ገብተው ነበር፡ ፡ አድገው፥ ተሹመው፥ ከብረው ነበረ።

አሁን ግን ለተመረጡበት ሳይበቁ ስለ ቀሩ፥ ቀልለው፥ ጎድለው፥ እውነት አጉድለው ስለ ተገኙ ከወንበራቸው መውረድ፤ በቤተ ክርስቲያን ዐውደ ምሕረት በታቦተ እግዚአብሔር ፊት ሰው በመግደል፥ ደም በማፍሰስ የእግዚአብሔርንም የመንግሥትንም ሕግ ተላልፈው ስለ ተገኙ ለሕግ እንዲቀርቡ፤ መንግሥትም ከቤተ ክርስቲያን ጎን ሆኖ በወንጀለኞች ላይ ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ እንጠይቃን። እኛ መሪያችን ክርስቶስ ነው። የምንከተለውም እሱን ነው፤ የምናዳምጠውም የእሱን ጥሪ ነው። የማንም ፖለቲካ ፓርቲ ተከታዮች አይደለንም። የክርስቶስ እንጂ የዓለም አይደለንም። ሁሉም ይህን ይወቅልን። ከዚህ ጋር አንድ ነገር ላስታውስ። ፓትርያርኩ በጥምቀት በዓል ላይ በአንድ በኩል ባለፉት ቀኖች የተደረገውን በቀል የሚያስታውስ ዛቻ የተሞላበት ቃል ሲነዙ በሌላ በኩል ደግሞ ከዚህ በፊት እንዳልተጠየቁ ሆነው ጥያቄ የሚያቀርብ ካለ ጥያቄውን ለመቀበል ዝግጁ መሆናንውን፥ በራቸው ክፍት መሆኑን ሲያስተጋቡ ነበር። ይህም በራዲዮ ተላልፎአል። እኔን ያስደነቀኝ፤ «የተበደለ ቢኖር፤» ሲሉ የተናገሩት ቃል ነው። በደል ብቻ ሳይሆን መግደል የፈጸመ ሰው በእግዚአብሔርም በሰውም ፊት ሲዋሽ ማየት መስማት ምን ያህል አሳፋሪ ነው; በብዙ ሺሕ የሚቆጠር ምእመን ባለበት ጥይት እንደ አፈር ሲረጩ፥ ሲያስረጩ ውለው ጻድቁን ገድሎ፥ አስገድሎ ሳይከሰሱ መቅረብ፥ ከሕግ ፊት አለመቅረብ እንዲህ እንደልብ ያናግር ይሆን; እግዚአብሔር ይስማው፤ እግዚአብሔር ይየው፤ እግዚአብሔር ይፍረደው።

**አለቃ አያሌው ታምሩ ዘዲማ ጊዮርጊስ፤ የኦርቶዶክሳዊው የሊቃውንት ጉባኤ ሰብሳቢ።**
**(ጦማር ጋዜጣ፤ ጥር ፲፩ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ. ም. )**

# መላው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ከፓትርያርኩና ተከታዮቻቸው ቃልና እጅ ቡራኬ እንዳይቀበል አገር አቀፍ ጥሪ ቀረበ።

## (አለቃ አያሌው ታምሩ ዘዲማ ጊዮርጊስ፡፡)

(መብሩክ ጋዜጣ፤ ሰኔ ፳፯ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ. ም.)

**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤ አሜን።**

**« መላው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ከፓትርያርኩና ተከታዮቻቸው ቃልና እጅ ቡራኬ እንዳይቀበል አገር አቀፍ ጥሪ ቀረበ። የወጣውን ሕግ የተቀበሉ፥ ከሥራ ላይ ያዋሉ እንደ አርዮስ እሱራን ውጉዛን ይሁኑ።** አለቃ አያሌው ታምሩ ከእንግዲህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተከታይ የሆነ ምእመን በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ቃልና እጅ፥ በሲኖዶሱ ዋና ጸሐፊ በአቡነ ገሪማና በተባባሪዎቻቸው ቃልና እጅ ቡራኬ እንዳይቀበል በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ ሥልጣን፥ በጴጥሮስ፥ በጳውሎስ፥ በማርቆስ፥ በቄርሎስ፥ በባስልዮስ፥ በቴዎፍሎስ፥ በተክለ ሃይማኖት ዘደብረ ሊባኖስ ቃልና በራሳቸው ማውገዛቸውን አስታወቁ፡፡ አለቃ አያሌው ታምሩ ይህን ያስታወቁት በግንቦቱ ሲኖዶሳዊ ጉባኤ አዲስ ያወጣው ሕገ ቤተ ክርስቲያን ላይ ያላቸውን አስተያየት እንዲሰጡንና ሐምሌ ፫ ወይም ፯ ቀን በሚከበረው የፓትርያርኩ በዓለ ሢመት ላይ የእሳቸው አመለካከት ምን ሊሆን እንደሚችል ለመገምገም ቃለ መጠይቅ ባደረግንላቸው ወቅት ነው፡፡ ይህንን የአለቃ አያሌውን ሙሉ ቃልና መልእክት የሚከተለው ነው፡፡

«ከሁሉ አስቀድሞ እግዚአብሔር ሥራችንን ይባርክልን እላለሁ፡፡ በመቀጠልም ስሜቴን እንኳ መቆጣጠር እስከሚያቅተኝ ድረስ እየተጨነቅሁ በቃለ ጉባኤ ተባዝቶ በጽሕፈት ቤቱ በኩል ለአስፈላጊው እንዲደርስ በተደረገውና ከሚያዝያ ፳፱ እስከ ግንቦት ፯ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ ም በሥራ ላይ የነበረው የጳጳሳትና የሊቃነ ጳጳሳት ስብሰባ ሲኖዶስ ጉባኤ ቤተ ክርስቲያን «ሕገ ቤተ ክርስቲያን» ብሎ ስላስተላለፈው ሕግ ያለኝን ሐሳብና ድምፅ ለመላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አባሎች በኢትዮጵያና በመላው ዓለም ለሚኖሩ ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን ሁሉ በእግዚአብሔር ስም አስተላልፋለሁ፡፡ በእግዚአብሔር ስም አሰማለሁ፡፡

**፩ኛ፤** ክርስቶስ በደሙ የመሠረታት ቤተ ክርስቲያን የምትመራው ወይም አመራር የምትቀበል ከእሱ ከራሱ ከመንፈስ ቅዱስ እንጂ ከሰው አይደለም። ይህንንም ራሱ ባለቤቱ ኢየሱስ ክርስቶስ፤ **«እስከ ዓለም ፍጻሜ እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ፤»** ያለውን ቃሉን ሲያስተላልፍ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጠው ትእዛዝ፤ «ሂዱ አስተምሩ፤ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አስተምሩ፤» የሚል ነው። ይህንንም መልእክት በሚፈጽሙበት ጊዜ ግን የሚመራቸው ማን እንደ ሆነ ሲያስረዳ፤ **«መንፈስ ቅዱስ ይመጣል፤ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችሁአል፤» ብሎአቸዋል። (ማቴ፤ ም ፳፰፥ ቍ ፲፱ - ፳። ዮሐ፤ ም ፲፮፥ ቍ ፲፫።)** አመራሩም ከሙሴ፥ ከኢያሱ የተለየ በውሥጣቸው ዐድሮ የሚመራቸው መሆኑን፥ ዓለም የማያውቀው እነሱ የሚያውቁት የእውነት መንፈስ መሆኑን በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፫ ቍጥር ፲፫ - ፲፰ በተጻፈ ቃሉ ገልጾ ልኮአቸዋል። እንግዲህ እግዚአብሔር በደሙ የዋጃትን ቤተ ክርስቲያን እንዲጠብቁ ጳጳሳትን የሚሾም፥ ጉባኤያቸውን የሚመራም እሱ ራሱ መንፈስ ቅዱስ ነው። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተዋሕዶ ሃይማኖት ትምህርት ይህ ነው። ሰው ጉባኤ ቤተ ክርስቲያንን አይመራም። ግን በኋላ ዘመን ራሱን እንደ እግዚአብሔር የሚቈጥር፥ እንደ እሱ ነኝ ብሎ መሥራት የሚያምረው በቤተ እግዚአብሔር የሚኖር ትዕቢተኛ እንደሚመጣ ቅዱስ ጳውሎስ ተናግሮአል። **(፪ ተሰ፤ ም ፪፥ ቍ ፬።)**

ይህ ካልሆነ በስተቀር በቤተ እግዚአብሔር አመራር ሰጪ እኔ ነኝ ብሎ የሚናገር ወይም እሱ ነው ተብሎ የሚነገርለት ማንም የለም። ሐዋርያት ራሳቸውም በመንፈስ ቅዱስ እንደ ተጠሩ በወንጌል ስብከት እንደ ተላኩ፥ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሮች፥ አገልጋዮች፥ መልእክተኞች እንደ ሆኑ ተናገሩ እንጂ፤ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ማኅበር እንደ ሆነች አስተማሩ እንጂ እነሱ ጌቶች፥ መሪዎች፥ አመራር ሰጪዎች እንደ ሆኑ፥ ቤተ ክርስቲያንም የእነሱ ተጠሪ እንደ ሆነች አልተናገሩም፤ አልጻፉም። የተፈጸመው አገልግሎት በጠቅላላ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት እንደ ተፈጸመ፥ እንደሚፈጸም፤ የተደረገ በደል ቢኖር ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ ላይ እንደ ተፈጸመ ጻፉ፤ ተናገሩ። ሐናንያ የተባለው ሰው የመጀመሪያዪቱን ቤተ ክርስቲያን አቋምና እርምጃ በተጠራጠረና በተፈታተነ ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስ፤ «መንፈስ ቅዱስን ታሳብለው ዘንድ እንዲህ በልብህ ሰይጣን ሞላን? ወይስ እንዴት ሞላ፤» ብሎ ገሠጸው እንጂ የእኔን ቃል፥ የእኔን መሪነት ተላለፍክ ብሎ አልገሠጸውም።

እንዲሁም፤ **«ሲጾሙና ሲጸልዩ ሳያልንና በርናባስን እኔ ለመረጥኩላቸው ሥራ ለዩልኝ ብሎ መንፈስ ቅዱስ አዘዛቸው፤»** ይላል እንጂ ሰው ለመረጠላቸው ሥራ አይልም። እንግዲህ፤ «ሰማይና ምድር የሚያልፉ ቢሆንም እንኳ ቃሌ አያልፍም፤ » ያለ አምላክ የመሠረተላት፥ የሠራላት ሕግ ምን ጊዜም የማያልፍ መሆኑ ቀጥተኛ እውነት ነው። በዚህ መሠረት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ የሚመራ

በመንፈስ ቅዱስ መሆኑን፥ ቅዱስ ያሰኘውን ቅድስናውን ያገኘው፥ የሚያገኘው ከመንፈስ ቅዱስ ብቻ መሆኑን ታምናለች። ሥራዋንም በዚሁ እምነት ስታከናውን ኖራለች፤ ታከናውናለችም። ከፓትርያርኩ ጀምሮ ሊቃነ ጳጳሳት፥ ጳጳሳት፥ ኤጲስ ቆጶሳት ሁሉ፤ **«ናነብር እደዊነ ዲበ ዝንቱ ኅሩይ ገብር ዘእግዚአብሔር፤» «በተመረጠ በዚህ የእግዚአብሔር አገልጋይ ላይ እጃችንን እንጭናለን፤»** በሚል አነጋገር ከሦስት ቊጥር ባላነሱ ኤጲስ ቆጶሳት ድምፅና ተግባር ቤተ ክርስቲያን የምትሾማቸው ሁሉ ተጠሪነታቸው የቤተ ክርስቲያን ነው እንጂ የአንድ ሰው አይደለም። ሁሉም ይህን ያውቃሉ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ሐዋርያውም፤ «ክርስቶስ በደሙ የዋጃትን ቤተ ክርስቲያን እንድትጠብቁ መንፈስ ቅዱስ ጳጳሳት አድርጎ የሾማችሁ እናንት ለመንጋውና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ፤» ወይም፤ «የተሾማችሁባቸውን መንጋዎችን ሁሉና ራቻችሁን ጠብቁ፤» ብሎ የተናገረ ስለዚህ ነው። (የሐ፤ ሥራ ም ፳፥ ቊ ፳፰።)

**፪ኛ፤** ይህ ከዚህ በላይ የጠቀስኩት ቋሚ መመሪያ ሲሆን ልዩ ልዩ መናፍቃን በቤተ ክርስቲያን ውሥጥ በተነሡበት ጊዜ ሁሉ ጉባኤ ጳጳሳት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት እየተሰበሰበ ቤተ ክርስቲያንን ከስሕተት፥ ከኑፋቄ ሲጠብቁ ኖረዋል። በኋላ ግን ከቤተ ክርስቲያን ክብር እየሸሹ፥ ወደ ዓለማዊ ክብር እየተጠጉ፥ የእግዚአብሔርን ኀይልና ሥልጣን መከታ አድርገው መሥራት ሲገባቸው በመንግሥታዊ የፖለቲካ ኀይልና ሥልጣን መጠቀም የፈለጉ መለካውያን ጳጳሳትና ሊቃነ ጳጳሳት በቤተ ክርስቲያን ላይ መከፋፈልን ስለ ፈጠሩ በምድር ላይ ዳግማዊ ክርስቶስ የሚባል መሪ አበጁ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ግን በዚህ የፈተና ጊዜ በታላላቆችና በአስተዋይ ሊቃውንቶቿ አስተዋይነት፥ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ጸንታ ኖረች። ለሰው አልተንበረከከችም። ይህም በኢትዮጵያ አስተዳደር መንግሥት የለውጥ ጊዜ እስከ መጣበት እስከ ፲፱፻፷፮ ዓመተ ምሕረት ድረስ ጸንቶ ኖሯል። ከዚያ ወዲህ ግን የሥጋዊው ቊስል ወደ መንፈሳዊው ተጋብቶ ይመስላል ኢትዮጵያ በቊስል ላይ ቊስል ተጨምሮባት በሥጋዊ አስተዳደር ኮሚዩኒዝም ያመጣባት በሽታ መንፈሳዊ አቋሟንም ጎድቶታል። በዚህም ምክንያት በቤተ ክርስቲያን ከደረሱት ዋና ዋና ችግሮች፤

ሀ፤ የሃይማኖት ሕፀፅና የሥርዓት መበላሸት፤
ለ፤ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውሥጥ ውሥጥ አደግ የሆኑ መናፍቃን መፈልፈልና የኑፋቄ መጻሕፍትን ማብዛት፤
ሐ፤ ፓትርያርኮቿ ወደ ራስ ትምክሕት፥ ወደ እብሪትና ወደ ትዕቢት በመተላለፋቸው ሲኖዶሱን የግል ግዛታቸው ማድረጋቸው፥ በገዛ ሥልጣናቸው ሲኖዶስ እያፈረሱ ሲኖዶስ መሠየማቸው፥ በመንግሥት የሥልጣን ድጋፍ ወደ ማዕረግ መውጣታቸው ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፤ በ0ምስተኛው ፓትርያርክ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ዘመን የታየው ደግሞ በውጭ ያዩት ዳግማዊ ክርስቶስ

ተብሎ መሰየምና በፓትርያርክነት ቢመረጡ በአምላክ ፊንታ ሆኖ መንፈስ ቅዱስን መጋፋት፥ ዳኝነቱን መርገጥ ሆኗል። ይህም በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ የማይጠገን ስብራት፥ የማይድን ቍስል ሆኖባታል።

**፫ኛ፤** እኔ በእነዚህ ፳፪ ና ፳፫ ዓመታት አቤቱታዬን ሳሰማ ኖሬአለሁ። ዕድል ሆነና ዛሬም እጮሃለሁ። ድምፄ ግን በውሃ ውሥጥ እንደሚናገር ሰው ተሰሚነት አላገኘም። ግን በእግዚአብሔር ላይ አሁንም ተስፋ አልቆርጥም። እንደገና እጮሃለሁ፤ እንደገና አቤት እላለሁ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ፍርሃታቸውን ከልባቸው አውጥተው ጥለው ለቤተ ክርስቲያናቸው፥ ለሀገራቸው፥ ለሃይማኖታቸው፥ ለክብራቸው መቆም እስከ ቻሉ ድረስ አቤቱታዬን አሰማለሁ።

ከዚህ በላይ የዘረዘርኩት እንደ መቅድም ያህል ሲሆን ፍሬ ነገሩ የሚከተለው ነው። እንደሚታወቀው ዘንድሮ በ፲፱፻፹፰ የተደረጉት የቤተ ክርስቲያኒቱ ጠቅላላ ስብሰባና የሊቃነ ጳጳሳት ስብሰባ አንደኛ በጥቅምት፥ ሁለተኛ በሚያዝያና በግንቦት መገናኛ ከሚያዝያ ፳፪ እስከ ግንቦት ፮ የተደረጉ ሲሆኑ ሁለቱም ጊዜዎች ሸር የተሞላባቸው ነበሩ። ይህንንም እንደሚከተለው እገልጻለሁ።

**ሀ፤** በቤተ ክርስቲያን የደረሱት ልዩ ልዩ ችግሮች ሁሉ በሲኖዶስ ተመክሮባቸው እንዲወገዱና እርምጃቸውም እንዲገታ በ፲፱፻፹፯ ጥቅምትና ኅዳር ወር ለሲኖዶሱ ማመልከቻ ስጽፍ መልእክቴ በጌታዬ በአምላኬ ትእዛዝ የተደረገ መሆኑን ገለጨ በአፈጻጸሙ ቸልተኛነት እንዳይታይበት ሲኖዶሱን በሾመ በመንፈስ ቅዱስ ዳኝነት ተማጽኜ አቤቱታዬ የእኔ ብቻ ሳይሆን በዐጸደ ሥጋና በዐጸደ ነፍስ ያሉ የኦርቶዶክሳውያን አበውና ምእመናን አቤቱታ መሆኑን ገልጬ ነበር ያቀረብኩት። ነገር ግን የሲኖዶሱ ዋና ጸሓፊ አባ ገሪማና ፓትሪያርኩ ሐሳባቸው እስከ አሁን በቤተ ክርስቲያን የኖረውን የመንፈስ ቅዱስን መሪነት ሽረው የራሳቸውን ጣዖታዊ መሪነት ለመተካት ኖሮ በጥቅምት ወር ፲፱፻፹፰ ዓመተ ምሕረት በተደረገው አጠቃላይ ጉባኤ ላይ ያቀረብኩትን አቤቱታ ጭምር ሳይቀበሉ ከመቅረታቸውም በላይ የመንፈስ ቅዱስን ዳኝነት፥ የሲኖዶሱን ሥልጣን ለግል አድመኞቻቸው ኮሚቴ አሳልፈው በመስጠትና በሱ ውሳኔ ተደግፈው የኑፋቄ መጽሐፍ ማውጣታቸውና መበተናቸው አንሶ ኦርቶዶክሳዊውን የሊቃውንት ጉባኤ አፍርሰዋል።

**ለ፤** ይህ በዚህ እንዳለ ሲኖዶሱ ተሰብስቦ ጉዳዩን እንዲያይ በግል ማመልከቻ፤ በነጻ ፕሬሱ በኩልም ተቃውሞዬን በማሰማት ላይ እያለሁ ሚያዚያ ፲፰ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓመተ ምሕረት የቅሬታ አስወጋጅና የሰላም ኮሚቴ በሚሉት የግል ኮሚቴያቸው ድጋፍ እኔን ካባረሩ በኋላ ከሚያዚያ ፳፪ እስከ ግንቦት ፮ ባደረጉት በአፈና የሲኖዶስ ስብሰባ ሕግ አስወጥተው በመንፈስ ቅዱስ ፊንታ ራሳቸው ፓትሪያርኩ ሲኖዶሱ ወንጌልን ለሚሰብክበት፥ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ለሚያስተምርበት ጉዞ አመራር ሰጪ

(ጣዖት) ወደ መሆን አድገዋል። በቤተ ክርስቲያን ስም ተሰይመው እግዚአብሔርንና ቤተ ክርስቲያንን ሊያገለግሉ የተሾሙ ኤጲስ ቆጶሳት፥ ጳጳሳትና ሊቃነ ጳጳሳት የሲኖዶሱ ዋና ጸሓፊ ሳይቀር ለቤተ ክርስቲያን ተጠሪ መሆናቸው ቀርቶ ለፓትሪያርኩ ተጠሪዎች እንዲሆኑ ሲያደርጉ በዚያ ሚያዚያ ፴ ቀን ተፈርሞ ጸድቋል በተባለውና በጽሕፈት ቤቱ አማካኝነት ለሚመለከተው ሁሉ እንዲተላለፍ የቃለ ጉባኤ ትእዛዝ በተሰጠበት ሕግ፤ ቤተ ክርስቲያን እስከ አሁን ስትሠራባቸው የኖሩት ሕጎችና ደንቦች ሁሉ በዚህ ሕግ ተሻሽለው ከስፍራቸው ሲወገዱ፥ አባ ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ ፈንታ የቤተ ክርስቲያኒቱን የአመራር ሰጪነት ቦታ ሲይዙ በቤተ ክርስቲያን ላይ የአምልኮ ጣዖት ዐዋጅ ታውጀባታል። ፓትሪያርኩ በሾማቸው በእግዚአብሔርና በቤተ ክርስቲያን ላይ በፈጸሙት ተግባር ታላቅ በደል ፈጽመዋል።

ከሳቸው ጋር ቃላቸውን ለማጽደቅ፥ ምኞታቸውን ለሟሟላት በሕጉ ላይ ፈርመዋል ተብሎ ስማቸው የተመዘገበላቸው ፴፩ቱ ጳጳሳትና ሊቃነ ጳጳሳትም እንደ ተባለው አድርገውት ከሆነ ለተፈጸመው በደል ተባባሪዎች ናቸው። ይህም እጅግ የሚያሳዝን ነው። የሚገርመው ደግሞ በዚሁ ሕግ በአንቀጽ ፲፬፤ «ፓትሪያርኩ የተዋሕዶ ሃይማኖትን የሚያፋልስ፥ ሕግጋተ ቤተ ክርስቲያንን የማይጠብቅ፥ ማዕረጉን የሚያጎድፍ ሆኖ መገኘቱ በተጨባጭ ማስረጃ ሲረጋገጥ በምልአተ ጉባኤ ያለአንዳች የሐሳብ ልዩነት በቅዱስ ሲኖዶስ ከተጠና በኋላ በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ መሠረት ከማዕረጉ ይወርዳል፤» የሚል ቃል አስፍሮ ሲኖዶሱን በአፈና ልዩ ሥልጣን ተጠቅመውና እንደ ሌለ አድርገው ካሳዩ በኋላ፤ **«የኑፋቄ መጻሕፍት በማሳተም የተዋሕዶ ሃይማኖትን አፋልሰዋል፤ ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ሳይጠብቁ ቤተ ክርስቲያን ከምታወግዛቸው ጋር የጸሎተ ቅዳሴና የማዕድ ተሳትፎ አድርገዋል፤ ቤተ ክርስቲያኒቱ ከምታወግዘው ፓፓ ቡራኬ ተቀብለዋል፤»** እያልን እየተቃወምን ለተቃውሟችንም ተጨባጭ ማስረጃ እያቀረብን፤ እሳቸውም ይህንን ሳይቃወሙ ይህ እንዳይቀጥል በሥልጣናቸው ተጠቅመው ኦርቶዶክሳዊውን የሊቃውንት ጉባኤ ሲያፈርሱ ጉዳዩን አይቶ ውሳኔ በመስጠት ፈንታ እንደገና በሕግ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስፍራ ተተክተው ለሲኖዶሱ ሥልጣንና ተግባር አመራር ሰጪ ይሆናሉ፤ የሲኖዶሱ አባሎች ሁሉ ለፓትሪያርኩ ተጠሪ ይሆናሉ፤ ሲል የወጣው አዋጅ አፈጻጸም ነው። ይህ ሕገ ቤተ ክርስቲያን ተብሎ የታወጀው ሕግ፤ **«እስመ ሜጥዋ ለዐመፃ ላዕሌከ፤» «ዐመፅን ወደ አንተ መለሷት፤»** ተብሎ እንደ ተጻፈ ቤተ ክርስቲያንን መካነ ጣዖት፥ ምእመናንን መምለኪያነ ጣዖት የሚያሰኝ ስለ ሆነ ምእመናን ሁሉ በሙሉ ድምፅ እንድትቃወሙት በእግዚአብሔርና በቤተ ክርስቲያን ስም እጠይቃለሁ።

**ሐ፤** ከአሁን ጀምሮ ማለት ይህ ቃል በነጻው ፕሬስ ከተላለፈበት ጊዜ ጀምሮ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ቃልና እጅ፥ በሲኖዶሱ ዋና ጸሓፊ በአቡነ ገሪማ ቃልና እጅ፥ ይህን አሁን የተጻፈውን ሕግ የቤተ ክርስቲያን ሕግ ብለው አጽድቀው በተባባሪነት አሳልፈዋል የተባሉ ጳጳሳትና ሊቃነ ጳጳሳት ሁሉ እውነት ሆኖ ከተገኘ የበደሉ

ተባባሪዎች ናቸውና በነሱ ቃልና እጅ ቡራኬ እንዳትቀበሉ፥ እንዳትናዘዙ፤ ስማቸውን በጸሎተ ቅዳሴ የሚጠሩ አለቆች፥ ቀሳውስት፥ ካህናት ካሉም የአምልኮተ ጣዖት አራማጅ ናቸውና ተጠንቀቁባቸው፤ ምክር ስጧቸው፤ እንቢ ካሉም ተለዩዋቸው። እንዲሁም ሐምሌ ፭ ወይም ፮ ቀን ይከበራል ተብሎ ሽርጉድ የሚባልለት በዓለ ሢመት የአሮን የወርቅ ጥጃ መታሰቢያ ሆኖ በቤተ ክርስቲያን ሊከበር የማይገባው ስለ ሆነ በዓሉ ከመድረሱ በፊት የሲኖዶሱ አባላት በአስቸካይ ተሰብስበው ሕጉን ካልሻሩና በጣዖትነት የተሰየሙትን አቡነ ጳውሎስን ከሥልጣናቸው ካላነሡ ምእመናን ይህንን በዓል እንዳታከብሩ ለቤተ ክርስቲያን ደሙን ባፈሰሰ አምላክ ስም፥ ቤተ ክርስቲያንን በሚመራና በሚጠብቅ በመንፈስ ቅዱስ ስም ጥያቄዬን አስተላልፋለሁ።

ምናልባት የሕጉን ጽሑፍ አንብቦ መረዳት የተሳነው፥ ግን በልዩ ልዩ ደጋፊዎቻቸው ተጭበርብሮ በቸልታ የሚመለከተው፤ ከዚያም ዐልፎ በሥልጣናቸው እየተመኩ ለቤተ ክርስቲያን ጥያቄ ጆሯችንን አንሰጥም ብለው ይህን በደል ያደረሱትን ፓትርያርክ አቡነ ጳውሎስን፥ በሦስት የሹመት ስም የሚንቀባረሩትን አባ ገሪማን፥ ለነሱ ድጋፍ የሚሰጡትንም ሁሉ፤ ጌታዬ አምላኬ፤ **«በምድር ያሰራችሁት በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤» ሲል በሰጠው ቃል በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ሥልጣን፤ በጴጥሮስ፥ በጳውሎስ፥ በማርቆስ፥ በቄርሎስ፥ በባስልዮስ፥ በቴዎፍሎስ፥ በተክለ ሃይማኖት ዘደብረ ሊባኖስ ቃል፤ ኃጥእ ደካማም በምሆን በእኔም በቀሲስ ወልደ ጊዮርጊስ ቃል አውግዤአለሁ። ይህን ሕግ የተቀበሉና ከሥራ ላይ ያዋሉ ሁሉ እንደ አርዮስ፥ እንደ መቅዶንዮስ፥ እንደ ንስጥሮስ፥ እንደ ፍላብያኖስ፥ እንደ ኬልቄዶን ጉባኤና ተከታዮቹ እሱራን፥ ውጉዛን ይሁኑ። በማይፈታው በእግዚአብሔር ሥልጣን አስሬአለሁ።**

ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ምስጋና ይሁን አሜን።

ማስጠንቀቂያ፤ አምላኬ ሂድ ተናገር ያለኝን ትእዛዝ ለእናንተ አድርሻለሁ። ሩጫዬንም ጨርሻለሁ። ከእንግዲህ ተጠያቂነቱ የእናንተ የምእመናንና ታሪክ ተጠያቂ ያደረገው የመንግሥት ነው። ለዚህም ምስክሬ ራሱ እግዚአብሔር፥ ቅዱሳን መላእክት፥ ሰማይና ምድር ናቸው።

**(አለቃ አያሌው ታምሩ ዘዲማ ጊዮርጊስ።)**

**(መብሩክ ጋዜጣ፤ ሰኔ ፳፮ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ. ም.)**

# የታላቁ ሊቅ የክቡር አባታችን የአለቃ አያሌው ታምሩ ዐጭር የሕይወት ታሪክ።

## በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ።

«ክቡር ሞቱ ለጻድቅ በቅድመ እግዚአብሔር።»
«የቅዱሳኑ ሞት በእግዚአብሔር ፊት የከበረ ነው።» (መዝ፤ ፻፲፭፣ ፲፭።)

### ፩፤ ልደታቸውና ትምህርታቸው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቀዋሚ ምስክር የሆኑት አለቃ አያሌው ታምሩ፤ ከአባታቸው ከአቶ ታምሩ የተመኙና ከእናታቸው ከወይዘሮ አሞኘሽ አምባዬ፤ በጎጃም ክፍለ ሀገር በብቸና አውራጃ በእነማይ ወረዳ በታላቁ ደብር ወገዳም በደብረ ድማኅ ቅዱስ ጊዮርጊስ ልዩ ስሙ ቤተ ንጉሥ በተባለ ቦታ መጋቢት ፳፫ ቀን ሺሕ ፱፻፲፭ ዓመተ ምሕረት በዕለተ ሆሣዕና ተወለዱ።

ያለፈውንም የወደፊቱንም የሚያውቅ ልዑል እግዚአብሔር ለበለጠ ክብርና አገልግሎት ያዘጋጃቸው ቢሆንም ዕድሜአቸው ለትምህርት ሳይደርስ ገና የሦስት ዓመት ተኩል ሕፃን ሳሉ በፈንጣጣ ሕመም ምክንያት የዐይናቸውን ብርሃን አጥተዋል። የስምንት ዓመት ዕድሜ ልጅ ሳሉ በዓለ ተክለ አልፋን ለማክበር ከአባታቸው ጋር ወደ ዲማ እንደ ሄዱ በዚያው ትምህርታቸውን ለመቀጠል ስላሰቡ ወደ ቤታቸው አልተመለሱም። ከዚህ ጊዜ ጀምሮም በቅርብ ቤተ ዘመድ እየተረዱ ለአንድ ዓመት ያህል ሲማሩ ከቆዩ በኋላ አባታቸው ስላረፉ ኑሮአቸው በትምህርት ቤት ብቻ ስለ ተወሰነ ከቤተ ሰብእ ጋር የነበራቸው ግንኙነት እየቀነሰ መጣ። ይህም ሁኔታ የሚፈልጉትን ትምህርት በአንድ ልብ ለመቀጠል ግድ ብሎአቸዋል።

ክቡር አለቃ አያሌው ታምሩ ምንም እንኳ ሥጋዊ የዐይን ብርሃናቸውን ቢያጡም ልበ ብርሃን በመሆናቸውና ትምህርትን ለመቀበል ፈጣን አእምሮን የታደሉ በመሆናቸው ካሰቡበት ለመድረስ አላገዳቸውም። በዚሁ መሠረት በ፲፭ ዓመት ዕድሜአቸው የቅኔ መምህር ለመሆን በቅተዋል። ስለ ዐይናቸው ብርሃንና ስለ ትምህርታቸው፤ «ምልጃ ዕርቅና ሰላም፤» በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ ፬ ላይ እንዲህ ሲሉ ገለጸዋል። «ይህ ሁሉ የተገኘው ገና በልጅነት ዕድሜዬ፤ በቅዱስ ሐዋርያ ያዕቆብ እንደ ተነገረው የምመራበት፣ የምኖረበት በወሰድከው በዐይኔ ፈንታ ዕውቀት ስጠኝ ብዬ የለመንኩት አምላኬ፤ «ለምኑ ይሰጣችኋል፤ ሹ ታገኛላችሁ፤

በር ምቱ ይከፈትላችኋል፤ ለሚወደኝ እኔ ራሴን እገልጥለታለሁ፤» ሲል በሰጠው ተስፋና በለገሰኝ የአእምሮ ምጽዋት መሆኑን ስለምረዳ ነው፤» ብለዋል።

ታላቁ ሊቅ አለቃ አያሌው ታምሩ በተወለዱበት አካባቢ ባሳለፉአቸው ዓመታት የቀሰሙአቸው ዋና ዋና የቤተ ክርስቲያን ትምህርቶችና ያስተማሩአቸው መምህራን እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል።

ሀ፤ መሪጌታ ከበበው፣ መሪጌታ እውነቴ፣ መሪጌታ ክንፉና መሪጌታ አልማው ከተባሉት መምህራን ጸዋትወ ዜማን ከጣዕመ ዝማሬው ጋር፤

ለ፤ አለቃ ማርቆስ፣ መሪጌታ ወልደ ኪዳን፣ መሪጌታ ያሬድ ከተባሉት መምህራን የግእዝን ቋንቋ ከጠቅላላ ሙያው ጋር፤

ሐ፤ አባ አካሉ፣ መምህር እጅጉ (ዘወልደ ማርያም) ከተባሉት መምህራን የሐዲሳትን ጣዕመ ትርጓሜ፤ ከብሉያት አራቱን ብሔረ ነገሥት፤ ትርጓሜ ዳዊት ከነቢያትና ከሰሎሞን ጋራ፤ የውዳሴ ማርያምና የቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ።

ከላይ የተጠቀሱት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፤ ከዚህ ያልተጠቀሱትንም ሌሎች ትምህርቶች ሰንቀው ሰፊ አገልግሎት ወደሚሰጡበት ወደ አዲስ አበባ ከተማ በ፲፱፻፴፱ ዓመተ ምሕረት አጎታቸውን ታላቁን ሊቅ ክቡር መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀምበሬን ተከትለው መጡ።

ክቡር አለቃ አያሌው ታምሩ ከዕውቀት ወደ ዕውቀት እያደጉ ከመሄዳቸውም በላይ ያወቅሁት ይበቃኛል ሳይሉ፤ ወደ አዲስ አበባም ከመጡ በኋላ፤

ሀ፤ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ መልካም ፈቃድ በጊዜው የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ተብሎ በሚጠራው ትምህርት ቤት ከስመ ጥሩው መምህር ፈላታዎስ መጽሐፈ ኢሳይያስን፣ መጽሐፈ ዐሥርቱ ወክልኤቱ ደቂቀ ነቢያትን፣ መጽሐፈ አስቴርን፣ መጽሐፈ ዮዲትንና መጽሐፈ ጦቢትን ከነ ሙሉ ትርጓሜአቸው፤

ለ፤ በዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ትምህርት ቤት ከመጋቤ ምስጢር ጌራ ስምንቱን ብሔረ ኦሪትና መጽሐፈ ዳንኤልን ከነ ትርጓሜአቸው፤

ሐ፤ ከመምህር ጽጌ (ኋላ ብፁዕ አቡነ ማርቆስ ዘጎጃም) የአርባዕቱን ወንጌል ትርጓሜ፤

መ፤ ከመምህር ገብረ ማርያም መጽሐፈ ኪዳንንና ትምህርተ ኅቡዓትን ተምረዋል።

አባታችን አለቃ አያሌው ታምሩ የቅድስት ተዋሕዶ ሃይማኖታቸውን ዕውቀት ካደላደሉ በኋላ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና በሌሎች አብያተ ክርስቲያን መካከል ያለውን ልዩነት ለማወቅ፤ እንዲሁም ባለ ማወቅ የተሳሳቱትን ለመመለስ፤ የእምነታቸውን መሠረትና የእንግሊዝኛ ቋንቋ፣ እንዲሁም ለዐይነ ሥዉራን የተዘጋጀውን የብሬል ጽሑፍ ለመማር ወደ እንጦጦ ወንጌላዊት ሚስዮን ትምህርት ቤት ገቡ። በዚያም የፈለጉትን ያህል መቀጠል ባይችሉም የብሬል ጽሑፍና መጠነኛ የሆነ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተምረው ወጥተዋል።

ክቡር አለቃ አያሌው ታምሩ ስለ ትምህርታቸው በአጠቃላይ፤ «የኢትዮጵያ እምነት በሦስቱ ሕግጋት፤» በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ ፲፫ ላይ የገለጹትን እንጠቅሳለን። «ትምህርቴ እንደ መምህሮቼና እንደ ትምህርት

ቤቶቹም ብዛት ሙሉ አይደለም። ዕውቀቴም አነስተኛ ነው። ይህንኑ ከመምህራኑ ከሞላ ጎደል የሰማሁትን የትምህርት ጣዕም በጥቂቱ እንዳውቀውና እንዳስተውለኝ ያደረገኝ፤ ምሬቱንም ያጠነከረብኝ ዐዲሱ ዘመን ብዙ የትምህርት ዐይነቶችን ስላስገኘና በወንጌላዊት ሚሲዮን ትምህርት ቤት በነበርኩበት ጊዜ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና በሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ያለውን ልዩነት በደንብ ለማጥናት ስላገዘኝ፤ ከዚያ ወዲህ ራሴን መቆጣጠር ስጀምር ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በሎንዶን ያሳተሙትን መጽሐፍ ቅዱስ በቤተ መጻሕፍት ወመዘክር አዘውትሬ መመልከቴ፣ ከመልአከ ብርሃን አድማሱ ጀምበሬና ከመምህር ይኄይስ ወርቄ ጋር በጥብቅ መነጋገሬ ነው። ሆኖም ዕውቀቴ በዚህ ሁሉ ፍጹም ሊሆን አልቻለም። ግን ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ፤ ስለ ቀናችው ሃይማኖቷና ስለ ተቀደሰው ምግባሯ፤ በእግዚአብሔርና በሷ መካከልም ስላለው ጥሩ ፍቅር በሕሊናዬ የሚወጣው የሚወርደው ሐሳብ እንደ እሳት ያቃጥለኛል። ቆሜ ተቀምጬ፣ ተኝቼ ተነሥቼ በምሄድበትና በማርፍበት፣ በምበላበትና በምጠጣበት ጊዜ ሁሉ ትሩር አድርጌ የምመለከተው እሱን ብቻ ነው። በዚህ ምክንያት በመኝታዬ ጊዜ እንኳ የጤና ዕንቅልፍ አጥቼ ሕልም ይሆንብኝና፤ «ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር፤» «አሐዱ ነገሩ ለኵሉ ዓለም፤» ያመጽኡ እምሳባ ወርቀ ወስኂነ፤» «ቃል ወልድ እኁየ ናሁ ውእቱ መጽአ፤» «ንግሥተ አዜብ ትትነሣእ አመ ዕለተ ደይን፤» «ናሁ መሰግላን መጽኡ እምብሔረ ጽባሕ፤» «ሁር ትልዎ ለዝንቱ ሠረገላ፤» «ቃል ሥጋ ኮነ፤» «ተሣሃለነ በሞተ ወልዱ፤» ስለሚሉትና እነሱንም ስለ መሳሰሉት ቃላት ሙሴን፣ ዳዊትን፣ ኢሳይያስን፣ ንግሥተ ሳባን፣ ማቴዎስን፣ ዮሐንስን፣ ሉቃስን፣ ፊልጶስንና ጳውሎስን ስጠይቅ አድራለሁ። ይሁን እንጂ፤ «ጥበብን የሚሻ ሰው ቢኖር ሳያወላውል ሳይጠራጠር ከእግዚአብሔር ይለምን፤ እግዚአብሔርም ንፍገት የሌለው አምላክ ነውና ይሰጠዋል፤» (ያዕ፤ ፩፣ ፭።) ብሎ ሐዋርያው ያዕቆብ እንደ ተናገረው፤ እግዚአብሔር አምላኬ የለመንኩትን ስላልነሣኝ፤ በዕውቀቴ ሳይሆን በቸርነቱ እየተረዳሁ ይህን መጽሐፍ ሳዘጋጅ ምስጋናዬን ለሱ አስቀድማለሁ፤» በማለት ገልጸዋል።

## ፪፤ መንፈሳዊ አገልግሎትና አስተዳደር።

ሀ፤ ወደ አዲስ አበባ ከመጡ በኋላ ዛሬ የክቡር ዐፅማቸው ማረፊያ በሆነው ደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን የቅኔ መምህርነት አገልግሎታቸውን በ፲፱፻፴፱ ዓመተ ምሕረት ጀመሩ። በመቀጠልም በዚሁ ደብር፤ መጀመሪያ የሊቀ ጠበብትነት ማዕረግ አግኝተው ያገለገሉ ሲሆን ኋላም የዚሁ ደብር አስተዳዳሪ በመሆን ሰፊ አገልግሎት አበርክተዋል።

ለ፤ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት የሊቃውንት ጉባኤ ተመርጠው ከሰኔ ወር ፲፱፻፶፰ ዓመተ ምሕረት ጀምሮ የስብከተ ወንጌል ክፍል አባል ሆነው አገልግለዋል።

ሐ፤ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሊቃውንት ጉባኤ አባልና ዋና ሰብሳቢ ሆነው ሠርተዋል። በዚህም የሥራ ዘመናቸው፤ የቤተ ክርስቲያን የወንጌል ትምህርት በመሆኑ ይህ አገልግሎት ሳይበረዝና ሳይከለስ እምነቱም፣ ትምህርቱም፣ ሥርዐቱም ተጠብቆ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ ለማድረግ የሚያስችለውን መንገድ ለመቀየስ በተሰጣቸው ኀላፊነት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ሌት ተቀን ሠርተዋል። ዐልፎ ዐልፎም ከውስጥም ሆነ ከውጪ ለሚነሡት መናፍቃን መልስ በመስጠት፣ በቤተ ክርስቲያኒቱ በየጊዜው የሚታተሙትን መጻሕፍት በማረምና ለኅትመት እንዲበቁ በማድረግ፤ ስለ ቤተ ክርስቲያንም ሆነ ስለ ቅድስት ሀገራችን ኢትዮጵያ ለሚጠየቁ ጥያቄዎች መልስ በመስጠት፤ በበዓላትም ሆነ በሌሎች አጋጣሚዎች በራዲዮ፥ በቴሌቪዥን፥ በመጽሔቶችና በጋዜጦች ትምህርትና ምክር በማስተላለፍ ሀገራዊና ሃይማኖታዊ ኃላፊነታቸውን ተወጥተዋል። ክቡር አለቃ አያሌው ታምሩ በነበራቸው ዕውቀትና ኀላፊነት፤ ሐዲስ ኪዳንን በግእዝና በአማርኛ ፥ መጽሐፈ ግጻዌ፥ ሃይማኖተ አበው የተባሉትን መጻሕፍት ከሌሎች የጉባኤው አባላት ጋር ተርጉመው እንዲታተሙ አድርገዋል። ከነዚህም በተጨማሪ በግላቸው ገድለ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስን፥ ገድለ ቅዱስ ጊዮርጊስን፥ ገድለ ቅዱስ ቴዎድሮስ በናድልዮስን ከግእዝ ወደ አማርኛ ተርጉመዋል።

መ፤ ከሊቃውንት ጉባኤ ሰብሳቢነት ሥራቸው ላይ ደርበው በተጨማሪ የኢተዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ መሥሪያ ቤት የታሪክና የሥነ ጽሑፍ ማደራጃ ዋና መምሪያ ሥራ አስኪያጅ በመሆን አገልግለዋል።

ሠ፤ በኢተዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ሊቀ መንበርነት በሚመራው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት የአስተዳደር ጉባኤ ውስጥ አባል ሆነው ሠርተዋል።

ረ፤ በትንሣኤ ዘጉባኤ ማሳተሚያ ድርጅት ውስጥ የመጻሕፍት አዘጋጅ ኮሚቴ አባል ሆነው አገልግለዋል።

ሰ፤ በቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ መንፈሳዊ ኰሌጅ ከ፲፱፻፶፬ እስከ ፲፱፻፷፬ ዓመተ ምሕረት፤ እንዲሁም በተግባረ እድ ትምህርት ቤትና በቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት መንፈሳዊ ትምህርት አስተምረዋል።

ቀ፤ ከኢትዮጵያ ዓይነ ሥውራን ማኅበር መሥራቾች አንዱ ሲሆኑ፤ መጀመሪያ የማኅበሩ ምክትል ፕሬዚዳንት ኋላም የቦርድ ሊቀ መንበር በመሆን አገልግለዋል።

## ፫፤ በግላቸው ያዘጋጁአቸው መጻሕፍት።

ክቡር አለቃ አያሌው ታምሩ በሕይወት ዘመናቸው ያበረከቷቸው አገልግሎቶች ዝርው ሆነው አልቀሩም። በመጽሐፍ ጥራዝ አዘጋጅተውና አሳትመው ለትውልድ ያስተላለፏቸው መጻሕፍት ዘጠኝ ሲሆኑ በይዘታቸው በሁለት የተከፈሉ ናቸው። በአንደኛው ክፍል ያሉት የቤተ ክርስቲያንንና የኢተዮጵያን ማንነት ለኢትዮጵያውያን ለማስተማር የተዘጋጁ ሲሆኑ፤ በሁለተኛው ክፍል ያሉት ደግሞ ከቤተ ክርስቲያን ውስጥም ሆነ ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ለተነሡና ለሚነሡ መናፍቃን መልስ በመስጠት የምእመናንን ልቦና ለማጽናት የሚያስችል መልእክት የሚያስተላልፉ ናቸው። ከነዚህ መጻሕፍት ውስጥ ዐምስቱ በቤተ ክህነት አገልገሎት ላይ የተዘጋጁ ሲሆኑ፤ አራቱ ደግሞ ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በግፍ ከታገዱበት ከ፲፱፻፹፫ ዓመተ ምሕረት በኋላ የተዘጋጁ ናቸው።

በቤተ ክህነት አገልገሎት ላይ በነበሩበት ጊዜ ያዘጋጇቸው፤ «መች ተለመደና ከተኰላ ዝምድና»፥ «የኢትዮጵያ እምነት በሦስቱ ሕግጋት»፥ «የኑሮ መሠረት ለሕፃናት»፥ «ወላዲተ አምላክ በኢትዮጵያ»፥ «የጽድቅ በር» የተባሉት መጻሕፍት ናቸው። ከሥራ ገበታ ከታገዱ በኋላ በመኖሪያ ቤታቸው ሆነው ያዘጋጇቸው፤ «ምልጃ፥ ዕርቅና ሰላም»፥ «ተአምርና መጽሐፍ ቅዱስ»፥ «መልእክተ መንፈስ ቅዱስ»፥ «ዜና ሕይወት ዘቅድስተ ቅዱሳን እመ አምላክ» የተባሉት ናቸው።

## ፬፤ የቤተ ሰብእ ሁኔታ።

ክቡር አለቃ አያሌው ታምሩ በቤተ ክርስቲያን ሥርዐት መሠረት በሥርዐተ ተክሊል ከወይዘሮ ርብቃ ልሳነ ወርቅ ጋር ሚያዝያ ፲፪ ቀን ፲፱፻፶ ዓመተ ምሕረት ጋብቻ ፈጽመው ፲ ልጆችና ፲፪ የልጅ ልጆች ለማፍራት ታድለዋል።

## ፭፤ ስለ ቅን አገልግሎታቸው የተሸለሚቸው ሽልማቶች።

ክቡር አባታችን አለቃ አያሌው ታምሩ እጅግ ይወዷቸውና ያከብሯቸው በነበሩት በግርማዊ ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ መልካም ፈቃድ፤

፩ኛ፤ በ፲፱፻፵፩ ዓመተ ምሕረት የመምህራን ሽልማት ሜዳይ፤

፪ኛ፤ በ፲፱፻፷፪ ዓመተ ምሕረት የኢትዮጵያ የክብር ኰከብ የፈረሰኛ ደረጃ ኒሻን ተሸልመዋል።

## ፯፤ ከቤተ ክህነት አገልግሎት ስለ መሰደዳቸው።

ክቡር አለቃ አያሌው ታምሩ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት፥ ትምህርት፥ ሥርዐትና አስተዳደር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተለወጠና እየተበላሸ መሄዱ በእጅጉ ያሳዝናቸው ስለ ነበር፤ የቤተ ክርስቲያኒቱ የሊቃውንት ጉባኤ ዋና ሰብሳቢ እንደ መሆናቸው መጠን፤ ጥፋቱ እንዲታረም ብዙ አቤቱታና ተማጽኖ ጉዳዩ ወደሚመለከተው ወደ ቤተ ክርስቲያኒቱ ቅዱስ ሲኖዶስ፤ ሲኖዶሱን በመሠረተና በሚመራው በመንፈስ ቅዱስ ስም ተማጽነው ቢያቀርቡም ሲኖዶሱ ጉዳዩን ለማፈን ከመሞከር በስተቀር ምንም እርምጃ ሳይወስድ ቀርቷል። እሳቸውም ያቀረቡት ጥያቄ መፍትሔ ባለማግኘቱ ጉዳዩን ለሚመለከተው ለኢተዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን ለማሳወቅና፤ በቤተ ክርስቲያን ላይ ዐመፅ የሚፈጽሙትን ፓትርያርኩንና የእሳቸው ተባባሪ የሆኑ ጳጳሳትን ባላቸው ከፍተኛ ኀላፊነተና ሥልጣነ ክህነት በሥልጣነ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፥ በሥልጣነ ጴጥሮስ ወጳውሎስ ለማውገዝ ተገደዋል። ከዚህም በተጨማሪ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካህናት በጸሎተ ቅዳሴ ጊዜ የዐመፀኛውን ፓትርያርክ ስም እንዳይጠሩ ውግዘት አስተላልፈዋል። ምእመናንም ከዐመፀኞች ካህናት ምንም ዐይነት አገልገሎት ማገኘት የማይችሉ መሆናቸውን ተገንዝበው ሕይወታቸውን በጥንቃቄ እንዲመሩ አሳስበዋል።

በዚህም ምክንያት ከ፶ ዓመት በላይ ካገለገሉበት የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በሐሰት ክስና የእምነት ክሕደት ቃላቸውን ባልሰጡበት ሁኔታ ያለ ምንም ጡረታ ከሥራ ገበታቸው ላይ በግፍ እንዲነሡ በመደረጉ ከሚያዝያ ወር ፲፱፻፹፫ ዓመተ ምሕረት ጀምሮ እስከ ዕለተ ዕረፍታቸው በመኖሪያ ቤታቸው ተወስነው ኖረዋል። በነዚህ ዓመታትም በየዕለቱ ለጸሎት ባዘጋጁት አነስተኛ ክፍል በመገኘት ወደ ልዑል እግዚአብሔር በመጸለይና በማልቀስ ይተጉ ነበር። ምእመናንም በተኲላ እንዳይነጠቁ በተለያዩ ጋዜጦች ትምህርትና ማበረታቻ ሲሰጡ ኖረዋል። ከቤተ ክህነት በግፍ ተሰድጄአለሁ በማለትም ሥራቸውን አልዘነጉም፤ ከላይ ከጠቀስናቸው መጻሕፍት ውስጥ አራቱን ያዘጋጁት በዚሁ ጊዜ ውስጥ ነበር። እንዲሁም መኖሪያ ቤታቸው ድረስ እየመጡ ለሚጠይቋቸው ሰዎች መልስና ምክር በመስጠት አገልግሎታቸውን ሳያቋርጡ ቤተ ክርስቲያን የጣለችባቸውን ኀላፊነት ሲወጡ ኖረዋል።

## ፰፤ ዕረፍታቸውና የቀብራቸው ሥነ ሥርዐት።

ክቡር አባታችን ምንም አገራቸውንና ቤተ ክርስቲያናቸውን ለማገልገል በቁርጥ ዐሳብ ሲሠሩ ቢኖሩም፤ ከአዳም ጀምሮ ለሰው ልጆች ሁሉ የተሰጠውን የሥጋ ሞት ለመቅመስ የእሳቸውም ተራ በመድረሱ፣ ለጥቂት ቀናት በሕመም ከሰነበቱ በኋላ ነሐሴ ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓመተ ምሕረት፤ እጅግ ይወዷት የነበረችው የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም መታሰቢያ የሆነው ጾመ ፍልሰታ ሱባዔ ሲጠናቀቅ በልጇ ፈቃድ የሰላም ዕንቅልፍ እንዳንቀላፉ ያለ ምንም ጻዕር ከዚህ ዓለም ወደ ዘለዓለም ሕይወት ተሸጋግረዋል። ከማረፋቸው ሦስት ቀናት በፊትም በተለየ የተመስጦ ራእይ ውስጥ ሆነው ብዙ ምስጢር ያላቸው ቃላት የተናገሩ ሲሆን፤ ከነዚህ ውስጥም፤ «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በመወከል ወደ ግብጽ ቤተ ክርስቲያን ሄደህ እንድታስተምር ተብዬ ተጠርቼአለሁና ልብሴን ስጡኝ፤ ከመንበረ ማርቆስ የወርቅ ሰዓትና የወርቅ ሣህን ተሸለምኩ፤ የተሸለምኩትን የወርቅ ሰዓት ስጡኝ፤» የሚሉ ይገኙባቸዋል።

የክቡር አባታችን የቀብር ሥነ ሥርዐት ነሐሴ ፲፯ ቀን ፲፱፻፱፺፱ ዓመተ ምሕረት ብዙ ዘመን ባገለገሉበት የአዲስ አበባው ደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ብዙ ሕዝብ በተገኘበት ተፈጽሟል። የዕረፍታቸው ፴ኛ ቀን መታሰቢያም መስከረም ፲፯ ቀን ፳፻ ዓመተ ምሕረት በጸሎት ታስቦ ውሏል።

ስለ ክቡር አባታችን አለቃ አያሌው ታምሩ ከብዙ በጥቂቱ፥ ከረጅሙ ባጭሩ ለመጥቀስ ሞከርን እንጂ የእሳቸው ትምህርት በብዙ ኢትዮጵያውያን ልብ ውስጥ የተጻፈ መሆኑ እሙን ነው። ትጉሁ የወንጌል ገበሬ አባታችን አባታቸው ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ እንደ ተናገረው ለእግዚአብሔር ኖረው ለእግዚአብሔር የሞቱ፤ ደም አልባ ሰማዕትነትን የተቀበሉ አባት ናቸው። ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለ፤ «እኔ በሕይወት ብኖር ክርስቶስን ለማገልገል ነው፤ ብሞትም ዋጋ አለኝ።» (ፊልጵ፤ ፩፥ ፳፩።)

አምላካችን እግዚአብሔር ለአባታችን አለቃ አያሌው ታምሩ (አቡነ ወልደ ጊዮርጊስ) በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት ዕረፍተ መንግሥተ ሰማያትን ያድልልን። ለባለ ቤታቸው፥ ለልጆቻቸው፥ ለልጅ ልጆቻቸው፥ በመንፈሳዊ ዕውቀት ኰትኵተው ላሳደጓቸው፤ እንዲሁም ለሚወዳቸውና ለሚያፈቅራቸው የኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን መጽናናቱን ይስጥልን።

**ክብር ምስጋና ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ፤ እንዲሁም ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም ይሁን። አሜን።**

## የሊቀ ሊቃውንት አለቃ አያሌው ታምሩ መጻሕፍት፡-

፩፤ የኑሮ መሠረት ለሕፃናት። (፲፱፻፶፫ ዓ. ም.)
፪፤ የኢትዮጵያ እምነት በሦስቱ ሕግጋት። (፲፱፻፶፫ ዓ. ም.)
፫፤ መቅ ተለመደና ከተኩላ ዝምድና። (፲፱፻፶፫ ዓ. ም.)
፬፤ ወላዲተ አምላክ በኢትዮጵያ። (፲፱፻፷፱ ዓ. ም.)
፭፤ የጽድቅ በር። (፲፱፻፷፱ ዓ. ም.)
፮፤ ምልጃ፥ ዕርቅና ሰላም። (፲፱፻፸፪ ዓ. ም.)
፯፤ ተአምርና መጽሐፍ ቅዱስ። (፲፱፻፸፫ ዓ. ም.)
፰፤ መልእክተ መንፈስ ቅዱስ። (፲፱፻፸፭ ዓ. ም.)
፱፤ ዜና ሕይወት ዘቅድስተ ቅዱሳን እመ አምላክ። (፲፱፻፸፱ ዓ. ም.)

### ፩፤ የኑሮ መሠረት ለሕፃናት። (፲፱፻፶፫ ዓ. ም.)



- ለግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፸ኛ ዓመት በዓለ ልደት መታሰቢያነት የተዘጋጀ ነው።
- በተለይ ለሕፃናት መማሪያነት ታስቦ የተዘጋጀ ስለ ሆነ መሠረታዊ (የመጀመሪያ ደረጃ) የሃይማኖት ትምህርት ይገኝበታል።
- የተዘጋጀው ለሕፃናት እንዲስማማ በማሰብ በሦስት ዐይነት መልክ ማለት በስድ ንባብ፥ በግጥምና በጥያቄ ነው።
- የግእዝና የአማርኛ ፊደል፥ ቁጥርና ፊደለ ሐዋርያ ይገኝበታል።
- የሥነ ፍጥረትና የሔዋን ተፈጥሮ ታሪክ ይገኝበታል።
- ዐሥሩ የኦሪት ትእዛዛትና ስድስቱ የወንጌል ትእዛዛት ተዘርዝረውበታል።
- ስለ ባልና ሚስት ሥልጣን፥ ስለ ባልና ሚስት መፈቃቀርና መከባበር ትምህርት ይሰጣል።
- ስለ ወላጆችና ስለ ልጆች፥ ስለ ገዢና ተገዢ መብት የተሰጠው የእግዚአብሔር ቃል ይገኝበታል።


- እግዚአብሔርን መፍራት፥ ንጉሥን ማክበር እንደሚገባ ያስተምራል።
- የዘወትር ጸሎትና ምስጋና ይገኝበታል።

## ፳፤ የኢትዮጵያ እምነት በሦስቱ ሕግጋት። (፲፱፻፶፫ ዓ. ም.)




- እምነት በኢትዮጵያ ያለውን አጠቃላይ ታሪክ ያቀርባል።
- ሦስቱ ሕግጋት የተባሉት ሕገ ልቡና፥ ሕገ ኦሪትና ሕገ ወንጌል መሆናቸውንና በእነዚህ ሕግጋት እምነት በኢትዮጵያ እንዴት እያደገ እንደ መጣ በስፋት ያብራራል።
- ኢትዮጵያ በሦስቱም ሕግጋት ጊዜ እግዚአብሔርን ከመከተል ያላቋረጠች አገር መሆኗን ያስረዳል።
- በሦስቱ ሕግጋት ጊዜ ኢትዮጵያ ከእግዚአብሔር ያገኘቻቸውን ሀብታት በዝርዝር ይገልጻል።
- ኢትዮጵያውያን እንዴት በሕገ ልቡናና በሕገ ኦሪት እየተመሩ በሕገ ወንጌል ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ለመቀበል እንደ በቁ ያብራራል።
- ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ በአንዳንድ የውጭ አገር ጸሐፊዎች የተጻፈውን በማስተባበል ከኢትዮጵያውያን አባቶች የተገኘውን እውነተኛ ታሪክ ያቀርባል።
- የግእዝን ቋንቋ መሠረትና እድገት ያትታል።
- ክህነት በኢትዮጵያ መቼ እንደ ተጀመረ ያመለክታል።
- የታላቁን ካህን የመልከ ጼዴቅን ኢትዮጵያዊነት ያስረዳል።
- የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት መሠረቱና እድገቱ እንዴት እንደ ሆነ ያስተምራል።
- ንግሥተ ሳባ ወይም ንግሥተ አዜብ ኢትዮጵያዊት መሆኗንና ከንጉሥ ሰሎሞን ቀዳማዊ ምኒልክን እንደ ፀነሰች ያስረዳል።
- ቀዳማዊ ምኒልክ ከእስራኤል ታቦተ ጽዮንንና መጻሕፍተ ብሉያትን ይዞ ከሌዋውያን ካህናት ጋራ ወደ አኲስም እንደ ተመለሰ ያስረዳል።
- ዐምስቱን አዕማደ ምስጢር በስፋትና በጥልቀት ያስተምራል።
- ፍቅረ እግዚአብሔርና ፍቅረ ቢጽ ምን እንደ ሆኑ ያስተምራል።
- ፍቅር፥ ጸሎት፥ ጾም፥ ምጽዋት፥ ስግደት፥ ትሕትና፥ ንጽሕና፥ ትዕግሥት፥ ንስሐ፥ ተዘክሮተ እግዚአብሔርና ምስጋና ምን እንደ ሆኑ፥ መሠረታቸው ምን እንደ ሆነና ጥቅማቸው ምን እንደ ሆነ ያብራራል።
- በኢትዮጵያ የሚከበሩ በዓላት የትኞቹ እንደ ሆኑና መሠረታቸው ምን እንደ ሆነ ያስተምራል።

## ፫፤ መች ተለመደና ከተኩላ ዝምድና። (፲፱፻፶፫ ዓ. ም.)



- ከአባ አየለ ተክለ ሃይማኖት ዘዐቢይ አዲ በ፲፱፻፶፩ ዓ. ም. ለተጻፈው «የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስለ ክርስቶስ ባሕርያት አካላዊ ተዋሕዶ የምታምነው ትምህርት» የተባለ መጽሐፍ ሙሉ መልስ ሆኖ የተዘጋጀ ነው።
- አባ አየለ፤ «የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ስለ ክርስቶስ የሚያምኑት እምነትና ትምህርት ልዩነቱ የቃል አገላለጽ እንጂ የምስጢር አይደለም፤» በማለት የገለጹትን ሐሳብ በመቃወም በመካከላቸው ሰፊ ልዩነት መኖሩን፥ ልዩነቱም ምን እንደ ሆነ በስፋትና በጥልቀት ያብራራል።
- በተዋሕዶ እምነትና በጸጋና በቅባት መካከል ያለውን ልዩነት በስፋት ያብራራል።
- በኢትዮጵያ ቤተ ክርያቲያንና በግብጽ መንበረ ማርቆስ መካከል ያለውን የእምነት አንድነት ያስረዳል።
- የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የራሷን ተወላጆች ጵጵስና መሾም እስከ ጀመረችበት ጊዜ ድረስ ጳጳሳት ለምን ከግብጽ መንበረ ማርቆስ እየተሾሙ ይመጡላት እንደ ነበረ ያስረዳል።
- «ባሕርየ መለኮት ከባሕርየ ትስብእት፤ አካለ መለኮት ከአካለ ትስብእት ስለ ተዋሐደ፤ ይህም ተዋሕዶ ከመዋሐድ በፊት በመለኮትና በትስብእት መካከል ያለውን ልዩነት አጥፍቶ አንድነትን አጸናው፤ ቃል ሥጋ ሆኖ ክርስቶስ ተባለ፤» በማለት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የምታምነውን እምነትና ትምህርት በስፋትና በጥልቀት ያብራራል።

## ፬፤ ወላዲተ አምላክ በኢትዮጵያ። (፲፱፻፴፱ ዓ. ም.)




- በኢትዮጵያ በተለይ ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ያለውን አስተሳሰብ፥ ትምህርትና ባህል የሚገልጽ ነው።
- ልዑል እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ኢትዮጵያን ለእናቱ ለእመቤታችን ርስት፥ ሕዝቧንም ዐሥራት አድርጎ መስጠቱን ያስረዳል።
- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሳለ «እነሆ ልጅሽ»፥ «እነኋት እናትህ» በማለት በእመቤታችንና በክርስቲያኖች መካከል የዐደራ እናትነትንና የዐደራ ልጅነትን እንደ መሠረተ ያስተምራል።
- ስለ እመቤታችን ዕረፍትና ትንሣኤ ይተርካል።
- ለእመቤታችን የሚገባውን አጠራር፥ ምልጃና ምስጋና ያስተምራል።
- እመቤታችን ስግደት፥ አምኃና በረከት እንደሚገባት ያስተምራል።
- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በእመቤታችን ስም የሚከበሩት በዓላት የትኞቹ እንደሆኑና እንዴት እንደሚከበሩ ይገልጻል።
- በአጠቃላይ፤ ኢትዮጵያ ስለ እመቤታችን የምታደርገውን ሁሉ አምላክ ናት ብላ ሳይሆን አምላክን የወለደች፥ የአምላክ እናት ናት ብላ መሆኑን፤ ይህም የክርስትና እምነት፥ ትምህርትና ሥርዓት ተስተካክሎ ወደ አገራችን ከገባበት ጊዜ ጀምሮ የኖረ እንጂ ኋላ የመጣ አለመሆኑን ያስረዳል።

## ፭፤ የጽድቅ በር። (፲፱፻፴፱ ዓ. ም.)




- በተለይ ጾምን በተመለከተ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ያለውን እምነት የሚገልጥና የሚያብራራ ነው።
- የጾምን ትርጉም ያስረዳል።
- የጾምን አጀማመርና ሥርዓት ይገልጻል።
- በብሉይ ኪዳን የነበረውን የጾም ሥርዓት ያብራራል።
- ጾም በሐዲስ ኪዳን ያለውን ቦታና የአፈጻጸም ሥርዓቱን ይዘረዝራል።
- በሐዲስ ኪዳን ስላሉት አጽዋማት (ዐቢይ ጾም፥ ሰሙነ ሕማማት፥ ጾመ ድኅነት፥ ጾመ ስብከት፥ ጾመ ሐዋርያት፥ ጾመ ፍልሰታ፥ ጾመ ገሃድና ጾመ ነነዌ) ገለጻ ይሰጣል።
- የጾም ኃይሎቿ ምን ምን እንደ ሆኑ ይዘረዝራል።
- አርምሞ ምን እንደ ሆነና ለምን እንደሚጠቅም ያስረዳል።
- የኅብረት ጾም ምን እንደ ሆነና በምን መልክ እንደሚፈጸም፥ ጥቅሙም ምን እንደ ሆነ ይገልጻል።

## ፮፤ ምልጃ፥ ዕርቅና ሰላም። (፲፱፻፺፪ ዓ. ም.)




- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በተለይ ምልጃንና ዕርቅን በተመለከተ ያላትን እምነት በጥልቀትና በስፋት ለማስተማር የተዘጋጀ ነው።
- ምልጃ ወይም ዕርቅ ምን ማለት እንደሆነ፥ ቃሉ ስንት ዐይነት መልኮችና አገባቦች እንዳሉት ያስረዳል።
- የምልጃ መልኮች ምንና ምን እንደሆኑ ያስረዳል።
- ምልጃ ወይም ዕርቅ በብሉይ ኪዳን በምን መልክ ይፈጸም እንደ ነበር ይገልጻል።
- ሰውን ከእግዚአብሔር ለማስታረቅ ከአዳም ጀምረው የነበሩ ካህናትና ነቢያት የፈጸሙትን ምልጃ ይዘረዝራል።
- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰውን ለመቤዠት የፈጸመውን የአስታራቂነት ሥራ በስፋት ያትታል።
- ጌታችን የአስታራቂነቱን ሥራ በመስቀል ላይ ሞቶ ከፈጸመ በኋላ የአስታራቂነትን ሥልጣን ለቅዱሳኑ እንደ ሰጠ ያስተምራል።
- የቅድስና ምንጭ እግዚአብሔር ቅድስናን ለአገልጋዮቹ እንዴት እንደሚያድል ያስረዳል።
- የመላእክት፥ የእመቤታችን፥ የመስቀል፥ የቤተ ክርስቲያንና የጻድቃንና የሰማዕታት ቅድስና እንዴት እንደ ሆነ፥ ልዩነቱም ምን እንደ ሆነ ያስረዳል።
- ሃይማኖት፥ ድኅነትና ሰላም ምን እንደ ሆኑ ያስረዳል።
- ጸጋና መሠረቱ ተገልጾበታል።
- 


## ፯፤ ተአምርና መጽሐፍ ቅዱስ። (፲፱፻፺፫ ዓ. ም.)




- ከጥላሁን መኮንን «መጻሕፍተ ኑፋቄ በመጽሐፍ ቅዱስ ዐይን ሲታዩ» በሚል ርእስ ለተጻፈ መጽሐፍ መልስ ሆኖ የተዘጋጀ ነው።
- የተዘጋጀው ለእመቤታችን ለምክሐ ደናግል ማርያም ክብር ሲሆን መታሰቢያነቱ ለክቡር አቶ ሙሉጌታ ገብረ ወልድ ነው።
- ተአምር፥ ገድልና ድርሳን ምን እንደ ሆኑ ይገልጻል።
- በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተአምር፥ ገድልና ድርሳን እየተባሉ የሚጠሩት መጻሕፍት የመጻሕፍት ቅዱሳትን ፍሬ ነገር የሚያብራሩ፥ የሚያስተምሩ እንጂ መጽሐፍ ቅዱስን የማይቃወሙ መሆናቸውን ያስተምራል።
- በተለይ ተአምር ምን ማለት እንደ ሆነና በብሉይ ኪዳንና በሐዲስ ኪዳን የነበረውንና ያለውን መልክ ያሳያል።
- ተአምርና መጽሐፍ ቅዱስ የማይለያዩ፥ የማይነጣጠሉ ጥንትና ፍጻሜ መሆናቸውን ከብሉያትና ከሐዲሳት ማስረጃ እያጣቀሰ የሚያስተምር ነው።
- አምላካችን በእመቤታችን አማካይነት ያደረገውን ተአምራት (ተአምረ ማርያም) ያስረዳል።
- ስለ እመቤታችን ቅድስና፥ ንጽሕና፥ ድንግልናና አማላጅነት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሚታመነውን ትምህርት ይገልጻል።

- ስለ እመቤታችን በብሉይ ኪዳን የነበሩትን አምሳላትና ቃላተ ትንቢት የትኞቹ እንደ ነበሩ፥ ፍጻሜያቸውም ምን እንደ ሆነ ያስረዳል።

## ፳፤ መልእክተ መንፈስ ቅዱስ። (፲፱፻፺፫ ዓ. ም.)



- የኢትዮጵያን ተስፋ የሚያበሥርና በልዩ ልዩ የታሪክ መጻሕፍት የተገለጠውን ዜና የሚያመለክት ሥዕል በመጽሐፉ የጀርባ ሽፋን ላይ ይገኛል።
- የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በተለይ ስለ መንፈስ ቅዱስ የምታምነውን እምነትና የምታስተምረውን ትምህርት ለመግለጽ የተዘጋጀ ነው።
- ስለ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፥ ስለ ልዩ ልዩ ሥራውም በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረትነት ለማስተማር የተዘጋጀ ነው።
- መንፈስ የሚለው ቃል ያለውን ትርጉምና መልኮቹን ይገልጻል።
- መንፈስ ቅዱስ ማን ነው? ወይም ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረትነት ሰፊና ጥልቅ መልስ ይሰጣል።
- ጌታችን የሰውን ልጅ ለመቤዠት ያደረገውን የአስታራቂነት ሥራ በዝርዝር ያቀርባል።
- ጌታ ወደ መስቀልና ወደ ዕርገት ያደረገውን ጉዞ በስፋት ያስረዳል።
- ክርስትና ምን ማለት እንደ ሆነ ያስረዳል።
- ማዕተብ ምን እንደ ሆነ ያስረዳል።
- ስለ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም እንዲሁም በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስላለው የቍርባን ሥርዓት ሰፊና ጥልቅ ገለጻ ያቀርባል።
- እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ እንዴት ለክርስቲያኖች ልዩ ልዩ ሀብቶችን እንደሚያድል ይገልጻል።
- መንፈስ ቅዱስ ክርስቲያኖችን እንዴት እንደሚጠራና ለመሥዋዕትነት እንደሚያዘጋጃቸው፥ ስምሪታቸውና ሰልፋቸውም እን ዴት እንደ ሆነ ያስረዳል።
- የክርስቶሳውያን መሣሪያዎች ምን ምን እንደሆኑና ጥቅማቸው ምን እንደ ሆነ ይዘረዝራል።
- የክርስትናን ሃይማኖት ጥልቀትና ርቀት፥ በውስጡም ያሉት ሀብቶች ምን ምን እንደ ሆኑ ይገልጻል።
- ስለ ፍቅርና ስለ አንድነት ሰፊ ትምህርት ይሰጣል።
- በማጠቃለያው በዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ ፪ና ፫ ያሉትን መምሪያዎች በመተርጐም መንፈስ ቅዱስ ለቤተ ክርስቲያን ኃላፊዎች የሰጠውን መምሪያ ቃል ያብራራል።

## ፱፤ ዜና ሕይወት ዘቅድስተ ቅዱሳን እመ አምላክ። (፲፱፻፺፱ ዓ. ም.)



- የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በተለይ ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የምታምነውን እምነት በመግለጽ በተለይ ባሉ በአንዳንድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካህናት እመቤታችንን አስመልክተው ለተጻፉ አንዳንድ ጽሑፎ ሆኖ የተዘጋጀ ነው።
- በሙሴ ድንኳንና በሰሎሞን ቤተ መቀደ የነበረችው ቅድስተ ቅዱሳን የእመቤታች እንደ ነበረች ያስረዳል።
- በእመቤታችን ጸሎት ውስጥ ያሉትን ቃ በማብራራት ስለ እመቤታችን ቅድስናና ያስተምራል።
- በመጽሐፈ ቀሌምንጦስና በመጽሐፈ ኩ ስለ እመቤታችን የተነገሩ ትንቢቶች ያብ
- በውዳሴ ማርያም፥ በቅዳሴ ማርያም፥ በ ያሬድ ድርሰቶችና በሌሎችም መጻሕፍ ሊቃውንት እመቤታችንን አስመልክቶ የ ትምህርት ያብራራል።
- እመቤታችን ከጥንተ አብሶ ነጻመሆኗንና ፍጥረት በአምላክ ቸርነት ታስባ፥ ተመ ጀምሮ እስከ ወላጆቿ ድረስ በንጹሕ ዘ በአባቶቿ ወገብ ተቋጥራ ከትውልድ ወ በ፷፮ቱ ትውልደ አበው እየተላለፈች መ ያስተምራል።
- እመቤታችን የተፈጠረችው ለሰው ዘር ሕይወት መሠረት ሆና መሆኑን ያስረዳ
- እመቤታችን በ፷፬ ዓመት ዕድሜዋ ጥር ለሰው ልጆች በተሠራው ሥርዐት ሞት መቀበሏን፥ ልጇ ነፍሷን ከሥጋዋ ለይቶ ሐዋርያት ሥጋዋን እንደ ሥርዐቱ በጌቴ መቃብር ማሳረፋቸውን፥ ግን መላእክት ከዚህ አንሥተው በገነት ከዕፀ ሕይወት ማሳረፋቸውን፤ በመጨረሻም ባረፈች በ ነሐሴ ፲፮ ቀን ጌታ በዕፀ ሕይወት ሥር መቃብር አስነስቶ ወደ መንግሥተ ሰማ እንዳሳረጋት ያስረዳል።

- እመቤታችን አምላክን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና መውለዷን፤ ከዚያም በኋላም የተመረጠችበትን ክብር አግኝታ፥ የአምላክ እናት ሆና ከፍጥረት ሁሉ በላይ በሆነ የክብር፥ የቅድስና፥ የልዕልና መዓረግ እስከ ዕለተ ምጽአት የምትመሰገን መሆኗን፥ በመንግሥተ ሰማያትም ምስጋና የማይቋረጥባት መሆኗን በቅዱሳት መጻሕፍት መሠረትነት ያስተምራል።

የመረጃ ምንጭ፡-https://aleqayalewtamiru.info/


ያልተፈታዉ
ዉግዘት

# ያልተፈታው ውግዘት!

## አለቃ አያሌው ታምሩ

## ጥያቄና መልስ፡፡

**ማስታወሻ፡- ይሄ ጽሑፍ ሲዘጋጅ ቃል በቃል አለቃ አያሌው የተናገሩትን ወደ ጽሑፍ ስቀይር የቃላት ግድፈት ይኖራልና ችግሩ የኔ ነው እንጅ የእሳቸው አይደለም፡፡ አስቀድሜ ይቅርታ እጠይቃለሁ፡፡**

የምንጠይቀወ ጥያቄዎች 20 ናቸው፡፡ ይዘናቸው የመጣነው ጥያቄዎች ፡፡ አባታችን እንዲያብራሩልን የምንፈልገው ፡-

1) ውግዘት ማለት ምን ማለት ነው?

2) አንድ ሠው ተወገዘ ሲባል ምንምን ሲሠራ ነው?

3)በጳትርያርኩና በርስዎ መካከል የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት ለምን አልተቻለም ?

4) ጳትርያርኩ ቢያጠፉ ወይም ሐይማኖት ቢያፍልሱ ራሳቸው በሠሩት ሥራ ይቀጣሉ እንጅ ካህናት አባቶች ተባባሪ ናቸው ተብለው ለምን ይወገዛሉ??

5) በቤተክርስቲያናችን ሁልጊዜ ሥለ ፍቅር እያስተማረች በርስወና በጳትርያርኩ መካከል ለምን ፍቅር ጠፍ??

6) ምእመኑን ለምን በቤተክርስቲያን ተገኝቶ እንዳያስቀድስ ታገደ??

7) ሠው በቤተክርስቲያን ተገኝቶ አስቀድስና ሥጋውን ደሙን ለመቀበል ለምን ተከለከለ??

8) የጌታ ሥጋወደሙ በካህናት አባቶች እጅ አትቀበሉ የጳትርያርኩ ተባባሪ ናቸው ለምን ተባለ??

9) የእናንተ የሐይማኖት አባቶች ፍቅር መጥፍት ለመናፍቃን በር አይከፍትም ወይ??

10) ዛሬ ዛሬ መናፍቃን በእነሡ በኩል ፍቅር ጠፍቷል እንደምታዮአቸው አንዱ አንዱን እያወገዘ ነው እያሉ ይሳለቁብናል በእርስዎ በኩል ይሄን እንዴት ያዩታል ??

11) ይህ ውግዘት የተላለፈው ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው ወይስ ለአዲስ አበባ ከተማ ብቻ??

12) ይህን ውግዘት የተቀበሉት ቤተክርስቲያን ስንት ናቸው? በውግዘቱስ አምነውበታል?? ይሄንም እንዲያብራሩልኝ??

13) የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሡሥ ክርስቶስ ቅዱስ
መስቀል በካህን አባቶች እጅ ለምን አትሳለሙ ተባለ??

14) ውግዘት ከተላለፈ ወዲህ ብዙ እናት አባቶች ፣ እህት ወንድሞች ከዚህ አለም በሞት የተለዩ አሉ እነዚህ ሠዎች እንደተወገዙ ነው የሞቱት ወይስ ተፈተው? ይሄን ቢያብራሩልኝ??

15) ይህ ውግዘት በግል ጋዜጣ ከማስተላለፈዎ በፊት ለምን በየቤተክርስቲያን ተገኝተው ለምእመኑ አላስተላፉም??

16) ይህ ውግዘት እስከመቼ ነው የሚቆየው? ለምን??

17) ይህ ውግዘት ከኢ.አ ውጭ የሠማ ሀገር አለ?? ካለ ውግዘቱን ተቀብለውታል ወይስ አልተቀበሉትም ??
18) ይሄን ውግዘት ብጹእ አባታችን ሠምተዋል ወይስ አልሠሙም??
19) ብጹእ አባታችን የግል ጋዜጣ አታንቡ ብለው አውግዘዋል የእርስዎ ውግዘት ደግሞ የተላለፈው በግል ጋዜጣ ነው ይሄ ሊጋጭ አይችልም ወይ??
20) አንዱ ያወገዘውን አንዱ ሊፈታው አይችልም ወይ?? ካልቻለ እስከመቼ በውግዘት ውስጥ ሊኖር ይችላል ? ወይስ ከቤተክርስቲያን እስከመቼ እርቆ ሳያስቀድሱ ይቆያሉ ? ጥያቄወቻችን እነዚህ ናቸው፡፡
…አባታችን እንደ እግዚአብሔር ቸርነት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ብዞዎቻችን የጠለቀ እውቀት የለንም እና ይቺን ከእርስዎ አባታችን ያለውን ሁኔታ ይጠቅማል ያሉትን ከ20ቹ ጥያቄ ውስጥ ይጠቅማል ያሉትን በእግዚአብሔር ስም እንዲያብራሩልን ነው፡፡

# <u>የአለቃ አያሌው ታምሩ መልስ</u>

## ጥያቄ፡- ውግዘት ማለት ምን ማለት ነው?

**መልስ(አለቃ አያሌው ታምሩ) ፡-** …በዚህ ጉዳይ ላይ ጥያቄዎች እየተነሡ በየጊዜው መልስ ተሰጥቶባቸዋል ፡፡ በቤተክርስቲያን ሥርአት ውስጥ አንድ ሠው ከቤተክርስቲያን ሕግ ውጭ ከሄደ ፤ እንኳን መሪ ሆኖ በምእመንነት ያለ ቢሆን ህጉን ከተላለፈ ይወገዛል፡፡

ሐይማኖት የተላለፈ ብቻ አይደለም ሥርአቱንም፡፡ እንኳን ይሄንን ያህል ጠቅላላውን የቤተክርስቲያን ሥርዓት ያፍለሠ ቀርቶ አንዱ ከአንዱ ጋር ተጣልቶ አልታረቅም ቢል ይወገዛል፡፡
ጌታችን አንድ ሠው ቢበድል መጀመሪያ ብቻህን፣ ሁለተኛ ሠው ጨምረህ ንገረው እምቢ ቢል ለቤተክርስቲያን ንገራት ቤተክርስቲንንም እምቢ ቢል እንደ አረመኔ ፣ እንደ ቀራጭ ይሁን ነው የሚለው ፡፡ ይሄ ውግዘት ነው፡ ፡ ከዚያ አያይዞ እውነት ልንገራችሁ በምድር ያሠራችሁት በሠማይ የታሠረ ይሆናል፡፡ በምድር የፈታችሁት በሠማይ የተፈታ ይሆናል፡፡ ነው የሚል፡፡ …የቤተክርስቲያን መሣሪያ ውግዘት ነው፡፡

## ጥያቄ ፡- አንድ ሠው ተወገዘ ሲባል ምንምን ሲሠራ ነው?

**መልስ(አለቃ አያሌው ታምሩ) ፡-** ምንም ምን ሲሰራ? ከቤተክርስቲያን ሕግ ውጭ የሆኑ ነገሮችን ሁሉ ካደረገ ይወገዛል፡፡ ትምህርት ሐይማኖት ካፋለሠ፣ ሥርዓት ከጣሠ ፣ ሕግ ካፈረሠ፣ ሐይማኖትን ካጠፋ በሠውም በእግዚአብሔር ላይ በደል ካደረሠና ተመክሮ ፣ ተነግሮ እምቢ ካለ ይወገዛል፡፡
ማውገዝ ማለት መለየት ማለት ነው፡፡ እንኳን በመንፈሳዊ ሕይወት በስጋዊ ሕይወት ድሮ አባቶች እንዲህ ያደርጉ ነበር፡- አንድ ሠው መክረውት እምቢ ካለ ከሡ ጋር ማንም ሠው የማህበራዊ ኑሮ ተሳትፎ እንዳያደርግ ፣ እሣት እንዳይጫጫር ፣ እቃ እንዳይዋዋስ፣ ቢታመም እንዳይጠየቅ ፣ ቢሞት እስከማይቀበር ድረስ ውሳኔ ይሰጡ ነበረ፡፡ ይሄ ውግዘት ማለት ነው፡፡ እና ቤተክርስቲያንም አንጻር መናፍቃን መናፍቃን እንደዚህማ ባይሆኑ ኒቅያ ጉባዔ አያስፈልግም ነበረ፣ እንዲህማ ባይሆን አያስፈልግም ነበረ፣ እንዲህማ ባይሆን የቁስጥንጥንያ ጉበዔ አያስፈልግም ነበረ፣ የኤፌሶን ጉባኤ አያስፈልግም ነበር፡፡ እነ አርዮስ፣ እነ መቅዶንደዮስ፣ እነ ንስጥሮስ …ተወግዘው አይለዩም ነበረ፡፡ እና ጳትርያርኩም ይሁኑ ግብረ አበሮቻቸው የኢትዮጵያን

ቤተክርስቲያን ሐይማኖት ጠብቀው ሊያስጠብቁ በሥጋው በደሙ የገቡትን መሃላ ስላፈረሡ ነው ያወገዝኩ በዚህ ምክንያት ነው፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ ለእብራውያን በፃፈው መልእክቱ ምን ይላል፡- በሙሴ ሕግ አንድ ሠው በሁለት በሦስት ምስክር ከተወቀሰ ይቀጣል ይላል፡፡ ግን ወልደ እግዚአብሔርን በደሙ ቃልኪዳን የተጋባና የተቀበለውን ቅድስና ያረከሠ፣ የጸጋውን መንፈስ ያዋረደ ቢኖር እንዴት አይቀጣም ? እና እነዚህ ጳትርያርኩም ሆኑ ፣ ጳጳሳቱ፣ ካህናቱ፣ በሥጋው በደሙ የገቡትን ፣ ለምእመናን፣ ለቤተክርስቲያን ፣ ለእግዚአብሔር የገቡትን ቃልኪዳን ስላፈረሡ አውግዣቸዋለሁ፡፡

አሁንም ቅዱስ ጳውሎስ በመጽሐፍ እኔ በሥጋ ከእናንተ ጋራ ባልኖር በመንፈሴ ከእናንተ ጋር ነኝ፡፡ እንዲህ ያለውን ሠው ዝምብላችሁ መመልከት አይገባችሁም፡፡ ስለዚህ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተሰብስባችሁ አውግዛችሁ ለዩት፡፡ ለሠይጣን ስጡት፡፡ ነው የሚል፡፡ አውግዛችሁ ለዩት ነው የሚል፡፡ እና እኔ ያወገዝኩት በመጽሐፍ ሥርዓት እንጅ ከመጽሐፍ ሥርዓት ውጭ አይደለም፡፡ ለዚህ ነው፡፡

## ጥያቄ፡- በጳትርያርኩና በእርስዎ መካከል የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት ለምን አልተቻለም ?

**መልስ(አለቃ አያሌው ታምሩ) ፡-** አይቻልምም! አልተቻለምም! አዎ እማይፈታበት ምክንያት እሳቸው ሲመለሡ ነው የሚፈታው፡፡ ወይም በመሃከላችን ዳኛ ሲኖር ነው የሚፈታ፡፡ በመሃከላችን ጉባኤ የሚጠራ ንጉሥ የለም ዛሬ፡፡ አሪዮስ ሲወገዝ የኒቅያን ጉባኤ የጠራው ቆስጠንጢኖስ የተባለው የምሥራቁ ንጉሠ ነገሥት ነው፡፡ መቅደኒዮስ ሲወገዝ ጉባኤውን የጠራው አርቃሊዮስ የተባለው የምስራቁ ንጉሰ ነገስት ነው፡፡ ንስጥሮስ ሲወገዝ ጉባኤውን የጠራው ቴወድዮስዮስ የተባለው የምሥራቁ ንጉሥ ነው፡፡ በኢትዮጵያም ነገስታቱ በነበሩበት ጊዜ ብዙ የተደጋገመ ጉባኤ ተደርጓል፡፡

✔በአፄ ፋሲል ጊዜ በካቶሊክ እና በኢትዮጵያውያን መሃከል ጉባዔ ተደርጎ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አፈጉባኤ እጨጌ በትረጊዮርጊስ ስለረቱ ካቶሊኮች መረታታቸውን አምነው ከሀገር እንደወጡ ተፈርዶባቸዋል፡፡

✔በአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት በቦሩ ሜዳ ጳጎችና ኦርቶዶክሳውያን እንዲከራከሩ ተደርጎ ጳጎች ስለተረቱ ተፈርዶባቸው ተቀጥተዋል ፡፡

ንጉሥ ቢኖር ይሄንን በዳኝነት ጉባዔ ጠርቶ ሊፈታው ይችል ነበረ፡፡ የኢትዮጵያ የቤተክርስቲያኒቱ የበላይ ጠባቂ ንጉሠ ነገሥት ነበረና፡፡ ዛሬ ንጉሠ ነገሥት የለም፡፡ ያለው መንግሥት በሐይማኖት አያገባኝም አለ፡፡ ይሄንን ምክንያት አድርገው የኢትየጵያን ቤተክርስቲያን ረገጡ፣ ክብሯን አሳደፉ፣ ሐይማኖቷን አፋለሱ ፣ ሥርአቷን ጣሱ ፣ ሕጓን አፈረሡ ፣ ለጳጳሳት አቤት አልኩ አብረው አበሩ የቤተክርስቲያንን ሕግ ሽረው አባ ጳውሎስ የሚመለኩበትን ሕግ አወጡ፣ ቤተክርስቲያን የጣወት ቤት ሆነች፣ እንደገና አለቆችና ካህናት የነሡ ተባባሪ ሆነው ጉዳዩን አስፈፀሙ ስማቸውን በፀሎት ሐይማኖት አትጥሩ ብየ ጠየኩ እምቢ አሉ፡፡

ስለዚህ ሁሉም ተባብረው በእግዚአብሔር ላይ ስላመጹ ፤ ምእመናን ይፈቱታል ብየ ነበር ምእመናንም እምቢ አሉ ፣ የሠበካ ጉባኤ አባሎችም ምእመናንም አብረው ተባብረው እምቢ አሉ፡፡ ምናለበት! ምናለበት! በሚል ቋንቋ ሐይማኖት አይቆምም ፡፡ ሁሉ ለራሡ ለሐይማኖት መቆም አለበት፡፡ እና ስለዚህ ሁሉም ተባብረው ስላመጹ አውግዣለሁ፡፡ ሁሉንም! እና የሚፈታውም የለም፡፡ የሚመለስ ከሌለ፡፡ ወይ እሳቸው ካልተመለሡ፡ ፡ ወይ ጳጳሳት ተመልሰው ሲኖዶሱን ካላቋቋሙ ፡፡ ሲኖዶስ ፈርሷል፡፡ ወይም ካህናት ደግሞ ተመልሰው ራሳቸውን ካለወቁ እና ከምእመናን ጋር አብረው ካልቆሙ ወይም ምእመናን እምብኝ ብለው እጃቸውን

ካልሰበሰቡና እንዳዘዝኳቸው ካላደረጉ መፍቻ የለኝም:: የሚከተለው መቅሰፍትና ፍርድ ነው:: የሚፈታ ይመጣል አይቀርም ይፈርዳል::

## ጥያቄ:- ጳትርያርኩ ቢያጠፉ ወይም ሐይማኖት ቢያፍልሱ ራሳቸው በሠሩት ሥራ ይቀጣሉ እንጅ ካህናት አባቶች ተባባሪ ናቸው ተብለው ለምን ይወገዛሉ??

**መልስ(አለቃ አያሌው ታምሩ) :-** ጳትርያርኩ ሲያጠፉ መሾም፣ መሻር ያለባቸው ቤተክርስቲያን ናት የምትሾማቸው የምትሽራቸው:: ጳትርያርኩ እኮ አምባገነን አይደሉም :: በጦር ጉልበት አይደለም የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን መንበር የወረሡት:: በልዩ ስልጣናቸውም አይደለም፣ መብትም የላቸውም፣ የወራሽነት መብት የላቸውም፣ ተመርጠው ነው የተሾሙ:: ሲሾሙ ደግሞ ምለው ነው:: የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን ስርዓት፣ እምነት ሊጠብቁ ነው:: ካልጠበቁ መሻር አለባቸው:: ካልሻሯቸው ይወቀሳሉ ፣ ይከሰሳሉ አብረዋቸው ይወገዛሉ::

## ጥያቄ:- በቤተክርስቲያናችን ሁልጊዜ ሥለ ፍቅር እያስተማረች በርስወና በጳትርያርኩ መካከል ለምን ፍቅር ጠፋ??

**መልስ(አለቃ አያሌው ታምሩ) :-** በእኔና በእሳቸው መካከል አይደለም ፍቅር የጠፋ :: በቤተክርስቲያን እና በእሳቸው(በጳትርያርኩ) መሀከል ነው:: እኔና እሳቸው አሁንም አልተጣላንም:: አልበደሉኝም አልበደልኳቸውም :: የግል ቂያሜም የለኝም:: ጸባችን ግን በቤተክርስቲያን ምክንያት ነው:: በእግዚአብሔር ላይ ደግሞ መታረቅ መተባበርም አይቻልም:: ሔሮድስና ጲላጦስም መበከረውት ነበር አልተደረገም :: በእግዚአብሔር ላይ መዋዋል ፣ በእግዚአብሔር ላይ ወዳጅነት መፍጠር አይቻልም:: ይሄማ ቢሆን ኖሮ ጌታ ለምንድነው በሠው ፊት ያመነብኝን እኔም በሠማይ በአባቴ ፊት አምንበታለሁ :: በሠው ፊት ያፈረብኝን እኔም በሠማይ አባቴ ፊት አፍርበታለሁ ለምን ይል ነበር::

ጌታ እኔ ሠይፍን እንጅ ሠላምን አላመጣሁም:: አባትን ከልጁ ፣ እናትን ከልጇ፣ ቤተሠብን ከቤተሠቡ ልለይ ነው የመጣሁ ያለው:: ታዲያ ይሄማ ቢኖር ኖሮ ምን ጸብ ነበረ በዓለም:: በዓለም ምን ሰማእታት ይገኙ ነበረ፣ ለምን ይሞቱ ነበረ:: ለምን ደማቸውን ያፈሱ ነበረ ፣ በእግዚአብሔር ላይ ውለታ መዋዋል ፣ ፍቅር መፍጠር አይቻልም::

## ጥያቄ:- ምእመኑን ለምን በቤተክርስቲያን ተገኝቶ እንዳያስቀድስ ታገደ??

**መልስ (አለቃ አያሌው ታምሩ) :-** ከቤተክርስቲያን ውጭ የሆነውን፣ ሐይማኖት የሚያፈልሰውን ፣ ስርአትን የሚያጣርሰውን አለቃ መከተል አይገባቸውም:: ምንድነው የሚል ጌታ:: በጎቼ ይላል ጌታ እስኪ የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 10ን እዮት ::

"በጎቼ ቃሌን ያውቃሉ እኔ በስማቸው እጠራቸዋሁ ይከተሉኛል:: ሌላውን ግን አያውቁትም ስለዚህ ቃሉንም አይሰሙትም አይከተሉትም:: ነው ያለ:: ከክርስቶስ ውጭ የሆነ እረኛ የለንም:: ከክርስቶስ ወሸጨሸ ጳትርያርክ የለንም:: ከክርስቶስ ውጭ የሆነ ካህን የለንም:: ከሌለ ምእመናን ሊሰሙት ፣ ሊቀበሉት፣ ሊከተሉት አይገባቸውም :: ማንን ነው የሚያስቀድሱት:: ማንንነው የሚቀድስ :: ዲያቢሎስ ይቀድሳል እንዴ:: አይቀድስም እኮ:: ይሄን አታውቁም :: ዲያቢሎስ እኮ አይቀድስም :: ቅዱሳን መላእክት ናቸው እንጅ የሚቀድሱ ዲያቢሎስ አይቀድሱም:: ቅዱስ ብሎም የእግዚአብሔርን ስም አይጠራም :: እና እነዚህ

እግዚአብሔርን የካዱ መቀደስ አይችሉም ፡፡ በእነሱ ድምጽም ማስቀደስ ደግሞ ማስቀደስ አይቻልም ፡፡ የቅዳሴ ተባባሪም መሆንም አይቻልም አንችልም ፡፡ ስለዚህ ምእመናን ከዚህ መታቀብ አለባቸው ፡፡ ምእመናን ናቸው ወንጀለኞች እንግዲያውስ፡-

1ኛ) ከበው እያጨበጨቡ

2ኛ) ሲወጡ ሲገቡ እጅ እየነሱ ቁጭ ብድግ እያሉ፡፡

3ኛ) ገንዘባቸውን እየሰበሰቡ እየሠጡ ለጣኦት አምልኮት ማጠናከሪያ ያደረጉት ቤተክርስቲያንን ያፈረሷት ምእመናን ናቸው፡፡ 800 መቶ ሽህ ብር የፈጀ መኪና የተገዛ በዛ በምእመናን ገንዘብ ምዝበራ ነው፡፡ አንድ ሚሊየን ተኩል የፈጀ ግብዣ የተጋበዘው ከቤተክርስቲያን በተፈፀመው ምዝበራ ነው፡፡ ምእመናን እጃቸውን ቢሰበስቡ ፣ የሠበካ ጉባኤ አደራውን ቢጠብቅ ኖሮ የገንዘብ ድሆች አብያተክርስቲያናት ራሳቸው እንደተናገሩት በገጠሪቱ ያለች ቤተክርስቲያን የምትረዳበት አታ በሙታን ሡሪ ቀሚስ ነው የሚቀደስ ብለው ራሳቸው በጉባኤ ተናግረዋል ይህን የሚሰሙ ምእመናን ናቸው ዝም የሚሉ የሚያጨበጭቡ፡፡ ደግሞስ በቤተክርስቲያን ላይ ደም እየፈሠሠ ደም አፍሳሽ ቅዱስ ነው እንዴ?? አይኑ አይቶ የለም ይሄ ህዝብ፡፡ የአዲስ አበባ ሕዝብ ሰምቶ የለም ፡፡ ከዚህ ነው ቅዳሴ የሚያገኘው እሱ??

## ጥያቄ፡- ሠው በቤተክርስቲያን ተገኝቶ አስቀድስና ሥጋውን ደሙን ለመቀበል ለምን ተከለከለ??

**መልስ (አለቃ አያሌው ታምሩ) ፡-** እኔ አልከለከልኩም ፡፡ የሚያቀብላችሁ ካገኛችሁ፡፡፡ ቅዳሴ የሚቀድስ ቄስ ካላችሁ አልከለክልም፡፡ የላችሁም ፡፡

## ጥያቄ፡- የጌታ ሥጋወደሙ በካህናት አባቶች እጅ አትቀበሉ የጳትርያርኩ ተባባሪ ናቸው ለምን ተባለ??

**መልስ (አለቃ አያሌው ታምሩ) ፡-** ስልጣነ ክህነት የላችሁም እኮ ነው የምላችሁ ፡፡ የጳትርያርኩ ተባባሪ የሆነ ሁሉ ሥልጣነ ክክህነት የለውም፡፡

**☞ምክንያቱም ፡-** ሚያዚያ 30 ቀን 1988ኢ.ም የወጣው ሲኖዶስ የፈረመበት ሕግ እስከዛሬ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የምትሰራባቸውን ደምቦች እና ህጎች አሻሽሎ የሚመራና ለሲኖዶሱ ተጠሪ የነበረውን ጳትርያርክ በመንፈስ ቅዱስ ፈንታ መሪ እንዲሆን ፣ አመራር ሰጭ እንዲሆን ፈቀደ፡፡ ቤተክርስቲያንና አባሎቿ የጳትርያርኩ ተጠሪ እንዲሆኑ አድርጓል፡፡ ከዚያን ጊዜ ወዲህ ጳጳሳትም፣ ቀሳውስትም፣ ራሳቸውን ሽረው የአባ ጳውሎሴ ፍጡራን ስለሆኑ አባ ጳውሎስ ደግሞ ስልጣነ ክህነት የመስጠት መብት ስሌላቸው አሁን ዛሬ የሚቀድሱ ፣ የሚያወድሱ ካህናት፣ ቄሶችም፣ ጳጳሶችም የሉንም፡፡ስለዚህ ካኗችሁም እኔ አልቃወምም ፡፡

## ጥያቄ፡- የእናንተ የሐይማኖት አባቶች ፍቅር መጥፋት ለመናፍቃን በር አይከፍትም ወይ??

**መልስ (አለቃ አያሌው ታምሩ) ፡-** ፍቅር አልጠፋም እኮ ነው የምላችሁ፡፡ ፍቅር የሚባል ነገር የለም፤ በእግዚአብሔር ፍቅር የለም፡፡ በእግዚአብሔር ቀልድ የለም፡፡ በእግዚአብሔር አድማ አለ እንዴ ፡፡ አድማ እኮ ነው፡፡ ምን አጣላን እኛ ምንም ጠብ የለንም፡፡

## ጥያቄ:- ይህ ውግዘት የተላለፈው ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው ወይስ ለአዲስ አበባ ከተማ ብቻ??

**መልስ (አለቃ አያሌው ታምሩ) :-** ለሞላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ አይደለም በሞላ አለም ላሉ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ነው፡፡ ክብራቸው ለተደፈረው ለኢትዮጵያውያን ሁሉ፡፡ በኢትዮጵያ ብቻ አይደለም በሞላ አለም ላሉ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ነው፡፡

## ጥያቄ:- ውግዘት ከተላለፈ ወዲህ ብዙ እናት አባቶች ፣ እህት ወንድሞች ከዚህ አለም በሞት የተለዩ አሉ እነዚህ ሠዎች እንደተወገዙ ነው የሞቱት ወይስ ተፈተው? ይሄን ቢያብራሩልኝ??

**መልስ (አለቃ አያሌው ታምሩ) :-** ትእዛዙን አክብረው ከሆኑ ተፈተዋል ፡፡ ትእዛዙን ካላከበሩ ግን እስረኞች ናቸው፡፡

## ጥያቄ:- ይህ ውግዘት በግል ጋዜጣ ከማስተላለፈዎ በፊት ለምን በየቤተክርስቲያን ተገኝተው ለምእመኑ አላስተላፉም??

**መልስ (አለቃ አያሌው ታምሩ) :-** በእኔ ሥልጣንማ ታገሸ‍ኛለሁ፡፡ ስለታገድኩ እኮ ነው በግል ጋዜጣ ለመተንፈስ የበቃሁት እንጅ ይህንማ እድል ካገኘሁ ለምን በጋዜጣ እናገራለሁ፡፡ መድረክ ላይ ነው የምናገረው፡፡

ጥር 24 ቀን 1988 ኢ.ም በተክለሃይማኖት ቤተክርስቲያን መጽሐፍ መበላሸቱን ፣ ሰውየው(ፓትርያርኩ) ከመንገድ ወጭ መሄዳቸውን በሚገባ ተናግሬያለሁ ፡፡ ከዚያ ቀደም ብሎም አንድ አመት ሙሉ ሲኖዶሱ እንዲያየው በደብዳቤ ፣ በቃልም ነግሬያለሁ፡፡ አምቢ ስላሉ ነው ፡፡ እንደ ጌታ ቃል ነው አንጅ ያወገዝኩኝ ከዛውጭ አልሄድኩም እኔ፡፡ መጀመሪያ ጠይቅ ፣ ሁለተኛ ሰዎችን ይዘህ ንገር፣ እምቢ ሲሉህ ለቤተክርስቲያን ንገር ከዚያ በኃላ አውግዝ ነው ያለኝ፡፡ እንዳዘዘኝ ነው ያደረኩ፡፡

## ጥያቄ:- ይህ ውግዘት እስከመቼ ነው የሚቆየው? ለምን??

**መልስ (አለቃ አያሌው ታምሩ) :-** እስከተፈታ ድረሥ፡፡ ነገሩ ውሳኔ እስካገኘ ድረስ ካላገኘ ያው ነው፡፡ አሪዮስ ተፈቷሎ? መቅድኒዮስ ተፈቷል? ንስጥሮስ ተፈቷል? አሁንም በዚህ አለም ብቻ አይደለም፤ በወዲያኛውም አለም ውጉዛን እሱራን ናቸው፡፡ በሠልጣነ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ እሱራን ውጉዛን ይሁኑ፡፡

## ጥያቄ:- ይሄን ውግዘት ብጹእ አባታችን ሠምተዋል ወይስ አልሠሙም??

**መልስ (አለቃ አያሌው ታምሩ) :-** ይስሙ አይስሙ ምንም የሚያጠያይቀኝ ነገር አይደለም፡፡

**ጥያቄ፡- ብጹእ አባታችን የግል ጋዜጣ አታንቡ ብለው አውግዘዋል የእርስዎ ውግዘት ደግሞ የተላለፈው በግል ጋዜጣ ነው ይሄ ሊጋጭ አይችልም ወይ??**

**መልስ (አለቃ አያሌው ታምሩ) ፡-** ምን ያጋጨዋል! እሳቸውም እንዳመጹ ናቸው እኔም ከእግዚአብሔር ጋር እንደቆምኩ ነኝ፡፡ ምን ይጋጫል፡፡ መጀመሪያ ጠበያቸው የማይሆን ሆነው ወተዋል ከወጡ በኋላ የሚያደርጉት ነገር የላቸውም፡፡ እውነት ከሆነ! እውነት ከሆነ! ውግዘቱን ለማገድ ከመሞከር ወይም በግል ጋዜጣ አታንብቡ ብሎ ከማስገደድ ይልቅ፣ የሊቃውንት ጉባኤን ከማፍረስ፣ ሲኖዶሱን ከማፍረስ ይልቅ የሊቃውንት ጉባኤ እንዳለ ፣ ሲኖዶሱም እንዳለ ፣ ኤኔን አቅርበው መጠየቅ ነበረባቸው፡፡ እውነቱ ይሄ ነው፡፡

**ጥያቄ፡- ውግዘቱ ከተላለፈ ወዲህ ብዙ እናቶች አባቶች እህቶች ወኽድሞች ከዚህ ዓለም የተለዩ እነዚህ ሠወች እንደተወገዙ ነው የሞቱት ወይስ እንደተፈቱ ነው የሚለው ጥያቄ ተመልሷል ግን ቢብራራልንና እንደው ትምህርት ብናገኝበት???**

**መልስ (አለቃ አያሌው ታምሩ) ፡-** እኔኮ ምርጫ ነው የሰጠሁኝ፡፡ አያችሁ ምእመናን ይህንን ስናገር የምትሰጡት ገንዘብ የበደል መፈፀሚያ ሆኗል፡፡ የእናንተም ደግሞ አለመቆጣትም ሰዎቹን ወደ አመፅ ሰዷቸዋል፣ ጋብዟቸዋል፡፡ እና እናንተ እጃችሁን ሰብስቡ ገንዘባችሁን በቤታችሁ ባንክ አሰናድታችሁ አስቀምጡ፡፡ ከዚያ ጋር ደግሞ ቄሱም፣ ፓፓሱም ፣ ሁሉም ራሳቸውን የሻሩ ስለሆነ ከነሱ የምታገኙት ነገር የለምና ተጠንቀቁ ብያለሁ ፡፡ ይሄን ከተናገርኩ በኋላ እምቢ ብለው አልፈው ተርፈው ምናለብን እንዴ እኛ ለምን መስቀል ከመሣለም እንከላከላለን ፤ ቄሱ ለምን መስቀል አያሳልመንም እያሉ የሄዱ ብዙዎች ናቸው፡፡ አነዚህ የራሳቸው አመፀኞች ናቸው እንደታሠሩ ናቸው አሁንም፡፡ አይ ከዚህ ተጸጽተው ፣ አክብረው ፣ የሞቱ ግን ፍቱሀን ናቸው ዋጋቸውም ይቆያቸዋል፡፡

*መስቀል እኮ ብቻውን መባረኪያ አይሆንም፡፡ ታውቃላችሁ፡ ፡* ለምንድነው ታዲያ አንጠረኛው አይባርክበትም ፣ ነጋዴው ለምን አይባርክበትም ለምንድነው?? መስቀሉ እኩል ነው የሠራው አንጥረኛው ነው፡፡ የሸጠውም ነጋዴው ነው፡፡ ለምንድነው ቄሡ ብቻ ስለያዘው መባረኪያ የሚሆን ለምንድነው?? የመባረክ ስልጣን ያለው ቄሡ ስለሆነ ነው፡፡ እና ያ ቄሥ ደግሞ እግዚአብሔርን ከካደ በረከት የለውም ማለት ነው፡፡ እናንተ ካህናት ይላል በትንቢተ ሚልኪያስ ፡- ስሜን አርክሳችኋል እና እኔም በረከቴን ከእናንተ ወስጃለሁ ፡፡ ነው የሚል፡፡

**ጥያቄ፡- እሸ አባታችን! ውግዘት ከባድ እስከ መሆኑ መጠን አጥፊው ነው የሚወገዘዉ ማለትም ሐይማኖት ወይም የከህደት መጽሐፍ የፃፉ ሰዎች ናቸው መወገዝ ያለባቸው፡ ፡ ካህናቶችን ለምሳሌ አምነውበት ቤተሰቦቻችን ቤተሰቦቻችን? ከስራ እንባረራለን ? ሁኔታውን አምነውበት በዚህ በውግዘቱ ላይ ያለውን እንቅስቃሴ ያደርጋሉ ማለትም ካህናት የሚፈፅሙትን አገልግሎታቸውን ሳያቋርጡ እስካሁን ይፈፅማሉ ስለዚህ ካህናትን የሚነካበት ምክንያቱ ምንድነው???**

**መልስ (አለቃ አያሌው ታምሩ) ፡-** ካህናት ከቤተክህነት የሚያገኙት ገንዘብ የለም፡፡ ለልብሳችን፣ ለምግባችን ብለው ሊያመካኙ አይችሉም፡፡ **ደሞ ከዚህ ነጻ ካልወጡ ካህናት አይደሉም፡፡ ጌታ ራሱ አንድ ባሪያ ለሁለት ጌታ መገዛት እንደማይችል እናንተም ለእግዚአብሔር እና ለገንዘብ ልትገዙ አትችልም ፡፡ ነው ያለ፡፡** ይህንንም ሲያብራራ ነገሩን በዚህ ብቻ ሳይወስን፡፡ ምክንያቶቹ ገንዘበሽ ፍለጋ የሚሠዱን ምክንያቶች ልብስና ፣ ምግብ ስለሆኑ ምን እንበላለን ፣ ምን እንለብሳለን ብላችሁ አታመካኙ ወፎችን፣ አበቦችን እዩ ብሎ በገንዘብ ምክንያት ከሱ እንዳንለይ አዝዟል፡፡ ከዚህ በላይ ካልሄድን እንኳን ካህንነቱ ምእመንነቱም አይሆን፡፡ እንኳን ካህንነቱ ምእመንነቱም አይሆን፡፡ ካህን ሆነንም ከዚህ በላይ መሄድ አለብን፡፡ እና የሚደርስብንን ሁሉ ተቀብለን ለክርስቶስ መመስከር በጎቹን መጠበቅ አለብን፡፡

አንድ በጎቹን እንዲጠብቅ የተሠየመ እረኛ አቅሙ እስከፈቀደ ድረስ ከአራዊት ጋር ተከላክሎ በጎቹን ማዳን አለበት፡ ፡ እሱ መሞት አለበት እንጅ እነሱን አሳልፎ መሥጠት የለበትም፡፡ እንኳን ለጥቅም ብሎ አሰልፎ ሊሰጣችሁ ስለ ህይወቱም ህይወቱን አሳልፎ እንዲ ሰጥላቸው ነው የታዘዘው፡፡

ጌታ ራሱ ስለበጎቼ ራሴን እለውጣለሁ ፡፡ ይህንንም ለሐዋርያቱ ፣ ለካህናቱ ፣ ሲያስተላልፍ ራሱን ለወንድሙ ለውጥ አድርጎ ከመስጠት የበለጠ ፍቅር ምን አለ ብሎ እንድንቀበለው ነው ያዘዘን ፡፡ የቤተክርስቲያኒቱ ሠወች የሆነ ሁሉ፣ አስተማሪወች የሆነ ሁሉ፣ ሰለ ምእመናን ህይወታችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ተጠይቀናል፡፡ እንኳን በልብስ በምግብ ራበን ፣ ጠማነ፣ ልናመካኝ ድቅርና፡፡ሌላውደግሞ አሁን በቤተክርስቲያን በኩል ያለው ይህን ምክንያት አይቀበለውም ፡፡ እግዚአብሔር ዋጋቸውን ይክፈላቸውና ብጹእ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ኮምኒዝም ወደ ኢትዮጵያ መግባቱን ፣ በር መክፈቱን ፣ ስር መስደዱን ሲያዩ በርስትና ጉልት ላይ፣ በመሬት ላይ የነበረው የቤተክርስቲያን ስርአት ወደፊት እንዳማይቀጥል ስላወቁ ለቤተክርስቲያኒቱ ቀሪ ሀብት ምእመናን ናቸው ብለው የሰበካ ጉባኤ ያቋቋሙ፣ ቤተክርስቲያን በምእመናን ገንዘብ እንድትተዳደር ነው፡፡ ያነንም ደግሞ ስልጣኑን ለቤተክህነት ሳይሰጡ በሎቶ ከተወሰነ ገቢ ለቤተክህነቱ መስሪያቤቶች ከወረዳ ወደ አውራጃ፣ ከአውራጃ ወደ ክፍለሀገር ወደ መንበረ ፓትርያርክ ፈሰስ እንዲደረግ ሲያደርጉ የቀረው ሀብት ግን በአጥቢያይቱ ምእመናን እና በካህናቱ እጅ እንዲጠበቅና ለዚያች ቤተክርስቲያን መረጃ፣ መቋቋሚያ ፣ መተዳደሪያ ፣ እንዲሆን ነው ቃለ ዓዋዲ ያወጡት፡፡

ለዚህም ደግሞ የሠበካ ጉባኤ ሲባል ምእመናን ብቻቸውን እንዳይሆን ካህናት ከምእመናን ፣ ምእመናን ከካህናት ተቀላቅለው በአስተዳዳሪው ተቀዳሚ ሊቀመንበርነት.... ሁላችሁም ታውቁታላችሁ፣ ካህናትም ያውቁታል፡፡ እና ይሄን እያወቁ እምበላው፣ የምለብሰው ፣ የለኝም እታገዳለሁ፣ እባረራለሁ ብለው ያደረጉት አድማግና ሴራ በእግዚአብሔር ላይ ትልቅ አመፅ ነው የፈፀሙት ካህናቱ፡፡ እና ራሳቸውን ደግሞ በገዛ እጃቸው ሽረዋል፡፡ የአባ ፓውሎስ ካህናት ነን ካሉ የጣአት ካህናት ናቸው ማለት ነው፡፡ እና ይሄ ስለሆነ ነውያወገዝኩአቸው፡፡ ስማቸውን በፀሎት ሐይማኖት አትጥሩ እነሡ ከምእመናን ጋር ቢቆሙ ኖሮ እስካሁን ፀቡ በርዶ ነበረ፡፡ ፍርድም ተገኝቶ ነበረ፡፡ አባ ጳውሎስም ይፀፀቱ ንስሃ ይገቡ ነበር፡፡ እንደገና ቤተመንግስት አይገዙም ነበረ፣ የጥይት መከላከያ መኪናም አያደራጁም ነበረ፡፡ እነሡ (ካህናት) ቢቀኑ ኖሮ ፡፡ እነሡ ናቸው ቤተክርስቲያንን ያፈረሷት፡፡

**ጥያቄ፡- አቡነ ፓውሎስ መወገዝ ያለባቸው ዛሬ ሳይሆን?? ያኔ ገና ሥልጣን ላይ ሳይወጡ ማለትም በፍትሐ ነገስት ላይ እንደሚናገረው "አንድ ፓትርያርክ በሕይወተ ሥጋ እያለ ሌላ ፓትርያርክ መሾም እንደሌለ"...አለ፡፡ ይሄ ሳለ እሳቸው በህይወትና እሳቸው ሥልጣን ላይ የወጡት፡፡ ስለዚህ ያኔ ነበር መወገዝ የሚገባቸው ዛሬ አልነበረም ምንም ሐይማኖት ቢያፋልሱም ?? እና ከዚያ ጋር አያይዘው ከሥራ መባረረወ ጋር የተያያዘ ነው?? እነ አቡነ ፓውሎስ መወገዝ የነበረባቸው ዛሬ ሳይሆን ያኔ ገና ሥልጣን ላይ እያሉ እርስዎ እዛ ቦታ ላይ በነበሩበት ሠአት ያኔ ነበር ማውገዝ የነበረባቸው?? የሚል የሚሰነዘር ቃል አለ?? ይሄ በእርስዎ በኩል እንዴት ይታያል???**

**መልስ (አለቃ አያሌው ታምሩ) ፡-** አባ ፓውሎስ ከፓትርያርክ ላይ አልገቡም ፡፡ ጥፋታችሁም አንዱ ይሄ ነው፡፡ ሁሉ የሚያልጎመጉመው ይሄን ነው፡፡ አመፅ ነው ይሄ፡፡አባ ፓውሎስ ከፓትሪያርክ ላይ አልተሾሙም፡ ፡ የማንንም ሹመት አልቀሙም፡፡ ባዶ ቤት አገኙ ገቡ ፡፡ እውነቱ ይሄ ነው፡፡ የቀደሙት ፓትርያርክ ነሐሴ 29 ቀን 1983 ኢ.ም በሲኖዶሱ ውሣኔ መንበራቸውን ትተው ሄዱ ከአስር ወር በኋላ አባ ፓውሎስ ተሾሙ፡፡ ይሄ በሠው ላይ ተሹመዋል ያሰኛል እንዴ፡፡ ለምንድነው በማይገባስ የምንከሳቸው ለምንድነው፡፡ **በሚገባው ባጠፉት ጥፋት ነው መከሠሥ ያለባቸው በዚህ አጥፊውም ተጠያቂውም ሲኖዶሱ እና ራሳቸው ሸሽተው የሄዱት ፓትርያርኩ ናቸው፡፡ በጎቻቸውን ትተው የሄዱት ፓትርያርኩ ናቸው የሚጠየቁት፡፡ ለምን በጎቻቸውን ጥለው ይሄዳሉ ፤ ስለበጎቻቸው ለምን ራሳቸውን አይለውጡም፡፡** መይ ጠየቁንና ፡፡ እዛ ብኖር እኔን ጠይቀውኛል እንዴ? አልጠየቁኝም ፡፡ እኔ ግን ተቃውሜላቸዋለሁ፣ ተከራክሬላቸዋለሁ፡፡ መውረድ አይገባቸውም ብየ ድምፄን አሰምቻለሁ፡፡ አላፍርም ቅር አይለኝም፡፡ በዚህ ቅር የሚለኝ ነገር አይደለሁም ፡፡ በጊዜው ተናግሬአለሁ ፡፡ ነገር ግን እሳቸውም ሾልከው ሄዱ ፡፡ሲኖዶሳቸውም አብሮ አቅፎ አጅቦ ሸኞቸው ፡፡ እውነቱ ይሄ ነው፡፡ እስከ የካቲተ አባ ዜና ማርቆስ ነበሩ፡፡ በእንደራሴነት የሚጠብቁ፡፡ ከየካቲት በኋላ ደግሞ አበሠ ኤፍሬም ተተኩ አባ ዜና ማርቆስም እንደሸኙ እሳቸውም ወተው ሄዱ፡፡ አባ ያእቆብ እንደገቡ የራሳቸውን የኤርትራን ነፃነት አደላደሉ፡፡ እዚህ ያለውን ለሚገባው ሰጥተው ሄዱ፡፡ ለመሠላቸው፡፡ እነሠ አባ ጳውሎስ የገቡ ክፍት ቤት እንጅ በሠው ላይ አልተሾሙም፡፡ ያም ቢሆን እኔ ከምርጫ ውስጥ አልገባሁም ፡፡ እምቢ ብየ ቀርቻለሁ፡፡

**ጥያቄ፡- እግዚአብሔር ለሰለሞን በሰጠው ቃልኪዳን በመጽሐፍ ነገሥት ተጽፎ እንደምናየው የእግዚአብሔር ሐይሎች ዘወትር በቤተክርስቲያን ላይ እንደሆኑ ይናገራል፡፡ እና የአቡነ ጳውሎስ ስም መጠራቱ የሳቸው ስም ሳይሆን መንበሩ የቅዱስ ማርቆስ መንበር ስለሚጠራ በዛ ቦታ ላይ የሚደረገው ማንኛውም ስርአት ቅዱስ ቁርባኑም ሌሎችም ስርአቶች ሁሉ የማያርግበትን ፣ ሌላ የማይቀበለበት ምክንያት ምን ላይ ነው???**

**መልስ (አለቃ አያሌው ታምሩ) ፡-** ካዱ! ካዱት! ሚስቱን የፈታ ሠው ባል ይባላል እንዴ?? ሚስቱን የፈተሠ ሠው ባል አይባልም፡፡ ፈቷል፡፡ በቃ፡፡ ሚስቱ የእሱ አይደለችም፡፡ መልሶ ማግባትም አይችልም ፡፡ እና መንበረ ማርቆስን ክደዋል፡፡ መንበረ ሊዮን በጌታ አድረዋል ፡፡ ከሮማ ፖፓ ቡራኬ ተቀብለዋል ፡፡ የተቀበሉትም በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የተቀበሉትን ቡራኬና በኢትየጵያ ቤተክርስቲያን የተቀበሉትን መሃላ አፍርሰዋል ፡ ፡ አቤቱታየ እኮ ይሄ ነበረ፡፡ የነገርኳችሁ ይሄ ነው፡፡ ቃልኪዳናቸውን አፍርሰዋል፡፡ ክርስቶስን ክደዋል፡፡

በመንበረ ማርቆስ ላይ አይደለም አሁን ያሉት፡፡ የሠሩት መንበረ ሊዮን ነው፡፡ ያለውም በመንግስተ ሊዮን ነው፡፡ በሐይማኖተ ሊዮን ነው ፡ ስለዚህ ውጉዝ ናቸው፡፡

**ጥያቄ ፡- አባታችን ይሄ ውግዘት አሁን ተላልፏል አይደለ፡፡ በዚህ ውግዘት መሀከል አንድ ሠው በሥጋ እያለ ብዙ ነገሮችን ያደርጋል ከዚህሽ በኋላ ደግሞ ውግዘቱን ካስተላለፉ በኋላ ወደ ማይቀረው ሞት የሚኬድበት መንገድ ደግሞ አለ፡፡ እግዚአብሔር አምላክ ከፉን ነገር ያርቀውና ይሄ ውግዘት እንደተላለፈ ወይ በእርስዎ ወይ በእሳቸው መካከል መለየት ቢኖር ውግዘቱ እንደታሠረ ነው ወይስ እንደተፈታ???**

**መልስ (አለቃ አያሌው ታምሩ) ፡-** እንደ ታሠረ ነው፡፡ ማንም አይፈታውም፡፡

**ጥያቄ፡- ማን ይፈታዋል? እስከመቼ ድረስ??**

**መልስ (አለቃ አያሌው ታምሩ) ፡-** ቤተክርስቲያን እስከተመለሠች ድረስ፡፡ ቤተክርስቲያኒቱ ተመልሳ ሲኖዶሱ የቤተክከ፣ የክርስቶስ ተጠሪ ካልሆነ ምንጊዜም አይፈታም ፡፡ የክርስቶስ የሆኑ ፓፓሳት ከሌሉ ካልተሾሙ አሁን ያሉትም እንዴውም አይሆኑም ፡፡ አሁን ያሉትም አይሆኑም ፡፡ ይሄን እወቁ፡፡ ለዚህ መድሃኒቱ ምእመናን ተሰባስበው ካህናቱንም አስገድደው እሽ ያሏቸውን በውድ እምቢ ያሏቸውን በግድ ለይተው አስወጥተው አሁንም አባ ጳውሎስን አውግዘው ራሳቸውን አስተካክለው ካልቆሙ በስተቀር ፡፡ ቤተክርስቲያን አሁንም የለችም፡፡ እንዲህ በመላ ደግሞ አትመለስም ፡፡ ይሄን እወቁ፡ ፡ በመላም አትመለስም ፡ ፡ አባ ጳውሎስ ድንገት ቢሞቱ ፤ እኔም ድንገት ብሞት ያሉት ጳጳሳት ፣ ያሉት ቀሳውስት ተተክተው የሚሠሩት ሥራ ምንም ዋጋ የለውም፡፡ ፍርድ ሳይፈረድ አጥፊውና አልሚው ሳይለይ በምንም አይነት የሚደረገው ነገር ሁሉ ዋጋ የለውም፡፡ ለዚህ ነው የጮህኩት አመት ሙሉ የሠው ያለህ የምል በዚህ መክንያት ነው፡፡ ነገሩ ጥብቅ ስለሆነ ከባድ ስለሆነ፡፡ ሠውማኮ ቢኖረን ኖሮኮ የተለየ ሠው ሁለት ሦስት ሰው እንኳን ቢሆን ይሆን ነበር፡፡

ሌላ ቀርቶ አባ ጳውሎስ ቢሞቱ አንድ ጳጳስ ለመሾም እነዚህ በዚያ ህግ ላይ የፈረሙት ሁሉ የመሾም መብት ስለሌላቸው፡፡ ያልፈረመ ጳጳስ ሦስት ከሌለ ቤተክርስቲያኒቱ እንደገና ጳትርያርክ መሾም አትችልም፡፡ ይሄን እወቁ፡፡ አትችልም፡፡ እንደገና ወደ ግብጽ መሄድ ነው፡፡

**ጥያቄ፡- አባታችን ! የርስወን ውግዘት የሚቀበል ሠው ይኖራል ማለትም አባት፡፡ የአቡነ ጳውሎስን የማይቀበል ነገር ግን እግዚአብሔር አያምጣውና እርስወ ቢለዩን እንኳን ያሠው ፈቶ በቦታው ላይ እውነተኛውን መተካት አይችልም???**

**መልስ (አለቃ አያሌው ታምሩ) ፡-** አይችልም!! ቤተክርስቲያን ካልተመለሰች አይቻልም እኮ ነው የምላችሁ ፡፡

## ጥያቄ:- ሥርአቱ ተስተካክሎ ማለት ነው??

**መልስ (አለቃ አያሌው ታምሩ) :-** ስርአቱ ከተስተካከለማ ሥርአቱ ያስተካክለዋል፡፡ እኔም እኮ ስርአቱ ይስተካከል ነው እንጅ ሌላ እኮ ውግዘት የለኝም እኔ፡፡ የነሰኮ አቤቱታነሦ ጩኸት ሥርአቱ ወደነበረበት ይመለስ ነው፡፡ ከተመለሦ ተመልሷል፡፡ ውግዘት የለም፡፡ ካልተመለሦ ግን ማንም ማንም ሊፈታው አይችልም፡፡ ክር አይደለ፣ ገመድ አይደል፣ ሽቦ አይደል ቀልድ ነው እንዴ፡፡፡

## ጥያቄ:- እሽ አባታችን! የኔ ጥያቄ ደግሞ ካህናቱና ጳጳሳቱ የተወገዙበትን ምክንያት ሰምተናል፡፡ ራሳቸው ፓትርያርኩ የተወገዙበት ምክንያት ምንድነው??? ከዚህ ጋር የሚያያዝ አንድ ጥያቄ ስላለኝ ነው የጠየኩወት፡፡ አንድ ጊዜ አቡነ ተክለሃይማኖት እሳቸውም ወደ ሮም ሄደው ከፓፓው ጋር ተገናኝተው አንዳንድ ውሰኔወችን ያሳለፉ ይመስለኛል???

**መልስ (አለቃ አያሌው ታምሩ) :-** አላሳለፉም!!! አላደረጉም !! አባ ተክለሃይማኖት(ሦስተኛው ጳትርያርክ) ድሄን አላደረጉም፡፡ በመንገድ ሃላፊነት አንድ ሰው በመንገዱ ለመሳሌ ፓፓው የሮማ ፓፓ አዲስአበባ ቢደርሥ እዚህ አጋጣሚ አባ ጳውሎስን ቢያገኙ፤ አባ ጳውሎስ በመንገድ መተላለፊያ ሮም ቢሄዱ ሮም ላይ ፓፓውን ቢያገኙ ይሄ አይደለም ተገናኙ የሚባለው፡፡

አባ ጳውሎስ በኦፊሴል በሚገባ በክብር ተጠርተው ሄደው በጸሎተ ቅዳሴ ፣ በጸሎተ ማእድ ተሳትፈዋል ፡፡ አስር ሺህ በሚገኙበት ምእመናንም ራሥሳቸውን አዋርደው እንደ ተራ ምእመን የካቶሊክ ፓፓውን ቡራኬ ተቀብለዋል ፡፡ አባ ተክለሃይማኖት እንዲህ አላደረጉም ፡፡

## ጥያቄ:- አባታችን! ሐዋርያው ጳውሎስ ያገኘው ሥልጣን ከእግዚአብሔር ነው፡፡ ካህናት አባቶቻችን ጳጳሳትም ያገኙት ሥልጣን ከእግዚአብሔር ይመስለኛል?? ስለዚህ ካህናት አባቶች የተሠጣቸውን ከእግዚአብሔር ያገኙትን ሥልጣን ማንኛውም ሰው የመግፈፍ ስልጣን አለው?? ሥልጣናቸውን የመቀማት ስልጣን አለው??

**መልስ (አለቃ አያሌው ታምሩ) :-** ማንኛውም ሠው ስትሉ ምን ማለት ነው፡፡ እኔምኮ የእግዚአብሔር ሰው ነኝ፡፡ አታውቁም ይህን፡፡ ሥልጣናቸውን ከእግዚአብሔር ቢያገኙት እኔም ከእግዚአብሔር የተገኘሁ ነኝ የሻርኳቸው፡፡ ያወገዝኳቸው እኔም ከእግዚአብሔር የተሾምኩ ነኝ፡፡ ይሁዳ ከእግዚአብሔር አልተሾመም ነበረ እንዴ?? አልካደም ? አልተሻረም? ይሁዳን እግዚአብሔር አልጠራውም ወይ ከሐዋርያት ጋራ፡፡ አልተሻረም? ማን ተሾመ ማቲያስ፡፡ ማነው የሾመው ? ሐዋርያት ፡፡ ሥርአቱ አንድ ነው፡፡ ጌታ በጠራቸው ሐዋርያት ቢሾሙ ሥርአቱ አንድ ነው፡፡ እና አባ ጳውሎስን እግዚአብሔር ሾማቸው? እግዚአብሔር አልሾማቸውም ቤተክርስቲያን ናት የሾመቻቸው፡፡ ካዱ ሻርናቸው፡፡ ካዱ አወገዝናቸው፡፡ ራሳቸውን በራሳቸው ሻሩ የሚለው ደግሞ የካዳቸው የለም፣ የሻራቸው የለም፡፡

በሐዋርያት ሥራ ምእራፍ 1 ከቁጥር 14 ጀምራችሁ ብታነቡ **ይሁዳ ትቷት የሄዳትን ይህቺን መልእክት የሚቀበለንን ሠው ምረጥልን ብለው ነው የጸለዩ፡፡ እንጅ የሻርነውን አላሉም፡፡ አባ ጳውሎስም ራሳቸው ናቸው ትተውት የሄዱት ሹመቱን፡፡ ሮም ሲገቡ ነው የተውት፡፡ የሮምን ፖፖ ቤት ለመግባት መድረኩን ሲረግጡ ነው የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን የካዱ፡፡**

**ጥያቄ:-** **በኒቅያ፣ በቆስጥንጥንያ፣ በኤፌሶን የተደረገውን ውግዘት በተመለከተ ባልወጣ ቀደምትም በተወገዙት ማለት መናፍቃኖች በተወገዙበት መልክ ሲወገዙ ማንንም ኖረም አልኖረም አቡነ ጳውሎስ ኖሩ እርስወም አልኖሩ፤ ተፈታም አልተፈታም በዛ አይነት ይወርዳል፡፡ ውግዘቱ፡፡ ሐይማኖቷ በትክክል ደረጃዋን እስከምትይዝ ድረሥ ፡ ፡ እኔ ጥያቄየ:-**

**1ኛ) ከህዝበ ክርስቲያን ጀምሮ እስከ ሊቃነ ጳጳሳት ድረሥ በአንድ ቃል ተወግዘዋል፡ ፡ ግዝቱን ያልተቀበሉ ሰዎች ወይም ህዝበ ክርክቲያን እንደመናፍቃን ነው ወይስ ሌላ ሥም ነው የሚሠጣቸው?? ማለት ከእነሡ ጋር አብረው ያሉት??**

**2ኛ) ሥልጣነ ክህነት ያላቸው፡፡ ከጳጳሳት እስከ ዲያቆናት አንቱ የሚያሰኛቸው ስም አላቸው፡፡ ይህንን ባንጠቀምበትና በተራ ሰው ስም ብንጠራቸው ጥፋት / ድፍረት ያስቆጥርብናል???**

**መልስ (አለቃ አያሌው ታምሩ) :-** አብረዋቸው ያሉት ሁሉም ማንም ይሁን ማንም ውጉዛን ናቸው ብያቸሁአለሁ፡፡ ከእነሱ ጋር የሆነ ሁሉ ማንም ይሁን ማን፡፡ ውጉዛን ናቸው፡፡ ራሳቸውንም በራሳቸው የሻሩ ናቸው፡፡ እኛ አይደለንም ፡፡ ክርስቶስን ሲተው ነው ስልጣኑ የቀረ፡፡ ክርስቶስ ከሌለ የክርሥቶስ ስልጣን የለም፡ ፡ ይሄን ታውቁ የለ፡፡ ክርስቶስ ከሌለ የክርስቶስ ስልጣን የለም፡፡ ክርስቶስ በሌለበት የክርስቶስ መንፈስ አያድርም ፡፡ይሄ ነው፡፡ ክርስቶስን የተወ ትቷል ፡፡ ሥለ ተወ የተሠጠው ጸጋ ሁሉ ተነስቷል፡፡ ባዶ ነው፡፡ ይሄ ነው፡፡

**ጥያቄ:-** **ከተወገዙበት አባቶች አንዱ ሲኖዶስ ተጠሪነቱ ለመንፈስ ቅዱስ ነው የሚል ነበር፡፡ ያኛው ተሽሮ ተጠሪነቱ ለአቡነ ጳውሎስ ተብሏል፡፡ ይሄኛው አባባል ስላልገባን ቢብራራልኝ???**

**መልስ (አለቃ አያሌው ታምሩ) :-** ለመንፈስ ቅዱስ የተባለው ለአባ ጳውሎስ ሲባል ምን ማለት ነው? እናንተ ራሳችሁ ፍረዱት፡፡ ተጠሪነቱ ለመንፈስ ቅዱስ ይል የነበረው ተለውጦ ለአባ ጳውሎስ ሲባል ምን ማለት ነው?? መንፈስ ቅዱስ ተሽሮ አባ ጳውሎስ ተሹሞ አይደለም፡፡ ታዲያ ምንድነው የምትለው፡፡ የአባ ጳውሎስ ፍቅር አለ የመንፈስ ቅዱስን ወንበር/መንበር መውረስ ይችላሉ ? መብታቸው ነው?? መንፈስ ቅዱስ እኮ ሿሚያቸው ነው እንጅ ጓደኛቸውኮ አይደለም፡፡

ሲኖዶስ በሚሰበሰብበት ጊዜ ከመሃል ክብ ጠረጴዛ ይደረጋል፡፡ ከዚያ ላይ ወንጌል ይደረጋል፡፡ መሪው መንፈስ ቅዱስ ነው ለዚያ ሲኖዶስ፡፡ ስለዚህ ውይይቱ በክብ ጠረጴዛ በእኩልነት እንጅ በበላይነት እና በበታችነት የለም፡ ፡ ያነን አስወግደው እሳቸው የመንፈስ ቅዱስን መንበር ከያዙ ጣኦት ናቸው ማለት ነው፡፡ እና እሳቸውን የተከተለ ሁሉ ጣኦታዊ ነው ማለት ነው፡፡

**ጥያቄ:-** **የጉባኤው ነገርስ እንዴት ነው? ማለቴ በአስራ አንድ በአስራ አንድ ሁሌ ትምህርት ይሰጣል ትምህርቱን የሚሰጡት በብዙ ወጣቶች ናቸው ውግዘቱን**

**የማይቀበሉ ናቸው ፡፡ በመማርም በኩልስ ምን መልእክት አለ? ስብከት በመተላለፉ ማለት ነው??**

**መልስ (አለቃ አያሌው ታምሩ) ፡-** ሰይጣን መቼለት ነው የወንጌል ሰባኪ ሆኖ የሚያውቀው ? መቼ ነው የተመረጠ ለወንጌል ሰባኪነት? አለ የምታውቁት በመጽሐፍ ቅዱስ ? እነሱ ሳያምኑ ማንን ነው የሚያሳምኑ? ሳይማሩ ማንን ነው የሚያስተምሩ፡፡ ክርስቶስን ሳያውቁ ወደ ማን ነው የሚጠሩት??

**ጥያቄ፡- ቅዳሴ ከነሱ ጋር መተባበር እንደሌለብን ተነግሮናል፡፡ ይሄንንም ደግሞ በጺጋ ተቀብለናል፡፡ ነገር ግን ቤተክርስቲያን ሄደን በባለፈው ጊዜ እንደተናገሩት ቅዳሴውን መጠለያ ይኖራል መጠላያ ውስጥ ገብተን በቅዳሴው ሰአት የራሳችንን የግል ጸሎት ብናደርግ የሚያመጣው ጥፋት ነገር ይኖራል???**

**መልስ (አለቃ አያሌው ታምሩ) ፡-** በቅዳሴ ላይ ሁለት ጸሎት የለም፡፡ ቤተክርስቲያን ሄዳችሁ አስቀድሱ አላልኩም፡፡ አሁን ለመሆኑ እንጸልይ ስትሉ አሁን ያድምጽ ማጉያ እያንባረቀ ልትጸልዩ ትችላችሁ ማለት ኘው?? እንኳን እናንተ እኔን እቤት የጸሎት ቤት አለችኝ በቃ እዜው ከፊቴ የቆመ ነው የሚመስል ግራማፎኑ ፡፡ እንዴት ሰንጥቆት እንደሚገባ አላውቅም፡፡

**ጥያቄ፡- አባታችን!! አሁን ብዙ ደካሞች እናቶች አሉ ፡፡ እነዚህ እናቶች ውግዘቱን የተቀበሉት ቤተክርስቲያን ላይ የማስቀደስ ወይም ስጋወደሙ የመቀበል አቅም የላቸውም ፡፡ ነገርግን በአቅራቢያቸው ባሉ ቤተክርስቲያን ተገኝተው የጌታን ስጋና ደም ለመቀበል ይፈልጋሉ እናም ይቀበላሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች የጌታን ሥጋና ደም የሚቀበሉ የተወገዙ ናቸው ወይስ አይደሉም???**

**መልስ (አለቃ አያሌው ታምሩ) ፡-** …እና በየጊዘው ካልተቀበልን ብለው ባይቸገሩ፡፡ ያንን አክብረው ፀሎታቸውን ቢፀልዩ አቡነዘበሰማያት ቢደግሙ እና ያለቻቸውን እድሜ ከእግዚአብሔር ጋር ቢያሳልፉ ብትነግሯቸው ነው የሚሻል፡፡

**ጥያቄ፡- አባ ጳውሎስ ተወግዘዋል እና የተባበሩት ምእመናን ከእነሡ ጋር የተባበሩት ምእመናን ከእነሱ ጋር ያለን ውግዘቱን ያልተቀበሉት እና የተቀበሉ ሰወች ያላቸው ግንኙነት እንዴት ነው?? በማህበራዊ ኑሮ ማለት ነው??**

**መልስ (አለቃ አያሌው ታምሩ) ፡-** …እኔ በቤተክርስቲያን ባለው ስነ ስርአት ነው፡፡ ማህበራዊ ኑሮን ግን ራሳችሁ ሊያስቡበት ይገባል፡፡

## ጥያቄ:- ማህበራዊ ኑሮ ላይ ሲባል የጽዋ ማህበር ላይ??

**መልስ (አለቃ አያሌው ታምሩ) :-** አይቻልማ!! እርጥብና ደረቅ አንድ ላይ ይሄዳል እንዴ፡፡ የሙትና የህያው አካል ማለት እኮ ነው፡፡ የሞተ አካልና ሕያው አካል አንድ ላይ ይኖራል? ለምንድነው ሐኪሞች ሰውየውን እግሩን የሚቆርጡት ፣ እጁን የሚቅርጡት ለምን እያሉ ነው፡፡ ምን እያሉ ነው፡፡ የማይሆን ስለሆነ እኮ ነው አብሮ መኖር አይቻልም ፡፡

## ጥያቄ:- የእግዚአብሔር ሰላምታ መሠጣጠት ይቻላል??

**መልስ (አለቃ አያሌው ታምሩ) :-** የእግዚአብሔር ሥርአት እኮ የሚኖረው እግዚአብሔር ሲኖር አይደለም እንዴ በመካከላችሁ ፡፡ እግዚአብሔርን የተወና እግዚአብሔር ያለውን አንድ ላይ፡፡ ሠላም አትበሏቸው አይደል እንዴ ያለው ሐዋርያው ዮሀንስ፡፡ ሰላም አትበሉት፡ ይሄን ስም ወደ እናንተ ይዞ የማይመጣ ከሆነ ፣ ይህንን ትምህርት ወደ እናንተ ይዞ የማይመጣ ከሆነ ሠላም አትበሉት ሠላም የሚለው በከፉ ሥራው ይተባበረዋልና፡፡ ነው ያለ፡፡ ቅዱስ ዮሀንስ ሐዋርያ በመልእክቱ፡፡

ጌታም ወደምትገቡበት ቤት ሁሉ አስቀድማችሁ በዚያ ሠላም የሚገባው ሠው እንዳለ ጠይቁ፡፡ ካለው ሠላማችሁ ይደርበት ከሌለው ግን ሰላማችሁ ወደ ራሳችሁ ይመለስላችሁ ነው ያለ፡፡ እና ሠላም የሚኖረው ክርስቶስ ሲኖር ነው፡፡ በይሉንታ እኮ አይደለም ሐይማኖት ፡፡ በይሉንታ ሊፈፀም አይችልም፡፡ እንደሱ ከሆነማ ብዙ ሰማእታት እናቶቻቸውን ፣ አባቶቻቸውን ፣ ወላጆቻቸውን አሳዳሪወቻቸውን እየተው ለምን ይሄዱ ነበረ ፡፡

**"እኔን የሚከተል ቢኖር ራሱን ይካድ " ነው ያለው፡፡**

## ጥያቄ:- አባታችን ! በፊት ቅዳሴ ጠዋት ጠዋት ተነስተን እንሄድ ነበር፡፡ አሁን ግን ቅዳሴው ስንቀር ከቤተሰቦቻችን ልዩ ሀሳብ እየተጠን ነው፡፡ ማለትም ከቅዳሴ ተለይቶ ምን አይነት ጸሎት ነው?? ስብከትም ስንቀር ምን አይነት ጸሎት ነው?? መስተካከል አለበት እያሉ ከቤተሰቦቻችን ፍቅር እያጣን ነው፡፡ እና ውግዘቱን ደግሞ አልተቀበሉትም እና ይሄን እንዴት ነው ማስረዳት የምንችለው ???

**መልስ (አለቃ አያሌው ታምሩ) :-** ቅዳሴ ካላስቀደሳችሁ አትጸልዩ የሚል ከየት አገኙ እነሱ፡፡ ቅዳሴና ጸሎት የተለያዩ ናቸው፡፡ ቅዳሴ ማስቀደስ ይቻላል በእርግጥ ከተቻለ፡፡ ስጋወደሙን መቀበል ይቻላል በእርግጥ ከተቻለ፡፡ ግን ካላደረጋችሁ አትጸልዩ የሚል ማነው ይሄን ያዘዘ ? ጸሎት ሌትም ቀንም ጧትም ማታም ሲሆን በ24ቱ ፣ ከዘረ ቢቀር በ12ቱ ፣ ከዛ በቀር በ7ቱ ሰአታት መጸለይ ይቻላል፡፡

ቅዳሴ በዚህ ሁሉ መቀደስ ይችላል እንዴ?? የቅዳሴ ስርአት ሌላ ነው የጸሎት ስርአት ሌላ ነው፡፡ ደሞ ስብከት የሚሉት ደግሞ አሁን የመጣ የፕሮቴስታንት ውርስና ቅርስ ነው እንጅ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን አይደለም ፡ ፡ ይሄ ዝምብሎ ማንም የሚፈነጭበት የቻለውም ያልቻለውም ሲደነፍ የሚውልበትና እንደ ሙዚቃ ዋሽንቱም፣ ከራሩም፣ መሠንቆውም የሚፈራረቅበት ይሄ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ስርአት አይደለም ፡፡ አይደለም ፡፡ ይሄ ሚስዮናውያንን ለማስገባት የተደረገ ሸር ነው፡፡ ለማስለመድ፡፡ ሕዝቡ ከየት መጡ እንዳይል ለማስለመድ የተደረገ ሸር ነው እንጂ ራሳቸውን የሚወጡበትን የሚገቡበትን የማያውቁ ጎረምሶች የወንጌል አስተማሪ ሆነው መላክ የለባቸውም፡፡

**ጥያቄ፡- በአሁኑ ሰአት እኛ ማለት ከነዚህ ሰወች አሁን ከተጠቀሱት አጠቃላይ አባቶች ከተለየን ራሳችንን እንዴት አድርገን እንጠብቅ ? ማለት በአሁን ሦአት እግዚአብሔርን ነቅፈው ከሚኖሩ ሦወች ጋር ሕብረት እንዳይኖረንና መጠንቀቅ እሚገባንን ጉዳይ አባታዊ ምክርና ትምህርት ቢሠጡን ?? አንዳንድ ምእመናኖች አሉ ክርስቲያኖች ውግዘቱን ተቀብሎ በእንዝላልነት፣ በምንቸገረኝነት በምን አለብኝነት ዝምብለው የሚጓዙ ምእመናኖች አሉ እና ከዚህ ውጭ ብዙ ክርስቲያኖች ምእመናኖች አሉ ለእነዚህ ክርስቲያኖችም ሆነ ለኛም ለሌሎችም እንደው በትምህርት መልኩ የሚያስተላልፉልን የሚችሉት???**

**መልስ (አለቃ አያሌው ታምሩ) ፡-** ከክርስቶስ ጋራ ካልሆኑ ምን ያረጉላችኋል? ከክርስቶስ ጋር ካልሆነ ምን ሊጠቅማችሁ ይችላል፡፡ " ከኔ ጋራ የማይሰበሰብ ይበትነኛል፤ ከኔ ጋር አንድ የማይሆን ጠላቴ ነው ያለ" ፡፡ እና እናንተ የክርስቶስ ከሆናችሁ ከክርስቶስ ጋር ያልሆነ ምን ያደርግላችኋል፡፡ የክርስቶስ የሆነ ሁሉ የክርስቶስ ያልሆነውን መተው አለበት፡፡ ምንድነው ያለ ቅዱስ ጳውሎስ ፡- በቆሮንቶስ 2ኛ ምእራፍ ስድስት ከቁጥር 14 "ተጠራጣሪወች አትሁኑ፤ በማያምኑ ሰዎች ቀምበር አትጠመዱ፤ በሕጋቸው አትያዙ ፣ ፅድቅን ከሐጥያት ፣ ጨለማን ከብርሃን ሚያደባልቅ ፣ ክርስቶስን ከሠይጣን፣ ምእመናን ከመናፍቃን የሚያቀላቅል የእግዚአብሔርንስ ታቦት በጣኦት ቤት የሚያኖር አለ ወይ ? ብሎ እንዲህ አድርጎ ነው የለየው፡፡ እስቲ እሽ አሁን ከነዚህ ነገሮች የትኛው ነው የምትሉት?? ጽድቅ ከሐጥያት ፣ ጨለማን ከብርሃን ፣ ምእመናን ከመናፍቅ ፣ ክርስቶስን ከሠይጣን፡፡ እኔ አይደለሁም የተናገርኩት የእግዚአብሔር ቃል በሐዋርያቱ አድሮ እንዲህ ግልጥ ፍርጥ ያለ ቋንቋ ሠጥቷል፡፡ በዚህ መሠረት ተመሩ እሺ ለሚላችሁም ንገሩ ፤ እምቢ ካላችሁ ራሳችሁን ጌታ ብሏል ትቢያችሁን አራግፍችሁ መመለስ ብቻ ነው፡፡ ሌላ መንገድ ከተቻላችሁ አሁን የካህናቱ ስህተት ምን እንበላለን የሚል ነው፡፡ የገንዘብ ምንጭ አዘጋጅታችሁ እሽ ያሏችሁን ካህናት ወደ እናንተ ብትጠሩ ሌሎችንም ልታድኑ ትችሉ ይሆናል ፡፡ የኔ የሚመስለኝ ብልሃት ይሄ ነው፡፡ ከዚህ በቀረ ሌላ የምላው ነገር የለኝም፡፡ እኔ በራሴ በበኩሌ ሕይወቴን አሳልፌ የሰጠሁኝ ስለሆነ ምንም የሚያከራክረኝ ነገር የለም፡፡
እስከተቻላችሁ ድረስ የሚሠማችሁን እሽ የሚላችሁን መልሱለት እምቢ ካለ ምንም ማድረግ አትችሉም፡፡

ተፈፀመ !!!

**ክቡር ሊቀ ሊቃውንት አለቃ አያሌው ታምሩ፡፡**

# የአለቃ አያሌው ታምሩ ጸሎት

† † †

## በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ አሜን!

...አቤቱ ቸር እግዚአብሔር አምላካችን ሆይ በዚህ እለት ፣ በዚህ ሠአት ፣በዚህ ስፍራ በቸርነትህ ስላሰባሰብከን እንደቸርነትህም የሚገባን እንድንወያይ ስላደረከን ከሁሉ አስቀድሞ ቅዱስ ስምህን እናመሠግናለን፡፡

ቸር እግዚአብሔር አምላካችን ሆይ በዚህ ስብሰባችን የሚጠቅመንን መንገድ ለመፈለግ እንጂ ማንንም ለመጉዳት ያላደረግነው የማናደርገውም መሆናችንን ስለምታውቅ አንተ ምናልባት ስህተት ቢኖረን ይቅርታ እንድታደርግልን እንለምንሀለን ፡፡ እንማልድሃለን፡፡

ጌታየ አምላኬ መድሀኒቴ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ እኔ አቅም የለኝም ፣ ጉልበትም የለኝም፣ ማንንም ለመጉዳት ማንንም ለመጥቀም አልፈልግም እንደማልፈልግም ታውቀዋለህ፡፡ ህሊናንም ፣ ሕይወቴንም የምትመረምረው አንተ ስለሆንክ ሁሉንም አንተ ታውቀዋለህ፡፡ ያዘዝከኝን ብቻ እንደሠራሁ አምናለሁ፡፡ ስለዚህ አሁንም ቤተክርስቲያኒቱ ከወደቀችበት የምትነሳበትን ፣ ከተሠበረችበት የምትጠገንበትን አዕይምሮ፣ ፍላጎት፣ ናፍቆት፣ በየምእመናኖችህ ልብ እንድታሳድር እለምንሀለሁ! እማልድሃለሁ፡፡ ጌታየ አምላኬ መድሃኒቴ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ጠላት ሠይጣን የተከልከውን እየነቀለ ፣ የዘራሃውን እያፈለሠ ነው ፡ ባሁን ጊዜ ያለው በኢትየጵያ ቤተክርስቲያን ላይ የተከልከውን መንቀል ነው፣ የበቀለውን ማጥፋት ነው እንጂ እንክርዳድ መዝራት እንኳን አይደለም ድብልቅ አይደለም የሆነ፡፡ ከላይ እስከ ታች በገንዘብና በሠው ሀይል፣ በጉልበት ሀይል፣ ቤተክርስቲያን ታፍና እየፈረሠች ነውና በደምህ ለዋጀሃት ቤተክርስቲያን አንተ የስንብት ስራ እንድትሰራ እለምንሃለሁ! እማልድሃለሁ፡፡

**ክብር ምስጋና ለአንተ ለአባትህ ለመንፈስ ቅዱስ ይሁን ! ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ !!**

**አሜን!!**

ማስታወሻ፡- ይሄ ጽሑፍ ሲዘጋጅ ቃል በቃል አለቃ አያሌው የተናገሩትን ወደ ጽሑፍ ስቀይር የቃላት ግድፈት ይኖራልና ችግሩ የኔ ነው እንጅ የእሳቸው አይደለም፡፡ አስቀድሜ ይቅርታ እጠይቃለሁ፡፡

**ሀብተ ማርያም (ተምዘ)**

# የአለቃ አያሌው ታምሩ

# የሕይወት ጉዞ በሦስቱ መንግሥታት ዘመን።

የዓለም ታሪክና ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚያስተምሩን መንፈሳውያን አባቶችና ዓለማዊ መሪዎች ተባብረው ለሕዝብና ለአገር ጥቅም የሠሩባቸው ዘመናት የመኖራቸውን ያህል፤ አንዱ አሳዳጅ ሌላው ተሳዳጅ ሆነው የታዩባቸው ጊዜያትም ብዙ ናቸው። ክቡር አባታችን አለቃ አያሌው ታምሩም ከልጅነት እስከ ዕርጅና ዕድሜያቸው ባለፉባቸው ሦስት የኢትዮጵያ የመንግሥት ሥርዓቶች ውስጥ ዐብሯቸው በተጓዘው ትውልድ ፊት ከተወጧቸው መንፈሳዊ ተግባሮች ጥቂቶቹን መጥቀስ አግባብነት አለው ብለን እናምናለን።

፩ኛ፤ የዐፄ ኀይለ ሥላሴ መንግሥት። የዐፄ ኀይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት አለቃ አያሌው ታምሩ ከልጅነት ወደ ጎልማሳነት የተጓዙበት ዘመን ነው። በዚህ ዘመንም ገና በወጣትነት ዕድሜያቸው በንጉሠ ነገሥቱ ፊት እግዚአብሔር ከፍተኛ ሞገስን እንደ ሰጣቸው ያስመሰከሩ የተለያዩ የታሪክ ክስተቶች ታይተዋል።

***ሀ፤ የኢትዮጵያ ዕውራን የተራድኦ ኅብረት ድርጅትን*** ለማቋቋም ከሌሎች ባልደረቦቻቸው ጋር ያደረጉትን ጥረት ንጉሠ ነገሥቱ ከከፍተኛ አድናቆት ጋር በመቀበል ስለ ደገፏቸው ተግባራዊ ሊሆን ችሏል። እሳቸውም ማኅበሩን መጀመሪያ በምክትል ሊቀ መንበርነት ኋላም በቦርድ ሊቀ መንበርነት መርተዋል።

***ለ፤ ንጉሠ ነገሥቱ የአለቃን ከፍተኛ የዕውቀት ብቃት በመገንዘብ*** በቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ሥር በሚገኙ ኮሌጆች የማታ ትምህርት ክፍሎች ውስጥ የሃይማኖት ትምህርት እንዲያስተምሩ ፈቅደውላቸዋል።

***ሐ፤ በተለያዩ መንግሥታዊ በዓላት በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ንግግር*** እንዲያደርጉ ገና በወጣትነት ዕድሜያቸው የተፈቀደላቸው ሲሆን እሳቸውም ሰውን ለማስደሰት ሳይሆን እግዚአብሔር የመራቸውን እውነተኛ ነገር ንጉሠ ነገሥቱንም ሆነ መኳንንትና መሳፍንቱን ያስደስታል፥ ያስከፋል ሳይሉ እውነቱን ፍርጥ አድርገው ያስተምሩ እንደ ነበረ በጊዜው የነበሩ የሚመሰክሩት ሐቅ ሲሆን አስደናቂው ነገር ግን የንጉሠ ነገሥቱ አለመቆጣት ነበር። ከንጉሠ ነገሥቱ ፊት ለመናገር ከተሰጧቸው ብዙ ዕድሎች በአንዱ የሰጡትን ትምህርትና ያስከተለውን ውጤት እንደሚከተለው በአጭሩ አቅርበነዋል። የተቀጸል ጽጌ በዓል በሚከበርበት አንድ አጋጣሚ ከንጉሠ ነገሥቱ ፊት ቀርበው ቅኔ እንዲቀኙና ንግግር እንዲያደርጉ ይፈቀድላቸዋል። በጊዜው በዕድሜ በጣም ወጣት ከመሆናቸው ጋራ በሥራ አገልግሎትም ብዙ የቆዩ አልነበሩም። ነገር ግን እግዚአብሔር አምላካቸው ገና በልጅነት ዕድሜያቸው ሞገስን ሰጥቷቸው ስለ ነበር በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ለመቆም ብዙ መውጣት መውረድ አላስፈለጋቸውም ነበር።

በዚያ ታሪካዊ ዕለት ያደረጉት ንግግር በአጭሩ ሲቀመጥ መልእክቱ የሚከተለው ነበር። «ግርማዊነትዎ የሚመሯትን አገር ኢትዮጵያን አያት ቅድመ አያቶችዎ እግዚአሔርን ከመፍራት ጋር ነበር ሲመሯት የኖሩ። ለዚህም ምክንያታቸው አገሪቱ ሀገረ እግዚአብሔር፥ ሕዝቧም ሕዝበ እግዚአብሔር መሆኑን በማወቃቸውና መረዳታቸው ነው። እስዎንም በአባቶችዎ ዙፋን ላይ ሲያስቀምጥዎ እሱ በሰጠዎት ጸጋ፥ በተፈጥሮ ብልህነትና በትምህርት ያዳበሩትን ዕውቀት በመጠቀም ጭምር አገርዎንና ሕዝብዎን በበለጠ እንዲያገለግሉ ፈቃዱ ሆኖ ነው። አገርዎ ኢትዮጵያና ቀብታ ያነገሠችዎ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ነውር ነቀፋ የሌለባቸው ናቸው። ግርማዊነትዎም ይህችን ሀገረ እግዚአብሔርና ቀብታ ያነገሠችዎትን ቤተ ክርስቲያን በነበረ ክብራቸውና

ታሪካቸው አንጻር የመጠበቅና ከተለያዩ የጠላት አመጣጦች የሚሰነዘርባቸውን አደጋ ሁሉ የመመከት ኃላፊነት አለብዎ። ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ሠለጠነ ከሚባለው ዓለም የሚያስፈልጋቸው የእደ ጥበብና የተለያየ ሙያ ነክ ሥልጣኔ እንጂ የሃይማኖት ወረርሽኝ አይደለም። ነገር ግን በአሁኑ ሰዓት ሃይማኖት የግል ነው አገር የጋራ ነው የሚለውን የግርማዊነትዎን መርኅ መግቢያ በማድረግ ከብዙ አቅጣጫ የሚወረወሩት ፍላፃዎች በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና በህልውናዋ ላይ እያነጣጠሩ ይገኛሉ። ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ርስቱ መሆኗን መዘንጋት አይኖርበትም። ይልቁንም ግርማዊነትዎ የዚህችን ታሪካዊና ገናና ቤተ ክርስቲያን ህልውና የመጠበቅ ኃላፊነት አለብዎ። ይህንንም የምልዎ የቤተ ክርስቲያን ዕድል ከእያንዳንዱ ኢትዮጵያን እመራለሁ ከሚል መሪ ዕድል ጋር የተጣመረ በመሆኑ ነው።

ዛሬ ዙሪያዎን ከበው የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ማፍረሻ ምክንያት ከእስዎ ለማግኘት በሥልጣኔና በዴሞክራሲ ስም ያሰፈሰፉ ሁሉ ነገ እስዎ ከእግዚአብሔር ተጣልተው ብቻዎን ቢቀሩ አጠገብዎ አይገኙም። ሁሉም ወደ ላኳቸው የውጪ ኀይሎች ጉያ ነው የሚገቡ። በዓለም የተለያዩ ክፍሎች ልዩ ልዩ ሃይማኖቶች ቢኖሩም እያንዳንዱ አገር ታሪካዊና ነባር የሥነ መንግሥትና የሥነ ሕዝብ አገነባብ አመጣጥ አንጻር ሁሉም አገር የራሱ ኦሪሴላዊ ሃይማኖት አለው። ይህም የየአገሩ የህልውና ምስጢር አስኳልና አውታር ነው። ይህንን ለመገንዘብ ግርማዊነትዎ የእኔን አስታዋሽነት ባይሻም በአባትዎ በዳዊት ዙፋን ላይ ያስቀመጠዎትን እግዚአብሔርንና ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን የተሰጠችውን ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠብቀው ይኑሩ። ይህን ባያደርጉ ራስዎንና አገሪቱን በአደጋ ላይ ይጥላሉ። ዙፋንዎም ለዘርዎ አይተርፍም፤» የሚል ነበር።

**ይ**ህን ንግግር በሚያደርጉበት ጊዜ ብዙዎች መኳንንት፥ መሳፍንትና ሹማምንት፤ «ይህ ልጅ ጃንሆይ ፊት ቢሰጡት ጊዜ ድፍረት አበዛ። ብሎ ብሎ እንዴት እንዲህ ይዘልፉቸዋል፤» በማለት እያጉረመረሙ እያሉ በቤተ መንግሥቱ አስተናጋጆች አማካይነት ከሰው መሐል አለቃ አያሌው (ያኔ መሪጌታ) ተጠርተው በተለየ ክፍል እንዲቆዩ ይደረጋል። እነዚያ ተቺዎችም፤ «አላርፍ ብሎ በገዛ እጁ ዋጋውን አገኘ፤ ታሰረ፤» እያሉ ይወያዩ ነበር። ከተወሰነ ቆይታ በኋላ ወደ ልዩ ክፍል ወስዶ እዚህ ጠብቅ ተብለሃል ያላቸው አስተናጋጅ ፫፻ ብር ይዞ መጥቶ፤ «ይህን ሽልማት ጃንሆይ ልከዋል፤» ብሎ ሰጣቸው። ከዚያም ወደ ቤታቸው ሄዱ።

በሌላ አጋጣሚ ንጉሠ ነገሥቱ ሲያገኟቸው በልዩ ትኩረትና ርኅራኄ አነጋግረዋቸው እንዳመሰገኗቸው፥ የሥራ ዕድልም እንደ ሰጧቸው በራሳቸው አንደበት ተናግረዋል። «ቅኔ ላበረከት ጃንሆይ ዘንድ ቀርቤ፤ «ግርማዊ ጃንሆይ! የተማርኩትን የማስተምርበት፥ ያልተማርኩትንም የምማርበት ዕድል ይሰጠኝ፤» ብዬ ነበር። እሳቸውም፤ «እሺ ያልተማርኩትን የምማርበት አንድ ጥያቄ ነው። የተማርኩትን የማስተምርበት የምትለኝ አንተ ምን ችሎታ አለህ?» አሉኝ። «እኔ ለወጣቱ የኢትዮጵያን ታሪክ ማስተማር እፈልጋለሁ። እስዎ አገር የጋራ፥ ሃይማኖት የግል ነው አሉ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀገሩን ከሃይማኖቱ፥ ሃይማኖቱን ከሀገሩ ለይቶ አያውቅም። ነገሥታቱ ራሳችሁ አንድ ነገር ሲነሣ የአገርህን ድንበር የሚዳፈር፥ የሃይማኖትህን ክብር የሚጻረር፥ ቤተ ሰብህን የሚበትን ጠላት መጥቷልና ተነሥ ነው የምትሉት። አሁን ግን ወጣቱን ትውልድ አባትህም እናትህም እኔ ነኝ ብለውት ዐዳሪ ትምህርት ቤት ሰበሰቡት። እየበላ እየጠጣ ከመራገጥ በቀር የሚያውቀው ነገር የለውም። አስተማሪዎቹ ደግሞ የሌላ አገር ዜጎች ናቸው። ሞግዚቶቹ ሁሉ ባዕዳን ናቸው። የራሳቸውን ታሪክ ከሚነግሩት በስተቀር የራሱን የሚያስተምረው የለም። እና ይሄ ከጠፋ በኋላ እንደገና ተመልሶ ቢፈለግ አይገኝም። ዛሬ ወደደም ጠላም፥ እንዲያው ለቅንጦት ብሎም ይሁን፤ ኀይለ ሥላሴ ይሙት፤ እያለ ያባቱ ማሳረፊያ ቢያደርግዎም አንድ ነገር ከመጣ እንኳን ደሙን የሚያፈስልዎ ውሃም

የሚረጭልዎ አያገኙም፤» አልኳቸው። ከዚያም ሣቁብኝ። ዐብረዋቸው የነበሩት አቶ ከበደ ሚካኤል ግን በጣም ተቆጡ። «ይሄ የወታደር አስተማሪ እንጂ የሲቪል አስተማሪ መሆን አይችልም አሉ።»»

በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን ካደረጓቸው ታዋቂ ንግግሮቻቸው ይልቁንም በጃንሆይ ዘመነ መንግሥት መጨረሻ ዋዜማ ላይ የተናገሩትን ንግግር በጊዜው ከነበሩት እማኞች አንዱ ኮሎኔል ቃለ ክርስቶስ ዐባይ «የኢትዮጵያ ታሪካዊና ፖለቲካዊ ሂደት፤» በሚባለው መጽሐፋቸው ገጽ ፩፻፲ ፩ ላይ እንደሚከተለው አስፍረውታል። «በዚህ ቀን ዝናቡ እያካፋ በቤተ መንግሥቱ በረንዳ ላይ ሕዝቡን ወክለው ንግግር ያደረጉት የተክለ ሃይማኖት ደብር አለቃ ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ ሲሆኑ ካደረጉት ንግግር መካከል ጥቂቱ ፍሬ ነገር ቢጠቀስ ቀጥሎ የተመለከተውን ይመስላል። «የግርማዊነትዎ መንግሥት ዐሥራ አንደኛው ሰዓት ላይ በደረሰበት ወቅት ኢትዮጵያ በታላቅ ችግርና ፈተና ውስጥ ተዘፍቃ ትገናለች፤» የሚል ንግግር በማሰማት ንግግራቸውን ደመደሙ።» ክቡር አባታችን አለቃ አያሌው ታምሩ ከነገሩን የምንገነዘበው ንጉሠ ነገሥቱ እንደ ንጉሠ ነገሥት ሳይሆን እንደ ዘመድ እንደ ጓደኛ በጣም ቅርበት ባለው ሁኔታ ያነጋግሯቸው እንደ ነበረ ነው።ከዚህ በመቀጠል የምንጠቅሰውም ለዚህ እማኝ መሆን ይችላል። ጃንሆይ፤ «የሞት መድኃኒቱ ምን ይሆን?» ብለው ይጠይቋቸዋል። እሳቸውም፤ «የሞት መድኃኒቱ ልጅን በዕውቀት በሃይማኖት አንጾ ማሳደግ ነው፤» ይላሉ። ጃንሆይም፤ «እውነት ብለሃል፤» ብለው መልስ ሰጥተዋቸዋል።

ዐፄ ኀይለ ሥላሴ የአለቃ አያሌው ታምሩን ልዩ ችሎታና ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን ጸጋ ጥሩ አድርገው የተገነዘቡ መሆናቸውን ከላይ የጠቃቀስናቸው የተለያዩ ሁኔታዎች የሚጠቁሙ ሲሆን በተለይ ደግሞ የተክለ ሃይማኖትን ቤተ ክርስቲያን እልቅና ሹመት ተከትሎ ተነሥቶ የነበረውን ተቃውሞ የዳኙበት ሁኔታ ከላይ የጠቀስነውን እምነት ያጠናክራል። ጊዜው ፲ ፱፻፷ ዓመተ ምሕረት ነበር። የያኔው ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ የደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን አለቃ ሆነው ይሾማሉ። የእልቅናው ሹመት በችሎታ፥ በምርጫ ሳይሆን እንደ ዘር ውርስ ለእኛ መተላለፍ ይገባዋል በሚሉ ሰዎች ሥር ያደሙ ሰዎች ከፍተኛ ተቃውሞ ያነሡና አዲሱ ተሿሚ አለቃ አያሌው ታምሩና ተቃዋሚዎቻቸው ንጉሠ ነገሥቱ ፊት እንዲቀርቡ ይጠራሉ። ንጉሠ ነገሥቱ የተቃዋሚዎቹን ተወካይ፤ «ተቃውሟችሁ ምንድነው?» ብለው ይጠይቃሉ።

«ጃንሆይ! አካለ ስንኩል ሰው ለቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ አገልግሎት ሊሾም አይገባውም የሚል ሕገ ቤተ ክርስቲያን አለ። እሱም ዐይነ ሥውር ስለ ሆነ በእልቅና ሊሾምብን አይገባም፤» ይላቸዋል። ጃንሆይም፤ «በየትኛው ሕገ ቤተ ክርስቲያን ነው ይህ የምትለው አንቀጽ ያለው?» ይሉታል። ሰውየውም አፉ እንዳመጣ ተናግሯልና የተጠየቀውን ጥያቄ መመለስ ይሳነዋል። ጃንሆይም በሁኔታው በጣም ተገርመው፤ «ወይ ግሩም! ያልተማረው የተማረውን እንዲህ አድርጎ ሲዘልፈው!» ካሉ በኋላ፤ «ከ፳ ዓመት በላይ ሲያስተምራችሁ ዐይነ ሥውር ነው አላላችሁም። ሹመት ሲያገኝ ነው ይህን ያመጣችሁት። እሱ ሥጋዊ ዐይኑ ቢጠፋ ልቡ ብሩህ ነው። ዕውራንስ እያያችሁ የማታዩ እናንተ ናችሁ። ሹመነዋል አንሽረውም፤» ብለው ሹመታቸውን አጸኑላቸው። ወደ እሳቸውም ዘወር ብለው፤ «ሹመቱን የሰጠንህ ወንጌል እንድታስተምርበት ነው። ቂም አትያዝባቸው፤ አስተምራቸው፤» ብለው አሰናብተዋቸዋል።

ለማጠቃለል ያህል በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን፤ መመስገን ያለበትን አመስግነው፥ መመከር ያለበትንም መክረው፥ መገሠጽ የሚገባውንየሚገባውን ገሥጸው፤ በተጨማሪም ነቢይ ሊያሰኛቸው በሚችል ደረጃ በትንቢት መልክ የሚጠቀሱ ታላላቅ መልእክቶችንም ያስተላለፉበት ዘመን ነው ለማለት ይቻላል።

## ፪ኛ፤ የደርግ ዘመን።

የደርግ ዘመን እንኳን እንደ አለቃ አያሌው ታምሩ ላለ የሃይማኖትና የአገር ጠበቃ ለማንኛውም ሰው ከፍተኛ ፈተናን የጋበዘ ከባድ ጊዜ መሆኑ በይፋ የታወቀ ነው። አለቃ አያሌው ታምሩ በንጉሡ ነገሥቱ ዘመን የጀመሩት ሐዋርያዊ ተጋድሎ በደርግ ዘመን ደረጃውን ጨምሮ ወደ ሰማዕትነት ተጋድሎ የገቡበት መባቻ ሆኖ ሊቆጠር ይችላል። በየካቲት ወር ፲ ፱፻፷፮ ዓመተ ምሕረት የተጀመረውን የለውጥ ንቅናቄ ተከትሎ በየቦታው የተቀጣጠለው የአብዮተኛነት መንፈስ ቤተ ክርስቲያንንም የጎበኛት ብዙ ሳይውል ሳያድር ነበረና ካህናትም በአለቆቻቸው ላይ የተቃውሞ ዐመፅ አካሂደዋል። ብዙዎችም አጋጣሚውን ለሐሰተኛ ዓላማቸው ማስፈጸሚያ ሲያውሉት ታይተዋል። ይህንኑ ተከትሎ አለቃ አያሌው ታምሩ ከግንቦት ወር ፲ ፱፻፷፮ ዓመተ ምሕረት ጀምሮ የተክለ ሃይማኖትን ቤተ ክርስቲያንን በእልቅና ማገልገል አቆሙ። ነገር ግን በጠቅላይ ቤተ ክህነት ውስጥ የሊቃውንት ጉባኤ ሰብሳቢ ከመሆን ጋር ከተለያዩ አድባራትና ገዳማት በሚቀርብላቸው ጥሪ መሠረት በጣም ብዛት ባላቸው የቤተ ክርስቲያን በዓላት ላይ በመገኘት እንኳን የተቃውሞ የምስጋና ቃል ለመናገር ያስፈራ በነበረበት በዚያ ቀውጢ ሰዓት የሕዝብና የቤተ ክርስቲያን አንደበትና ሕሊና ሆነው በሃይማኖት ትምህርት ረኀብና በፍትሕና መልካም አስተዳደር ጉድለት የተንገበገበውን ኢትዮጵያዊ ሕዝበ ክርስቲያን ሲያስተምሩና ሲያጽናኑ ኖረዋል።

በወታደራዊው መንግሥት ዘመን በሕዝብ ላይ የተፈጸሙትን ዘግናኝ ግፎችና በቤተ ክርስቲያንና በአጠቃላይ በሃይማኖት ላይ የተቃጣውን የክሕደት ትምህርት በጥብቅ በመቃወማቸው በተደጋጋሚ ወደ ሕዝብ ደኅንነት ቢሮ እየተከሰሱ የቀረቡ ሲሆን በደርጉ ሊቀ መንበርና ምክትል ሊቀ መንበር ፊትም ቀርበው ከፍተኛ ተግሣጽ ደርሶባቸዋል። የሚከተሉትን ለታሪክ ማስታወሻነት እናቀርባለን።

### ሀ፤ የጎጃም ክፍለ ሀገር ተልዕኮ።

ደርግ ሥልጣን ከያዘ በኋላ በነበሩት የመጀመሪያዎቹ አንድና ሁለት ዓመታት የጎጃም ሕዝብ የደርግን ሥልጣን አልቀበልም ብሎ ክፉኛ ተቃውሟል። የሕዝቡ የመሬት ይዞታ ሥርዓት የጭሰኝነትና የገባርነት ሳይሆን የትውልድ ሥርዓትን የሚከተል ነበርና መሬት የመንግሥት ነው የሚለው ዐዋጅ የእያንዳንዱን ሰው የመሬት ባለቤትነት የሚያሳጣ በመሆኑ፤ የነፍስ ወከፍ መሣሪያ ጉዳይም ሕዝቡ ለዘመናት ያዳበረው ባህል ከመሆኑ ጋራ የራስን፥ የቤተ ሰብንና የአገርን መብትና ክብር የሚዳፈር ጠላት ሲነሣ የሚመክትበት መከላከያ መሆኑን ስለሚያምን፤ እንዲሁም የደርግ መንግሥት ለሃይማኖት የነበረው አመለካከት ይልቁንም «እግዚአብሔር የለም» የሚለውን ኮሚዩኒስታዊ ዐዋጅ ስላልወደደው የጎጃም ሕዝብ በከፍተኛ ደረጃና በግንባር ቀደምትነት የደርግን መንግሥት በመቃወም በተለያዩ መልኮች ቅሬታውን በተደጋጋሚ እየገለጠ ነበረ።

በዚህ ወቅት ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ከጎጃም ክፍለ ሀገር የተለያዩ አውራጃዎችና ወረዳዎች ተወላጅ የሆኑ፥ የሕዝቡን ሥነ ልቡና የሚያውቁ፥ በሕዝቡም ዘንድ ተሰሚነት ያላቸው በአዲስ አበባ የሚኖሩ ሰዎችን አሰባስቦ ትእዛዝ ይሰጣል። ከተጠሩት ሰዎች መካከል አለቃ አያሌው ታምሩ አንዱ ነበሩ። ትእዛዙን የሰጡት ኮሎኔል አጥናፉ አባተ ሲሆኑ መልእክቱም የሚከተለው ነው። «ወደ ትውልድ ቀዬአችሁ ሄዳችሁ ሕዝቡ ዓላማችንን እንዲረዳና እንዲተባበረን አስረዱልን። የእኛ ዓላማ የሰፊው ሕዝብ መብትና ፍላጎት የሚከበርበትን ሥራ መሥራት ነውና በእኛና በሕዝቡ መካከል የሽምግልና አገልግሎት እንድትሰጡ መርጠናችኋል።» አለቃም ይህን መልእክት ተቀብለው ለመሄድ የማይችሉ መሆናቸውን ይናገራሉ። ሰሚ ግን አላገኙም። የሽምግልና አገልግሎት ስጡን የሚለው ጥያቄ መሸፋፈኛ ልብስ እንጂ መልእክቱ ጫና የተቀላቀለ ትእዛዝ እንደ ሆነ በጣም ግልጽ ነበር። የደርግን የትእዛዝ ጫና በደንብ ሲያጠኑት ደግሞ የተመረጡት

ሽማግሌዎች በሕዝባቸው ላይ ያንዣበበውን አደጋ የሚያሳያቸው ስለ ነበረ መሞከር የሚችሉትን ለመሞከር ተመካክረው ሄዱ።

አለቃ አያሌው ታምሩ ወደ ተላኩበት የትውልድ አካባቢያቸው ደርሰው ምክር እንዲለግሱት ለሰተበሰበው ሕዝብ ያደረጉት ንግግር በአጭሩ ሲቀርብ ይህን ይመስል ነበር። «የተወደዳችሁ ወገኖቼ! አገራችሁ ኢትዮጵያ ሀገረ እግዚአብሔር እናንተም ሕዝበ እግዚአብሔር ናችሁ። የራሳችሁን ወግ፥ ባህል፥ ሃይማኖት፥ ሰብአዊ ክብር ለይታችሁ እንደምታውቁ አምናለሁ። አሁን በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት የሕዝቡን ወግ፥ ባህል፥ ሃይማኖት፥ ሰብአዊ ክብር ጠብቆ አስተዳድራለሁ ባይ ነው። ይህን ቃሉን ከጠበቀ መልካም ነው። ከእናንተ የሚያጋጨው ነገር ይኖራል የሚል ግምት የለኝም። መብታችሁን፥ ክብራችሁን፥ ሃይማኖታችሁን ልንካ ካለ ግን ለሃይማኖታችሁ፥ ለክብራችሁ፥ ለመብታችሁ መሟገት እንዳለባችሁ እመክራችኋለሁ፤» የሚል ነበር።

ለዚህ ጉዳይ የተላከው ቡድን አባላት በጎጃም ቆይታቸው ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ሲንቀሳቀሱ እያንዳንዱን እንቅስቃሴያቸውን የሚቆጣጠሩ የደርጉ ሹማምንት ነበሩ። እነዚህ ሹማምንት የቡድኑን አባላት ዕለታዊ እንቅስቃሴ በመወሰን በዚህ ግቡ፥ በዚህ ውጡ እያሉ ይሰጡ የነበረው አመራር በአለቃ አያሌው ታምሩ ዘንድ ተቀባይነት አላገኘም ነበር። በእያንዳንዱ ባለፉበት መንደር ማግኘት የሚፈልጓቸውን የአገርና የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ባሉበት አካባቢ ሲያልፉ ይጓዙበት የነበረውን መኪና የሚነዳውን ሹፌር እዚህ አቁም፥ እዚያ አቁም እያሉ በማዘዝ ከላያቸው ሆነው መንገዳቸውን ከሚቆጣጠሩት ሹማምንት አመራር ውጪ ሲንቀሳቀሱ ሊቃወሟቸው የሞከሩትን ሰዎች፤ በነጻነት የመንቀሳቀስ መብቴን አትንፈጉኝ፤ እዚህ ያመጣችሁኝ ከሕዝቡ ጋር እንድመክር፥ እንድነጋገር እስከ ሆነ ድረስ እናንተ በፈለጋችሁት ሳይሆን እኔ በመረጥኩት መንገድ ነው ማነጋገር ያለብኝ በማለት የወሰዱትን አቋም ዐብሯቸው የተጓዙት የቡድኑ አባላት ዛሬም በመገረም ይስታውሱታል።

አለቃ አያሌው ወደ አዲስ አበባ ከተመለሱ በኋላ በደርግ ጽሕፈት ቤት እንደሚፈለጉ ተነግሯቸው ከቤተ መንግሥት በተላከ መኪና ወደዚያው ተወሰዱ። የደርጉ ሊቀ መንበር ኮሎኔል መንግሥቱ ኀይለ ማርያምና ምክትል ሊቀ መንበር ኮሎኔል አጥናፉ አባተ በአንድ ቢሮ ውስጥ ይጠብቋቸዋል። ኮሎኔል መንግሥቱ ክፉኛ ተቆጥተዋል። በሽጉጣቸው ሰደፍ ጠረጴዛ ይደበድባሉ። ኮሎኔል አጥናፉ ጥያቄ አቀረቡ። «አገር እንዲያረጋጉ ቢላኩ እንዴት ሕዝቡን በእኛ ላይ እንዲነሣ ቀስቅሰው ይመጣሉ?» ብለው ለአለቃ ጥያቄ ያቀርባሉ። አለቃም፤ «እኔ በመጀመሪያም ለእናንተ መልእክት አልመጥንም አትላኩኝ ብዬአለሁ። የለም አይሆንም፤ ሄደህ የሕዝቡን መብት አክብረን እንደምናስተዳድረው አስተማምነህ ንገርልን፤ ከእኛ አንተን ያምናሉ፤ አላችሁኝ። ሄጄም የላካችሁኝን ተናገርኩ። ሌላ ምን አጠፋሁ?» ብለው መልሰው ይጠይቃሉ። ኮሎኔል አጥናፉ ሌላ ጥያቄ አልጨመሩም። የኮሎኔል መንግሥቱ ነበር ተራው። «ዕዉር ገደለ ታሰኘኛለህ እንጂ አንተን እዚህ መግደል ነበር፤» በማለት በገዛ ንዴታቸው ጨሱ። ከዚህ በኋላ ማንም ተጨማሪ ነገር አልተናገረም። ተግሣጹ አለቀ። አለቃም ከነ መሪያቸው እንዲወጡ ተነግሯቸው ወደ ቢሮሯቸው ተመለሱ።

አለቃ አያሌውን ከሸኙ በኋላ ሁለቱ ኮሎኔሎች ደጃች ከበደ ተሰማንና በጊዜው በእስር ቤት ውስጥ የነበሩትን ንቡረ እድ ድሜጥሮስ ገብረ ማርያምን ስለ አለቃ አያሌው ታምሩ አቋምና የኋላ ታሪክ ይጠይቃሉ። ሁለቱም ሰዎች የአለቃ አያሌውን አገር ወዳድነትና የሚናገሩትም ነገር ሁሉ ለአገር ለወገን ይበጃል ብለው ያመኑበትን እንጂ ለተለየ ወገን ወግነው የአንድ ቡድን አቋም ወይም ሐሳብ ለማስፈጸም የሚንቀሳቀሱ አይደሉም ብለው ያስረዷቸዋል። ኮሎኔል መንግሥቱም ከሁለቱ ሰዎች ያገኙትን ምስክርነት ቦታ የሰጡት ይመስላል።

## ለ፤ የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ጉባኤ።

ደርግ በመጀመሪያዎቹ የሥልጣኑ ዘመናት ከፈጸማቸው አስከፊ ሥራዎች አንዱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን የዓላማው ማስፈጸሚያ ለማድረግ የተንቀሳቀሰበት ስልት ነበረ። ከወጠናቸው ስልቶች አንዱ «የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ጉባኤ» የሚባል ጉባኤ ማቋቋምና በጉባኤው ውስጥ የራሱን ዓላማ የሚያራምዱ አባላት በማስገባት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሕጋዊ ፓትርያርክ የነበሩትን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስን ከሥልጣን ማውረድና ለራሱ ፖለቲካ የሚመቸውን ሰው መሾም፥ የቤተ ክርስቲያንን መርኆ ከኮሚዩኒስት መርኆዎች ጋር አንድ እንደ ሆነ የሚያሳይ ዓላማ ማራመድ ይገኝበታል። በጊዜው በተቋቋመው ጉባኤ ውስጥ እንዲሠሩ ከተመረጡት ውስጥ ጨርሶ ለደርጉ ዓላማ የማይመቹ ሰዎች የነበሩ ሲሆን፤ የደርግን ዓላማ በሚያራምዱና በእነሱ መካከል ከፍተኛ የሆነ ልዩነት እየተፈጠረ በመምጣቱ እኒያ የደርጉ መሣሪያ መሆን ያልፈለጉ ሰዎች ለቤተ ክርስቲያን ይጠቅማል ያሉትን በቅን ልብ በማቅረብ፥ ጉዳት ያስከትላል ብለው ያመኑበትንም በግልጽ በመናገራቸው የተነሣ እንደ ጠላት ተፈረጁ። ከነዚህ መካከል ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ በቤታቸው ውስጥ እንዳሉ በጥይት ተደብድበው በአካላቸው ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሲደርስባቸው ዶክተር ሐዲስ የሻነው የተባሉት ለእስር ተዳርገዋል። አለቃ አያሌው ታምሩ ደግሞ ከከፍተኛ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ጋር ከኮሚቴው ታግደዋል።

### ሐ፤ ሐውልቱና የታኅሣሥ ገብርኤል በዓል።

ጊዜው ፲ ፱፻፸፯ ዓመተ ምሕረት የታኅሣሥ ገብርኤል በዓል ነበረ። በዚያ ዓመት በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል አካባቢ የኮሎኔል መንግሥቱ ኀይለ ማርያም ምስል ያለበት ሐውልት ተሠርቶ ቆሞ ነበር። አለቃ አያሌው ታምሩ በብሥራተ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ተገኝተው እንዲያስተምሩ ተጋብዘው ነበርና በዚያ ተገኝተው ነበር። ቅዳሴና የታቦቱ ዑደት ከተፈጸመ በኋላ በቦታው ለተገኘው ብዙ ሕዝብ ትምህርት መስጠት ጀመሩ። ስለ በዓሉ ታላቅነትም አስተማሩ። የበዓሉ ባለ ታሪኮች ሠለስቱ ደቂቅ ንጉሡ ናቡከደነፆር ላሠራው ሐውልት አንሰግድም በማለታቸው የተቀበሉትን መከራና እግዚአብሔርም ቅዱስ ገብርኤልን ልኮ እንዴት ከተጣሉበት እሳት እንዳወጣቸው በማስታወስ ካስተማሩ በኋላ፤ ወደ ሕዝቡ ዕለታዊ ሕይወት በመግባት፤ በጊዜው የነበሩት የአገሪቱ መሪዎች የሐውልት መታሰቢያ ለማቆም የሚያበቃ አንድም የረባ ነገር ሳይሠሩ ምስላቸው ያለበት ሐውልት ማቆማቸው ከናቡከደነፆር ሥራ ጋር የሚመሳሰል መሆኑን፤ ምእመናን ለዚህ ሐውልት ሳይሆን ለአምላካቸው ለእግዚአብሔር ብቻ ክብርን ሊሰጡ እንደሚገባ የሚገልጽ ቅኔ ለበስ ተግሣጽ ይናገራሉ። ትምህርቱን ጨርሰው ወደ ቤታቸው ሲያመሩ ከመንገድ ላይ የሕዝብ ደኅንነት ሰዎች አፍነው ወደ ደኅንነት ቢሮ ይወስዷቸዋል። ያፈኗቸው ሰዎች አለቃ ያደረጉትን ንግግር በመቅረጸ ድምፅ ቀርጸው ይዘው በማስረጃ ለአለቆቻቸው ከሰሷቸው።ጉዳዩ የቀረበላቸው ኃላፊ ግን፤ «እባክዎ አለቃ! መንግሥትን የሚተች ነገር አይናገሩ። በጣም ብዙ ጊዜ እስዎን እንድንከታተል፥ እንድናስወግድ ትእዛዝ ተሰጥቶናል። ግን የቤተ ሰብ ታሪክዎን ስናጠና የብዙ ልጆችና የቤተ ሰብ ኃላፊ ነዎት። ስለዚህ የሚጎዳዎትን ነገር ለማድረግ ተቸግረናል። አሁንም የምንጠይቅዎ እንዲህ ዐይነት ትምህርት ከማስተላለፍ እንዲቆጠቡ ነው፤» በማለት አሰናብተዋቸዋል።

## መ፤ ቀኝ እጃችሁን አንሡ።

ከማእከላዊ ዕድሜ ጀምሮ ወደ ኋላ ያለ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ እንደሚያስታውሰው እግዚአብሔር የለም የሚለው ትምህርት በይፋ በኢትዮጵያ የተነገረበት ዘመን የደርግ ዘመን ነው። ይህ የክሕደት ትምህርት የተነገረው በቤተ መንግሥትና በሕዝባውያን ቦታዎች ብቻ ሳይሆን በቤተ ክህነትም ነበር። ይህ ዘመን በቤተ ክህነቱ የስብከተ ወንጌል አዳራሽ ውስጥ «በስመ ማርክስ ኤንግልስ ወሌኒን ብንል ምናለበት?» ተብሎ እስከ

መነገር የተደረሰበት ከፍተኛ ክሕደት የተፈጸመበት ጊዜ እንደ ነበረ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን በይፋ ሄደው መሳለም የፈሩበት፥ ልጆቻቸውን ክርስትና ማስነሣት ያፈሩበት፥ የእግዚአብሔርን ስም በግልጥ መጥራት የተሰቀቁበት ጊዜ ነበር። በዚህ ጊዜ ነበረ በአንዱ የመስቀል ደመራ በዓል ዕለት አለቃ አያሌው ታምሩ በመስቀል ዐደባባይ ለተሰበሰበው ሕዝብ ትምህርት እንዲሰጡ የተጋበዙት።

የመስቀል ዐደባባይ ብዛት ባለው ሕዝብ ተሞልቷል። ሕዝቡም ሥነ ሥርዓቱን ይከታተላል። መዘምራን በዕለቱ የሚቀርበውን ያሬዳዊ ዜማ አሰሙ። አለቃ አያሌው ደግሞ ትምህርት ሊሰጡ ቀረቡ። ትምህርት በሚሰጡበት ጊዜ የሆነውን ነገር በጊዜውና በቦታው የነበሩት ፕሮፌሰር ነቢያት ተፈሪ እንደሚከተለው አቅርበውታል። «በደርግ ዘመን መስቀል በዓል በሚከበርበት ጊዜ አብዮት ዐደባባይ ይባል ነበረ አሁን እንኳ ለስሙ መስቀል ዐደባባይ ተብሏል ለደመራ ወጥተው በሚያስተምሩበት ጊዜ ኻያና ሠላሳ ሺ ሰው ተሰብስቧል፤ ትዝ ይለኛል ብቻ ባልሳሳት አብዮተኛ ፓርቲዎች ወይንም ድርጅቶች አንድ የሆኑበት አምስት ድርጅቶች አንድ የሆኑበት ጊዜ ነበርና በዚያን ጊዜ ደርግ ሕዝቡን እየሰበሰበ በያደባባዩ መፈክር ያስተምር ነበር። ሁሉም ሰው አብዮታዊት እናት አገር ወይም ሞት! እያለ ግራ እጁን እየወረወረ ሁላችንም እንል ነበር። እሳቸው ስለ መስቀል አስተማሩና ከጨረሱ በኋላ አሁን እንግዲህ ይህንን ከተረዳችሁ አሉና «መስቀል ኃይላችን ነው! መስቀል መድኃኒታችን ነው!» ብለው ቀኝ እጃቸውን አንሥተው ይጮሃሉ። ሕዝቡ ዝም አለ መሰለኝ። ኋላ ሁለተኛ ደገሙት። ሕዝቡ ምን እንደሚፈልጉ ገባው። ከዚያ ሕዝቡ «መስቀል ኃይላችን ነው! መስቀል መድኃኒታችን ነው!» አለና ቀኝ እጁን ወረወረና መፈክር አሰማ። ከዚያ «መስቀል መድኃኒታችን ነው! መስቀል ቤዛችን ነው!» ሲል በቃ አለቀ። ሕዝቡን ሙሉ በሙሉ ቀየሩት። ከዚያ በኋላ ሕዝቡ ተበረታቶ ወደ ቤተ ክርስቲያን ማምራት ጀመረ። እስከዚያ ድረስ ግን የሃይማኖት ጉዳይ ተዳፍኖ ነበር።»

## ሠ፤ የደርግ ውድቀት ዋዜማና ሚያዝያ ጊዮርጊስ።

፲ ፱፻፹፫ ዓመተ ምሕረት ደርግ በሕዝቡ ላይ ሲሠራ የኖረውን ግፍ ሁሉ ዘንግቶ ከመጣበት የውድቀት ጥሪ ለመዳን በከፍተኛ ደረጃ የተፍጨረጨረበት ዓመት ነበር። ቀደም ባሉት ዓመታት ሙልጭ አድርጎ ሲሰድባቸው የነበሩትን ቀደምት የኢትዮጵያ ነገሥታት ይልቁንም እነ ዐፄ ቴዎድሮስን፥ እነ ዐፄ ዮሐንስንና እነ ዐፄ ምኒልክን በተለያዩ የብዙኃን መገናኛዎች እያነሳሣ የሕዝቡን ወኔ መቀስቀሻና የዘመቻ ማዘጋጃ ዘዴ ብሎ ይዞት ነበር። ነጋ ጠባ ስለነዚህ ቀደምት ነገሥታት ጀብዱና አገር ወዳድነት፥ አትንኩኝ ባይነት ብዙ ይባል ብዙም ይጻፍ ነበር።

ሚያዝያ ፳፫ ቀን ፲ ፱፻፹፫ ዓመተ ምሕረት የሰማዕቱ የቅዱስ ጊዮርጊስ በዓል በአራዳ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በሚከበርበት ጊዜ አለቃ አያሌው ታምሩ በቤተ ክርስቲያኑ ተገኝተው እንዲያተምሩ ተጋብዘው ነበር። እሳቸውም ስለ ሰማዕቱ ተጋድሎና በሃይማኖት ስላገኘው የድል አክሊል ዘርዝረው አስተማሩ። «ዛሬ በከፍተኛ የችግር አዘቅት ውስጥ የወደቀችውን አገራችሁን ኢትዮጵያንና ሃይማኖታችሁን ለመታደግ በሃይማኖት ጸንታችሁ መንፈሳዊ ተጋድሎ አድርጉ። የቴዎድሮስ ነኝ፥ የዮሐንስ ነኝ፥ የምኒልክ ነኝ እያሉ ጉራ መንዛት የትም አያደርስም። እነሱ በጊዜያቸው መሥራት ያለባቸውን ሠርተው የማይጠፋ ስም ተክለው ሄደዋል። እናንተም ዛሬ የራሳችሁን ግዴታ መወጣት አለባችሁ። ቤተ መንግሥትና ቤተ ክህነት ተባብረው የካዱትን እግዚአብሔርን፥ በድለውናል፥ ጨቁነውናል ብለው ያንቋሸሿቸውን የነገሥታቱን ስም ዛሬ የጦርነት ዘመቻ ነጋሪት መጎሸሚያ ማድረጋቸው ተገቢ አይደለም። እናንተም እነሱ የሚሉትን ተከትላችሁ ራሳችሁንና ሌላውን ወገናችሁን መጨረሻ ወደ ሌለው እልቂት መክተት የለባችሁም። በአሁኑ ሰዓት ከግራ ከቀኝ የሚጎሰመው የጦር ነጋሪት አገራችንንም ራሳችንንም ወደማያባራ ተጨማሪ መከራ የሚመራ ነው። ንስሐ አልገባችሁም፤ የበደላችሁትን እግዚአብሔርን ይቅርታ አልጠየቃችሁትም። ባለፈው ፲ ፯ ዓመት የተሠራው

በደል በጣም ከፍተኛ ነው። እግዚአብሔር ጨርሶ የለም ተብሎ ተክዷል። መንግሥትም ሕዝብም ተባብረው ካዱት። መንግሥት፤ አሮጌዋ ቤተ ክርስቲያን ትውደም፤ እግዚአብሔር የሚባል አምላክ የለም፤ ብሎ በካድሬዎቹ አማካኝነት ሰበከ። ብዙ ሕዝብም እግዚአብሔርን ክዶ በሶሺያሊዝም ጸበል ተጠመቀ። በለውጥ ስም፤ ልጆች ወላጆቻቸውን፥ ወንድም ወንድሙን ገደለ። እናቶች የልጆቻቸውን እርም በሉ። ብዙ እልቂትም በአገሪቱ በሞላ ተካሄደ። ቤተ ክርስቲያንም በራሷ ካህናት ተዋርዳለች። ካህናት የፖለቲካ ካድሬዎች፥ የአብዮት ጠባቂዎች ሆነው ሠሩ። በእጃቸው የወገኖቻቸውን ደም አፈሰሱ። ደም ባፈሰሱበት እጅ ወደ ቤተ መቅደስ ገብተው የወልደ እግዚአብሔርን ሥጋ ወደሙ አቀረቡበት። ጳጳሳትና መምህራን ሶሺያሊዝምና ክርስትና አንድ ናቸው፤ ማርክስ እንዲህ አለ፥ ሌኒን እንዲህ አለ ብንል ምን አለበት? ይቤ ማቴዎስ፥ ይቤ ማርቆስ እንል የለም ወይ፤ ብለው በእግዚአብሔርና በቤተ ክርስቲያኑ ላይ አፌዙ። ከግፈኞች ጋር በየዐደባባዩ፥ በየፖለቲካ ሸንጎው ተሰልፈው የግፍ ድግስ አድማቂዎች ሆኑ። በቤተ ክህነቱ የስብከተ ወንጌል አዳራሽ ውስጥ፤ «በስመ ማርክስ ኤንግልስ ወሌኒን፤» እየተባለ ፌዝ ተነገረበት። እግዚአብሔር በሆነው ነገር ሁሉ አዘነ። የሕዝቡም፥ የመንግሥትም ልብ ባለ መመለሱ አሁንም ወደ ተከታይ የመከራ አዘቅት እየወረድን እንገኛለን። ስለዚህ እዘኑ፤ ልባችሁን በፍጹም ንስሐና ኀዘን ለእግዚአብሔር ስጡ፤» በማለት አስተማሩ፡፡

## ረ፤ የዐዋጅ ምሕላና በቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን የተሰጠ ትምህርት።

በወታደራዊው መንግሥት የመጨረሻ የሥልጣን ቀናት፤ ሕዝቡ ከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ ወድቆ ነበር። እያንዳንዱ ቀን ሊያስከትል ስለሚችለው ነገር ማንም እርግጠኛ ካለመሆኑ ጋራ አንዱ ካንዱ ይሻላል ብሎ ሊመርጣቸው ከማይችል ሁለት ኀይሎች ጋርም የተፋጠጠበት ወቅት ነበር። በአንድ በኩል፤ አለሁ አልሞትኩም እያለ የሚፈክረው ወታደራዊ መንግሥት፤ በሌላ በኩል ደግሞ ወደ ፊት እየገፋ የነበረው ተቃዋሚ ኀይል አካሄድ ብዙም ግልጽ ስላልነበረ የሕዝቡን ጭንቅ ይበልጥ አባብሶት ነበር።

በዚህ ሰዓት ሕዝቡ በየሃይማኖቱ እየተሰበሰበ የምሕላ ጸሎት ጀመረ። በየአብያተ ክርስቲያን ሕዝብ እየተሰበሰበ አለቀሰ፤ ተከዘ፤ እግዚአብሔርን ይቅርታ ጠየቀ። ያንዣበበው የእልቂት ደመና እንዲገፈፍም ተማጸነ። በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክስርቲያን ታላቅ የምሕላ ጸሎት እንዲደረግ በይፋ ተነገረና በዕለቱ ብዙ ሕዝብና የቤተ ክህነት ባለ ሥልጣኖች ተገኙ።

በዚሁ ዕለት አለቃ አያሌው ታምሩ በቦታው ተገኝተው እንዲያስተምሩ ተጋበዙ። ያስተማሩት ትምህርትም በአጭሩ ይህን ይመስል ነበር። «በሕዝብና በአገር ላይ ያንዣበበው የጥፋት ደመና ይገፈፍ ዘንድ ሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር እያቀረበ ያለው እግዚኦታ አስፈላጊና ተገቢም ነው። ግን በተለይ የዛሬውን የጸሎት መርኀ ግብር ያስያዙ ባለ ሥልጣናት የት አሉ? ዛሬ እንደ ነነዌ ሰዎች ነው በእግዚአብሔር ፊት መውደቅ የሚገባን። ምክንያቱም የመጣው ፍርድ፥ አበሳና ውድቀት ማንንም ከማን ሳይለይ የሚያንገላታ በመሆኑ ነው። በአገራችን በጎ ነገር ይሆን ዘንድ ከዋናው መሪ እስከ ዝቅተኛ ኑሮ ድረስ ያለው ሕዝብ ከልባዊ ጾምና ጸሎት ጋር በእግዚአብሔር ፊት ሊወድቅ ይገባል። አለዚያ ግን ዛሬም ቢሆን ለኢትዮጵያ የተመቸ ነገር አይገኝም፤» በማለት ዛሬ ላይ ሆነው ሲያስቡት ብዙዎች እንደ ትንቢት የሚቆጥሩትን ትምህርት ሰጥተዋል፡፡

ማንም ሰው ምንም ነገር ደፍሮ በማይናገርበት በዚያ የአፈና ዘመን በተለያዩ መድረኮች ላይ በአለቃ አያሌው ታምሩ የተላለፉ ትምህርቶችን ስንመለከት፤ ቆራጥነታቸውን፥ አገርና ወገን ወዳድነታቸውን፥ እንዲሁም ለሃይማኖታቸውና ለሰብአዊ ክብር ቀናዒ እንደ ነበሩ በግልጽ መገንዘብ እንችላለን።

## ፫ኛ፤ የኢሕአዴግ ዘመን።

ይህ ዘመን ገና ከጅምሩ ለአለቃ አያሌው ታምሩ እጅግ አስቸጋሪና አስጨናቂ ነበር። ሃይማኖትን፥ አገርንና ታሪክን በተመለከተ ይሰነዘሩ የነበሩ ጥንቃቄ የጎደላቸው ትችቶች ሕዝብን፥ አገርንና መንግሥትን ይጎዳሉ የሚል ጥብቅ እምነት ነበራቸው።

ታላቁ አባት ዕዝራ ስለ ኢየሩሳሌም እንዲህ እያለ ይጨነቅ ነበር። «አገራችን ኢየሩሳሌም በጠፋች በሠላሳ ዘመን ዕዝራ እባል የነበርኩ እኔ ሱቱኤል በባቢሎን ነበርኩ። በመኝታዬም እኔ ተኝቼ ነበር፤ ፊቴ ግን ተገልጦ ነበር። የኢየሩሳሌምን ጥፋቷን አይቼአለሁና፤ በባቢሎን የሚኖሩ ሰዎችን ተድላ ደስታም።» (ዕዝ፤ ሱቱ፤ ፩፥ ፬።) ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊትም፤ «ኢየሩሳሌም ሆይ! ብረሳሽ ቀኜ ትርሳኝ፤ ባላስብሽ ምላሴ በጕሮሮዬ ይጣበቅ፤ ከደስታዬ ሁሉ በላይ ኢየሩሳሌምን ባልወድ፤» (መዝ፤ ፻፴፮፥ ፭ እና ፮።) እያለ ስለ ኢየሩሳሌም ይጨነቅ ነበር። አለቃ አያሌው ታምሩም ለአገራቸው፥ ለወገናቸውና ለቤተ ክርስቲያን ከነበራቸው ፍቅር የተነሣ አብዝተው ያዝኑና ይጨነቁም ነበር። ይህም በእሳቸው ዕድሜ፥ ዕውቀትና የኃላፊነት ደረጃ ከነበሩ የአገር ሽማግሌዎች የሚጠበቅ ነበር።

ከዚህም በመነሣት በቀደሙት መንግሥታት ዘመን እንዳደረጉት ሁሉ ለሕዝብ፥ ለአገር፥ ለመንግሥት ይበጃል ብለው ያመኑበትን ሳይፈሩና ሳያፍሩ በግልጥ ተናግረዋል። «ይህ ትውልድ አባቶቹን ማወቅ አለበት። ታሪኩን ማወቅና አባቶቹ ያወረሱትን አገርም በአንድነቱ መጠበቅ አለበት። ከኖኅ ዘመን ጀምሮ የነጻነቱና ከእግዚአብሔር አምላክ ጋር የተጋባው ቃል ኪዳን ምልክት የሆነችውን ሰንደቅ ዓላማውንም ማክበር ይገባዋል፤» በማለት ደጋግመው አስተምረዋል።

## ሀ፤ ኅዳር ቁስቋምና ለትግራይ ተወላጆች የቀረበ መንፈሳዊ ጥሪ።

ቀኑ ኅዳር ፮ ቀን ፲ ፱፻፹፫ ዓመተ ምሕረት ነበር። በአዲስ አበባ ከተማ ሰሜን አቅጣጫ በምትገኘው በመንበረ መንግሥት ቁስቋም ቤተ ክርስቲያን ብዙ ሕዝበ ክርስቲያን ተሰብስቧል። ምክንያቱ በዓለ ቁስቋምንና የጾመ ጽጌን ፍቺ በዓል ለማክበር ነበረ። የዕለቱ አስተማሪ አለቃ አያሌው ታምሩ ነበሩ። አለቃ «በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ» ብለው ጀመሩ። በትምህርታቸውም ስለ እመቤታችን ስደት፥ ስለ ቁስቋም ታሪክ፥ ወደ ኢየሩሳሌም ስለ መመለሷ፥ ከእመቤታችን ስደት ፫፻ ዓመት በኋላ በግብጽ ስለ ተሠራው የመታሰቢያ ቤተ ክርስቲያን፥ በዚህ በዓል ምክንያት ኢትዮጵያውያን ነገሥታትና ንግሥታት ስላደረጓቸው መንፈሳዊ ተሳትፎዎች፥ ስመ ጥሩዋ ኢትዮጵያዊት ንግሥት እቴጌ ምንትዋብ በጎንደር ስላሠሯት የደብረ ቁስቋም ቤተ ክርስቲያን፥ ስለ ጾመ ጽጌ፥ ስለ ማኅሌተ ጽጌ በዝርዝር አስተማሩ።

ከዚያም በመቀጠል፤ በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያምና በልጇ ስደት በረከትን ካገኙ የኢትዮጵያ አውራጃዎች አንዱ የሆነው ምድረ ትግራይ ከሌሎች ቅዱሳን የኢትዮጵያ መካናት ጋር የተጣመረ የታሪክ ተዘምዶ ያለው ከመሆኑ ባሻገር ከታቦተ ጽዮን ጀምሮ ለኢትዮጵያ ለተሰጡ ልዩ ልዩ ሥጋዊና መንፈሳዊ በረከቶች ምንጭና ቦይ ሆኖ የኖረ ነው። አሁን በደረስንበት ወቅትም ሥጋዊና መንፈሳዊ ሥልጣን በሙሉ ለትግራይ ሕዝብ ተሰጥቷል። ይህ ታላቅ ሕዝብ የተሰጠውን መንፈሳዊና ሥጋዊ ሥልጣን አገሪቱንና ቤተ ክርስቲያንን ከውድቀት ለማንሣት ሊሠራበት ይገባል። ይህ ሳይሆን ቀርቶ ሕዝብና እግዚአብሔርን የሚያሳዝን ሥራ ቢሠራ ግን ትዝብትንና የታሪክ ተወቃሽነትን ያተርፋል፤ የሚል ሐሳብ ያለው ሰፊ ትምህርት ሰጥተዋል።

ይህን መልእክታቸውን የሚያጠናክርና ሰፋ ያለ ግንዛቤን ለምእመናን ሊያስጨብጥ የሚችል መልእክትም «ማዕበል» በተባለ ጋዜጣ ላይ በኅዳር ፯ ቀን ፲ ፱፻፹፯ ዓመተ ምሕረት አስተላልፈዋል። በዚሁ ጋዜጣ ላይ፤ «በልዩ ልዩ ጊዜ ልዩ ልዩ ሐሳቦችን በመቈርቈር በቅንነት አቅርቤአለሁ። ተንኰለኞች ግን ቀናውን እያጣመሙ ብዙ አሉባልታ መንዛታቸውን ዐውቃለሁ። እኔ ግን ከእውነት በስተቀር በዚህ ታላቅ ሕዝብ ላይ መጥፎ አስተሳሰብ እንደ ሌለኝ አምላኬ ያውቃል። ለፍርሀት ምክንያት ከሆኑኝ ነገሮች ግን ብዙዎቹ ተፈጽመዋል። የሥጋዊውን መሥመር ብተወው እንኳ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ አቡነ ጳውሎስ ከነ አክሊላቸው፥ ከነ ልብሰ ተክህኗቸው ለሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የጌታ አዳር መግባታቸው፥ በተራ ምእመን ደረጃም ከፓፓው ቡራኬ መቀበላቸው፥ የክሕደትና የኑፋቄ መጽሐፍ ማሳተማቸውና መበተናቸው፥ አርቶዶክሳዊውን የሊቃውንት ጉባኤ ማፍረሳቸው፥ ተጠሪ የሆኑለትን ሲኖዶስ መሻራቸው፥ በኢየሱስ ክርስቶስና በመንፈስ ቅዱስ ፈንታ ራሳቸውን የቤተ ክርስቲያን አመራር ሰጪ አድርገው መሠየማቸው፥ ሲኖዶሱን የግል ተጠሪያቸው ማድረጋቸው፥ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ልዕልና፥ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትን እውነትነት፥ የአኵስምንና የታላቁን የትግሬ ክርስቲያን ሕዝብም ታላቅነት የሚፈታተንና ትዝብት ላይ የሚጥል ነው፤» በማለት የተሰማቸውን ስጋት ገልጠዋል።

## ለ፤ በአሁኑ ወቅት ባለው የቤተ ክርስቲያን አመራር ላይ የነበራቸው ተቃውሞ።

የወቅቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ አባ ጳውሎስ ሐምሌ ፭ ቀን ፲ ፱፻፹፬ ዓመተ ምሕረት በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በተካሄደ ሥነ ሥርዓት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፭ኛ ፓትርያርክ ተብለው ተሾሙ።

በ፲ ፱፻፹፭ ዓመተ ምሕረት ፓትርያርኩ ወደ ሮም ሄደው ባደረጉት ጉብኝትና በተሳተፉባቸው አንዳንድ ሥነ ሥርዐቶች የተነሣ ቅር የተሰኙት የቤተ ክርስቲያኒቱ የሊቃውንት ጉባኤ ዋና ሰብሳቢ አለቃ አያሌው ታምሩ፤ «ለአንድ ሺ ፭፻ ዓመት በውግዘት ከተለያየናቸው ክፍሎች ጋራ እንዴት እንዲህ ያለ ሥራ ሊሠሩ ቻሉ? የቀደሙ አባቶቻችንን ግዝት፥ የቤተ ክርስቲያኒቱን ሥርዓት ሊጠብቁ፥ ሊያስጠብቁ በክርስቶስ ሥጋና ደም ምለው የለም ወይ?» ብለው ጠየቁ። ይህ ጥያቄያቸው በኃላፊነታቸውና በሙያ ግዴታቸው አንጻር እንደ ተነሣ ጥያቄና ተቃውሞ ሳይሆን እንደ ድፍረት ተቆጠረባቸው።

ክቡር አባታችን አለቃ አያሌው ግን፤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሮም ጥገኛ መሆን የለባትም፥ ፓትርያርኩ መሓላቸውን አፍርሰዋል፥ ጉዳዩንም ቅዱስ ሲኖዶስ ሊያየው ይገባል በሚለው አቋማቸው ጸኑ። በይበልጥ ደግሞ ሐምሌ ፭ ቀን ፲ ፱፻፹፭ ዓመተ ምሕረት ያዩት ራእይ ያነሡትን ጥያቄ በቆራጥነት እንዲገፉበት ምክንያት ሆነ። ይህንንም ራሳቸው በአንደበታቸው እንደሚከተለው ገልጸውታል። «ዛሬ ካለው የቤተ ክርስቲያን አመራር ጋራ ወደ ትግል ሰልፍ እንድገባ ያደረገኝ የኔ ፈቃድ፥ ዐቅምም አይደለም። በ፲ ፱፻፹፭ ዓመተ ምሕረት ሐምሌ ፭ ቀን ኦፕራሲዮን ሆኜ በሰመመን ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ በሥርዓተ ሙታን ወደ አምላኬ ፊት ቀርቤ የተሰጠኝ ትእዛዝ ነው። በዚያች ሰዓት፤ ከቅዱስ ማርቆስ እስከ ሳድሳዊ ቄርሎስ የነበሩ የእስክንድርያ ፓትርያርኮችና ሊቃነ ጳጳሳት፥ ከአትናቴዎስ፥ ከሰላማ እስከ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የነበሩ የኢትዮጵያ ሊቃነ ጳጳሳትና ፓትርያርኮች የእሳት ነበልባል በከበበው፥ የእሳት ልሳን ያለው መጋረጃ በተንጣለለበት በዚያ አዳራሽ፥ በዚያ የግርማ ዙፋን ግራና ቀኝ ተሰልፈው ቁመው ነበር። በኤፌሶን ጉባኤ ንስጥሮስን ያወገዘው የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ቄርሎስ በመንበሩ ፊት ለፊት ቆሟል።

ቀድሞ የተወገዘው ንስጥሮስ የማዕረግ ልብሱን ተገፎ በስተጀርባው ቆሟል። አባ ጳውሎስ በማዕረጋቸው እንዳሉ ተከስሰው ከንስጥሮስ ጎን ቁመዋል። በዐጸደ ነፍስ የሚገኙት የእስክንድርያና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አበው፤ አባ ጳውሎስ ሺ ስድስት መቶ ዓመት የኖረ ውግዘት ጥሰው፥ በሥጋው በደሙ የማሉትን መሓላ አፍርሰው የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን የሮም ቅኝ ግዛት ስላደረጉ፤ ፍርድ ይሰጥልን ሲሉ ለኀያሉ አምላክ አቤቱታ አቀረቡ። ከዙፋኑ የመጣው መልስ ግን፤ እስከ ዕለተ ምጽአት ፍርድ የቤተ ክርስቲያን ነው፤ የሚል ነበረ። ይህ ሁሉ በሚከናወንበት ጊዜ የማላውቀው ኀይል ከዚህ ዓለም ነጥቆ ከቅዱስ ቄርሎስ ጎን አሰልፎኝ ከቆየ በኋላ ከዙፋኑ የመጣው ድምፅ፤ አንተ ያየኸውን፥ የሰማኸውን ለቤተ ክርስቲያን፥ ለምእመናን ንገር፤ ሲል አዝዞ ወደ ነበርኩበት መለሰኝ። ይህ ትእዛዝ ነው እዚህ ሰልፍ ውስጥ ያስገባኝ። ኢትዮጵያዊ፥ ኦርቶዶክሳዊ የሆነ ሁሉም ስለ ቤተ ክርስቲያኑ አጥብቆ መታገል አለበት።»

**በራእይ የተሰጣቸውን መልእክትም መጀመሪያ ለፓትርያርኩ ቀጥሎም ለቅዱስ ሲኖዶስ ቢያቀርቡም ጉዳዩ በመታፈኑ ለእያንዳንዱ ጳጳስ በግል ደብዳቤ ለማሳወቅ ተገደዱ። ኅዳር ፳፫ ቀን ፲ ፱፻፹፯ ዓ፤ ም፤ ለቅዱስ ሲኖዶስ የላኩት ደብዳቤ ሙሉ ቃል የሚከተለው ነበር።**

«ጥቅምት ፲ ፯ ቀን ፲ ፱፻፹፯ ዓመተ ምሕረት ስለ ቤተ ክርስቲያናችን ያለውን ጠቅላላ ሁኔታ በመግለጥ ቅዱስ ሲኖዶስ እርምጃ ወስዶ ቤተ ክርስቲያንን ከውድቀት እንዲያድን፤ ይህን ሳያደርግ ግን ወደ ሌላ ሥራ እንዳይገባ ሲኖዶሱን በሾመና በሚመራ በመንፈስ ቅዱስ ዳኝነት ተማጽኜ የጻፍኩትን ማመልከቻ ለሲኖዶሱ ጽሕፈት ቤት አቅርቤ ነበረ። እስከ አሁን ለሲኖዶሱ አለመቅረቡንና ሲኖዶሱም ያልተወያየበት መሆኑን ስለ ተረዳሁ እንደገና ቅጂውን አንዳንድ የቀሩ ቃላትንም በማስተካከል በፖስታ ቤት በኩል ልኬዋለሁ። የሲኖዶሱ ብፁዓን አባሎች እንደምታውቁት እኔ አንድ ተራ ድኻና ደካማ ሰው ነኝ። ግን ያለሁበት የሥራ ወንበር በታሪክ ፊት ተጠያቂነት ያለው ነው። ለዚህ ነው መላልሼ ለማመልከት የተገደድኩት፡፡

ብንወድም ባንወድም በአሁን ጊዜ ያለነውን የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ታሪክ ተጠያቂ አድርጎናል። በእግዚአብሔር ፊትም መጠየቅ ይጠብቀናል። ቤተ ክርስቲያንና ኢትዮጵያ በሕግ አንድ ሆነው ከመኖር ከተለያዩበት ከ፲ ፱፻፷፯ ዓ፤ ም፤ ጀምሮ እስከ ዛሬ ኢትዮጵያ ከውድቀት ወደ ውድቀት በመሄድ ላይ ስትሆን ድንበሯን፥ ሰንደቅ ዓላማዋን፥ ሃይማኖቷን፥ አገርነቷን፥ ሕዝቧን እያጣች ነው። ቤተ ክርስቲያንም ስሟን፥ ክብሯን፥ ታሪኳን፥ ሃይማኖቷን፥ ሀገረ ስብከቷን፥ ጽዮንንና መመኪያዋን የክርስቶስን መስቀል እያጣች ነው።

ጠላቶቿና የአገሯ ጥንተ ጠላቶች እየተተከሉ አገሯና እሷ ግን ከህልውናቸው እየተነቀሉ ናቸው። እግዚአብሔር መንፈሳውያን ሰዎቹን፤ «ክላህ በኃይልከ ወአንሥእ ቃልከ ወኢትምሓክ።» «በኃይል ጩኽ፤ ድምፅህን አሰማ፤ ይሉኛል አትበል፤» እያለ ሲቀሰቅሳቸው መኖሩ ይታወቃል።

በዚህ ምክንያት ነቢያትና ሐዋርያት ተከታዮቻቸውም በሰው ፊት በዓለም እየተናቁና እየተጠሉ ፍቅሩንና ዐደራውን ሲመሰክሩ ኖረዋል። ዛሬም ያለነው የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ይበልጡንም በከፍተኛ አመራር ላይ ያሉ አባቶች ስለ ኢትዮጵያ፥ ስለ ትውልዷ፥ ስለ ቤተ ክርስቲያኗ፥ ስለ ሃይማኖቷ፥ ስለ ታሪኳ ተጠያቂዎች ናቸው። ተጠያቂዎች ነን። ሌላ ማድረግ ባይቻል እንኳ ድምፅን ማሰማት ከቤተ ክርስቲያን በኩል የሰውም የእግዚአብሔርም ግዴታ ነው።

ስለዚህ እላይ እንደ ጠቀስኩት በዚህ ደብዳቤ አማካይነት የፊተኛውን ቅጂ እንደገና አቅርቤአለሁ። ከዚህ በፊት ሲኖዶሱ ተወያይቶበት በቤቱ ውስጥ በሚሰጠው ውሳኔ ይፈጸማል በማለት ወደ ውጪ አላሰማሁም። አሁን ግን በዚህ በኩል ፍሬ ማግኘት ካልተቻለ ጉዳዩን ክርስቲያኑ ሕዝብ እንዲያውቀው ለማድረግ የወሰንኩ መሆኔን በፍጹም ትሕትና ስገልጽ አሁንም ሲኖዶሱ የቤተ ክርስቲያንን ጉዳይ በቸልታ እንዳያልፈው ሞቷም

የእናት ሞት ነውና ችላ እንዳይለው በድጋሚ ሲኖዶሱን በሾመና በሚመራ በመንፈስ ቅዱስ ዳኝነት ተማጽኜአለሁ።»

**ክቡር አባታችን አለቃ አያሌው ታምሩ ጥቅምት ፲ ፯ ቀን ፲ ፱፻፺፯ ዓ፤ ም፤ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስና ቅዱስ ፓትርያርክ የጻፉት ደብዳቤ ሙሉ ቃል የሚከተለው ነበር።**

«ይህን ምድራዊና ሰማያዊ ፥ ሥጋዊና መንፈሳዊ ሕይወትን የሚዳስስ ፤ በዐጸደ ሥጋ ፥ በዐጸደ ነፍስ ያሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አበውና ልጆቻቸው የተባበሩበትን አቤቱታ ሳቀርብ ከባድ ኀዘን እየተሰማኝ ነው ።

ቅዱስ ፓትርያርክ!

ቅዱሳን አባሎች!

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ክብር ፥ ባህል ፥ እምነት ፥ ሥርዓት ፥ መንግሥትና ቋንቋ ያቋቋመች የማትናወጥ ከመሆኗ ጋር ከሔኖክ ፥ ከኖኅ ፥ ከመልከ ጼዴቅ ፥ ከነቢያትና ከሐዋርያት የተላለፈውን ትምህርት ፥ ሥርዓት ፣ እምነት ከትውልድ ወደ ትውልድ ስታስተላልፍ የኖረች ፥ በማስተላለፍ ላይ ያለች ፍኖተ ሕይወት መሆኗ የተረጋገጠ ነው ።

ቅዱሳን አበውን ፥ ኀያላን ነገሥታትን ፥ ልዑላን መሳፍንትን ፥ ክቡራን መኳንንትን ፥ ዐይናሞች ሊቃውንትን በሥጋ በነፍስ ወልዳ ያሳደገች የሌላ የማትፈልግ የራሷንም የማትለቅ ዕጥፍ እናት ፥ ስንዱ እመቤት ናት ።

በቅዱስ መጽሐፍ ስለ ቅድስናዋ እግዚአብሔር ደጋግሞ የመሰከረላት አገራችን ኢትዮጵያም ቅድስት ክብርት አገር ናት ። ሰይጣን በእባብ አድሮ አዳምንና ሔዋንን እንደ ተዋጋቸው ሁሉ በልዩ ልዩ ሥጋውያንና መንፈሳውያን የውጭ ጠላቶች ዐድሮ ኢትዮጵያን ሲዋጋ ኖሯል ። ዛሬም በመዋጋት ላይ ነው ። ነገር ግን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትጥቋን አጥብቃ ከቆመች ሳታርፍ ፥ ከዘረጋች ሳታጥፍ በኖረችበት ዘመን ሁሉ ኢትዮጵያ ሳትደፈር ኖራለች ። በ፲ኛው መቶ ዓመት የጉዲት ወረራ ፥ በ፲ ፮ኛው መቶ ዓመት የግራኝ ወረራ ፥ በ፲ ፯ኛው ፥ በ፲ ፰ኛው ፥ በ፲ ፱ኛውና በ፳ኛው መቶ ዓመት ተደጋግሞ የደረሰው የካቶሊክ ፥ የፕሮቴስታንት ፥ የቱርክና የግብጽ እስላማዊ ወረራ ተደጋግሞ

የከሸፈው ባልተበረዘውና ባልተከለሰው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የእምነት ኀይል ነው ። የአምስቱ ዓመት የፋሺስት ወረራም ጉዳት ማድረሱ የታወቀ ቢሆንም ከሥሩ የተነቀለው ÷ ቋጥቋጦው የተመከመከው ÷ እንደ አንበጣ በዝቶ የመጣው የፋሺስት ሠራዊትም የውሃ ሽታ ሆኖ የቀረው በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የእምነት ኀይልና በልጆቿ ደም ነው ።

ዛሬ ሁሉ ባላገር ነኝ በማለት ለአገሪቱ ባለ ውለታ መስሎ ይታይ እንጂ ለ፲ ሺ ዓመታት ለኢትዮጵያ ቆማ የኖረች የሰላም ፋና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ናት ። ታሪክን መለስ ብለን ስንመለከት ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ሌላ ሃይማኖት ÷ ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሌላ የሃይማኖት ክፍል ለመሻት ÷ ለመጠጋት ነገሥታቱ ወይም ሕዝቡ በሞከሩበት ጊዜ ሁሉ የእግዚአብሔር ቁጣና ቅጣት አለ ። ሲመለሱ ይመለሳል ። ይህም ዝንባሌ ከሥጋዊ ወገን እንጂ ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አበው በኩል የታየበት ጊዜ የለም ።

የነቢያት ÷ የሐዋርያት እምነት ከተሰበከበት ጊዜ ጀምሮ በሐዋርያት ዘመንም ሆነ በተከታታዩ ዘመን በውጩ የታየውና የተነገረው የመናፍቃን ትምህርትና ግብር በኢትዮጵያ የታየበት ጊዜ የለም ። ይልቁንም በ፬፻፶፩ ዓመተ ምሕረት በኬልቄዶን በተደረገው ጉባኤ ምክንያት በውግዘት መለያየት ከተደረገ ወዲህ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከሮምና ከቁስጥንጥንያ ጋር ምንም ዐይነት ግንኙነት ሳታደርግ እስከ ፳ኛው ክፍለ ዘመን ኖሯለች ።

በዚህ ዘመን ሁሉ የአበው ሥርዓት ሳይፈርስ ÷ ሕጉም ውግዘቱም ሳይጣስ ተጠብቆ ኖሮአል ። ልዩ ልዩ የሃይማኖት ተከታዮች የመንግሥት መልእክተኞች እየሆኑ ጠብ እየቀሰቀሱ ÷ ጦርነት እያስነሡ ቢፈታተኗትም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አበው ግን በመስቀልና በሰንደቅ ዓላማቸው ሥር ሆነው ደማቸውን ሲያፈሱ ኖሩ እንጂ የመላላት ግንባር አላሳዩም ። ከዚህም የተነሣ በ፲ ፱፻፳፲ ዓመተ ምሕረት የዘመተው የፋሺስት ሠራዊት ኢትዮጵያን ሲወጋ ስንቅና ትጥቁን አዘጋጅታ ባርካ ያዘመተችው የልዮን መንበር ስትሆን በዚህም ጦርነት ሁለቱ ታላላቅ አባቶች አቡነ ጴጥሮስና አቡነ ሚካኤል ሰማዕትነትን ሲቀበሉ ÷ በደብረ

ኢባኖስ ÷ በዝቋላ ÷ በዱማ ÷ በዋሸራና በሌሎችም አብያተ ክርስቲያን ብዙ ካህናትና ምእመናን መሥዋዕት ሆነዋል ። ይህም በጦር ሜዳና አምስት ዓመት ሙሉ በየጫካው ከተደረገው ጦርነት ሌላ ነው ።

ከብዙ መሥዋዕትነት በኋላ ጠላት ድል ሆኖ ኢትዮጵያ እንደገና ስትቋቋም በኢትዮጵያ ድሮ ያልነበረ አዲስ ነገር ተፈጠረ ። የሥጋውያኑ ብቻ ሳይሆን የመንፈሳውያኑም አስተያየት እግዚአብሔርን የተወ ÷ ወደ ጠላቶቹና ወደ አገሯቸው ጠላቶች ÷ ወደ ቤተ ክርስቲያንና ወደ ሩሳቸው ጠላቶች ያዘነበለ ሆነ ። በዚህም ምክንያት ፤ «ሃይማኖት የግል ነው ፤ አገር የጋራ ነው ፤ » የሚል ዐዋጅ ታውጆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ÷ በሀገረ ስብከቷም ላይ የካቶሊክ ÷ የፕሮቴስታንት ÷ የእስላም መንበር ተቋቋመ ። ነጻ ሀገረ ስብከትም ተሰጠ ። የቤተ ክርስቲያኒቱ አባቶችና ካህናትም ሳይከላከሉ ቀሩ ።

ስለዚህም እግዚአብሔር ከሠላሳ ዓመት ትዕግሥት በኋላ በኢትዮጵያና በሕዝቧ ላይ ከባድ ፍርድ ፈረደ ። ዐሥራ ሰባት ዓመትም ያያቹሁት የምታውቁት ልዘረዝረው የማልችለው ብዙ ግፍ ተፈጸመ ። አገሪቱ ወደቀች ፤ ተናደች ፤ ፈረሰች ። አሁን ኻያ አንድ ዓመቷ ነው ። ሕዝቡ በሥቃይ ውስጥ ሆኖ አቤት አቤት ቢልም ከቤተ ክርስቲያን በኩሉ የጸጸት ምልክት አልታየም ። እንዲያውም ፤

፩ኛ ፤ ሁለተኛው ፓትርያርክ በውጭ ጠላቶች ቀስቃሽነት ÷ በቤተ ክርስቲያን አንዳንድ አባሎች ተባባሪነት ከመንበር ወርደው ተገደሉ ።

፪ኛ ፤ በመሐመድ ጋዳፊና በሊብያ ጉባኤ ድጋፍ «ሃይማኖት አይለያየንም» የሚል ቤተ ክርስቲያንን ከጉልላቷ ከመስቀል ላይኛ ባዶ ሩስ አድርጎ ከእስላም መስጊድ አገናኝቶ የተሣለ ምልክት ያለበት ወንጌልን የሚነቅፍና ቁርኣንን የሚያቅፍ መጽሐፍ በቤተ ክርስቲያን ታትሞ ተበተነ ፡ ፡

፫ኛ ፤ የኮሚኒስት ማኒፌስቶ ለመጀመሪያ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ማተሚያ ቤት ታትሞ የተበተነ ሲሆን በዚሁ መሠረትነት የቤተ ክርስቲያን ስብከት ፤ ወንጌልና

ሶሺያሊዝም አንድ ነው ፤ የኮሚኒስት ሥርዐት የሐዋርያት ሥርዐት ነው በሚል መሠመር ተስፋፋ ።

፬ኛ ፤ በ፲ ፱፻፸ ዓመተ ምሕረት መጨረሻ ላይ ፤ «ከአገር ወዲያ ሃይማኖት የለም ፤» በሚል አርእስትና ፤ «ብቸኛው ፓትርያርክ ፤» በሚል አርእስት ከኢትዮጵያ በአብዮቱ የተጠመቁ ጳጳሳት ያስፈልጓታል የሚል አስተያየት የያዘ «ዜና ቤተ ክርስቲያን» በተከታታይ ከታተመ በኋላ ፤ ጥቅምት ፲ ፬ ቀን ፲ ፱፻፸፮ ዓመተ ምሕረት የአዲስ አበባ አድባራትና ገዳማት አስተዳዳሪዎች ÷ ቀሳውስትና ዲያቆናት ÷ መዘምራንና ማኅበረ ምእመናን ÷ በጊዜው የነበሩት ሦስተኛው ፓትርያርክ በተገኙበት ፤ «አሮጌዪቱ ቤተ ክርስቲያን ትውደም! አሮጌው ሲኖዶስ ይውደም! ሲኖዶስ ቅዱስ አይባልም!» የሚል መፈክር በስብከተ ወንጌል አዳራሽ ከተሰማ በኋላ የፌተኞቹ አበው ጳጳሳት በጡረታ ተገልለው የነበረው ሲኖዶስ ፈረሰ ። ጥር ፲ ፫ ቀን ፲ ፱፻፸፫ ዓመተ ምሕረት አዲስ ሲኖዶስ ተመሠረተ ።

፫ኛ ፤ ቤተ ክርስቲያኒቱ ለኮሚኒስት ሥርዐት የጀርባ አጥንት ሆና ከመገኘቷ የተነሣ እንኳን መዘምራኑ ÷ ዲያቆናቱ ÷ ቀሳውስቱና መነኮሳቱ ሳይቀሩ የቀበሌ ሊቃነ መናብርት ÷ የአብዮት ጥበቃ ሠራዊት ÷ የሸንጎ አባል በመሆን የክርስቶስንና የሰውን ደም አንድ ላይ ሲቀዱ ኖረዋል ። በጠቅላይ ቤተ ክህነት የኮሚኒስቶቹ ድርጅት ተቋቁሞ ሲያራምደው የኖረው ሥርዐት በአቶ መኰንን ታደሰ የመኢሠማ ሊቀ መንበርነት በ፲ ፱፻፸ ዓመተ ምሕረት በኮሚኒስት ሰንደቅ ዓላማ የቤተ ክህነትን ግቢ አስጊጦ ደም ለማፍሰስ ተዘጋጅቶበት የነበረውን የዐመፃ ዝግጅት እግዚአብሔር ባያበርደው ኖሮ ውጤቱ አሳዛኝ በሆነ ነበር ። ነገር ግን ያን ኀይል እግዚአብሔር ባወቀ ስለ ሻረው ብዙዎች ቢጨፈጨፉም ሥር ሳይሰድ ተነቅሎ ቀርቷል ። ለዚያ የዐመፅ መንግሥት የቤተ ክርስቲያን አባሎች ባደረጉት ድጋፍ የሃይማኖት እኩልነትን ከመደገፋቸውም በላይ መስቀል ለጨረታ ቀርቧል በእናት አገር ጥሪ ምክንያት ጾም ተሽሮ ሥጋ እንዲበላ ሲደረግ የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎችም እየባረኩ አብልተዋል ። ««በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ» በማለት ፈንታ «በስመ ሌኒን ወማርክስ ወኤንግልስ» ብለን

ምናለበት? ይቤ ማቴዎስ ፥ ይቤ ማርቆስ የሚባል ከሆነ ይቤ ሔኖክ ፥ ይቤ ማርክስ ፥ ይቤ ኤንግልስ ብንል ምናለበት ፤» የሚል ተነግሯል ፡ ፡

፺፭ ፤ በከፍተኛ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት ሳይቀር የኮሚኒስት ዶብተር የተያዘበት ጊዜም ነበር ። በተደጋገመ ጊዜ ከልዩ ልዩ ሃይማኖት ክፍሎች ጋር በአፍሪቃ አዲስ ኮሚኒስት ሳይቀር የአንድነት ስብሰባ ተደርጓል ። በዚህም ጊዜ ሁሉ ከቤተ ክርስቲያኒቱ መልእክተኞች ለሌሎች «ወንድሞቻችን» የሚል ቃል ሲቀርብ ከሌሎች ግን መልስ አልነበረም ።

፺፯ ፤ ኢትዮጵያ ጠብቃው የኖረችው ትምህርተ ሃይማኖት በአበው ተጠብቆ የኖረውን ያህል ፤ ቃሉ ተለውጦ ፥ እምነቱ ተናውጦ ፥ መሠረቱ ፈርሶ በኑፋቄ ጠባይ ተዘጋጅቶ የቀረበው መጽሐፍ ቅዱስ «በሲኖዶስ ታይቶ ተመርምሮ ተፈቅዷል» የሚል መግለጫ ይዞ ስለ ወጣ ምእመናን በታላቅ ችግር ላይ ይገኛሉ ። በዚህ ጊዜ ሁሉ አቤት ባዮች አልጠፉም ። በተለይም የኪቃውንት ጉባኤ የተደጋገመ አቤቱታውን አቅርቧል ። ግን ሰሚ አላገኙም ። ከዚህም ጋር ፤ «የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መሠረተ እምነት» ፥ «ትምህርተ መለኮት» ፥ «የዋልድባ ታሪክ» በሚሉ ስሞች የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርት የሚቃረኑ መጻሕፍት ታትመው ተበትነዋል ። እነዚህም መጻሕፍት ፤ «እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የውርስ ኀጢአት አለባት ፤ መንፈስ ቅዱስ አካሉ ዝርው ነው ፤ መለኮት በአካል ሦስት ነው ፤» የሚል ትምህርት የተሰራጩባቸው በመሆኑ ጉዳዩን ለ፬ኛው ቅዱስ ፓትርያርክ በአቤቱታ ብናቀርብም ሳይቀበሉን በመቅረታቸው የሰው ድጋፍ ባናገኝም እግዚአብሔር ግን ፍርዱን ገልጧል ።

እስከዚህ ድረስ የተሠራው ሁሉ በአገር ውስጥ የተወሰነ ፥ ከአገር ውስጥ ያልዘለለ ነው ተብሎ ሊገመገም የሚችል ነበረ ። አሁን ግን ወደ ውጭ እየወጣን ነው ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከ«አንድ ባሕርይ» ባዮች ክበብ እየወጣች ፥ ከእኅቶቿ ከእስክንድርያ ፥ ከሶርያ ፥ ከአንጾኪያ ፥ ከአርሜንያ አብያተ ክርስቲያን እየተለየች ፥ «ወልድ ዋሕድ ፣ ከሚለው ትምህርቷ

እየተነሸራተተች ÷ የአበውን ውግዘትና ግዝት እየጣሰች ÷ ስለ ክብሯ ስለ ሃይማኖቷ የተሰዉላትን የቅዱሳኖቿን ደምና ዐጽም እየተራመደች ÷ ከምእመናን ጋራ ቃል ኪዳን የተጋባችበትን የወልደ እግዚአብሔርን ደም እየረገጠች ፤ «ፍኖተ አሕዛብ ኢትሑሩ ወኢትደዩ ባሕርየክሙ ቅድመ አርጎው ፤» የሚለውን የጌታን ቃልና ፤ «ወበሓሂ ጥቀ ኢትበልዎ እስመ ዘይቤሎ በሓ ይሳተፎ በምግባሩ እኩይ ። ወይእዜኒ ዕቀቡ ርእሰክሙ ወኲሎ መራኅየ ዘሎቱ ሤመክሙ መንፈስ ቅዱስ ከመ ትርአዩ ቤተ ክርስቲያኑ ለክርስቶስ እንተ አጥረያ በደሙ ። ወአነ አአምር ከመ ይመጽኡ እምድኅሬየ ተኲላት መሰጥ እለ ኢይምሕክዋ ለመርዔት ወእምውስቴትክሙ ይትነሥኡ አደው እለ ይሜህሩ ጠዋየ ነገረ ከመ ያግብዕዎሙ ለአሕዛብ ኀቤሆሙ ፤» የሚለውን ቃለ እግዚአብሔር ቸል እያለች ወደ «ሁለት ባሕርይ» ክበብ በመግባት ላይ ትገኛለች ። ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥም ፤

፮ኛ ፤ በ፲ ፱፻፹፫ ዓመተ ምሕረት በሮማ ቤተ ክርስቲያን በከፍተኛ ደረጃ የክብር እንግዳ ሆና ተገኝታለች ፤ የክብር ጉብኝት አድርጋለች ፤ በጸሎት ÷ በማእድ ተሳትፋለች ፤

፯ኛ ፤ በ፲ ፱፻፹፬ ዓመተ ምሕረት በኮንስታንትኖፕል ወይም በኢስታንቡል ተመሳሳይ ሥራ ፈጽማለች ። በዚህም በምድር ላይ ዳግማዊ ክርስቶስ እየተባለ የሚጠራውን ÷ የማይሳሳት መምህር ÷ በዓለም ያለች ቤተ ክርስቲያን ያንተ ጉልት ናት እየተባለ የሚመሰገነውን የሮማ ፓፓ ÷ ቅዱሰ ቅዱሳን እየተባለ የሚጠራውን የቁስጥንጥንያ ፓትርያርክ በመወዳጀት የንስጥሮስና የልዮን መንበር ቤተ ሰብእ ሆናለች ።

፰ኛ ፤ በ፲ ፱፻፹፭ ዓመተ ምሕረት መግቢያ ላይ ፤ «መኑ ዘያኀብሮ ለክርስቶስ ምስለ ቤልሆር ወመኑ ዘይከፍሎሙ ለመሃይምናን ምስለ ንፉቃን ፤» የሚለውን ጥያቄ ሳታዳምጥ በሰላም ስም ክርስቶስም ሰላሙም በሌሉበት በዓለማውያን ጉባኤ ተገኝታለች ።

በዚህ ጉባኤ ላይ በኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ እንከን የለሽ ፍጹም ሰላም እንዳለ ፥ «በአሁኑ ጊዜ ሰላም የለም የሚል ካለ ይምጣ በፊቴ ይናገር ፤» በማለት ምስክርነቷን የሰጠችው ቤተ ክርስቲያን መስከረም ፲ ቀን ፲ ፱፻፹፯ ዓመተ ምሕረት በቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን መዘምራን ፤ «ነግሠ በጽድቅ ወለብሱ ጽርዓ ጽድቅ ፤» የሚለውን የነገሥታት መዝሙር እየዘመሩ ፥ ሊቃውንቱም ፤ «መንበረ ፀባዖት ኢረስአት ተወክፎተ ነግድ ሀጌ ፥ አምጣነ ተወክፈት ዮም ጳውሎስሃ ዐዌጌ ። ኦ ዘመን ዘመነ እንስሳ ፥ ዲበ ሠረገላ ትጼዓን በዘባነ ፈረስ ወሀርጌ ፥ ኀየንተ ነጋሢ ሰሎሞን ወኀየንተ ዳዊት ዐዌጌ ፥ ለጳውሎስ ቡሩኬሁ ተወከፍ በጸጋ ወተቀጸል ጽጌ ፤» የሚል ቅኔ እያጎረፉላት የዘውድ በዓሏን ስታከብር ምእመናኖቿ ግን በከባድ ኀይል ግዳጅ ከፍርድ ቤት አካባቢ ታፍሰው በሺ በሚመጠን ቍጥር እየተደበደቡና እየተረገጡ በደረቁ ወደ ተላጩበት እስር ቤት በመግባት ላይ ነበሩ ።

ይህም ለዚህች ታላቅ ቤተ ክርስቲያን ምን ዐይነት የታሪክ መልክ እንደሚኖረው አላውቅም ። ምክንያቱም በሮማ አሲሲ ጉባኤ ላይ ያደረገችው ንግግር መስከረም ፯ ቀን ፲ ፱፻፹፯ ዓመተ ምሕረት ከጠዋቱ ፮ ሰዓት በቫቲካን ሬዲዮ ጣቢያ ለዓለም ተላልፏል ። መስከረም ፲ ቀን ፲ ፱፻፹፯ ዓመተ ምሕረት በቅድስት ሥላሴ ያደረገችው በዓልም ሆነ በምእመናኖቿ ላይ የተፈጸመው በደል በመገናኛ መሣሪያዎች ለዓለም ተላልፏል ። የምእመናኑ በደል ያሳዘናቸው ሁሉ ድምፃቸውን አሰምተዋል ። ቤተ ክርስቲያን ግን ስለ ልጆቿ ፥ ስለ በጎቿ ምንም ያሰማችው ድምፅ የለም ። ይህም እንኳን ከሥሔል ከዶሮ እናት ያነሰች አድርጓታል ። እንግዲህ ለዚህች ነባርና ታላቅ ቤተ ክርስቲያን ይህ ታሪኳ ነውን?

፩ኛ ፤ በደሴ ኩታ በር ሜዳ ከእስላም ፈረሰኞች ጋር ፈረሰኛ ሆና ተገኝታለች ።

፪ኛ ፤ በሶደሬ የኤድስ ሴሚናር የወሲብ ሥርዓተ ትምህርት አሰጣጥ ሴሚናር መክፈቻ ላይ ከመገኘቷም በላይ እስከ ፍጻሜው አባል ሆናለች ።

፫ኛ ፤ በጣም የሚያሳዝነው በዚህ ፳፮ ዓመት የግፍ ዘመን ውስጥ ከሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ቍጥር በይበልጥ ግፍ የተፈጸመባቸው ፥ ደማቸው የፈሰሰ

ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን ብቻ መሆናቸውና በዚያው አንጻር ደግሞ ለፓትርያርኩ አቋም ጠንክሮ የምትታገል ይህቺው ቤተ ክርስቲያን ብቻ መሆኗ ነው ። እኳ የፓትርያርኩ ደጋፊ በመሆኗ ስለ ምእመናኖቿ ባትናገርም ከ፹፮ ዓመት በየስፍራው በግፍ የፈሰሰው የአባቶቿ የምእመናን ደም ግን ከአቤልና ከዘካርያስ ደም በላቀ ድምፅ አቤቱታውን እያሰማ ነው ።

ቅዱስ ፓትርያርክ!

ብፁዓን አበው!

ይህ ነገር በሲኖዶስ ተመክሮበት ካለተቀጨና ለዘለዓለም ካልተነቀለ ከባድ ችግር የሚያስከትል መሆኑን እየገለጽኩ አቤቱታዬን ሳቀርብ ÷ በመግቢያው እንደ ጠቀስኩት ይህ አቤቱታ በዐጸደ ነፍስና በዐጸደ ሥጋ ያሉ የኦርቶዶክሳውያን አበውና ልጆቻቸው ÷ ከቅዱስ ማርቆስ እስከ ሳድሳዊ ቅዱስ ቄርሎስ ያሉ የእስክንድሪያ ሊቃነ ጳጳሳት ÷ ከአትናትዮስ ከሰላማ እስከ ቅዱስ ቴዎፍሎስ ያሉ የኢትዮጵያ ሊቃነ ጳጳሳትና ፓትርያርኮች በክርስቶስ ፊት የቆሙበት ጠንካራ አቤቱታ መሆኑን በመግለጽ ይህን ማመልከቻ አቅርቤአለሁ ።

ለፍጻሜውም ሲኖዶሱ በቸልታ እንዳይመለከተውና ሳይነጋገርበት ÷ ውሳኔ ሳይሰጥበት ÷ የቤተ ክርስቲያንን ውርደት ከላይዋ ሳያነሣ ÷ ዕርቃኗን ሳይከድን ÷ ለሰለባ ከወደቀችበት ከጠላቷ ከልዮን መንበር ፊት አስነሥቶ ቀጥ አድርጎ በሁለት እግሯ እንደ ነበረች ሳያቆማት ÷ ህልውናዋን ሳያጸናላት እንዳይቀር ሲኖዶሱን በሾመና በሚመራ በመንፈስ ቅዱስ ዳኝነት ተማጽኜአለሁ ። »

## ሐ፤ ከቤተ ክህነት የሥራ ገበታቸው ስለ መታገዳቸው።

«በጊዜው ሳይጠሉ፥ ሳይናገሩ ብልጣ ብልጥ ሆኖ፥ አመስግኖ፥ ተወዶ፥ ተመስግኖ ሙብላት፥ መኖር የሚቻልበት ጊዜ ነው። ለእኔ ግን አምላኬ ይህን አልፈቀደልኝም። ስለዚህም ነፍስ ዐውቄ ቤተ ክርስቲያንን አገለገልኩባቸው በምላቸው በነዚህ ፺ ዓመታት፤ በመናገሬ፥ በማስተማሬ፥ መጻሕፍትን በመጻፌ፥ ለልዩ ልዩ ጥያቄዎች መልስ በመስጠቴ፤ ከቤተ ክርስቲያን ተቃዋሚዎች፥ ከኢትዮጵያ ጠላቶች፥ ከግብር አበሮቻቸው ብቻ ሳይሆን፤ መንግሥታዊ ፖለቲካ ይጋፋል፥ የእኛን ዕድል ይሻማል በሚሉኝ ሁሉ ዘንድ ሁል ጊዜም የክስ ዓላማ፥ የከሳሽ አፍ መፍቻ ሆኜ ኖሬአለሁ፤» በማለት አባታችን አለቃ አያሌው ታምሩ፤ «ምልጃ፥ ዕርቅና ሰላም፤» በተሰኘው መጽሐፋቸው ገጽ ፫ እና ፬ ላይ የገለጹት አገላለጽ በተደጋጋሚ በሕይወታቸው ውስጥ ታይቷል።

መንፈሳዊ ሰውን በመንፈሳዊ መንገድ የሚጓዘው ካልሆነ በስተቀር የሚገነዘበው የለምና ክቡር አለቃ አያሌው ታምሩ ያቀረቡት አቤቱታ እንደ ዋዛ፥ እንደ ቀልድ፥ እንደ ትዕቢት፥ እንደ ተራ ቅዠት ተቈጠረ። ለረጅም ዓመታት በመሪጌታነት፥ በሊቀ ጠበብትነት፥ በደብር አስተዳዳሪነት፥ በሊቃውንት ጉባኤ ሰብሳቢነት ቤተ ክርስቲያንንና አገርን ያገለገሉ ባለ ውለታ፤ «ቤተ ክርስቲያን ለጽድቅ ብላ በምትሰጠው ምጽዋት ልቡን ያሳበጠ ተራ ዐይነ ሥውር ፤» ተብሎ ከመሰደብ ጀምሮ እጅግ የሚሰቀጥጡ አስነዋሪ ቃላትን የተጠቀመው፤ «የቅሬታ አስወጋጅና የሰላም ኮሚቴ» ከሥራ ኃላፊነታቸው እንዲነሡ ወሰነባቸው።

በቤተ ክርስቲያኒቱ ድርጅታዊ መዋቅር ውስጥ «መንፈሳዊ ፍርድ ቤት፤» የሚባል አካል እያለ ከላይ የተጠቀሰው ኮሚቴ ለምን እንዳስፈለገ ካለመታወቁ ባሻገር፤ ውሳኔውን ከመስጠቱ በፊት አለቃን እንደ ተከሳሽ አቅርቦ አላነጋገራቸውም። የኮሚቴውን ውሳኔ በመንተራስም በወቅቱ የሲኖዶሱ ዋና ጸሐፊና የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ በአባ ገሪማ ፊርማ ወጪ የሆነ የስንብት ደብዳቤ በሚያዝያ ፲ ፰ ቀን ፲ ፻፹፰ ዓመተ ምሕረት ተጽፎላቸው ከ፶ ዓመት በላይ ካገለገሉበት የቤተ ክህነት አገልግሎት እንዲገለሉ ተደረገ። ሚያዝያ ፲ ፰ ቀን ፲ ፱፻፹፰ ዓ፤ ም፤ በአባ ገሪማ ተጽፎ ለአባታችን ለአለቃ አያሌው ታምሩ እንዲደርሳቸው የተደረገው ደብዳቤ የያዘው ሙሉ ቃል የሚከተለው ነበር።

«በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት ተመድበው ሥራን መሥራት ከጀመሩበት ጊዜ አንሥቶ ቤተ ክርስቲያኒቱ ለምትመራበት ቀኖና ተገዢ ባለመሆን በየጊዜው በሚፈጽሙት አፍራሽ ተልዕኮ ችግር ሲፈጥሩ መቆየትዎና ዛሬም ቢሆን ችግር ከመፍጠር ያልተገቱ መሆንዎ ከማንም የተሰወረ አለመሆኑ ይታወቃል።

ይሁንና ይህ ከአንድ ምሁር ነኝ ባይ የማይጠበቅ አላስፈላጊ ተግባር በሚፈጸምበት ወቅት ሁሉ ቤተ ክርስቲያኒቱ በትዕግሥት ከምትመለከትዎ በቀር አንዳችም የወሰደችው የተግሣጽ ወይም የእርምት ርምጃ እንደ ሌለ ግልጽ ነው። ስለ ሆነም በየጊዜው የሚፈጽሙት ቃለ ዘለፋ ቤተ ክርስቲያኒቱ ከምትችለው በላይ ከብደት እየጨመረ በመምጣቱ መነሻ፥ ጉዳዩ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የቅሬታ አስወጋጅና የሰላም ኮሚቴ ስብሰባ ቀርቦ ከተገመገመና ከተጣራ በኋላ፤

፩፤ «አለቃ አያሌው ታምሩ የሊቃውንት ጉባኤ ሰብሳቢ ሲሆኑ አባላቱን ሰብስበውና አወያይተው ማቅረብ ሲገባቸው ሕጋዊ ምስክርነት ሊሰጡበት የማይችሉትን ጽሑፍ ጥቅምት ፲ ፯ እና ኅዳር ፳፫ ቀን ፲ ፱፻፹፯ ዓ፤ ም፤ የርሳቸውን ስሜት ብቻ በማስተጋባት ራሳቸውን ከቅዱስ ሲኖዶስና ከአስተዳደሩ በላይ በማድረግ በአሁኑ ጊዜ በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ሕጋዊ አሠራር እንደ ሌለና ቤተ ክርስቲያንም እንደ ሌለች በመቁጠር በከፍተኛ ደረጃ የሚከናወነውን ሐዋርያዊ እንቅስቃሴ ሕገ ወጥ እንደ ሆነ አድርገው በመጻፍ በልዩ

ልዩ የዜና ማሰራጫ አውታሮች ሳይቀር በማሰራጨታቸውና የቤተ ክርስቲያኒቱን አስተዳደር በመዝለፋቸው አፈጻጸማቸው ከሥራና ከቤተ ክርስቲያን አባልነት የሚያሰርዝ ተግባር ሆኖ በመገኘቱ፤

፪፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትሕትናን የምታስተምር የበላይና የበታች ተከባብረውና ተፈቃቅረው እንዲኖሩ መልካም አርአያ ሆና የቆየች ስትሆን አለቃ አያሌው ታምሩ ግን ወቅትና ጊዜን እየጠበቁ የቤተ ክርስቲያናችን ቅዱሳን አበው የሆኑትን ሁሉ በማዋረድ ለመጥፎ ተግባር አርአያ ሆነው በመገኘታቸው፤

፫፤ አለቃ አያሌው ታምሩ በተለያዩ የግል ጋዜጦች የሚጽፏቸውና የሚያስተላልፏቸው መልእክቶች ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን የሚያፋልሱ፥ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን የሚያፈርሱ ከመሆናቸውም በላይ እናትና አባትህን አክብር እያለች የምታስተምረውን የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን መመሪያ ጥሰው የመሪዎቿን ክብር በመድፈራቸው፤

፬፤ በስም ተጠቃሹ በየዐውደ ምሕረቱ የሚሰጡት ትምህርት ከፖለቲካ ጋር የተቆራኘ የራሳቸውን ዝና ለማዳበር ብቻ የሚጠቀሙበት እንጂ በትክክል የእግዚአብሔርን ቅዱስ ቃል ለማስተማር የማይጠቀሙበት መሆኑ ካለፉት የረጅም ጊዜ ልምዳቸው የታየ በመሆኑ፤

፭፤ በአጠቃላይም ዘወትር ከሚፈጽሙት አላስፈላጊ ተግባር እንዲቆጠቡ ቢመከሩም፥ ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን በመድፈሩ ተግባር እየገፉበት ከመሄዳቸው በቀር ተጸጽተው የሚመለሱ እንዳልሆነ ስለ ተረጋገጠ፥ በዚህና በመሳሰለው ምክንያት ሁሉ የመጨረሻ የሥነ ሥርዓት ርምጃ በመውሰድ ከሚያዝያ ፩ ቀን ፲ ፱፻፹፰ ዓ፤ ም፤ ጀምሮ ከቤተ ክርስቲያኒቱ ከማናቸውም ሥራና ጥቅም እንዲሰናበቱ እንዲደረግ» ሲል በመተቸት ከላይ የተጠቀሰው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የቅሬታ አስወጋጅና የሰላም ኮሚቴ ሚያዝያ ፲ ፯ ቀን ፲ ፱፻፹፰ ዓ፤ ም፤ ባደረገው ስብሰባ አስተዳደራዊ ውሳኔ ሰጥቷል።

ስለዚህ ከቅሬታ አስወጋጅና የሰላም ኮሚቴ በተላለፈው ውሳኔ መሠረት ከሚያዝያ ፩ ቀን ፲ ፱፻፹፰ ዓ፤ ም፤ ጀምሮ ከሥራና ደመወዝ የተሰናበቱ መሆኑን እናስታውቃለን።» የአለቃ አያሌው ታምሩ የሃይማኖት መምህርነት በዐውደ ምሕረት ላይ ብቻ ቆሞ ከመናገር ባሻገር የሚያስተምሩት ክርስቲያናዊ ትምህርት በእያንዳንዱ ዕለታዊ የኀብረተ ሰቡ ሕይወት ላይም ተግባራዊ ሆኖ የማየት ፍላጎትና እምነትን የተላበሰ በመሆኑ፤ ከመንፈሳዊው ሕይወት ባሻገር በሥጋዊ ሕይወትም የሰዎች መብት ይከበር ዘንድ፥ አግባብነት የሌለው ጭቆናና ግፍንም በዝምታ ተቀብሎ መኖር የክርስቲያን ተግባር አለመሆኑን ራሳቸውን ምሳሌ በማድረግ አሳይተዋል።

ቤተ ክህነት ያላግባብ፥ ያለ ሥርዓት ከሥራ ገበታቸው ላይ ሲያግዳቸው፤ ሠርቶ የመኖር፥ ለተቀመጡበት የሥራ ኃላፊነት የመታመን፥ የባላገርነት መብትና የሕግ የበላይነት አለ ወይስ የለም የሚሉትን መሠረታዊ ጥያቄዎች መሠረት በማድረግ የአገሪቱ የፍትሕና የርትዕ ሥርዓት በሚፈቅደው በኩል ጉዳያቸው በፍርድ ቤት እንዲታይ ጥያቄ አቅርበዋል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሊቃውንት ጉባኤ ሰብሳቢ አለቃ አያሌው ታምሩ፤ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያቀረቡት ጥያቄና ተማጽኖ መንፈሳዊ መንገድን የተከተለና ስለ እግዚአብሔርና ስለ ቤተ ክርስቲያን ክብር የተደረገ ቢሆንም፤ «የአባቶችን ክብር ተዳፍረዋል፤» በመባል ከሥራ ከተባረሩበት ከሚያዝያ ወር ፲ ፱፻፹፰ ዓመተ ምሕረት ጀምሮ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሥራ ክርክር ችሎት፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤትን በመክሰስ መዝገብ ከፍተው ሲከራከሩ ቆይተው ጉዳዩ የካቲት ፪ ቀን ፲ ፱፻፺፫ ዓመተ ምሕረት ውሳኔ አግኝቶ ነበር።

አለቃ ያለአግባብ ከሥራ ተባርሬአለሁ ሲሉ የክስ መዝገቡን የከፈቱ ሲሆን፤ የጠየቁት መፍትሔ ያለአግባብ የተቋረጠው ውዝፍ ደመወዜ ተከፍሎኝ ወደ ሥራዬ እንድመለስ ይወሰንልኝ የሚል ነበር። በሌላ በኩል በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት በኩል ለስንብቱ ሕጋዊ ምክንያት ነው ተብሎ የቀረበው፤ አለቃ አያሌው በተለያዩ ጋዜጦች ላይ በሰጡት ቃለ ምልልስና መግለጫ ፓትርያርኩንና የቅዱስ ሲኖዶስ አባላትን ዘልፈዋል የሚል ነበር። ለዚህ ማፍረሻ አለቃ በበኩላቸው ያቀረቡት ክርክር በአጠቃላይ፤ እንደ አንድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ባለቤትና በተለይ እንደ ሊቃውንት ጉባኤ ሰብሳቢነቴ የቀና ሃይማኖቴን መጠበቅ ግዴታዬም ኃላፊነቴም ሲሆን ይህን ግዴታየንና ኃላፊነቴን የተወጣሁትም በሕገ መንግሥታዊ መብቴ አድማስና ጥላ ሥር ነው በማለት ነበር።

ፍርድ ቤቱ፤ አለቃ አያሌው ታምሩ የፈጸሟቸው ድርጊቶች የሕገ መንግሥታዊ መብታቸው ማረጋገጫ እንደ ሆነ አረጋግጦ ያለአግባብ ከሥራ መሰናበታቸውን ወስኗል። ነገር ግን አሠሪውና ሠራተኛው የተቆራኙበት የሥራ ሁኔታ ከፍተኛ ችግር ያለበት በመሆኑ ሠራተኛው ወደ ሥራ ቢመለሱ የሚፈጠረውን ችግር በማገናዘብ የመመለሳቸውን ነገር አስተላልፎታል። ቢሆንም ከሚያዝያ ፲ ፱፻፹፰ ዓመተ ምሕረት ጀምሮ ያለው ውዝፍ ደመወዝ፥ ካሣ፥ ሌሎች በሕግ የተሰጡ ጥቅሞች፥ ወጪና ኪሳራ እንዲከፈላቸውና መብታቸው እንዲጠበቅ ወስኗል።

በዚህ ውሳኔ ላይ የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት ለአለቃ አያሌው ታምሩ ደመወዝ እንዲከፈል የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም፤ እንዲሁም አለቃ አያሌው ታምሩ ካሣ ተከፍሏቸው ይሰናበቱ መባሉን በመቃወም በየበኩላቸው ይግባኝና መስቀለኛ ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ጥቅምት ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓመተ ምሕረት ባሳለፈው ውሳኔ ይግባኙን ውድቅ በማድረግ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ውሳኔ አጽንቷል።

በመጨረሻም የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት፤ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል በማለት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልክቷል። የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ኅዳር ፳፬ ቀን ፲ ፱፻፺፩ ዓመተ ምሕረት ባሳለፈው ውሳኔ፤ ሁለቱ ፍርድ ቤቶች ለአለቃ አያሌው ታምሩ የወሰኑላቸው የደመወዝና የካሣ ክፍያ እንዳይከፈላቸው ወስኖ፥ ወደ ሥራቸውም እንዳይመለሱ የተሰጠውን ብይን አጽንቶ ጉዳዩ በዚሁ ተቋጭቷል። አባታችን አለቃ አያሌው ታምሩ ከፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተጓዙበት ረጅም የሙግት ጊዜ መንፈሳዊና ሥጋዊ መብታቸውን ለማስከበር የአገሪቱ ሕግና ደንብ በሚፈቅደው መሠረት የተከራከሩ ቢሆንም፤ የተሰጠው ውሳኔ ግን ሁለቱንም ያልተመረኮዘ በመሆኑ በአሳዛኝነቱ በታሪክ ፊት ሲወሳ ይኖራል።

## መ፤ አለቃ አያሌው ታምሩ ያስተላለፉት ግዝትና ምክንያቶቹ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አመራር ላይ ያዩትን ችግር በማስመልከት የቤተ ክርስቲያኒቱ የሊቃውንት ጉባኤ ሰብሳቢ የነበሩት አለቃ አያሌው ታምሩ ችግሩ ሥር ሳይሰድ ገና ከጅምሩ እንዲታረም ማሳሰቢያና ተማጽኖ ካቀረቡ በኋላ በማስከተልም ቃለ ግዝት አስተላልፈዋል። ቃለ ግዝታቸው በመጀመሪያ የወጣው ሰኔ ፳፺ ቀን ፲ ፱፻፹፰ ዓመተ ምሕረት በ«መብሩክ» ጋዜጣ ላይ ነበር። ይኸም እንደሚከተለው ይነበባል።

**«ሀ፤** በቤተ ክርስቲያን የደረሱ ልዩ ልዩ ችግሮች ሁሉ በሲኖዶስ ተመክሮባቸው እንዲወገዱና እርምጃቸውም እንዲገታ በ፲ ፱፻፹፯ ዓመተ ምሕረት ጥቅምትና ኅዳር ወር ለሲኖዶሱ ማመልከቻ ስጽፍ መልእክቴ በጌታዬ በአምላኬ ትእዛዝ የተደረገ መሆኑን ገለጬ በአፈጻጸሙ ቸልተኝነት እንዳይታይበት ሲኖዶሱን በሾመ

በመንፈስ ቅዱስ ዳኝነት ተማጽኜ አቤቱታዬ የእኔ ብቻ ሳይሆን በዐጸደ ሥጋና በዐጸደ ነፍስ ያሉ የኦርቶዶክሳውያን አበውና ምእመናን አቤቱታ መሆኑን ገልጬ ነበር ያቀረብኩት። ነገር ግን የሲኖዶሱ ዋና ጸሓፊ አባ ገሪማና ፓትሪያርኩ ሐሳባቸው እስከ አሁን በቤተ ክርስቲያን የኖረውን የመንፈስ ቅዱስ መሪነት ሽረው የራሳቸውን ጣዖታዊ መሪነት ለመተካት ኖሮ በጥቅምት ወር ፲ ፱፻፹፰ ዓመተ ምሕረት በተደረገው አጠቃላይ ጉባኤ ላይ ያቀረብኩትን አቤቱታ ጭምር ሳይቀበሉ ከመቅረታቸውም በላይ የመንፈስ ቅዱስን ዳኝነት፥ የሲኖዶሱን ሥልጣን ለግል አድመኞቻቸው ኮሚቴ አሳልፈው በመስጠትና በነሱ ውሳኔ ተደግፈው የኑፋቄ መጽሐፍ ማውጣታቸውና መበተናቸው አንሶ ኦርቶዶክሳዊውን የሊቃውንት ጉባኤ አፍርሰዋል።

**፲፤** ይህ በዚህ እንዳለ ሲኖዶሱ ተሰብስቦ ጉዳዩን እንዲያይ በግል ማመልከቻ፤ በነጻ ፕሬሱ በኩልም ተቃውሞዬን በማሰማት ላይ እያለሁ ሚያዚያ ፲ ፰ ቀን ፲ ፱፻፹፰ ዓመተ ምሕረት የቅሬታ አስወጋጅና የሰላም ኮሚቴ በሚሉት የግል ኮሚቴያቸው ድጋፍ እኔን ካባረሩ በኃላ ከሚያዚያ ፳፪ እስከ ግንቦት ፯ ባደረጉት በአፈና የሲኖዶስ ስብሰባ ሕግ አስወጥተው በመንፈስ ቅዱስ ፈንታ ራሳቸው ፓትሪያርኩ ሲኖዶሱ ወንጌልን ለሚሰብክበት፥ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ለሚያስተምርበት ጉዞ አመራር ሰጪ (ጣዖት) ወደ መሆን አድገዋል። በቤተ ክርስቲያን ስም ተሰይመው እግዚአብሔርንና ቤተ ክርስቲያንን ሊያገለግሉ የተሾሙ ኤጲስ ቆጶሳት፥ ጳጳሳትና ሊቃነ ጳጳሳት የሲኖዶሱ ዋና ጸሓፊ ሳይቀር ለቤተ ክርስቲያን ተጠሪ መሆናቸው ቀርቶ ለፓትሪያርኩ ተጠሪዎች እንዲሆኑ ሲያደርጉ ሚያዚያ ፴ ቀን ተፈርሞ ጸድቋል፤ የተባለውና በጽሕፈት ቤቱ አማካኝነት ለሚመለከተው ሁሉ እንዲተላለፍ በቃለ ጉባኤ ትእዛዝ የተሰጠበት ሕገ ቤተ ክርስቲያን እስከ አሁን ቤተ ክርስቲያን ስትሠራባቸው የኖሩት ሕጎችና ደንቦች ሁሉ በዚህ ሕግ ተሻሽለው ከስፍራቸው ሲወገዱ፥ አባ ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ ፈንታ የቤተ ክርስቲያኒቱን የአመራር ሰጪነት ቦታ ሲይዙ በቤተ ክርስቲያን ላይ የአምልኮ ጣዖት ዐዋጅ ዐውጀውባታል። ፓትሪያርኩ በሾማቸው በእግዚአብሔርና በቤተ ክርስቲያን ላይ በፈጸሙት ተግባር ታላቅ በደል ፈጽመዋል። ከራሳቸው ጋር ቃላቸውን ለማጽደቅ፥ ምኞታቸውን ለሚሟላት በሕጉ ላይ ፈርመዋል ተብሎ ስማቸው የተመዘገበላቸው ፴፬ቱ ጳጳሳትና ሊቃነ ጳጳሳት እንደ ተባለው አድርገውት ከሆነ ለፈጸሙት በደል ተባባሪዎች ናቸው።

ይህም እጅግ የሚያሳዝን ነው። የሚገርመው ደግሞ በዚሁ ሕግ አንቀጽ ፲ ፬፤ «ፓትሪያርኩ የተዋሕዶ እምነትን፥ ሕግጋተ ቤተ ክርስቲያንን የማይጠብቅ፥ ማዕረጉን የሚያጎድፍ ሆኖ መገኘቱ በተጨባጭ ማስረጃ ሲረጋገጥ በምልአተ ጉባኤ ያለአንዳች የሐሳብ ልዩነት በቅዱስ ሲኖዶስ ከተጠና በኋላ በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ መሠረት ከማዕረጉ ይወርዳል፤» የሚል ቃል አስፍሮ ሲኖዶሱን በአፈና ልዩ ሥልጣን ተጠቅመውና እንደ ሌለ አድርገው ካሳዩ በኋላ የኑፋቄ መጻሕፍት በማሳተም የተዋሕዶ ሃይማኖትን አፋልሰዋል፤ ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ሳይጠብቁ ቤተ ክርስቲያን ከምታወግዛቸው ጋር የጸሎት ቅዳሴና የማዕድ ተሳትፎ አድርገዋል፤ ቤተ ክርስቲያኒቱ ከምታወግዘው ፓፓ ቡራኬ ተቀብለዋል፤ እያልን እየተቃወምን ለተቃውሟችንንም ተጨባጭ ማስረጃ እያቀረብን፤ ራሳቸውም ይህንን ሳይቃወሙ ይህ እንዳይቀጥል በሥልጣናቸው ተጠቅመው ኦርቶዶክሳዊውን የሊቃውንት ጉባኤ ሲያፈርሱ ጉዳዩን አይቶ ውሳኔ በመስጠት ፈንታ እንደገና በሕግ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስፍራ ተተክተው ለሲኖዶሱ ሥልጣንና ተግባር አመራር ሰጪ ይሆናሉ። የሲኖዶሱ አባሎች ሁሉ ለፓትሪያርኩ ተጠሪ ይሆናሉ ሲል የወጣው አዋጅ አፈጻጸም ነው።

ይህ ሕገ ቤተ ክርስቲያን ተብሎ የታወጀው ሕግ፤ «እስመ ሜጥዋ ለዐመፃ ላዕሌከ፤» «ዐመፅን ወደ አንተ መለሷት፤» ተብሎ እንደ ተጻፈ ቤተ ክርስቲያንን መካነ ጣዖት፥ ምእመናንን መምለኪያነ ጣዖት የሚያሰኝ ስለ ሆነ በሙሉ ድምፅ እንድትቃወሙት በእግዚአብሔርና በቤተ ክርስቲያን ስም እጠይቃለሁ፡፡

**ሐ፤** ከአሁን ጀምሮ ማለት ይህ ቃል በነጻው ፕሬስ ከተላለፈበት ጊዜ ጀምሮ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ቃልና እጅ፥ በሲኖዶሱ ጸሐፊ በአቡነ ገሪማ ቃልና እጅ፥ ይህን የተጻፈውን ሕግ የቤተ ክርስቲያን ሕግ ብለው አጽድቀው በተባባሪነት አሳልፈዋል የተባሉ ጳጳሳት እውነት ሆኖ ከተገኘ የነሱ ተባባሪዎች ናቸውና በነሱ ቃልና እጅ ቡራኬ እንዳትቀበሉ፥ እንዳትናዘዙ፤ ስማቸውን በጸሎተ ቅዳሴ የሚጠሩ አለቆች፥ ቀሳውስት፥ ካህናት ካሉም አምልኮ ጣዖት አራማጅ ናቸውና ተጠንቀቁባቸው፤ ምክር ስጧቸው፤ እንቢ ካሉም ተለዩዋቸው።

እንዲሁም ሐምሌ ፭ ወይም ፮ ቀን ይከበራል ተብሎ ሽርጉድ የሚባልለት በዓለ ሢመት የአሮን የወርቅ ጥጃ መታሰቢያ ሆኖ በቤተ ክርስቲያን ሊከበር የማይገባው ስለ ሆነ በዓሉ ከመድረሱ በፊት የሲኖዶሱ አባላት በአስቸካይ ተሰብስበው ሕጉን ካልሻሩና በጣዖትነት የተሰየሙትን አቡነ ጳውሎስን ከሥልጣናቸው ካላነሡ ይህንን በዓል እንዳታከብሩ ለቤተ ክርስቲያን ደሙን ባፈሰሰ አምላክ ስም፥ ቤተ ክርስቲያንን በሚመራና በሚጠብቅ በመንፈስ ቅዱስ ስም ጥያቄዬን አስተላልፋለሁ።

ምናልባት የሕጉን ጽሑፍ አንብቦ መረዳት የተሳነው፥ ግን በልዩ ልዩ ደጋፊዎቻቸው ተጭበርብሮ በቸልታ የሚመለከተው፤ ከዚያም ዐልፎ በሥልጣናቸው እየተመኩ ለቤተ ክርስቲያን ጥያቄ ጆሯችንን አንሰጥም ብለው ይህን በደል ያደረሱትን ፓትርያርክ አቡነ ጳውሎስን፥ በሦስት የሹመት ስም የሚንቀባረሩትን አባ ገሪማን፥ ለነሱ ድጋፍ የሚሰጡትንም ሁሉ፤ ጌታዬ አምላኬ፤ «በምድር ያሰራችሁት በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ » ሲል በሰጠው ቃል በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ሥልጣን፤ በጴጥሮስ፥ በጳውሎስ፥ በማርቆስ፥ በቄርሎስ፥ በባስልዮስ፥ በቴዎፍሎስ፥ በተክለ ሃይማኖት ዘደብረ ሊባኖስ ቃል፤ ኃጥእ ደካማም በምሆን በእኔም በቀሲስ ወልደ ጊዮርጊስ ቃል አውግዣለሁ።

ይህን ሕግ የተቀበሉ፥ ከሥራ ላይ ያዋሉ ሁሉ እንደ አርዮስ፥ እንደ መቅዶንዮስ፥ እንደ ንስጥሮስ፥ እንደ ፍላብያኖስ፥ እንደ ኬልቄዶን ጉባኤና ተከታዮቹ እሱራን፥ ውጉዛን ይሁኑ። በማይፈታው በእግዚአብሔር ሥልጣን አስሬአለሁ።

ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ምስጋና ይሁን አሜን።

**ማስጠንቀቂያ፤** አምላኬ ሂድ ተናገር ያለኝን ትእዛዝ ለናንተ አድርሻለሁ። ሩጫዬን ጨርሻለሁ። ከእንግዲህ ተጠያቂነቱ የእናንተ የምእመናንና ታሪክ ተጠያቂ ያደረገው የመንግሥት ነው። ለዚህም ምስክሬ ራሱ እግዚአብሔር፥ ቅዱሳን መላእክት፥ ሰማይና ምድር ናቸው።

አለቃ አያሌው ታምሩ ዘዲማ ጊዮርጊስ።»

## ሠ፤ አለቃ አያሌው ታምሩ ባስተላለፉት ግዝት ዙሪያ የተሰጡ አስተያየቶች።

ባለፉት ፲ ፪ ዓመታት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አመራር ላይ የተቀመጡ መሪዎችን በሚመለከት አለቃ አያሌው ታምሩ በራእይ ስለ ተሰጣቸው መልእክትና ስላስተላለፉት ውግዘት የሚያነጋግሩ ወይም ከወዲያ ወዲህ የሚመላለሱ የተለያዩ አመለካከቶች መኖራቸው ይታወቃል። በራእይና በሕልም መንፈሳዊ መልእክትን መቀበል ለክርስቲያን አባቶች አዲስ ነገር እንዳልሆነ የታወቀ ስለ መሆኑ ከመጽሐፍ ቅዱስ እጅግ ብዙ ታሪኮችን እናገኛለን። የሚከተሉት ለአብነት ያህል ቀርበዋል።

ሀ፤ «የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፤ ሂድ፤ በኢየሩሳሌም ጆሮ ጩኽ፤ እንዲህም በል … » (ኤር፤ ፪፥ ፩።)

ለ፤ «በሠላሳኛው ዓመት በአራተኛው ወር ከወሩ በአምስተኛው ቀን በኮቦር ወንዝ በምርኮኞች መካከል ሳለሁ ሰማያት ተከፈቱ፤ የእግዚአብሔርን ራእይ አየሁ።» (ሕዝ፤ ፩፥ ፩።)

ሐ፤ «ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ አሳየኝ፤» (አሞጽ ፯፥ ፩።)

መ፤ «የእግዚአብሔር ቃል ወደ አማቴ ልጅ ወደ ዮናስ እንዲህ ሲል መጣ።» (ዮና፤ ፩፥ ፯።)

በእንዲህ ያለ ሁኔታ ከእግዚአብሔር መልእክት የተቀበሉ አባቶቻችንም ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ፈቀቅ ሊሉ አልወደዱም። ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ፤ «ንጉሥ አግሪጳ ሆይ! ስለዚህ ከሰማይ የታየኝን ራእይ እንቢ አላልሁም፤» በማለት ለአምላኩ የነበረውን ታዛዥነት ገልጦአል። (የሐ፤ ሥራ ፳፮፥ ፲ ፱።)

ከዚህ በተጨማሪም እጅግ ብዛት ያላቸው ኢትዮጵያውያን ቅዱሳን የእግዚአብሔርን መልእክት በመቀበል እስከ ነገሥታቱ እልፍኝ ድረስ ቀጥ ብለው በመግባት የታዘዙትን ተናግረዋል። ይህ ሁሉ የሃይማኖትና የታሪክ እማኝነት እያለ ክቡር አለቃ አያሌው ታምሩ በራእይ ስለ ተሰጣቸው መልእክት የተናገሩትን ለመቀበል የከበዳቸው ሰዎችና ድርጅቶች ነበሩ።

ከነዚህ ውስጥ ጥቂት ግለሰቦችና ዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ፤ «ራእይ አላዩም፤» «ክህነት ሳይኖር ውግዘት፤» «የቤተ ክርስቲያንንና የአባቶችን ክብር ደፍረዋል፤» ወዘተ የሚሉ ማእከላዊ ነጥቦች ዙሪያ በፍሬ ነገር ሳይሆን በተራ ስድቦች የታጀቡ ትችቶችና ተቃውሞዎችን ጽፈዋል። እነሱ ለጻፏቸው ትችቶችና ተቃውሞዎች ደግሞ ከዚህ በታች ያሰፈርናቸው መልሶች በጊዜው ተሰጥተዋል። ከነዚህ መካከል ሁለት የኅትመት ውጤቶችን እንደሚከተለው እናቀርባለን።

«ባለፈው ሳምንት የመብሩክ ጋዜጣ እትማችን ከአለቃ አያሌው ታምሩ ጋር ያደረግነውን ቆይታ በክፍል አንድ ዝግጅታችን ማቅረባችን ይታወሳል። ይህንኑ ጉዳይ በተመለከተ ወደ እኛ ስልክ በመደወልም ሆነ እና ወደ ሲኖዶሱ አባላቶች ስልክ በመደወልና በግንባርም በመገናኘት ለዚህ ዝግጅት አፍራሽም ሆነ ገንቢ ሐሳብና አስተያየት ካለ ለግንዛቤ እንዲረዳ ሰፊ ዘገባ ለማጠናከር ጥረት በማድረግ ሰንብተናል።

በግንባር ካገኘናቸው ሁለት አባቶች በተናጠል እንደ ገለጹልን ከሆነ መጠራጠር አይገባም። አያሌው ዕድሜ ልኩን እግዚአብሔርን ሲያገለግል የኖረ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለው፥ ፍጹም ከልቡ የእግዚአብሔር ወዳጅ ነው። እንዲህ ያለ ልበ ብርሃን ሰው ቀርቶ፥ አጥብቆ አምላኩን የሚማጸን ፍጡር እንኳ ከፈጣሪው መልስ ማግኘት ይችላል። ጥርጣሬያችንን እናስወግድ። የጊዜው ጉዳይ አላመች አለ እንጂ በአባትነት በክብር መቀመጥና በአቋራጭ አምላክን ለመማጸን መንገድ በሆነን ነበር በማለት አስተያየታቸውን ሰንዝረዋል።

አንድ ሊቀ ጳጳስ የሆኑ ታዋቂ አባት ደግሞ፤ አለቃ አያሌው እኛም ሁላችን የምናምንባቸው አምላካቸውን ሌት ተቀን በጸሎት የሚማጸኑ፥ እኔም ሆንኩ ሌሎች ለሃይማኖታቸው ቀናዒ መሆናቸውን የምናውቀው ነው። ነገ አፈር የሚጠብቃቸው እንደሳቸው ያሉ ታላቅ ሰው ራእይ ሳያዩ አይቻለሁ ለማለት የማይደፍሩ ጥብቅና ድንቅ ሰው መሆናቸውን ማንም የቤተ ክርስቲያኒቱ አመራር አባል ያውቃል ያምንባቸዋልም፤ በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተውናል።» (መብሩክ ጋዜጣ፥ ግንቦት ፳፪ ቀን ፲ ፱፻፹፫ ዓ፤ ም።)

«ሐዋርያት እንኳ እርስ በርሳቸው በምስጢር በቤታቸው፥ በቤተ ክርስቲያን፥ በዐደባባይም ቢሆን የወንጌል ሥራ እንዲቃና ብዙ ይጋጫሉ፤ ብዙ ይከራከራሉ፤ ብዙ ይነጋገራሉ። ታዲያ እኔ የሊቃንውንት ጉባኤ ሰብሳቢ ሆኜ ፴፫ ዓመት የሠራሁ ሰው፥ የቤተ ክርስቲያኒቱ ካህን፥ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ እጅ የተቀባሁ ካህን በቤተ ክርስቲያን ካሉት ሊቃውንት ምንም እንኳ እንደነሱ እሆናለሁ ባልልም በመጠኑ ከቁጥር የገባሁ ሰው፤ የቤተ ክርስቲያን እምነት፥ ሥርዓትና ትምህርት ሲዛባ ዝም ብሎ መመልከት ይገባኛልን? ጌታዬ ተናገር፥ ዝም አትበል እያለ ጩህ ነው እኮ የሚለኝ። ጌታዬ ጩህ፥ ጉሮሮህ እስኪነቃ ጩህ፥ ድምፅህ እስኪጠፋ ጩህ ይለኛል። የሚቀሰቅሰኝ ይኸው ነው። እና የተናገርኩት በዚሁ ምክንያት ነው እንጂ በዕውቀት ከሌላው እበልጣለሁ ብዬ አልተናገርኩም፤ አልናገርምም። የሚበልጠኝ አለ፤ የሚያንሰኝም አለ። ደግሞም ብዙዎቹ አይበልጡኝም፤ ሁሉም አያንሱኝም። አሁን ያሉት መጽሐፉን ያዘጋጁት ግን ከእኔ በታች ናቸው። » (ጦማር ጋዜጣ፥ ግንቦት ፲ ፩ ቀን ፲ ፱፻፹፫ ዓ፤ ም።)

ክቡር አባታችን አለቃ አያሌው ታምሩ ከቤተ ክህነት ከተገለሉ በኋላ እንደ ቀደሙት ዘመናት በዐደባባይ ወጥተው ሕዝቡን የማስተማርና የመምከር ዕድል አላገኙም። በአዲስ አበባ የሚገኙ አድባራትና ገዳማት ዐውደ ምሕረቶች፥ የሠርግና የቀብር ሥነ ሥርዓቶች፥ በዓላትና የተለያዩ የትምህርት መስጫ አዳራሾች፥ መንግሥታዊ ራዲዮ፥ ቴሌቪዥንና ጋዜጦች የሊቁን ርቱዕ አንደበት፥ በአገር፥ በሃይማኖትና በወገን ፍቅር የነደደ ትምህርት ለማስተጋባት አልታደሉም። ከላይ በዘረዘርናቸው ቦታዎች ሁሉ እንዳያስተምሩ በቀጥታም ሆነ በእጅ አዙር ማዕቀብ ተጣለባቸው። አለቃም የቁም እስረኛ ለመሆን ተገደዱ።

ሆኖም ግን እሳቸው አልተረቱም። ክፍት ሆኖ ባገኙት መንገድ ሁሉ ሃይማኖትን፥ የአገር ፍቅርን፥ አንድነትን እስከ ዕለተ ዕረፍታቸው ድረስ አስተማሩ። ለዚህ አባባላችንም በመኖሪያ ቤታቸው ተወስነው በቆዩባቸው ፲ ፮ ዓመታት ያመረቷቸው የሃይማኖትና የምግባር ትሩፋቶች ምስክሮች ናቸው። ጥቂቶቹን እንደሚከተለው እንዘረዝራለን።

ሀ፤ በማኅበረ በኵርና ዘወትር ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ በመኖሪያ ቤታቸው በመገኘት ለሚማሩ ምእመናን የሚሰጡትን የስብከተ ወንጌል አገልግሎት በስፋት በመቀጠል፤

ለ፤ ለአገራቸው፥ ለወገናቸውና ለቤተ ክርስቲያን ሰላም፥ አንድነትና ነጻነት በመጾምና በመጸለይ፤

ሐ፤ በተለያዩ ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ፩ መጻሕፍትን በማዘጋጀትና በማሳተም፤

መ፤ በሃይማኖት፥ በታሪክ፥ በቋንቋ፥ በፖለቲካና በተለያዩ በዓላት ዙሪያ የሚነሡ ጥያቄዎችን አስመልክቶ ከግለ ሰቦች፥ ከጋዜጠኞች፥ ከዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችና ምሁራን ለሚቀርቡ ጥያቄዎች መልስ በመስጠት፤ በግምት ከ፷ እስከ ፹ የሚደርሱ ቃለ መጠይቆችና መግለጫዎችን በመስጠት፤

ሠ፤ በሕመምና በተለያየ ችግር ተይዘው የእሳቸውን ምክርና ጸሎት ለሚሹ ሁሉ ምንም ዐይነት የቀንና የሰዓት ገደብ የሌለበት የማጽናናትና የጸሎት ድጋፍ በማድረግ ከአንድ አባት የሚፈለጉ መንፈሳዊ አገልግሎቶችን ሲአበረክቱ ቆይተዋል፡፡

# አባታችን ስለ ቤተ ክርስቲያን አንድነትና ክብር የነበራቸው ጥንቃቄ።

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሚታወቀው በኋላ ዘመን የተነሡ መናፍቃን ያመጡት የሐሰት ትምህርት በቀደመችው ቤተ ክርስቲያን ላይ የማይጠፋ ጠባሳ ማሳረፉ ይታወቃል። ይህም አንድነትን ከክርስቲያኖች ዘንድ ማራቁ የሚታወቅ ነው።

በዘመናችንም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሊቃውንት ጉባኤ ሰብሳቢ የነበሩት አለቃ አያሌው ታምሩ በቤተ ክርስቲያኒቱ አመራር ላይ የነበራቸውን ተቃውሞ መግለጣቸውንና ማውገዛቸውን ቀደም ብለን ገልጸናል። አለቃ አያሌው ታምሩ ስለ ቤተ ክርስቲያኒቱ እምነት፥ ሥርዓትና ትምህርት በነበራቸው ቀናዒነትና ከአምላክ በተሰጣቸው ትእዛዝ የተነሣ ያስተላለፉትን ቃለ ውግዘት የተቀበሉ ብዙ ሺ ኦርቶዶክሳውያን መኖራቸውም ይታወቃል። በነዚህ ባለፉት ፲ ፪ ዓመታት ውስጥ በየአብያተ ክርስቲያኑ የሚካሄደው አምልኮተ እግዚአብሔር ሁኔታ ደስ ያላሰኛቸው ብዙዎች ምእመናን አለቃ ሌላ የተገነጠለች ቤተ ክርስቲያን እንዲያቋቁሙ ደጋግመው ጠይቀዋቸው ነበር። የአለቃ አያሌው መልስ ግን፤ «ባለፉ ዘመናት በቤተ ክርስቲያን አንድነትና ህልውና ላይ የተፈጠሩ የልዩነት ነቀርሳዎች ሳያንሡ እኔ እንዲህ ያለውን የጥፋትና የውድቀት መንገድ ለቤተ ክርስቲያኔ አላበጅም። መሆን ያለበት ሌላ ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አንድ ነች። ሌላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የለችም። እኛ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልጆች ነን። ማድረግ ያለብን ሌላ ተገንጣይ ቤተ ክርስቲያን ማበጀት ሳይሆን ቤተ ክርስቲያናችን በራሷ ሕግ የምትመራበትን ጥረት ሁሉ ማድረግ ነው፤» የሚል ነበር።

ከዚህ ጠንካራና ታማኝ አመለካከታቸው በመነሣትም ምእመናን ቤተ ክርስቲያናቸውን ተጠንቅቀው እንዲጠብቁና ከደረሱባት ችግሮች እንዲታደጉ የቤተ ክርስቲያናቸውም ባለ ቤቶች እንዲሆኑ የሚያስችሏቸውን የመፍትሔ ሐሳቦች በመጠቆም ተደጋጋሚ ጥሪዎችን አስተላልፈዋል። ከብዙዎቹ የተወሰኑትን እንደሚከተለው እንጠቅሳለን።

*ሀ፤ «እንግዲህ በእኔ በኩል አቤቱታየን ሁሉን ማድረግ ለሚቻለው ለኢትዮጵያ አምላክ ማቅረብ ብቻ ነው። እናንተም ምእመናን ፈቃዳችሁ ከሆነ በፖለቲካ ስብከት የሚደረደርላችሁን ሁሉ ወደ ጎን ትታችሁ በዚህ የዐቢይ ጾም ወራት በየቀኑ ጧትና ማታ ለተወሰኑ ደቂቃዎች በኅያሉ አምላክ ፊት ስለ ቤተ ክርስቲያናችሁ፥ ስለ ሃይማኖታችሁ፤ በዚህ ምክንያትም ከሚመጣው ፍርድ ለመዳን በእግዚአብሔር ፊት በመቆምና አቤቱታ በማቅረብ እንድትተባበሩኝ በኢትዮጵያ አምላክ ስም እጠይቃለሁ።» (ማዕበል፥ የካቲት ፲ ፬ ቀን ፲ ፱፻፺ ዓ፤ ም።)*

*ለ፤ «ምእመናን ቤተ ክርስቲያናችሁን ልትጠብቁ ይገባል። ጠብቁ የምላችሁ ከቤታችሁ ሌቦች ነው። የናንተ የራሳችሁን ሰዎች ነው። ቤታችሁን እንዲጠብቁ ተቆጣጠሯቸው። ውሻ እንኳ ባቅሙ ቤት ይጠብቃል። የኛ የምትሏቸው ሰዎች የቤታችሁን በር እየከፈቱ እያስበዘበዙት ነው። በዓላችሁን ንስሐ ገብታችሁ አክብሩት። እግዚአብሔርን በድላችሁታል፤ ክዳችሁታል። ሥጋው ደሙ በሌለበት፥ ጥምቀት በሌለበት፥ ቡራኬ በሌለበት ቤተ ክርስቲያን ስሙን እየጠራችሁ የምታደርጉት ዐመፅ እግዚአብሔርን በጣም አሳዝኖታል። ከፍርድ በፊት እንድትመለሱ ያስፈልጋል። ክርስቲያኖች ሁሉ ቤታችሁን ጠብቁ። ወዮላችሁ ጳጳሳት! ወዮላችሁ ኤጲስ ቆጶሳት! እናንተ አትገቡም፤ ለሚገቡት በር ዘግታችሁ የምታደናግሩ ስለ ሆነ ይፈረድባችኋል። ይህች ለዘመናት የቆየች እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን እንዳትፋረዳችሁ ክርስቲያኖች ሁሉ ወደ እውነት ተመለሱ። በዛሬው በትንሣኤው ቀን እነዚያ ተጠራጥረው የነበሩ ደቀ መዛሙርት ተመልሰዋል፤ አምነዋል። «እናንተ በሙሴ ኦሪትና በነቢያት፥ በመዝሙር የተጻፈውን አስቀድሜ የነገርኳችሁ አልነበረም ወይ፤» ሲላቸው*

ተገሥጸው፥ ደንግጠው ተጸጽተዋል፤ አምነዋል፤ ለጸጋውም በቅተዋል። እናንተም ዛሬ ያላችሁ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባሎች ሁሉ ቀሳውስት፥ ዲያቆናት፥ የሰበካ ጉባኤ አባላት፥ ወጣቱ፥ አዛውንቱ፥ ጐልማሳው፥ ሴቱ፥ ወንዱ ሁሉ ቤተ ክርስቲያን አለ እያላችሁ ስትዋኙ የነበራችሁ፥ ጥምቀት በሌለበት፥ ቍርባን በሌለበት፥ ጸጋ በሌለበት በአታላይ ቀሳውስትና ጳጳሳት ተታላችሁ እግዚአብሔርን የተጋፋችሁ ሁሉ ንስሐ ግቡ። ይህን ብታደርጉ ከፍርድ ትድናላችሁ። እንዲህ ባትሆኑ እግዚአብሔር ይመጣል። ፍርዱን የሚያመልጣት የለም። ጆሮ ያለው ይስማ። እውነተኛ ልብ ላላችሁ ሁሉ እግዚአብሔር ዐስበ ትንሣኤውን፥ በረከቱን ያድላችሁ።» (ሚያዝያ ፲ ፰ ቀን ፲ ፱፻፺ ዓ፤ ም።)

ሐ፤ «በተደጋጋሚ ጥሪዬን አሰምቼአለሁ። በቅድሚያ ከአባ ጳውሎስ አስተዳደር መለየት፥ ከጳጳሳቶቻችሁ መለየት፤ ደረጃውን የጠበቀ ውግዘት የሰነዘርኩት በዚህ ምክንያት ነው። የቤተ ክርስቲያኒቱ ካህናት በሙሉ በጸሎተ ቅዳሴ የአባ ጳውሎስን ስም እንዳይጠሩ፥ ምእመናንም በጸሎተ ቅዳሴ ስማቸው በሚጠራበት ቤተ ክርስቲያን ሕፃናቶቻቸውን እንዳያስጠምቁ፥ መስቀል እንዳይሳለሙ፥ እንዳይቈርቡ፥ እንዳያቈርቡ፥ እንዳያስቀድሱ፥ እንዳይሰበሰቡ፥ መባዕ እንዳያወጡ። ይሄን ቢያደርጉ ተስፋ ይኖራል። አሁን የልደታ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ጀምረዋል። ልክ እንደነሱ እስከ አሁን ባይደረግም ወደ ፊት ግን መላው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ይህን አርኣያነት ተከትለው ቤተ ክርስቲያኒቱን ከሮም ቤተ ክርስቲያን ቅኝ ተገዥነት ነጻ ማውጣት አለባቸው። ከሁሉም የሚያሳዝነው እንደ ዝቋላ፥ ደብረ ሊባኖስ፥ አኵስም ያሉ ታላላቅ መንፈሳዊ አካባቢዎች ላይ አባ ጳውሎስ «ሊቀ ጳጳስ ዘአኵስም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት» ነኝ እያሉ ሲያሾፉባቸው ዝምታን መምረጣቸው ነው። ምነው ገንዘብ የሚዘረፈውን ያህል ስሙም ይዘረፋል እንዴ? በጣም የሚያሳዝን ነገር ነው። ከዚህ በበለጠ የሚያስገርመው ደግሞ የትግሬ ካህናት መጀመሪያ በአባ ጳውሎስ ላይ ተቃውሞ አለን እያሉ ነበር፤ አሁን አባ ጳውሎስ «ሊቀ ጳጳስ ዘአኵስም» ተብለው ስለ መጠራታቸው ግን ያሉት የለም። ይህ ሁሉ ግን የማይሆን ስለ ሆነ በተለይ አድባራትና ገዳማት ግንባር ቀደም ሆነው ቤተ ክርስቲያናቸውን ያስከብሩ። ይህ ቢሆን መልካሙ ነገር ሁሉ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለመንግሥትም ይገኛል። ይህ ካልተቻለ ደግሞ እንደ አቡነ ገብርኤል ግልጡን እየመሰከሩ ባየነው በሰማነው ብለው መናገር አለባቸው።» (ኢትኦጵ፥ ሐምሌ ፳፫ ቀን ፲ ፱፻፺፫ ዓ፤ ም።)

ከዚህም በተጨማሪ በተለያዩ ጊዜያት የቤተ ክርስቲያንን ክብርና እምነት የሚነኩ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ድምፃቸውን አሰምተዋል። በሰኔ ወር ፲ ፱፻፺፬ ዓመተ ምሕረት ፳፰ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳት መስቀላቸውን አኑረው፥ ጫማቸውን አውልቀው ተፈተሹ፤ የሚል ዜና በዜና ማሰራጫዎች በሰሙበት ጊዜ አለቃ አያሌው ታምሩ ሁኔታው አሳዝኗቸው በጉዳዩ ላይ መግለጫ ሰጥተዋል። ይህንንም **«ኢትኦጵ» የተባለው ጋዜጣ ሰኔ ፲ ፪ ቀን ፲ ፱፻፺፬ ዓመተ ምሕረት፤ «ጫማ ማውለቅ የመጨረሻ ንቀትና ውርደት ነው፤» በሚል ርእስ በዝርዝር አስቀምጦታል። በዚህ ጋዜጣ ላይ የወጣውን መግለጫ በከፊል እንደሚከተለው አቅርበነዋል።**

### «በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤ አሜን።

ሰኔ ፭ ቀን ፲ ፱፻፺፬ ዓመተ ምሕረት ታትሞ በነጻ ጋዜጦች ከተላለፈው መልእክት አንዱ ዜና እጅግ በጣም አሳዝኖኛል። ልቤንም አቍስሎታል። የምወጣው ቢሆን ኖሮ የጠፉት ዐይኖቼም የዕንባ ደመና ሆነው ቢያግዙኝ በዕንባ ባጠብኩት ደስ ይለኝ ነበር። ግን አልቻልኩም። ይህ ዜና፤ ታላቁ አባት ያዕቆብ ስለ ሌዋዊው ዮሴፍ ከልጆቹ አንዱ ልጅህን አውሬ በላው ሲል በነገረው ጊዜ ከደረሰበት ኀዘን በላይ እኔን ይመረኛል። ካህኑ ዔሊም ልጅህ ተማረከ፥ ታቦተ ጽዮንም ተማረከች ብለው ሲነግሩት ከመረረው ወሬ በበለጠ የዛሬው ይመረኛል። ግን ካህኑ ዔሊ፤ ልጆቹ በኃጢአታቸው ነው፤ ሲያጥቡት ያድፋል እጅ፥ ሲመክሩት ይጠፋል ልጅ

እንደሚባለው ተዉ ስላቸው እንቢ ብለው ነው። የታቦተ ጽዮን መማረክ ግን እጅግ ያሳዝነኛል፤ ብሎ ተናግሮ ነበር። እኔም ሰኔ ፬ ቀን ፲ ፱፻፺፬ ዓመተ ምሕረት የወጣውን ዜና ከሰማሁ ወዲህ የምለው እንደዚሁ ነው። ጋዜጣው ፳፰ ጳጳሳት መስቀላቸውን አኑረው፥ ጫማቸውን አውልቀው ተፈተሹ የሚለውን ዜና ሲጽፍ ለጋዜጠኛው ምን ያህል እንደ ተሰማው፥ እንደ መረረው ነው የተገነዘብኩት። በድርጊቱና በሁኔታው ተማሮ ነው እንጂ ችላ ቢል አይጽፈውም ነበር። ብዙ ሰው ደግሞ ይህን ሲያነብ የሚለው አለ። አንዳንዱ፤ «አዬ ጉድ፤ » ይል ይሆናል። ሌላው ደግሞ፤ «ይበላቸው!» የሚል ይኖራል። ይበላቸው ግን አይደለም የሚባለው። እነዚህ ሰዎች የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ናቸው ብሎ የሚያምንበት መንገድ የለም። ነገር ግን በእነሱ ምክንያት የቤተ ክርስቲያን ክብር መደፈር የለበትም። ሕዝቡንና አገሩን የሚያስከብረው ክፍል ሕጉን ካልጠበቀ፥ ሕጉን ጠብቆ በተግባር ካልታየ ሌላውም ሕጉን እንዲጠብቅ እንዴት ማስተማር ይችላል? ይሄ በጣም ያስቸግራል። መንግሥት በሃይማኖት፥ ሃይማኖት በመንግሥት ጣልቃ አይገባም ተብሎ በሕገ መንግሥቱ ላይ ተጽፎ ይገኛል። ይሄ ደግሞ ከዚያው ከምንጩ ጀምሮ መከበር አለበት። ጫማ ማውለቅ እኮ ቀላል ነገር አይደለም። ተራ ነገርም ሊባል የሚገባው አይሆንም። ንብረት መውረስ፥ መብት መግሠሥ ይቻል ይሆናል፤ ጫማ ማውለቅ ግን የመጨረሻው ንቀት፥ ጥቃትና ውርደት ነው። … ይህ በጣም የሚያሳዝን መንግሥትንም ሕዝብንም የሚጎዳ እንጂ የሚጠቅም አይመስለኝም። የማዝነውም ለዚህ ነው። ጳጳሳቶቻችን እስከዚህ ድረስ ዘልቀዋል። ታዲያ እኮ ነገሩን የሚያበላሸው የምእመናን ዝምታ ነው። እኔ አቤቱታ ማቅረብ ከጀመርሁ ስድስት ዓመት ሆኖኛል። ጳጳሳት ከሃይማኖት ወጥተዋል፤ ሥርዓታቸውን አፍርሰዋል፤ በሥጋው በደሙ የገቡትን መሓላ አፍርሰዋል፤ የሌላ ዜጋ ሆነዋልና የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያንንና የምእመናንን ክብር የሚጠብቅ የለም። ከዚያም ዐልፎ ጥምቀት የሚያጠምቅ፥ ቊርባን የሚያቈርብ የለምና ይታሰብበት ስል አቤቱታ ካቀረብሁ ረጅም ጊዜዬ ነው። ይኸው በዐይንም በግብርም ታየ። ሕዝብ ግን፤ «እኛ ምን እናደርጋለን? እግዚአብሔር የፈቀደውን ይሹም፤» የሚል ቋንቋ ይዞ በቸልታ ሁሉን ነገር ስላበላሸ እዚህ አሳፋሪ ሁኔታ ላይ እየደረስን ነው። አሁንም ይህ ተግባር ቤተ ክርስቲያንን አይጎዳም፤ እግዚአብሔርንም አይጎዳም። በዚህ የእግዚአብሔር ክብር አይቀነስም። ግን የሚያስከትለው ቅጣት የከፋ ይሆናል። »


አለቃ አያሌው ታምሩ
(ካህን፣ሐዋርያ፣ ደራሲና ተርጓሚ)
በተለያዩ ጋዜጦችና፣ መጽሔቶች ያስተላለፏቸው ማሳሰቢያዎችና ትምህርቶች።
ኢትዮጵያ የዓለም ብርሃን
ኢትዮጵያ የዓለሙ ገዢ


ኢትዮጵያ የዓለም ብርሃን